ቀኛዝማች ፡ ሙላት ፡ በየነ ።

በይግባኝ ፡ ከሳሽ ፤ ሐቢብ ፡ ከቢሬ ፤
በይግባኝ ፡ ተከሳሽ ፤ ሚ/ ዳንኤል ፡ ኢጐ ፤

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቁጥር ፡ ፭፻፴፫/፹

የንግድ ሕግ ፤ የግል ማኅበርን ስለማፍረስ ፤ ተጨማሪ ማስረጃን በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ስለማቅረብ፤ ብርቱ ጠብና አለመግባባት ለማኅበሩ መፍረስ በቂ ምክንያት ስለመሆኑ የማኅበሩ መመሥረቻ ጽሑፍና የመተዳደሪያ ደንብ ከመዘጋጀቱ በፊት ስለ ነበሩት ስምምነቶች ውጤት ፤ የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥሮች ሺ፯፻፴፩ ፣ ሺ፰፻፹፰ ፤ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ቁጥሮች ፫፻፵፭ ፣ ፫፻፳፰ ፤ የንግድ ሕግ ቁጥሮች ፭፻፵፪ ፣ ፪፻፲፰ ፤ ፭፻፲ ፤ ፭፻፲፪ ፤ ፭፻፲፯—፭፻፲፰ ፤ ፫፻፲፬ ፤ ፭፻፹ ፤ ፪፻፲፱—፪፻፹፫ ፣ ፭፻፹፱ (፩)

በይግባኝ ባይና በመልስ ሰጪው መሀከል ያለው አለመግባባት ከዚህ በፊት ያቋቋሙትን የሽርክና ማኅበር ለማፍረስ በቂ ምክንያት ነው በማለት የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ፍርድ በመቃወም የቀረበ ይግባኝ ።

ውሳኔ ፤ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሳኔ ጸንቷል ።

፩/ ተጨማሪ ማስረጃ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ለማቅረብ የሚቻለው በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ በቁጥር ፫፻፳፰/፩/ሀ/ለ/ የተደነገገው ሲሟላ ብቻ ነው ።

፪/ የሽርክና ማኅበር ባቋቋሙት ሰዎች መሀከል ብርቱ አለመግባባትና ጠብ ከተፈጠረ ይህ በቂ ምክንያት ሆኖ ማኅበሩን ሊያፈርስ ይችላል ።

፫/ ማኅበሩ ከመቋቋሙ በፊትም ሆነ በኋላ ባቋቋሚዎቹ መሀከል የተደረጉ የግል ስምምነቶች በሙሉ በማኅበሩ መመሥረቻ ጽሑፎችና በመተዳደሪያ ደንቦች ውስጥ የተወሰኑትን ድንጋጌዎች ወይም ሌሎች ሕጎች ሊሽሩ ወይም ሊለውጡ አይችሉም ።

ውሳኔ

ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በቁጥር ፡ ፫፻፵፭ ፡ መሠረት ፡ ተጨማሪ ፡ ምስክሮች ፡ ላሰማ ፡ በማለት ፡ ጠይቋል ። በይግባኝ ፡ ሰሚ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ተጨማሪ ፡ ማስረጃ ፡ ሊቀርብ ፡ የሚችለው ፡ በሥነ ፡ ሥርዓቱ ፡ ሕግ ፡ በቁጥር ፡ ፫፻፳፰፡ ንዑስ ፡ ቁጥር ፡ ፩ ፡ (ሀ) እና ፡ (ለ) በተደነገገው ፡ መሠረት ፡ ፩ኛ/ይግባኝ ፡ የተባለ በትን ፡ ፍርድ ፡ ወይም ፡ ውሳኔ ፡ የሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የቀረበለትን ፡ ማስረጃ ፡ አለ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ሳይቀበለው ፡ ሲቀር ፤ ፪ኛ/ ተጨማሪ ፡ ማስረጃ ፡ መስማት ፡ ወይም ፡ መቀበል ፡ ተገቢ ፡ ነው ፡ ሲባል ፡ ወይም ፡ ትክክለኛ ፡ ፍትሕ ፡ ለመስጠት ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ሲታይ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ በከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ምስክሮች ፡ እንዲያስማ ፡ እንዲፈቀ ድለት ፡ ጠይቆ ፡ ነበር ፤ የጠየቀውም ፡ መልስ ፡ ሰጭዎች ፡ ፋብሪካውን ፡ እንሽጥ ፡ በማ ለት ፡ ለመጠየቃቸውና ፡ ለማስቸገራቸው ፡ እንዲሁም ፡ ከሌላ ፡ ሰው ፡ ጋር ፡ ተስማም ተው ፡ ለመሥራት ፡ ለማቀዳቸውና ፡ አገራችውም ፡ ለመሄድ ፡ ፈልገው ፡ ደጋግመው ፡ የጠየቁ ፡ ለመሆናቸው ፡ በምስክሮች ፡ ላስረዳ ፡ በማለት ፡ ነበር ። የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ግን ፡ አልተቀበለውም ። ያልተቀበለውም ፡ በተገቢ ፡ ምክንያት ፡ ነው ። እኛም ፡ ተስማምተንበታል ። የተስማማንበትንም ፡ ምክንያት ፡ ከዚህ ፡ ቀጥለን ፡ እናስረዳለን ።

ከሳሽ ፡ የአሁኖቹ ፡ መልስ ፡ ሰጭዎች ፡ ክስ ፡ ያቀረቡት ፡ ማኅበሩ ፡ በንግድ ፡ ሕግ በቁጥር ፡ ፰፻፵፪ ፡ እና ፡ በቁጥር ፡ ፪፻፲፰ ፡ መሠረት ፡ ይፍረስልን ፡ በማለት ፡ ነው ። ማኅበሩ ፡ ይፍረስልን ፡ የሚሉበትንም ፡ ምክንያት ፡ በዝርዝር ፡ አቅርበዋል ። ፍርድ ቤቱም ፡ መመልከትና ፡ መወሰን ፡ ያለበት ፡ የቀረበውም ፡ ምክንያት ፡ በቂ ፡ ከሆነ ፡ ማኅበሩ ፡ እንዲፈርስ ፡ ይደረጋል ፤ ካልሆነ ፡ ግን ፡ ይፍረስልን ፡ በማለት ፡ የቀረበው ጥያቄ ፡ ይሠረዛል ። መልስ ፡ ሰጭዎች ፡ በነሱና ፡ በይግባኝ ፡ ባዩ ፡ መካከል ፡ አለመግ ባባትና ፡ ብርቱ ፡ ጭቅጭቅ ፡ መፈጠሩን ፡ አስረድተዋል ። ይግባኝ ፡ ባዩም ፡ በመከላ ከያ ፡ አላፈረሰውም ። ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ላስረዳ ፡ የሚለው ፡ መልስ ፡ ሰጭዎች ፡ ፋብሪካ ውን ፡ እንሽጥ ፡ ማለታቸውን ፤ ከሌላ ፡ ጋር ፡ ለመሥራት ፡ ማቀዳቸውንና ፡ አገራችን እንሒድ ፡ ማለታቸውን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ መልስ ፡ ሰጭዎች ፡ ያቀረቡት ፡ ምክንያት ፡ እውነት ፡ አለመሆኑን ፡ ላስረዳ ፡ በማለት ፡ አይደለም ። ስለዚህ ፡ ላቅርብ ፡ የሚለውን ፡ ማስረጃ ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ያልተቀበለው ፡ በሚገባ ፡ ስለሆነ ፡ እኛም ፡ አልተቀበልነውም ።

እንግዲህ ፡ ወደዋናው ፡ ክርክር ፡ እንመለስ ፤ በከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የተከ ራከሩበትን ፡ መዝገብ ፡ መርምረን ፡ እንዳገኘነው ፡ ከሳሾች ፡ የአሁኖች ፡ መልስ ፡ ሰጭዎች ፡ ብላክ ፡ ፐርል ፡ የተባለው ፡ የግል ፡ ማኅበር ፡ እንዲፈርስ ፡ አጣሪና ፡ አከፋ ፋይም ፡ እንዲሾምላቸው ፡ ለከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አመልክተው ፡ ተከሳሹ ፡ የአ ሁኑ ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፡ ቀርቦ ፡ ከተከራከረ ፡ በኋላ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የተባለው ፡ ማኅበር ፡ እንዲፈርስና ፡ ሂሳብ ፡ አጣሪ ፡ እንዲሾም ፡ ወስኗል ። ይግባኙም ፡ የቀረበው ፡ በዚሁ ፡ ውሳኔ ፡ ላይ ፡ ነው ።

መልስ ፡ ሰጭዎች ፡ ማኅበሩ ፡ እንዲፈርስ ፡ የጠየቁት ፡ ፩ኛ/ በመልስ ፡ ሰጭዎቹና ፡ በይግባኝ ፡ ባዩ ፡ መካከል ፡ አለመግባባትና ፡ ብርቱ ፡ ንትርክ ፡ ተፈጥሯል ፤ ፪ኛ/ ይግ ባኝ ፡ ባዩ ፡ የማኅበሩን ፡ የሂሳብ ፡ ደብተሮች ፡ ለማሳየትም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ኦዲተር ፡ ተሹሞ ፡ ሂሳብ ፡ እንዲያደርግ ፡ ፈቃደኛ ፡ አልሆነም ፤ እንዲሁም ፡ የመልስ ፡ ሰጭዎ ችን ፡ ድርሻ ፡ ለመክፈል ፡ አልፈለገም ፡ በማለት ፡ ነው ። ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ በበኩሉ ፡ ማኅ በሩ ፡ ሊፈርስ ፡ አይገባውም ፡ በማለት ፡ የሚከራከረው ፤

፩ኛ/ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ወጭ ፡ ሁሉ ፡ ከኪሱ ፡ አውጥቶ ፡ ሥራ ውን ፡ ሊያቋቁምና መልስ ፡ ሰጭዎችም ፡ ለአምስት ፡ ዓመት ፡ በደመወዝ ፡ ሊያገለ ግሉ ፡ ከአምስት ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ ባለዕኩል ፡ ሆነው ፡ ትርፉን ፡ ዕኩል ፡ ሊካፈሉ ፡ ይግ ባኝ ፡ ባዩና ፡ መልስ ፡ ሰጭዎቹ ፡ ሮም ፡ ላይ ፡ ባደረጉት ፡ ስምምነት ፡ መሠረት ፡ ይግ ባኝ ፡ ባዩ ፡ ማናቸውንም ፡ ወጭ ፡ ከፍሎ ፡ የተባለው ፡ ማኅበር ፡ የተቋቋመ ፡ ስለሆነ ፡ መልስ ፡ ሰጭዎች ፡ ለማህበሩ ፡ ማቋቋሚያ ፡ ግማሹን ፡ ካፒታል ፡ እንደከፈሉና ፡ ባለ ዕኩል ፡ እንደሆኑ ፡ በማስመሰል ፡ ማኅበሩ ፡ ይፍረስልን ፡ የማለት ፡ ጥያቄ ፡ ያቀረቡት ፡ አላግባብ ፡ ነው ።

፪/ መልስ ፡ ሰጭዎች ፡ ማኅበሩ ፡ እንዲፈርስ ፡ የጠየቁት ፡ በቅን ፡ ልቦና ፡ ሳይሆን ፡ ይግባኝ ፡ ባዩን ፡ ለማሳጣትና ፡ ከሌላ ፡ ኢጣሊያዊ ፡ ጋር ፡ ተስማምተው ፡ ለመሥራት ፡ አቅደው ፡ በመሆኑ ፡ ሮም ፡ ላይ ፡ በተደረገው ፡ ስምምነት ፡ ግዴታቸውን ፡ ከመፈጸም በቀር ፡ ማኅበሩ ፡ እንዲፈርስ ፡ ሊጠይቁ ፡ ስለማይችሉ ፡ ጥያቄያቸው ፡ ውድቅ ፡ መሆን፡ ይገባዋል ፡ በማለት ፡ ነው ።

ይግባኝ ፡ ባዩና ፡ መልስ ፡ ሰጭዎች ፡ በየበኩላቸው ፡ ያቀረቡት ፡ ክርክር ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ያለው ፡ ሲሆን ፡ ከዚህ ፡ ቀጥለን ፡ ክርክራቸውን ፡ ከሕጉ ፡ ጋር ፡ በማዛመድ ፡ እናመዛዝናለን ። በመጀመሪያ ፡ ሮም ፡ ላይ ፡ ስለተደረገው ፡ ስምምነት ፡ የቀረበውን ፡ ክርክር ፡ እንመርምር ፤ ይግባኝ ፡ ባዩና ፡ መልስ ፡ ሰጭዎች ፡ ኤሮሴልና ፡ ኮዝሜቲክስ ፡ ለመሥራትና ፡ ለመሸጥ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ እናቋቁማለን ፡ ብለው ፡ የተስማሙ ፡ መሆናቸው ፡ አልተካደም ። ነገር ፡ ግን ፡ መመልከት ፡ ያለብን ፡ ብላክ ፡ ፐርል ፡ የተባለው ፡ ኩባንያ ፡ የተቋቋመው ፡ በሮሙ ፡ ስምምነት ፡ አማካይነት ፡ ሳይሆን ፡ ይግባኝ ፡ ባይና ፡ መልስ ፡ ሰጭዎች ፡ የንግዱን ፡ ሕግ ፡ ተከትለው ፡ በተፈራረሙበት ፡ የመመስረቻ ፡ ጽሑፍና ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፡ መሆኑን ፡ ነው ። በመሠረቱ ፡ አንድ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ በሚያዝዘው ፡ መሠረት ፡ በተዘጋጀ ፡ የመመሥረቻ ፡ ጽሑፍና ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ አማካይነት ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ አግኝቶ ፡ ከተቋቋመ ፡ በኋላ ፡ የሚሠራውም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ የሰውነት ፡ መብቱን ፡ አጥቶ ፡ የሚፈርሰው ፡ በተቋቋመበት ፡ ደንብና ፡ በንግዱ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ነው ። ማኅበረተኞቹ ፡ ማኅበሩ ፡ ከመቋቋሙ ፡ በፊት ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ከተቋቋመ ፡ በኋላ ፡ ያደረጉት ፡ ግላዊና ፡ የውጭ ፡ ስምምነት ፡ በመተዳደሪያ ፡ ደንቡ ፡ የተጻፈውን ፡ ወይም ፡ በሕጉ ፡ የተደነገገውን ፡ ሊሽረውና ፡ ሕጋዊ ፡ ውጤት ፡ ሊያሳጣው ፡ አይችልም ። ምክንያቱንም ፡ ቀጥሎ እናስረዳለን ፤

ኃላፊነቱ ፡ የተወሰነ ፡ የግል ፡ ማኅበር ፡ የሚቋቋመው ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ በቁጥር ፡ ፭፻፲ ፡ ፭፻፲፪ ፡ ፭፻፲፫ ፡ ፭፻፲፬ ፡ ፭፻፲፭ ፡ እና ፡ ፭፻፲፮ ፡ በተጻፈው ፡ መሠረት ፡ የመመሥረቻ፡ ጽሑፍና ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ተዘጋጅቶ ፡ በቁጥር ፡ ፭፻፳ ፡ ፪፻፲፱ ፡ ፪፻፳ ፡ ፪፻፳፩ ፡ ፪፻፳፪ ፡ ፪፻፳፫ ፡ በታዘዘው ፡ መሠረት ፡ ደግሞ ፡ ለሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ በማስታወቂያ ፡ ከተገለጠና ፡ ከተመዘገበ ፡ በኋላ ፡ ነው ። በዚህ ፡ አኳኋን ፡ የተቋቋመ ፡ ኃላፊነቱ ፡ የተወሰነ ፡ የግል ፡ ማኅበር ፡ የሚመራውና ፡ የሚተዳደረው ፡ በደንቡና ፡ ሕጉ ፡ በሚያዘው ፡ መሠረት ፡ ነው ። እንዲሁም ፡ ሊፈርስ ፡ የሚችለው ፡ በንግድ ፡ ሕግ ፡ በቁጥር ፡ ፭፻፴፪ ፡ ንዑስ ፡ ቁጥር ፡ ፩ ፡ በተጻፈው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ነው ። ከዚህ ፡ ውጭ ፡ የተደረገ ፡ ግላዊ ፡ ስምምነት ፡ ማኅበሩን ፡ ከቶ ፡ ሊመለከተው ፡ አይችልም ። እንግዲህ ፡ ይግባኝ ፡ ባዩና ፡ መልስ ፡ ሰጭዎች ፡ ሮም ፡ ላይ ፡ ቀደም ፡ አድርገው ፡ የግል ፡ ስምምነት ፡ የተፈራረሙ ፡ መሆኑ ፡ ቢታወቅም ፡ የተባለው ፡ የግል ፡ ማኅበር ፡ የተቋቋመውና ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ ያገኘው ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ ተስማምተውና ፡ ፈርመው ፡ ባስመዘገቡት ፡ የመመሥረቻ ፡ ጽሑፍና ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ስለሆነ ፡ ሮም ፡ ላይ ፡ የተደረገው ፡ ስምምነት ፡ ስለማኅበሩ ፡ መፍረስ ፡ የቀረበውን ፡ ጥያቄ ፡ ሊመለከተው ፡ አይችልም ።

ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ የሮሙ ፡ ስምምነት ፡ ተፈጻሚነት ፡ አለው ፡ በማለት ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በቁጥር ፡ ፩ሺ፯፻፴፩ ፡ እና ፡ ፩ሺ፯፻፳፯ ፡ የተጻፈውን ፡ ድንጋጌ ፡ ጠቅሶ ፡ ተከራክሯል ። በቁጥር ፡ ፩ሺ፯፻፴፩ ፡ ንዑስ ፡ ቁጥር ፡ ፩ ፡ የተጻፈው ፡ በሕጉ ፡ አግባብ ፡ የተጻፉ ፡ ውሎች ፡ በተፈራረሚቻቸው ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ሕግ ፡ ናቸው ፡ ይላል ። በዚህ ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ሮም ፡ ላይ ፡ የተፈራረሙት ፡ ውል ፡ በይግባኝ ፡ ባዩና ፡ በመልስ ፡ ሰጭዎች ፡ መካከል ፡ ሕግ ፡ ነው ፡ ብንልም ፡ ኩባንያው ፡ የተቋቋመው ፡ በመመሥረቻ ጽሑፍና ፡ በመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፡ ስለሆነ ፡ ይህ ፡ ውል ፡ ኩባንያውን ፡ የሚ

መለከት ፡ አይደለም ። ከዚህም ፡ በላይ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ሮም ፡ ላይ ፡ የተደረገውን ፡ ውል ፡ ተስማምተው ፡ የፈረሙ ፡ ቢሆንም ፡ ከዚህ ፡ ስምምነት ፡ በኋላ ፡ ኩባንያው ፡ የሚቋቋምበትን ፡ ዓላማና ፡ ሥራ ፡ እንዲሁም ፡ የያንዳንዱን ፡ ማኅበረተኛ ፡ የአክሲዮን ፡ ድርሻ ፡ መብቱንና ፡ ግዴታውንም ፡ ዘርዝረው ፡ ጽፈውና ፡ ተፈራርመው ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንቡንም ፡ አዘጋጅተው፡ የተባለውን ፡ የግል ፡ ማኅበር ፡ ያቋቋሙ ፡ በመሆኑ ፡ የሮሙ ፡ ስምምነት ፡ በዚህ ፡ እንደተተካ ፡ ስለሚቆጠር ፡ ስለኩባንያው ፡ መፍረስ ፡ ጉዳይ ፡ በቀረበው ፡ ጥያቄ ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ። በቁጥር ፡ ፩ሺ፰፻፵፰ ፡ የተጻፈው ፡ አንዱን ፡ ውል ፡ በሌላ ፡ ውል ፡ ስለመተካት ፡ ይናገራል ። አንድ ፡ ውል ፡ በሌላ ፡ ውል ፡ ተተካ ፡ የሚባለው ፡ ተዋዋዮቹ ፡ የቀድሞውን ፡ ግዴታ ፡ በሌላ ፡ ግዴታ ፡ ለመተካት ፡ መፍቀዳቸውን ፡ ግልጥ ፡ በሆነና ፡ በማያጠራጥር ፡ አኳኋን ፡ ሲገልጡ ፡ ነው ። ይግባኝ ፡ ባዩና ፡ መልስ ፡ ሰጭዎቹ ፡ የተባለውን ፡ የግል ፡ ማኅበር ፡ ያቋቋሙበትን ፡ የመመሥረቻ ፡ ጽሑፍና ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ እንደተመለከትነው፡ የሮሙን ፡ ስምምነት ፡ ለማስቀረት ፡ እንደፈቀዱ ፡ ያሳያል ። ስለዚህ ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ የጠቀሳቸው ፡ አንቀጾች ፡ ክርክሩን ፡ የማይደግፉ ፡ በመሆናቸው ፡ ክርክሩን ፡ ውድቅ ፡ አድርገነዋል ።

ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ማኅበሩ ፡ የተቋቋመው ፡ ካፒታሉን ፡ በሙሉ ፡ ራሴ ፡ ከፍዩ ፡ ነው ፤ መልስ ፡ ሰጭዎች ፡ የከፈሉት ፡ ገንዘብ ፡ የለምና ፡ ማኅበሩ ፡ እንዲፈርስ ፡ ለመጠየቅ ፡ መብት ፡ የላቸውም ፡ ብሏል ። እላይ ፡ እንደገለጥነው ፡ አንድ ፡ ኩባንያ ፡ ሲቋቋም ፡ እያንዳንዱ ፡ ማኅበረተኛ ፡ ያገባው ፡ የመዋጮ ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፡ በመመሥረቻ ፡ ጽሑፍ ፡ ላይ ፡ መገለጥ ፡ እንዳለበት ፡ ሕጉ ፡ ግልጥ ፡ አድርጎ ፡ ይደነግጋል ። የተባለው ፡ ኩባንያ ፡ የተቋቋመበትን ፡ የመመሥረቻ ፡ ጽሑፍና ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ እንደተመለከትነው ፡ ዋና ፡ ካፒታል ፡ ፹ሺ ፡ ብር ፡ ሆኖ ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ፵ሺ ብር ፡ መልስ ፡ ሰጭዎች ፡ ደግሞ ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ፳ሺ ፡ ብር ፡ አዋጥተው ፡ በሙሉ ፡ የተከፈለ ፡ መሆኑን፡ ይገልጣል ። እንግዲህ ፡ ማኅበሩ ፡ ሲቋቋም ፡ የያንዳንዳቸው ፡ መዋጮ ፡ ልክና ፡ ይኸውም ፡ የተከፈለ ፡ መሆኑ ፡ ታውቆ ፡ የተመዘገበ ፡ ሲሆን ፡ ድርሻቸውን ፡ አልከፈሉምና፡ መብት ፡ የላቸውም ፡ በማለት ፡ የቀረበው ፡ ክርክር ፡ ዋጋ ፡ የለውም ። ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ እንደሚለው ፡ የመልስ ፡ ሰጭዎቹን ፡ ድርሻ ፡ ከፍሎ ፡ እንደሆን ፡ ባግባቡ ፡ ይጠይቃል፡ እንጂ ፡ በዚህ ፡ የተነሳ ፡ የማኅበሩን ፡ ሕጋዊ ፡ ሰውነትና ፡ የማኅበረተኞቹን ፡ ሕጋዊ ፡ መብት ፡ ሊቀንስባቸው ፡ አይችልም ። አንድ ፡ ማኅበረተኛ ፡ ከኪሱም ፡ አውጥቶ ፡ ከፍሎ ፡ ይሁን ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ከፍሎለት ፡ የማኅበር ፡ አባል ፡ ከሆነ ፡ የአባልነት ፡ መብት ፡ አለው ። ሌላው ፡ ማኅበረተኛ ፡ ከፍየልህ ፡ ነበር ፡ በማለት ፡ መብቱን ፡ ሊገፈው ፡ አይችልም ።

መልስ ፡ ሰጭዎች ፡ የማኅበሩ ፡ መሥራች ፡ አባሎች ፡ እንደመሆናቸው ፡ መጠን ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ በቁጥር ፡ ፭፻፵፪ ፡ እና ፡ ፪፻፲፰ ፡ በሚያዝዘው ፡ መሠረት ፡ ማኅበሩ ፡ እንዲፈርስ ፡ ጠይቀዋል ። ለዚህም ፡ ካቀረቡት ፡ ምክንያት ፡ አንዱ ፡ በይግባኝ ፡ ባዩና ፡ በመልስ ፡ ሰጭዎች ፡ መካከል ፡ ብርቱ ፡ ንትርክና ፡ ጭቅጭቅ ፡ መፈጠሩን ፡ ነው ። ያቀረቡትን ፡ ማስረጃ ፡ እንደተመለከትነው ፡ በአንደኛው ፡ መልስ ፡ ሰጭና ፡ በይግባኝ፡ ባዩ ፡ መካከል ፡ አለመግባባት ፡ መፈጠሩንና ፡ በዚህም ፡ የተነሳ ፡ እየተወነጃጀሉ ፡ የማኅበሩ ፡ ሥራ ፡ መቆሙን ፡ ለመረዳት ፡ ችለናል ። አለመግባባትና ፡ ጭቅጭቅ ፡ የግል ፡ ማኅበር ፡ እንዲፈርስ ፡ ከሚያደርጉት ፡ ምክንያቶች ፡ አንዱ ፡ ስለሆነ ፤ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ማኅበሩ ፡ እንዲፈርስ ፡ ያዘዘው ፡ በሚገባ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ውሳኔውን ፡ አጽንተን ፡ ይግባኙን ፡ አሰናብተናል ።

ለከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይጻፍ ።

ጥር ፡ ፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የሰጠነውን ፡ የማገድ ፡ ትዕዛዝ ፡ አንስተናል ።

SUPREME IMPERIAL COURT

Addis Ababa, Div. No. 1

Justices:

Afenegus Teshome Haile Mariam

Ato Tadesse Tekle Giorghis

Kegnazmatch Mulat Beyene

HABIB KEBIR v. DANIEL EGU

Civil Appeal No. 533-60

Commercial Law—Dissolution of a private limited company—additional evidence on appeal—serious disagreement as a good cause for dissolution—Obligations preceding the memorandum and articles of association— Civ. Code Arts. 1731, 1828, *Civ. Proc. Code Arts.* 327. 345*(1) (a) (b); Comm. Code Arts.* 542, 218, 510, 512, 516—518, 314, 520, 219—223, 524 *(1).*

On appeal from the decision of the High Court holding that disagreement that existed between the appellant and the respondents justified the dissolution of the Company they had jointly established.

Held: Decision affirmed.

1. Additional evidence on appeal is permitted only where the provisions of Arts. 345(1) (a) & (b), Civ. Proc. Code are satisfied.

2. The existence of a serious disagreement among the partners of an enterprise is a good cause for the dissolution of the enterprise.

3. Private agreements entered into by members of a Company prior to or after the formation of the Company may not affect or derogate legal provisions or the provisions contained in the memorandum or Articles of Association.

JUDGMENT

The Appellant, pursuant to Article 327 of the Civil Procedure Code, applied for permission to call additional witnesses. On appeal additional evidence may be adduced pursuant to Article 345 (1) (a) and (b) only where

1. the Court from whose decree or order the appeal is preferred has refused to admit evidence which ought to have been admitted;

2. the calling of additional evidence is deemed necessary for determination of the matter in dispute or in the interests of justice.

Appellant had prayed in the High Court for permission to call witnesses. He sought to prove by witnesses that the Respondents had repeatedly requested the sale of the factory, that the Respondents intended to carry out commercial activities with another person and that they repeatedly requested to return to their country of origin. The High Court denied the application for lack of good cause. We find the order of the High Court sustainable and shall herein below set forth the reasons.

The Plaintiffs, present Respondents, brought an action for the dissolution of the company pursuant to Article 542 and 218 of the Commercial Code. They have set forth in detail the causes for dissolution. The Court has to determine whether the cause alleged is good and sufficient for the dissolution, and should it so determine it shall pronounce the dissolution of the company; if otherwise it shall reject the application. The Respondents have shown that there exists serious disagreement between them and the Appellant did not disprove this in his defence. The Appellant seeks to prove that Respondents expressed their intention to sell the factory, that they planned to carry out commercial activities with another person and that they had expressed their desire to return to their country. The Appellant did not seek to disprove the reasons given by the Respondents. Therefore, we find that the High Court properly rejected the Appellant's application to introduce additional evidence.

We shall now revert to the main issue. From an examination of the High Court record, it appears that Plaintiffs, present Respondents, applied to the High Court for the dissolution of a private limited company carrying out commercial activities under the designation "Black Pearl" and for the appointment of liquidators. The High Court, after hearing the Appellant pronounced the dissolution of the company and the appointment of liquidators. The Appeal is preferred from this decision.

The Respondents applied for the dissolution of the company alleging that 1. Serious disagreement exists between the Respondents and the Appellant; 2. Appellant refused the Respondents access to the company's books and did not consent to the appointment of an auditor to audit the company's book and was not willing to distribute their share in the profits. The Appellant contends that the company should not be dissolved on the ground that:

1. The company was formed pursuant to the agreement entered into between Appellant and Respondents in Rome whereby Appellant undertook to establish the company at his own expenses and the Respondents undertook to render him services at fixed salaries for a period of five years and at the expiration of which it was provided that they would share equally with the Appellant in the profit; that the Appellant established the company with his own expense; that the request for the dissolution of the company made by the Respondents purporting to have contributed half of the capital for the formation of the company and purporting to be joint owners of the company is not proper.

2. The Respondents' request for the dissolution of the company is not made in good faith but to discredit the Appellant's business acumen and with intent to carry out commercial activities with a certain Italian and therefore the Respondents are bound by the Rome contract and may not request the dissolution of the company. The contentions rendered by the Appellant and Respondents have been summarized herein above and we shall now proceed to consider these contentions in light of the relevant legal provisions. We shall at the outset consider the argument advanced with respect to the Rome contract. It has not been contested that the Appellant and Respondents agreed to form a partnership for the manufacture and sale of aerosol and cosmotics. However, it is to be noted that the business organization designated "Black Pearl" was not formed by virtue of the Rome contract but pursuant to the memorandum and articles of association signed by the Appellant and Respondents in compliance with the Commercial Code. The cardinal rule is that where a business organization is formed pursuant to a memorandum and articles

of association duly drawn in accordance with the Commercial Code said business organizations shall acquire legal personality, and shall be managed in accordance with the law, the memorandum and articles of association. Private agreements entered into by members of the company prior to or after the formation of the business organization may not affect or derogate legal provisions or the provisions contained in the memorandum or articles of association and we shall herein below set forth the reasons therefore.

A private limited company is formed after the memorandum and articles of association thereof are drawn pursuant to the provisons of Articles 510, 512, 516, 517, 518 and 314 of the Commercial Code and after the said business organization is made known to third parties and is registered pursuant to Articles 520, 219, 220, 221, 222 & 223 of the Commercial Code. A private limited company formed in such manner shall be managed and shall operate in accordance with the law and its by-laws. Likewise it may be dissolved in accordance with Article 524 (1) of the Commercial Code. Any other private agreement shall not affect the company. Although the Appellant and Respondents had earlier signed an agreement in Rome, the said company was formed and acquired legal personality by virtue of the memorandum and articles of association signed by both parties and by virtue of the registration thereof. Therefore, the Rome contract is not material in considering the request for the dissolution of the company.

The Appellant contended that the Rome contract is relevant to the matter in dispute and invoked Articles 1731 and 1828 of the Civil Code in support thereof. Article 1731 (1) provides that the provisions of a contract lawfully formed shall be binding on the parties as though they were law. Even if we hold that by virtue of these provisions the Rome contract is law between the Appellant and the Respondents, this contract may not affect the company because it was formed pursuant to the memorandum and articles of association. Furthermore, although both parties agreed to and signed the Rome contract, they had thereafter drawn and signed the memorandum and articles of association wherein the business purpose of the company, the amount of subscription and the rights and obligations of each member were set forth in detail. Therefore, the Rome contract is deemed to have been substituted by the memorandum and articles of association and it does not have any bearing on the application seeking the dissolution of the company. Article 1828 relates to novation. Novation shall be deemed to occur when the parties express the unequivocal intention to substitute the original obligation by another. The memorandum and articles of the association manifest the Appellant's and Respondents' intentions to extinguish the Rome contract. Therefore, the legal provisions invoked by the Appellant do not support his argument and we do not therefore find this argument tenable.

The Appellant stated that he had subscribed the whole amount of the capital for the formation of the company and that as the Respondents had not made any contribution, they have no right to request the dissolution of the company. As we have already observed, the law clearly provides that when a company is formed the amount of contribution made by each member shall be shown in the memorandum of association. The memorandum and articles of association establishing the company show that the amount of the company's capital is E $ 80,000. The Appellant contributed E $ 40,000 and each of the Respondents contributed E $ 20,000 and that said capital was fully paid up. Whereas the amount of capital subscribed and fully paid up by each member was known at the time of the formation and registration of the company, the contention that Respondents did not pay

their contribution and may not therefore request the dissolution of the company is not sustainable. If the Appellant as alleged has paid the contribution due from the Respondents then he may bring an action to recover said sum but he may not on this ground cause the company to be divested of legal personality and the members to be deprived of their legal rights. Where one becomes a member of a company either by paying his contribution from his own pocket or by having it paid by someone else, on his behalf then he acquires all the rights inherent in membership. Another member may not divest him of his rights on the ground that he had paid his contribution on his behalf. As the Respondents are the founders of the company, they have requested the dissoluton of the company pursuant to Articles 542 and 218. One of the grounds they raised in favour of dissolution is the existence of serious disagreement between the Appellant and the Respondents. The evidences introduced by the Respondents tends to show that disagreement exists between them and that this disagreement engendered recrimination against one another which resulted in the cessation of the company's operation. Whereas the existence of serious disagreement among the members is one of the good causes for dissolution of a private limited company, the order of the High Court for the dissolution of the company is valid. Therefore we hereby affirm the decision of the High Court and dismiss the appeal.

The High Court shall be so notified.

We have lifted the injunction ordered on January 11, 1969.

ጠቅላይ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡

አዲስ ፡ አበባ ።

ዳኞች ፤

አፈንጉሥ ፡ ተሾመ ፡ ኃይሌ ፡ ማርያም ፤

አቶ ፡ ታደሰ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፤

አቶ ፡ ኃይሌ ፡ በፀሎት ።

የይግባኝ ፡ መዝገብ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፸፩/፷፩፡

የፍርድ ቤት ሥልጣን ፤ ክስን ወደ ሌላ ሥፍራ ማዛወር ፤ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥሮች ፮፻፶፩፣፮፻፶፪(ለ) ፤ ፫፻፹፫ ሀ/መ ፤ ፯፻፶፯ ፣ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥሮች ፺፱ ፤ ፩፻—፩፻፬ ፤ ፩፻፯፣፯ ፤ ፩፻፱ ፤ ፩፻፲፯ ፤

ዐቃቤ ሕጉ ጉዳዩ ወደ አዲስ አበባ ከፍተኛው ፍ/ቤት ተዛውሮ እንዲታይ ሲል ያቀረበውን ጥያቄ ፍ/ቤት ስላልተቀበለው የቀረበ ይግባኝ ፤

ውሳኔ ፤ ውሳኔው ተሽሯል ፡

፩· አብዛኛውን ጊዜ የወንጀል ክስ መቅረብ ያለበት ወንጀሉ በተፈጸመበት ሥፍራ በሚገኘው ፍ/ቤት ነው።

፪· ጉዳዩ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ከቁጥር ፩፻ እስከ ፩፻፬ ውስጥ ከተነገሩት አንዱ ሲሆን ግን መቅረብ ያለበት ዐቃቤ ሕጉ በመረጠው ፍ/ቤት ነው ።

ውሣኔ ፤

ይህ ፡ ይግባኝ ፡ የቀረበው ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ጥቅምት ፡ ፲፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በሰጠው ፡ ትዕዛዝ ፡ ላይ ፡ ነው ። መዝገቡን ፡ መርምረናል ። ከሳሹ ፡ የአሁኑ ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ በመልስ ፡ ሰጭው ፡ ላይ ፡ የወንጀል ፡ ክስ ፡ አቅርቦ ፡ ክሱም ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ አስቻለው ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲታይለት ፡ ጠይቋል። ተከሳሽ ፡ የአሁኑ ፡ መልስ ፡ ሰጭ ፡ በጠበቃው ፡ አማካይነት ፡ እምነት ፡ ክህደት፡ ከመስጠቱ ፡ በፊት ፡ ክሱ ፡ መታየት ፡ የሚገባው ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ሳይሆን ፡ ወንጀሉ ፡ በተሠራበት ፡ ሥፍራ ፡ ባስቻለው ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ተቃውሟል ። የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤትም ፡ መቃወሚያውን ፡ ተቃውሞ ፡ ከባዱ ፡ ወንጀል ፡ ተሠራ ፡ የሚባለው ፡ በሐረር ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ስለሆነ ፤ ክሱን ፡ እዚህ ፡ ለአነስተኛው ፡ መስርቶ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ወንጀል ፡ ከተፈጸመበት ፡ ቦታ ፡ ምስክሮችና ፡ ተከሳሽ ፡ ከሐረር ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ መጥተው ፡ ይታይ ፡ ማለት ፡ ተገቢ ፡ አይደለም ፡ ብሎ ፡ ተችቶ ፡ ክሱ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ በቁጥር ፡ ፺፱ ፡ ፩፻ ፡ መሠረት ፡ ሐረር ፡ ላስቻለው ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀርቦ ፡ እንዲታይ ፡ መዝገቡ ፡ በሬጅስትራሩ ፡ በኩል ፡ ሐረር ፡ ላስቻለው ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲላክ ፡ አዝዞ ፡ አሰናብቷቸዋል ። ይግባኙም ፡ የቀረበው ፡ በዚህ ፡ ትዕዛዝ ፡ ላይ ፡ ነው ።

ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ በጻፈው ፡ የይግባኝ ፡ ማመልከቻ ፡ ይግባኝ ፡ ያለበትን ፡ ምክንያት ፡ ገልጧል ። ያቀረበውም ፡ ምክንያት ፤ ተከሳሹ ፡ የአሁኑ ፡ መልስ ፡ ሰጭ ፡ የተከሰሰው ፡ በአራት ፡ ዓይነት ፡ ወንጀል ፡ ሲሆን ፡ ወንጀሉም ፡ የተፈጸመው ፡ በአዲስ ፡ አበባና ፡

በድሬዳዋ ፡ ስለሆነ ፡ በዚሁ ፡ ረገድ ፡ የቀረበው ፡ ክስ ፡ የሚታይበትን ፡ ሥፍራ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ በቁጥር ፡ ፩፻፯ ፡ መሠረት ፡ የሚወስነው ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ሲሆን ፡ ሐረር ፡ ላስቻለው ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይተላለፍ ፡ የተባለው ፡ በማይገባ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ነው ።

ተከሳሽ ፡ የአሁኑ ፡ መልስ ፡ ሰጭ ፡ በበኩሉ ፡ ክሱ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መታየት ፡ አይገባውም ፡ የሚልበትን ፡ ምክንያት ፡ መጋቢት ፡ ፳ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በተጻፈ ፡ ሰባት ፡ ገጽ ፡ ማመልከቻ ፡ ዘርዝሮ ፡ አቅርቧል ። ፍሬ ፡ ነገሩም ፡ አብዛኛው ፡ ወንጀል ፡ ተፈጽሟል ፡ የሚባለውም ፡ ሆነ ፡ ውጤቱም ፡ የታወቀው ፡ የግል ፡ ከሳሽና ፡ ተከሳሽ ፡ በሚኖሩበት ፡ ሥፍራ ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ የወንጀሉም ፡ ክስ ፡ በፖሊሱ ፡ የተመረመረውና ፡ ለክፍሉ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ የቀረበው ፡ ሐረር ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ስለሆነና ፡ በመከላከያም ፡ አቀራረብ ፡ በኩል ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ መታየቱ ፡ በተከሳሹ ፡ ላይ ፡ ችግር ፡ ስለሚፈጥር ፡ በሥነ ፡ ሥርዓቱ ፡ ሕግ ፡ በቁጥር ፡ ፮ ፤ ፺፱ ፤በተጻፈው ፡ መሠረት ፡ ሐረር ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ባስቻለው ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲታይ ፡ የታዘዘው ፡ ይጽናልኝ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ይህን ፡ የማይቀበለኝ ፡ ቢሆን ፡ ደግሞ ፡ በቁጥር ፡ ፩፻፲፯(፪) ፡ መሠረት ፡ ክሱ ፡ ተነጥሎ ፡ እንዲታይ ፡ ይታዘዝልኝ ፡ የሚል ፡ ነው ።

እንግዲህ ፡ በሁለቱም ፡ በኩል ፡ የቀረበውን ፡ የሕግ ፡ ክርክር ፡ በማመዛዘን ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሰጠው ፡ ትዕዛዝ ፡ በሚገባ ፡ መሆን ፡ አለመሆኑን ፡ እንመረምራለን ። ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ያቀረበውን ፡ የክስ ፡ ማመልከቻ ፡ እንዳየነው ፡ መልስ ፡ ሰጭው ፡ ፈጽሟል ፡ የተባለው ፡ ወንጀል ፡ በአራት ፡ ተከፋፍሏል ። ከነዚህም ፡ ውስጥ ፡ አንዱን ፡ ወንጀል ፡ የሠራው ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ላይ ፡ ነው ፡ ሲባል ፤ ሁለተኛውን ፡ ወንጀል ፡ ደግሞ ፡ የሠራው ፡ ድሬዳዋ ፡ ከተማ ፡ ነው ፡ ተብሏል ። ሦስተኛውንና ፡ አራተኛውን ፡ ወንጀሎች ፡ የት ፡ ሥፍራ ፡ እንደፈጸመ ፡ አልተገለጠም ። እንዲያውም ፡ የነዚህን ፡ የሦስተኛውንና ፡ የአራተኛውን ፡ ወንጀሎች ፡ ክስ ፡ ለማየት ፡ ሥልጣን ፡ ያላቸው ፡ የበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ናቸው ፡ ተብሏል ። ቢሆንም ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ በቁጥር ፡ ፩፻፱ (፫) መሠረት ፡ ከአንደኛው ፡ ክስ ፡ ጋር ፡ አጣምሮ ፡ ለከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አቅርቧል ። እንግዲህ ፡ ጥያቄው ፡ ክሱ ፡ የሚሰማውና ፡ የሚታየው ፡ የት ፡ ሥፍራ ፡ በሚያስችለው ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ሆኖ ፡ ይታያል ። የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ በወንጀል ፡ ነገር ፡ ረገድ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ስላላቸው ፡ ሥልጣን ፡ በቁጥር ፡ ፮ ፡ እና ፡ በአንደኛው ፡ ሠንጠረዥ ፡ በተጻፈው ፡ መሠረት ፡ ይደነግጋል ። በአንደኛው ፡ ሠንጠረዥ ፡ የተጻፈው ፡ የወንጀሉን ፡ ዓይነትና ፡ ወንጀሉንም ፡ ለማየት ፡ ሥልጣን ፡ ያለውን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይናገራል። በቁጥር ፡ ፮ ፡ የተጻፈው ፡ ደግሞ ፡ ከቁጥር ፡ ፺፱ ፡ እስከ ፡ ፩፻፯ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ እንዲያስችሉ ፡ በተወሰነላቸው ፡ የግዛት ፡ ክልል ፡ ውስጥ ፡ የተሠራውን ፡ የወንጀል ፡ ነገር ፡ ለማየት ፡ ሥልጣን ፡ ያላቸው ፡ መሆኑን ፡ ይናገራል። ይኸውም ፡ የአንድ ፡ ወንጀል ፡ ክስ ፡ የሚቀርበው ፡ የት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነው ፡ የማለት፡ ጥያቄ ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፤ በአንደኛው ፡ ሠንጠረዥ ፡ የተጻፈውን ፡ ቀጥሎም ፡ በቁጥር ፡ ፮ ፡ ማለት ፡ ከቁጥር ፡ ፺፱ ፡ እስከ ፡ ፩፻፯ ፡ የተደነገገውን ፡ መመልከት ፡ ያስፈልጋል ፡ ማለት ፡ ነው ። እንግዲህ ፡ በዚህ ፡ በቀረበልን ፡ ነገር ፡ ክሱ ፡ የሚታይበትን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ለመወሰን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ኃይለ ፡ ቃል ፡ የጠቀስናቸውን ፡ ድንጋጌዎች ፡ እንመልከት ፤

(ሀ) ስለአንደኛው ፡ ክስ ፤ እምነት ፡ ማጉደል ፡ በቁጥር ፡ ፯፻፵፩ ፡ እና ፡ ፯፻፵፪ ፡ (ለ) ፡ መሠረት ፡ የቀረበ ፡ ክስ ፡ ስለሆነ ፡ በሠንጠረዡ ፡ መሠረት ፡ ሥልጣኑ ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነው ። ተሠራ ፡ የተባለው ፡ ደግሞ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ላይ ፡ ስለሆነ ፡ የሚታይበት ፡ ሥፍራ ፡ በቁጥር ፡ ፺፱ ፡ መሠረት ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ነው ።

(ለ) ስለሁለተኛው ፡ ክስ ፤ ስለአታላይነት ፤ በቁጥር ፡ ፮፻፶፮ ፡ መሠረት ፡ የቀረበ ፡ ክስ ፡ ስለሆነ ፡ በሠንጠረዡ ፡ መሠረት ፡ ሥልጣኑ ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነው ። ተሠራ ፡ የተባለው ፡ ደግሞ ፡ ድሬዳዋ ፡ ስለሆነ ፡ የሚታይበት ፡ ሥፍራ ፡ በቁጥር ፡ ፺፱ ፡ መሠረት ፡ ድሬዳዋ ፡ ነው ።

(ሐ) ስለሦስተኛውና ፡ ስለአራተኛው ፡ ክስ ፤ ሐሰተኛ ፡ ሰነድ ፡ ስለመፍጠር ፤ በቁጥር ፡ ፫፻፹፫ ፡ (ሀ) (መ) የቀረበ ፡ ክስ ፡ ስለሆነ ፡ ሥልጣኑ ፡ የአውራጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ነው ። ወንጀሉ ፡ የተሠራበት ፡ ቦታ ፡ ስላልታወቀ ፡ የሚታይበት ፡ ሥፍራ ፡ በቁጥር ፡ ፩፻፰ ፡ በንዑስ ፡ ቁጥር ፡ (ሀ) መሠረት ፡ ነገሩን ፡ ለማየት ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ማናቸውም ፡ የአውራጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤት በሚያስችልበት ፡ ሥፍራ ፡ ነው ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደተመለከተው ፡ ተከሳሹ ፡ የተከሰሰባቸው ፡ ሁለት ክሶች ፡ በቁጥር ፡ ፺፱ ፡ እና ፡ በሠንጠረዡ ፡ መሠረት ፡ መታየት ፡ የሚገባቸው ፡ ሐረር ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ባስቻለው ፡ ከፍተኛው ፍርድ ፡ ቤት ፤ እንዲሁም ሦስተኛና ፡ አራተኛው ፡ ክስ መታየት ያለበት ሥልጣን ባለው በማናቸውም ፡ አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቢሆንም ፤ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ በቁጥር ፡ ፩፻፺፯ ፡ ፩፻፺፱ ፡ (፫) ፡ ፩፻፲፯ ፡ በተጻፈው ፡ መሠረት ፡ ክሱን ፡ አጣምሮ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ላስቻለው ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አቅርቧል ። ይህም ፡ ሕጋዊ ፡ አሠራር ፡ ነው ። ምክንያቱም ቀጥሎ ያለው ፡ ነው ፤

በመሠረቱ ፡ ሕግ ፡ ሲደነገግ ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ ሊነሳ ፡ የሚችለውን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሁኔታ ፡ የሚመለከቱ ፡ ድንጋጌዎች ፡ እንዲይዝ ያስፈልጋል ። የሥነ ሥርዓቱም ሕግ ፡ በክስ አቀራረብ ፡ ረገድና ፡ ክሱም ፡ ስለሚታይባቸው ፡ ቦታዎች ፡ እንዲሁም ስለ ፍርድ ቤቶች ሥልጣን ፡ የሚያጋጥሙትን ፡ ልዩ ልዩ ፡ ሁኔታዎች ፡ የሚመለከቱ ፡ ድንጋጌዎች ፡ እንዲኖሩበት ተደርጓል ። እነዚህ ፡ ድንጋጌዎች ፡ መታየት ያለባቸው ፡ ተነጥለው ፡ ሳይሆን አንዱን ከሌላው ፡ ጋር ፡ በማዛመድና ፡ በማገናዘብ ነው ። ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ አንድ ፡ ድንጋጌ ፡ ብቻውን ፡ አይታይም ፤ ከሌላው ፡ ጋር ፡ በማገናዘብ ፡ መሟላት አለበት ። ከሌላው ጋር ሳይገናዘብ ፡ በቁሙ የሚታይና ፡ የሚተረጎም ፡ ከሆነማ ፡ ሕጉ ፡ ፍጹምነት ፡ የሌለውና ፡ አንዱ ፡ ድንጋጌ ፡ ከሌላው ፡ ጋር ፡ ተቃራኒና አፍራሽ ፡ መስሎ ይታያል ።

እንግዲህ ስለክስ ፡ አቀራረብ ፡ ክሱ ፡ ስለሚታይበት ቦታና ፡ ነገሩም ፡ ስለሚሰማበት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የተጻፉት ፡ ድንጋጌዎች ፡ አንዱን ፡ ከሌላው ጋር ፡ በማገናዘብ፡ ስንመለከታቸው ፡ በመልስ ፡ ሰጭው ፡ ላይ ፡ የቀረበው ፡ ክስ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ላስቻለው፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የቀረበው ፡ በሚገባ ፡ ሆኖ ፡ እናገኘዋለን ።

በመሠረቱ በቁጥር ፡ ፺፱ ፡ በተጻፈው መሠረት ፡ የወንጀል ፡ ክስ ፡ የሚታየው ፡ ወንጀሉ ፡ በተፈጸመበት ፡ ሥፍራ ሥልጣን ፡ ባለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነው ። ይህ ፡ ድንጋጌ ቢኖርም ፡ ቅሉ ፡ በቁጥር ፡ ፩፻ ፡ ፩፻፩ ፡ ፩፻፪ ፡ ፩፻፫ ፡ ፩፻፬ ፡ የተጻፈው ሁኔታ ፡ ባጋጠመ ፡ ጊዜ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ክሱን ፡ ሲያቀርብ በቁጥር ፺፱ ፡ የተጻፈውን ፡ ድንጋጌ ፡ ላይከተል ፡ ይችላል ። እንዲሁም ፡ በቁጥሩ ፡ በተጻፈው ፡ መሠረት ፡ በተከሳሹ ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ክሶች ፡ በቀረቡ ፡ ጊዜ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ በክሱ ፡ ማመልከቻ ፡ የተመለከተው ፡ እያንዳንዱ ፡ ክስ ፡ በቁጥር ፡ ፺፱ ፡ መሠረት ፡ የሚታዩበት ፡ ሥፍራ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥፍራ ፡ ቢሆንም ፤ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ በቁጥር ፡ ፺፱ ፡ የተጻፈውን ፡ ድንጋጌ ፡ እንዲከተል ፡ አይገደድም ። ይኸውም ፡ ከቁጥር ፡ ፩፻፩ ፡ እስከ ፡ ፩፻፬ ፡ የተጻፈው ፡ ሁኔታ ፡ ባጋጠመው ፡ ጊዜና ፡ እንዲሁም ፡ በቁጥር ፡ ፩፻፲፮ ፡ መሠረት ፡ በሚቀርቡ ፡ የወንጀል ፡ ክሶች ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ በቁጥር ፡ ፭፻፺ ፡ በተደነገገው ፡ መሠረት ፡ ክሱ ፡ የሚታይበትን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይወስናል ፡ ማለት ፡ ነው ።

ከፍ ፡ ብለን ፡ እንደገለጥነው ፡ ተከሳሹ ፡ የአሁኑ ፡ መልስ ፡ ሰጭ ፡ ፈጽሟል ፡ በመ ባል ፡ የተከሰሰው ፡ በአራት ፡ ወንጀሎች ፡ ነው ። ሁለቱ ፡ ክሶች ፡ በሠንጠረዡ ፡ መሠ ረት ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሥልጣን ፡ ሲሆኑ ፡ በቁጥር ፡ ፺፱ ፡ መሠረት ፡ የሚታ ዩበት ፡ ቦታ ፡ ደግሞ ፡ አዲስ ፡ አበባና ፡ ድሬዳዋ ፡ ነው ። የቀሩት ፡ ሦስተኛውና ፡ አራተ ኛው ፡ ክሶች ፡ ደግሞ ፡ የአውራጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሥልጣን ፡ ሲሆኑ ፡ የሚታዩበትም፡ ቦታ ፡ በማናቸውም ፡ አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሆኖ ፡ ይታያል ። ነገር ፡ ግን ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ተከሳሹ ፡ የአሁኑ ፡ መልስ ፡ ሰጭ ፡ የተከሰሰባቸው ፡ ነገሮች ፡ አራት ፡ ዓይነ ትና ፡ ወንጀሎቹ ፡ የተፈጸሙበት ፡ ሥፍራና ፡ ነገሩን ፡ ለማየትም ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤትና ፡ የአውራጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቢሆንም ፡ ቅሉ ፡ ሦስተኛውና ፡ አራተኛው ፡ ክሶች ፡ በቁጥር ፡ ፩፻፱ ፡ ንዑስ ፡ ቁጥር ፡ ፫ ፡ መሠረት፡ ከአንደኛው ፡ ክስ ፡ ጋር ፡ ተጣምረው ፡ እንዲሁም ፡ ሁለተኛው ፡ ክስ ፡ በቁጥር ፡ ፩፻፲፮፡ መሠረት ፡ ከአንደኛው ፡ ክስ ፡ ጋር ፡ ተደርቦ ፡ ሁሉም ፡ ክሶች ፡ ባንድነት ፡ ሆነው ፡ በቁ ጥር ፡ ፩፻፯ ፡ መሠረት ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ለሚወስነው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መቅረብ ፡ ይኖርባ ቸዋል ። ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ እንዲቀርቡ ፡ የወሰነው ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ባስቻለው ፡ የከፍተ ኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነው ። እንግዲህ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ የሥነ ፡ ሥርዓቱ ፡ ሕግ ፡ የሚያዝ ዘውን ፡ ተከትሎ ፡ ያቀረበውን ፡ ክስ ፡ ተቀብሎ ፡ በመስማት ፡ ፈንታ ፡ ከባዱ ፡ ወንጀል ፡ የተፈጸመው ፡ ሐረር ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ነው ፡ በሚል ፡ አስተሳሰብ ፡ ወደዚያ ፡ እንዲ ዛወር ፡ የተወሰነው ፡ በሚገባ ፡ ሆኖ ፡ አላገኘነውም ።

መልስ ፡ ሰጭው ፡ በጻፈው ፡ ማመልከቻ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ በቁጥር ፡ ፩፻፲፮ ፡ ንዑስ ፡ ቁጥር ፡ ፪ ፡ መሠረት ፡ ክሱ ፡ ተነጥሎ ፡ ተፈጸመ ፡ በሚባ ልበት ፡ ቦታ ፡ እንዲታይ ፡ እንዲደረግለት ፡ ጠይቋል ። በቁጥር ፡ ፩፻፲፮ ፡ ንዑስ ፡ ቁጥር ፡ ፪ ፡ የተጻፈው ፡ የቀረቡት ፡ ክሶች ፡ ባንድነት ፡ መታየት ፡ አለባቸው ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የክ ሶቹ ፡ ባንድነት ፡ መታየት ፡ በተከሳሹ ፡ መከላከያ ፡ ችግር ፡ የሚያመጣበት ፡ የመሰለ ፡ እን ደሆነ ፡ ክሶቹ ፡ ተነጣጥለው ፡ ለየብቻቸው ፡ እንዲሰሙ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ፡ ይላል ። በዚህ ፡ ረገድ ፡ ክሱ ፡ ተነጥሎ ፡ ይታይልኝ ፡ በማለት ፡ የሚቀርበው ፡ ጥያቄ ፡ መቅረብ ፡ ያለበት ፡ ነገሩን ፡ ለሚያየው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለይግባኝ ፡ ሰሚው፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ስላልሆነ ፡ አልተቀበልነውም ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ በሰጠነው ፡ ምክንያት ፡ ሁሉ ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሰጠ ውን ፡ ትእዛዝ ፡ ሽረን ፡ ክሱ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀድሞ ፡ ቀር ቦበት ፡ እነበረው ፡ ችሎት ፡ እንዲታይ ፡ አዝዘናል ። ለከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይጻፍ ።

መጋቢት ፡ ፲፭ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡

SUPREME IMPERIAL COURT

Addis Ababa, Div. No. I

Justices:

Afenegus Teshome Haile Mariam

Ato Taddesse Tekle Giorghis

Ato Haile Betselot

Criminal Appeal No. 171/61

Jurisdiction—venue. - Crim. Pro. Code Arts. 99, 107,6,116,109,100-104; Penal Code Arts. 641. 642 (b), 383(a) (d), 656.

Appeal preferred against the order passed by the High Court rejecting the motion of the public prosecutor to transfer the case to a High Court in Addis Ababa.

Held: Reversed.

1. The general rule is that offences should be tried in the Court of the locality where the act was committed.
2. Where, however, the case falls under Arts. 100-104 of the Criminal Procedure Code the suit may be filed in a Court selected by the public prosecutor.

JUDGMENT

This appeal is preferred against the order passed by the High Court on Oct. 22, 1968. We have studied the file. The Public Prosecutor (present Appellant) preferred charges against the Respondent and moved that the offences be tried by the High Court sitting in Addis Ababa. The Defendant (present Respondent), represented by counsel, prior to entering his plea objected that the offence should be tried by the court within the local limits of whose jurisdiction said offence was alleged to have been committed. The High Court sustained the objection and held that as the more serious offence was allegedly committed in Harar Governorate General, it is not proper to file charges on the less serious offences in Addis Ababa and apply for the appearance in Addis Ababa of witnesses and the Defendant, residing in Harar. It dismissed the case; ordered the registrar to forward the record to the Harar High Court in order that the Court may try the offence pursuant to Articles 99-100 of the Criminal Procedure Code. Wherefor this appeal is taken.

In his memorandum of appeal, the Public Prosecutor has set forth the grounds of objection to the order appealed against. Grounds of objection are: that the Defendant (present Respondent) was charged on four counts; that the offences were committed in Addis Ababa and Diredawa; that in such cases Article 107 of the Criminal Procedure Code authorizes the Public Prosecutor to decide which court shall have jurisdiction to try the offences charged and that therefore the order passed by the Court to the effect that the offence be tried by the Harar High Court is erroneous.

The Defendant (present Respondent), on his part, has stated in detail, in his seven-page application, dated March 17, 1969, his arguments in support of the

contention that the case should not be tried in the Addis Ababa High Court. The substance of the application is: that most of the offences were allegedly committed and the consequences allegedly ensued in the area within which the injured party and the Defendant reside; that investigation into the offence was conducted by the police and the result thereof was forwarded to the Public Prosecutor at Harar; that trying the case in Addis Ababa would create inconvenience in introducing defence witnesses and that therefore the order passed by the High Court should be affirmed pursuant to Article 6, 99 and 100 of the Criminal Procedure Code. Should the application be rejected he requested the Court to order separate trials pursuant to Article 116(2).

Therefore, having considered the legal arguments presented by both parties, we shall examine whether the order passed by the High Court is appropriate. The Public Prosecutor's charge alleges that the Respondent committed four offences. One of these offences was allegedly committed in Addis Ababa, while the second was allegedly committed in Diredawa. It has not been disclosed where the third and fourth offences were committed. Indeed it has been averred that it is the lower courts that may exercise jurisdiction with respect to the third and fourth charges. However, pursuant to Article 109(3) of the Criminal Procedure Code, the Public Prosecutor joined these charges with the first charge and filed them in the High Court. Therefore, the question is which High Court may try the offences charged.

Article 6 and the first schedule of the Criminal Procedure Code define the jurisdiction of courts regarding criminal cases. The first schedule specifies the different kinds of offences and the court having jurisdiction to try said offences. Article 6 provides that in accordance with Articles 99-107 courts shall have the power to try offences committed within the local limits of their jurisdiction. Therefore, where a question arises regarding the court where a charge should be filed, it is necessary to refer to the First Schedule first and then to Article 6 which cross-refers to Article 99-107.

Hence, in the case at bar, we shall consider the provisions cited hereinabove to determine which court may exercise jurisdiction.

a) First charge - Breach of trust and aggravated breach of trust contrary to Articles 641 and 642 (b) Penal Code; in accordance with the first schedule this falls within the jurisdiction of the High Court. Since it was allegedly committed in Addis Ababa it is to be tried in Addis Ababa in accordance with Article 99.

b) Second charge - Fraudulent misrepresentation contrary to Article 656 Penal Code. This falls within the jurisdiction of the High Court in accordance with the First Schedule. Since it was allegedly committed in Diredawa it is to be tried in Diredawa in accordance with Article 99.

c) Third and Fourth charges since these deal with creating a false instrument contrary to Article 383(a) (d) Penal Code, it is within the jurisdiction of the High Court. Since the place where the offences were allegedly committed is not known it is to be tried in any Awraja court with material jurisdiction pursuant to Article 102(a).

As noted above, although the first two charges must be tried by the High Court at Harar pursuant to Article 99 and the First Schedule, and although the third and fourth charges may be tried by any Awraja court, the Public Prosecutor has joined and filed the charges in the Addis Ababa High Court. This is a lawful act and the reasons therefor are set forth hereinbelow.

The cardinal rule is that when a law is promulgated it must cover the different situations which are likely to arise in the future. The Criminal Procedure Code was designed to embrace provisions concerning the filing of charges, places of trial and jurisdiction of courts. These provisions must not be considered in isolation but as a whole by interrelating one with the other. A rule of law is never considered in isolation; it must be related to and supplement other rules of law. If it is considered and interpreted without having regard to other provisions the law will appear to be incomplete and one provision will appear to be contradictory and inconsistent with the other.

Thus, when we consider as a whole the provisions governing the framing of a charge, the place of trial and the jurisdiction of courts, we find that the charge against the Respondent was properly filed in the Addis Ababa High Court.

The general principle is that a criminal offence is tried at the place where the crime is committed by a court with jurisdiction in accordance with Article 99. However, in cases falling under Articles 100, 101, 102, 103, 104 the Public Prosecutor need not comply with Article 99. Where pursuant to Article 116 several charges are joined against the same defendant, the Public Prosecutor is not bound to act in accordance with Article 99, although the said provision may provide that each charge be tried in a different place. Consequently, by virtue of Article 107 the Public Prosecutor shall decide the court in which the charge shall be filed regarding cases that fall under Articles 101-104 and in charges filed pursuant to Article 116.

As we have stated above, the Respondent is charged with having committed four different offences. Pursuant to the schedule the two charges fall within the jurisdiction of the High Court and pursuant to Article 99 their places of trial are Addis Ababa and Diredawa. The third and fourth charges fall within the jurisdiction of the Awraja Court and it appears that they may be tried by any Awraja Court. Notwithstanding the fact that the Defendant is charged with having committed four different kinds of offences that the places wherein the offences were allegedly commited are different and that the courts exercising jurisdiction are the High Court with respect to some offences and the Awraja Court with respect to the rest, the third and the fourth charges may be joined with the first pursuant to Article 109, the second charge may be joined with the first pursuant to Article 116 and all charges ought to be filed with the court which the Public Prosecutor pursuant to Article 107 decides to have jurisdiction. He decided to file the charge in the Addis Ababa High Court. Thus, instead of trying the charges filed by the Public Prosecutor in conformity with the procedure, the High Court erroneously decided that the case be transferred to Harar Governorate General on the ground that the serious offence was committed there.

In his application, the Respondent requested pursuant to Article 116(2) that the offences charged be tried separately at the place wherein they were allegedly committed. Article 116(2) provides that all charges must be tried together but where the accused is to be embarassed in his defence, the court shall order that the charges be tried separately. A motion for separate trial should be made to the court of first instance and not to the Appellate court and therefore we have denied the motion.

Therefore, for the reasons stated hereinabove, we hereby quash the order passed by the High Court and remand the case to the Addis Ababa High Court for further proceeding.

March 20, 1969

የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤
አዲስ ፡ አበባ ።

ዳኞች ፤

አቶ ፡ አሰፋ ፡ ሊበን ፤

አቶ ፡ አበበ ፡ አውግቸው ፤

አቶ ፡ መሐመድ ፡ ብርሃን ፡ ኑርሁሴን ።

ከሳሽ ፤ ታንከሬ ፡ ጋርበን ፡ ኩባንያ ፡ ኃላፊነቱ ፡ የተወሰነ ፡

ተከሳሽ ፤ አቶ ፡ ሞላ ፡ ማሩ ፤

የክሱ ፡ ምክንያት ፡ ተገቢ ፡ ያልሆነ ፡ የንግድ ፡ ውድድር ፡ ተደረገ ፡ በማለት ፤
የፍርድ ፡ መዝገብ ፡ ቁጥር ፡ ፱፻፲፱/፶፱

የንግድ ሕግ ፣ ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር ፣ የንግድ ምልክት ስለማሳከር ፤ የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥሮች ከሺ.፪፻፶፯—ሺ.፪፻፷፭ ፤ የንግድ ሕግ ቁጥሮች ፴ ፤ ፵ ፤ ፵፯ ፥ ፶፰ ፤ ፻፴፩ ፤ ፻፵፩ ፥ ፻፶፰ ፥ ፻፶፱ ፤ ፻፷፩ ፤ ፻፷፮ ።

ተከሳሽ የከሳሽን የንግድ ምልክት እያወቀ በማሳከር ይጠቀምበታል በማለት የቀረበ ክስ ፣

ውሳኔ ፤ ተከሳሽ ተፈርዶበታል ፤
ስለ ልዩ የንግድ ምልክት የተደነገገ ሕግ ባይኖርም ተከሳሽ የፈጸመው በንግድ ሕግ መሠረት ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር ነው ።

ፍርድ

የከሳሽ ፡ ጠበቃ ፡ በክርክሩ ፡ የሚከተለውን ፡ አቅርቧል ፤ ከሳሽ ፡ ጐርዶን ፡ ጂን ፡ ተብሎ ፡ የሚጠራው ፡ ዕውቅ ፡ መጠጥ ፡ ባለቤት ፡ ነው ። ተከሳሹ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የከሳሹን ፡ የጐርዶን ፡ ጂን ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ ፍጹም ፡ ተመሳሳይ ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ አውጥቶ ፡ የጐርዶን ፡ ጂን ፡ ነው ፡ በማለት ፡ የሚሸጥ ፡ መሆኑን ፡ ከሳሽ ፡ ተረድተዋል ፡ በማለት ፡ ፩ኛ ፡ ፪ኛ ፡ ፫ኛ ፡ ተብለው ፡ የተመዘገቡትን ፡ የከሳሽ ፡ ማስረጃዎች ፡ አቅርቧል ።

እንደዚሁም ፡ ከሳሽ ፡ የከሳሽ ፡ ጠርሙስ ፡ ማለት ፡ ፫ኛ ፡ የከሳሽ ፡ ማስረጃ ፡ የተከሳሽ ፡ ጠርሙስ ፤ ፬ኛ ፡ የከሳሽ ፡ ማስረጃ ፡ ተብለው ፡ ሁለት ፡ ጠርሙሶች ፡ ቀርበዋል ።

ክርክሩን ፡ በመቀጠል ፡ ከሳሽ ፡ የሚቃወም ፡ በጠርሙሶቹ ፡ ላይ ፡ የሚታየው ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ በጠቅላላው ፡ ተመሳሳይ ፡ ስለሆነ ፡ ሕዝቡ ፡ በተከሳሹ ፡ ተሠርቶ ፡ የሚሸጠውን ፡ ጂን ፡ ጐርዶን ፡ ጂን ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ በመታለል ፡ ሊገዛ ፡ ስለሚችል ፡ ነው ፤ በተባሉት ፡ ጠርሙሶች ፡ የሚታየው ፡ የምልክት ፡ ተመሳሳይነት ፡ አውቆ ፡ የተደረገ ፡ የመገልበጥ ፡ ተግባር ፡ ነው ፤ በተለይም ፡ በተባለው ፡ ጠርሙስ ፡ ምልክት ፡ ላይ ፡ የሚነበበው ፡ የተከሳሹ ፡ የቴሌፎን ፡ ቍጥር ፡ ኢ.ኤስ.ኤስ.ቲ.ዲ. ፩ሺ፯፻፷፱ ፡ ጐርዶን ፡ ጂን ፡ ተሠርቶ ፡ የወጣበትን ፡ ዓ ፡ ም ፡ የሚገልጽ ፡ የጐርዶን ፡ ምልክት ፡ ነው ። በተጨማሪ ፡ ጋርደንስ ፡

የሚለው ፡ ጐርዶንስ ፡ ከሚለው ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ ጋር ፡ ተመሳሳይነቱ ፡ ለዓይንም ፡ ለጆሮም ፡ የሚደናገር ፡ ስለሆነ ፡ መጠጥ ፡ ሻጮች ፡ ጠጪውን ፡ ለማደናገር ፡ ይመቻቸዋል ። ለማሳከር ፡ የተደረገ ፡ መሆኑን ፡ በይበልጥ ፡ የሚያስረዳ ፡ የጋርደን ፡ ጂን ፡ ምልክት ፡ የሚነበብበት ፡ ፬ኛ ፡ የከሳሽ ፡ ማስረጃ ፡ በውስጡ ፡ ያለው ፡ ተገልብጦ ፡ እንደገና ፡ የተሞላ ፡ የጐርዶን ፡ ጂን ፡ ጠርሙስ ፡ ነው ፡ ብለዋል ። በ፳/፫/ ፶፳ ፡ በፋይል ፡ ቁጥር ፡ ፲፪ ፡ በወጣው ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሄራልድ ፡ ጋዜጣ ፡ ከሳሽ ፡ የጐርደንስ ፡ ድራይ ፡ ጂን ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ የግል ፡ ባለቤትና ፡ ባለንብረት ፡ መሆኑን ፡ በዚህም ፡ የሚገለገል ፡ እሱ ፡ ብቻ ፡ መሆኑን ፡ የእርያው ፡ ራስና ፡ ጐርደንስ ፡ የሚለው ፡ የእርሱ ፡ መሆኑን ፡ ገልጦ ፡ ማስታወቂያ ፡ አውጥቷል ፡ ብለዋል ።

ከሳሹ ፡ ለአንዳንድ ፡ የተከሳሽ ፡ መልሶች ፡ በሰጠውም ፡ መቃወሚያ ፡ ተከሳሽ ፡ የንግድ ፡ ውድድር ፡ የሚመለከታቸው ፡ በንግድ ፡ ሕግ ፡ የተጠቀሱትን ፡ ሰዎች ፡ ነው፡ ያለውን ፡ ተቃውሞ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፴፬ ፡ ማንኛውንም ፡ ሰው ፡ የሚመለከት ፡ ነው ፡ ብለዋል ። አስመራ ፡ ያለ ፡ ነጋዴ ፡ በጐርዶን ፡ ጠርሙስ ፡ መነገዱን ፡ ከሳሽ ፡ አያውቅም ፤ የንግድ ፡ ምልክትን ፡ ስለማስመዝገብ ፡ የወጣ ፡ ሕግ ፡ ስለሌለ ፡ ለጉዳዩ ፡ አግባብ የለውም ፡ ሲል ፡ ተከራክሮ ፤ ስለንግድ ፡ ውድድር ፡ በጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የተፈረደ ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፪፻፵/፶፯ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ መዝገብ ፡ ተጠቅሶ ፡ ግልባጩን ፡ አያይዘዋል ። እንደዚሁም ፡ በተመሳሳይ ፡ ክርክር ፡ ለከሳሹ ፡ ሦስት ፡ ሌሎች ፡ አገሮች ፡ የተሰጡ ፡ የሦስት ፡ ፍርድ ፡ ግልባጭ ፡ አያይዘዋል ።

ተከሳሽ ፡ በበኩሉ ፡ በሰጠው ፡ መልስ ፡ ከሳሽ ፡ በጠቀሰው ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፴፬ ፡ (፩)፡ ሀ ፡ እና ፡ ፩፻፴፬ ፡ (፪)፡ ሀ ፡ ሊጠቀም ፡ አይችልም ፤ የንግድ ፡ ውድድር ፡ የሚከለክለው ፡ ለነጋዴው ፡ ወኪል ፡ ሠራተኛና ፡ ለሌሎችም ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፴ ፡ ፵ ፡ ፵፯ ፤ ፶፰ ፤ ፩፻፵፬ ፡ ፩፻፶፰ ፡ ፩፻፶፱ ፡ ፪፻፬ ፡ እና ፡ ፪፻፳ ፡ ጠቅሶ ፡ ሌሎች ፡ ነጋዴዎች ፡ ግን ፡ ቢወዳደሩ ፡ የሚከለክል ፡ ሕግ ፡ የለም ፡ ብለዋል ። የተጠቀሰው ፡ ቁጥር፡ ፩፻፴፬ ፡ ስም ፡ ማጥፋትንና ፡ በሐሰት ፡ ወሬ ፡ መንዛትን ፡ ያመለክታል ፡ ግን ፡ ከከሳሽ ፡ ማስረጃዎች ፡ ይህን ፡ የሚያስረዱ ፡ የሉም ፡ ብልዋል ።

ተከሳሽ ፡ መከላከያውን ፡ በመቀጠል ፡ በከሳሽና ፡ በተከሳሽ ፡ ጠርሙሶች ፡ ላይ ፡ ያሉ፡ ምልክቶች ፡ የተለያዩ ፡ ናቸው ፡ ብሎ ፡ ልዩነታቸውን ፡ እንደሚከተለው ፡ ገልጽዋል ። ፩ኛ ፡ የከሳሽ ፡ ፫ኛ ፡ ማስረጃ ፡ የጐርዶን ፡ መጠጥ ፡ ስም ፡ የያዘ ፡ ነው ። ፪ኛ ፡ የከሳሽ ፡ ፫ኛ፡ ማስረጃ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ መለያ ፡ ተኰላ ፡ ነው ፤ የከሳሽ ፡ ፬ኛ ፡ ማስረጃ ፡ የተከሳሽ ፡ መለያ ፡ ሁለት ፡ አንበሶች ፡ ናቸው ፤ ፫ኛ ፡ የከሳሽ ፡ ፫ኛ ፡ ማስረጃ ፡ የጠርሙሱ ፡ ክዳን ፡ ቆርቆሮ ፡ ሲሆን ፡ የተከሳሽ ፡ ፬ኛ ፡ ማስረጃ ፡ የተከሳሹ ፡ ጠርሙስ ፡ ክዳን ፡ ቡሽ ፡ ነው ፤ ፬ኛ ፡ በእንግሊዝኛ ፡ ሞላ ፡ ማሩ ፡ ከሚለው ፡ ምልክት ፡ ሁለት ፡ አንበሶች ፡ ከሰው ፡ ስዕል ፡ ጋር ፡ ሲኖርበት ፡ የከሳሽ ፡ ሌላ ፡ ነው ፤ ፭ኛ ፡ ከሳሽ ፡ ጠርሙሱ ፡ ላይ ፡ ዲስትለሪ ፡ ለንደን ፡ የሚል ፡ ሲኖር ፡ በተከሳሹ ፡ ላይ ፡ ሊኩርስ ፡ ፋክቶሪ ፡ ላይን ፡ የሚል ፡ አለ ፤ ፮ኛ ፡ በጠርሙሱ ፡ መጨረሻ ፡ የከሳሽ ፡ ዘ—ሐርት ፡ አፍ ፡ ኤ ፡ ጉድ ፡ ኮክቴል ፡ ሲል ፡ በተከሳሹ ፡ ጠርሙስ ፡ ዘ—ቤስት ፡ ስቲሙላንት ፡ አፍ ፡ ዩር ፡ አፒታይት ፡ የሚል ፡ ነው ። ፯ኛ ፡ በግራና ፡ በቀኝ ፡ ያሉት ፡ አበቦች ፡ የከሳሽ ፡ ሐምራዊ ፡ ቀለም ፡ ሲሆን ፡ የተከሳሽ ፡ አረንጓዴ ፡ ነው ፤ ፍሬዎቹ ፡ የከሳሽ ፡ ሦስትና ፡ አንድ ፡ ሲሆኑ ፡ የተከሳሽ ፡ አንድ ፡ ሦስትና ፡ አራት ፡ ናቸው ፡ በማለት ፡ ተከሳሽ ፡ ሰባት ፡ ልዩነት ፡ አቅርቧል ። ተከሳሽ ፡ ክርክሩን ፡ በመቀጠል ፡ የከሳሽና ፡ የተከሳሽ ፡ መጠጦች ፡ በሰባት ፡ ምልክቶች ፡ ሲለያዩ ፡ ድራይ ፡ ጂን ፡ በሚለው ፡ ስም ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ የሚመሳሰሉት ፤ በዚህ ፡ ስም ፡ የአስመራው ፡ የመጠጥ ፡ ፋብሪካ ፡ (፪ኛ ፡ የተከሳሽ ፡ ማስረጃ)፡ የአዲስ ፡ አበባው ፡ መርከበኛ ፡ እንዱስትሪ ፤ ፫ኛ ፡ የተከሳሽ ፡ ማስረጃ ፤ ይጠቀሙበታል ፡ ብልዋል ። በተጨማሪም ፡ ተከሳሽ ፡ የከሳሽን ፡ ስም ፡ አላጠፋም ፤ የንግድ ፡ ምልክቱን ፡ አልወሰደም ፤

ድራይ ፡ ጂን ፡ የመጠጥ ፡ ስም ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የከሳሽ ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ አይደለም ፡ ብልዋል ። እንዲሁም ፡ ተከሳሹ ፡ ስለ ፡ መጠጥ ፡ ሚያዝያ ፡ ፭/፶፰ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ድምፅ ፡ ጋዜጣ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፴፰ ፡ አውጥቶ ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ መቃወሚያ ፡ አልቀረበም ። በጐርዶን ፡ ጂን ፡ መጠጥ ፡ ጠርሙስ ፡ ሌላ ፡ ባለአረቄ ፡ እንዳይገለገል ፡ ማስታወቂያ ፡ አልወጣም ፤ ስለዚህ ፡ ውሀ ፡ ቢቀዳበት ፡ አረቄ ፡ ቢያኖርበት ፡ ምንም ፡ ልዩነት ፡ የለም ፡ ብልዋል ።

የከሳሽና ፡ የተከሳሽ ፡ ክርክር ፡ ባጭሩ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተገለጸው ፡ ነው ። የክርክሩ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ የከሳሽና ፡ የተከሳሽ ፡ የንግድ ፡ ምልክቶች ፡ ይመሳሰላሉ ፡ ወይ ? መመሳሰላቸውስ ፡ ገዥዎችን ፡ ያሳስታል ፡ ወይ ፡ ነው ። ደግሞም ፡ የንግድ ፡ ምልክቶቹ ፡ ይመሳሰላሉ ፡ አይመሳሰሉም ፤ ያሳስታሉ ፡ አያሳስቱም ፡ ሲባል ፡ ጠርሙሶቹን፡ ጐን ፡ ለጐን ፡ አስቀምጦ ፡ በማስተዋል ፡ እየመረመረ ፡ ለሚያስተያያቸው ፡ ሰው ፡ ሳይሆን ፡ በጠቅላላው ፡ ለሕዝብ ፡ ለማንኛውም ፡ መጠጥ ፡ ገዥ ፡ ነው ።

የከሳሽ ፡ ማስረጃዎች ፡ በጽሑፍም ፡ ያሉት ፡ ጠርሙሶች ፡ በኤግዚቢት ፡ ቀርበው ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ታይተዋል ። የንግድ ፡ ምልክቶቹ ፡ ተመሳሳይነትና ፡ ማሳከር ፡ አያጠራጥርም ። ከሳሹ ፡ ያሳከራሉ ፡ ብሎ ፡ በተለይ ፡ የጠቀሳቸው ፡ ተመሳሳይነቶች ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱም ፡ ጐልተው ፡ የታዩት ፡ ጋርደን ፡ ስለሚለው ፡ የተከሳሽ ፡ ምልክት ፡ በተለይም ፡ እንግሊዝኛው ፡ ጐርደንስ ፡ ከሚለው ፡ የከሳሽ ፡ ምልክት ፡ ጋር ፡ በዓይንም ፡ ሲታይ ፡ ይመሳሰላል ሲነገርም ፡ በድምፅ ፡ ለጆሮ ፡ ይመስላል ። ተከሳሹ ፡ ጐልተው ፡ የሚታዩ ፡ ጥቃቅን ፡ ልዩነቶች ፡ ምልክቶቹ ፡ በዚህ ፡ በዚህ ፡ ይለያሉ ፡ ብሎ ፡ አቅርቧል ። እነዚህ ፡ ጥቃቅን ፡ ልዩነቶች ፡ የከሳሹን ፡ ምልክቶች ፡ በማሻሻል ፡ ልዩነት ፡ ያላቸው ፡ ለማስመሰል ፡ የተሞከረ ፡ ለመሆኑ ፡ ግምት ፡ ከመስጠታቸው ፡ በላይ ፡ ልዩነቶቹ ፡ ጠርሙሶቹን ፡ ጐን ፡ ለጐን ፡ አስቀምጦ ፡ ሥራዬ ፡ ብሎ ፡ ለሚመረምር ፡ ሰው ፡ በቂ ፡ ይሆኑ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለጠቅላላው ፡ ሕዝብ ፡ ለመጠጥ ፡ ገዥው ፡ ሁሉ ፡ በቂ ፡ ልዩነቶች ፡ ናቸው ፡ ለማለት ፡ አይቻልም ። ከሞላ ፡ ስምና ፡ ከሞላ ፡ ምልክት ፡ ተከሳሹ ፡ የከሳሹን ፡ ምልክት ፡ እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ አስመስሎ ፡ መሥራቱ ፡ ለማሳከርና ፡ በከሳሹ ፡ ዝና ፡ ለመጠቀም ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ ዓላማ ፡ አለው ፡ ተብሎ ፡ አይገመትም ።

የተከሳሽ ፡ ጠበቃ ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፴፬ ፡ የነጋዴውን ፡ ወኪልና ፡ ሌሎች ፡ ከነጋዴው ፡ ጋር ፡ በሥራ ፡ የቅርብ ፡ ግንኙነት ፡ ያላቸውን ፡ ሰዎች ፡ ነው ፡ የሚመለከተው ፡ ያለው ፡ ስህተት ፡ ነው ። ቁጥር ፡ ፩፻፴፬ ፡ ማንኛውንም ፡ ነጋዴ ፡ የሚመለከት ፡ ነው ። እርግጥ ፡ የንግድ ፡ ውድድር ፡ በሕግ ፡ የተፈቀደ ፡ ነው ። ለምሳሌ ፡ ተከሳሹ ፡ ከከሳሹ ፡ የበለጠና ፡ ዝነኛ ፡ የሆነ ፡ ጂን ፡ ሠርቶ ፡ የከሳሹን ፡ ወይም ፡ የሌላ ፡ ነጋዴ ፡ ምልክት ፡ ሳያስመስል ፡ ራሱ ፡ በፈጠረው ፡ መለያ ፡ ሲሸጥና ፡ በመጠጡ ፡ ተወዳጅነት ፡ የከሳሹን ፡ ወይም ፡ የሌላ ፡ ነጋዴ ፡ ምልክት ፡ ሳያስመስል ፡ ራሱ ፡ በፈጠረው ፡ መለያ ፡ ቢሸጥና ፡ በመጠጡ ፡ ተወዳጅነት ፡ የከሳሹን ፡ ወይም ፡ የሌሎችን ፡ ነጋዶች ፡ ደንበኞች ፡ ቢወስድ ፡ ይህ ፡ ተገቢ ፡ የንግድ ፡ ውድድር ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ለረጅም ፡ ዘመን ፡ የኖረውን ፡ የአንዱን ፡ ነጋዴ ፡ የታወቀ ፡ ምልክት ፡ አስመስሎ ፡ ቀድቶ ፡ ይሄው ፡ ነጋዴ ፡ የሚሸጠውን ፡ ዓይነት ፡ ዕቃ ፡ መሸጥ ፡ በቁጥር ፡ ፩፻፴፬ ፡ ተገቢ ፡ ያልሆነ ፡ የንግድ ፡ ውድድር ፡ ነው ። ተከሳሽ ፡ በከሳሹ ፡ ጠርሙስ ፡ ሌሎችም ፡ ነጋዴዎች ፡ ይጠቀማሉ ፤ እኔም ፡ አልከለከልም ፡ ብልዋል ። ከሳሽ ፡ በጠርሙሱ ፡ የተከራከረው ፡ በንብረትነቱ ፡ አይደለም ፤ ለምሳሌ ፤ ተከሳሹ ፡ በዚህ ፡ ጠርሙስ ፡ ወተት ፡ ቢሸጥበት ፡ ከሳሽ ፡ የሚቃወም ፡ አይመስለንም ። የከሳሽ ፡ አቤቱታ ፡ ተከሳሹ ፡ በራሴ ፡ ጠርሙስ ፡ እኔ ፡ የምሸጠውን ፡ ዓይነት ፡ መጠጥ ፡ የኔን ፡ ምልክት ፡ የሚመስል ፡ ምልክት ፡ አድርጎ ፡

በመሸጥ ፡ ደንበኞቼን ፡ አሳስቶብኛል ፡ የሚል ፡ ነው ። የከሳሽ ፡ አቤቱታ ፡ በሚገባ ፡ የቀረበ ፡ ነው ። ተከሳሹ ፡ በከሳሹ ፡ ጠርሙስ ፡ መሸጡ ፡ ተመሳሳይነቱን ፡ በይበልጥ ፡ አጉልቶታል ።

ከሳሽ ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ ባለቤት ፡ ለመሆኑ ፡ ማርች ፡ ፳/፺፰ ፡ በወጣው ፡ በቁጥር፡ ፴፯ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ሄራልድ ፡ ጋዜጣ ፡ አስታውቋል ። ተከሳሽ ፡ ከሳሽ ፡ ምልክቱን ፡ በንግድ ፡ ሚኒስቴር ፡ አላስመዘገበም ፡ ብልዋል ። ምልክቱን ፡ ላለማስመዝገቡ ፡ ማስረጃ፡ አላቀረበም ። ነገር ፡ ግን ፡ ከሳሽ ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ በኢንተርናሽናልና ፡ በኢትዮጵያም ፡ ለረጅም ፡ ጊዜ ፡ የታወቀ ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ ባለቤት ፡ ከመሆኑ ፡ በላይ ፡ የንግድ ፡ ምልክትን ፡ ስለማስመዝገብ ፡ የወጣ ፡ ሕግ ፡ ስለሌለ ፡ ከሳሹ ፡ የታወቀ ፡ መብቱን ፡ ሊነጠቅ ፡ አይችልም ። ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተገለጠው ፡ መሠረት ፡ ተከሳሽ ፡ ተገቢ ፡ ያልሆነ ፡ የንግድ ፡ ውድድር ፡ ማድረጉ ፡ ስለተረጋገጠ ፡ ተከሳሽ ፡ ይህ ፡ ፍርድ ፡ ከተሰጠበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ የከሳሽን ፡ የጐርዶን ፡ ጂን ፡ ምልክት ፡ ከሥራ ፡ ላይ ፤ ከማዋል ፡ እንዲያቋርጥና ፡ በምልክቱ ፡ እንዳይገለግል ፡ ወደፊትም ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ በሚያሳክር ፡ ምልክት ፡ እንዳይጠቀም ፡ ብለን ፡ ፈርደናል ። በዚህ ፡ ክርክር ፡ ከሳሽ ፡ ስላወጣው፡ ኪሣራና ፡ የጠበቃ ፡ አበል ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነሥርዓት ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፷፫ ፡ እና ፡ ፩፻፷፬ ፡ መሠረት ፡ ዘርዝሮ ፡ ሲያቀርብ ፡ ይታያል ።

ይህ ፡ ፍርድ ፡ ዛሬ ፡ ኅዳር ፡ ፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ተሰጠ ።

HIGH COURT

Addis Ababa

Judges:

Ato Assefa Liben

Ato Abebe Awgichew

Ato Mohamed Berhan Nurhussen

Distiller's Co. Ltd. v. Ato Mola Maru.

Civil Case No. 919-59

Unfair trade competetion—imitation of trade mark—Civ. Code Arts. 1240–56; Comm. Code Arts. 30,40,47,55,134,144,158,159,204–5.

Defendant was charged with deliberate copying of Plaintiff's trade marks which the former allegedly used on bottles in which drinks of the same class as that of Plaintiff were sold.

Held: Defendant liable.

Although there is no legislation covering questions of trade mark the act of defendant constitutes unfair competetion as governed by the Commercial Code.

JUDGMENT

Counsel for Plaintiff has argued as follows:

That Plaintiff is the proprietor of Gordon's Dry Gin which is known throughout the world, and that it has come to the knowledge of Plaintiff that sales are taking place in Ethiopia of Dry Gin by Defendant under a get-up substantially similar to that of Gordon's Dry Gin. In order to sustain this argument Counsel for Plaintiff has submitted in Court Exh. P.1 and P.2. Besides, the Plaintiff also produced in Court Plaintiff's bottle as Exh. P.3 and the bottle used by Defendant as Exh. P. 4.

Counsel for Plaintiff has argued that the imitation of the get-up as a whole, that is to say, the general appearance of the labelled bottle, is particularly objectionable and tends to deceive purchasers as to the origin of the Dry Gin produced by Defendant; that there is no doubt that the resemblance is due to deliberate copying, and that the many similarities of minute details in the two labels could not have occurred by coincidence; that the most obvious example of this is the use by Defendant of his telephone number to correspond with the statement "ESST'D 1769" which refers to the date when Gordon's Dry Gin was first produced. In addition to the above the name Garden's is confusingly similar to the trade name Gordon's. That this imitation of get-up provides a weapon for a dishonest bartender who is enabled to pass-off Garden's Dry Gin in response to orders for the more expensive Gordon's Dry Gin. A clear evidence that proves unquestionably an attempt to confuse and deceive the public is that the bottle bearing the Gordon's label (Exh. P 4) is in fact a refilled Gordon's Dry Gin bottle. Counsel for Plaintiff went on to state that Plaintiff published a notice in the Ethiopian Herald dated

5-3-55 (No. 37 file 12) claiming ownership *inter alia* of Gordon's Dry Gin label, the device of the Boar's Head and the word 'Gordons.'

In reply to the defence put-up by Defendant, who argued that unfair competition covers persons who are only mentioned in the Commercial Code, Counsel for Plaintiff stated that the Provisions of Article 134 of the Commercial Code duly cover any person engaged in trade practice.

Counsel for Plaintiff stated that Plaintiff does not know that a trader in Asmara uses in his trade the bottles of Gordon's Dry Gin; that no law for registration of trade marks has yet been enacted has no connection with the present case. Counsel for Plaintiff has presented to the Court a copy of a judgment given in Civil Case No. 1240-56 in connection with a case of unfair competition. In addition, Counsel for Plaintiff has introduced in evidence copies of judgments given in favour of Plaintiff in similar cases by Courts of three different countries.

In his reply Defendant has argued that Plaintiff cannot sustain its claim under the Provisions of Articles 134 (1) (a) and 134 (2) (a) of the Commercial Code. That according to Articles 30, 40, 47, 55, 144, 158, 159, 204 and 205 of the Commercial Code the question of unfair trade practice covers only those who are employees, agents and others who have such relations with the merchant. He said that there is no law which restrains merchants other than the above from carrying on such trade competition. That Article 134 of the Commercial Code cited by Plaintiff in the present case deals with false statement and defamation, whereas none of the evidence adduced by Plaintiff proves that any such act is committed by Defendant. Defendant went on to state that the labels appearing on the bottles of Plaintiff and Defendant are entirely different. Defendant argued (1) that Plaintiff's bottle (Exh. P.3) bears the name Gordon's; (2) that the trade mark bearing on Plaintiff's bottle (Exh. P.3) is a Boar's Head whereas Defendant's bottle (Exh. P.4) bears the trade mark of two lions; (3) that Plaintiff's bottle has a metalic seal whereas Defendant's (Exh. P.4) has a cork seal; (4) Defendant's bottle bears the name of Molla Maru with the trade mark of two lions and a picture of a man, whereas Plaintiff's bottle bears a different name and trade mark; (5) that Plaintiff's bottle bears the words Distillery London, whereas Defendant's bottles bear the words Liquors Factory Line; (6) the words depicted at the bottom of Plaintiff's bottle are "The Heart of a Good Cock-tail" whereas at the bottom of Defendant's bottle are written the words "The best Stimulant of Your Apetite"; (7) the flowers at the right and left sides of Plaintiff's bottle are purple in colour whereas Defendant's are green. That the fruits appearing at Plaintiff's bottle are three and one, whereas Defendant's are one, three and four. In all Defendant has quoted such seven diff-ferent items between his bottle and that of Plaintiff's.

Defendant stated that although the trade marks appear in both, the bottles of Plaintiff and Defendant have seven different items. The only thing which is found to be similar in both bottles are the words Dry Gin. Defendant stated that the Asmara Liquor Factory (Ex. D.2) and the Merkebegnia Industry of Addis Ababa (Exh. D.3) are using these names in selling their products.

In addition, Defendant argued that he has not made defamatory statements and never exercised unfair competition against Plaintiff. He asserted that 'Dry Gin' is a name of a liquor and not the trade mark of Plaintiff. Defendant stated that he has published a notice in the Addis Zemen Gazetta dated April 13th 1964 No. 138 and no one has objected to such notice for a period of one year. He also said that there has not been any notice published restricting the use by others of the

Gordon's Dry Gin Bottles. He said that if one uses said bottle for water or any other drink it is all the same.

The above is the argument exchanged between Plaintiff and Defendant. The important questions to be answered are the following:-

Are there similarities between the labels used by Plaintiff and Defendant? And if so to what extent do such similarities confuse and deceive the public? These questions are not directed to persons who can place said bottles side by side and compare the similarities existing between the two bottles. This question, as far as the Court is concerned, has reference to the general consumer at large.

The bottles Plaintiff has produced in Court as exhibits were closely watched and observed by the Court while in session. There is no doubt that the labels used in both bottles are of similar type and confusing. In particular the Court has been able to observe that the words Garden's and Gordon's appearing especially in English on the two bottles are quite similar and confusing when even closely seen. Even when these two names are pronounced one cannot tell the difference unless he hears them spoken clearly and precisely. However, Defendant has pointed out other minor differences between the two labels.

From what the Court saw the said minor differences are made up in such a way as to create confusion between the two get-ups. As a matter of fact such minor differences can only be traced by persons who put and compare the two set-ups side by side and this requires a special treatment. In view of the fact that there exists a great number of other labels the reason why Defendant has done his best to create such similarities between his get-up and that of Plaintiff's is nothing but an act intended to benefit from the get-up and reputation enjoyed by Plaintiff.

Counsel for Defendant has argued that the question of unfair competition has reference only to commercial agents and employees as for Article 134 of the Commercial Code and as such this cannot apply in the present case. In the Court's opinion the said argument is wrong since the provisions of Article 134 cover any and all merchants engaged in such business.

It is true that competition in commercial business is allowed by law. That is to say if a merchant produces the best quality of drink and attracts the consuming public without using the labels of another, such is a fair competition. However, the purpose of imitating the labels used by another for a long time is an act of unfair competition which falls under the provisions of Article 134 of the Commercial Code.

Defendant has argued also that since other merchants are using the bottles belonging to Plaintiff there is no reason why he cannot use them. This argument has no relevance to the present case since Plaintiff has not raised the question of ownership of such bottles. We are convinced that Plaintiff will have no objection if Defendant uses Plaintiff's bottles for sale of milk. What Plaintiff contends in the present case is that Defendant is using Plaintiff's bottles for the sale of the same kind of liquor Plaintiff produces and in doing so Defendant has confused and deceived the public.

In our opinion and as far as the law is concerned the petition made by Plaintiff is proper. The fact that Defendant admits using Plaintiff's bottles for selling such liquors gives more weight to the similarities which Defendant has imitated from Plaintiff.

According to the proof adduced it is evident that Plaintiff is the owner of Gordon's Dry Gin label (Ethiopian Herald dated March 5th 1955 No. 37). At the same time Defendant has contended that Plaintiff has not registered his labels with the Ministry of Commerce & Industry. Nevertheless, this allegation has not been supported by evidence.

Whereas Plaintiff's products sold under the said labels are known all over the world such get-ups cannot be taken away from them under the pretext that there do not exist laws which cover the registration of trade marks.

In view of all the reasons stated above the Court found that Defendant has committed an act of unfair competition and we hereby restrain Defendant from using the said similar labels for the sale of his products from the date of this judgement and to stop using in future any such labels similar to that of Plaintiff.

November 4, 1968

ጠቅላይ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤

አዲስ ፡ አበባ ፤ ፩ኛ ፡ ችሎት ።

ዳኞች ፤

ሚስተር ፡ ገብርኤል ፡ ደባስ ፤

ግራዝማች ፡ ተሰማ ፡ ነገደ ፤

አቶ ፡ ጸጋይ ፡ ተፈሪ ።

ይግባኝ ፡ ባይ ፤ ወይዘሮ ፡ ሲልቪያ ፡ ዜቪ ።

መልስ ፡ ሰጭ ፤ ሬናቶ ፡ ዜቪ

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፱፻፱/፶፯ ።

የቤት ሰብ ሕግ ፤ ፍቺ ፤ የቤት ሰብ ሽማግሌዎች በሰጡት ውሳኔ ላይ ለፍርድ ቤት ይግባኝ ስለማለት ፤ ተወላጅነት ፤ ሃይማኖትና የፍቺ ምክንያቶች ፤ የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥሮች ፮፻፷፯ ፤ ፯፻፴፯ ፤ ፮፻፹፫ ።

የቤት ሰብ ሽማግሌዎች በድምጽ ብልጫ ለፍቺ በቂ ምክንያት ስለሌለ ተጋቢዎቹ ሊፋቱ አይችሉም በማለት የሰጡትን ውሳኔ የከፍተኛው ፍ/ቤት ስላጸናው ይህን ፍርድ በመቃወም የቀረበ ይግባኝ ፤

ውሳኔ፡— የከፍተኛው ፍርድ ቤት ፍርድ ተሽሮ የቤት ሰብ ሽማግሌዎች በአነስተኛ ድምፅ የሰጡት ውሳኔ ጸንቷል ።

፩. የቤት ሰብ ሽማግሌዎች የሰጡት ውሳኔ ያለአግባብ ሆኖ ሲገኝ ለፍርድ ቤት ይግባኝ ማለት ይቻላል ።

፪. የቤት ሰብ ሽማግሌዎች የፍቺን ጉዳይ በሚወስኑበት ጊዜ የፍትሐ ብሔሩን ሕግ በጥብቅ መከተል አለባቸው ።

፫. የቤት ሰብን ኑሮ የሚያናጋና ባልየውንም ሆነ ሚስቲቱን የሚያሳፍር መጥፎ ልማድ ለፍቺ በቂ ምክንያት ሊሆን ይችላል ።

፬. ሃይማኖት ፍቺን ሊያስቀር አይችልም ።

ፍርድ

አመልካችዋ ፡ በጠበቃቸው ፡ አማካይነት ፡ ጥቅምት ፡ ፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፫ ፡ ዓ ፡ ም፡ በተጻፈው ፡ ማመልከቻቸው ፡ ሲያመለክቱ ፡ አመልካችዋና ፡ መልስ ፡ ሰጭው ፡ የተጋቡት ፡ እንደ ፡ ኤውሮፓ ፡ አቆጣጠር ፡ ሚያዝያ ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሆኖ ፡ በካቶሊክ ፡ ሃይማኖት ፡ ሥርዓት ፡ ጋብቻ ፡ ነው ። በጋብቻው ፡ መሠረትም ፡ አሥር ፡ ሰባትና ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ የሆናቸው ፡ ሶስት ፡ ልጆች ፡ ወልደዋል ። አመልካችዋና ፡ መልስ ፡ ሰጪው ፡ ሶስት ፡ ልጆች ፡ ቢወልዱም ፡ አብሮ ፡ ለመኖር ፡ መግባባትና ፡ ስምምነት ፡ በማጣታቸው ፡ አመልካችዋ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ፍች ፡ እንዲደረግ ፡ በቤተ ፡ ዘመድ ፡ ዳኞች ፡ ጠይቀው ፡ ስለ ፡ ነበር ፡ የተመረጡት ፡ አምስት ፡ የዘመድ ፡ ዳኞችም ፡ ስለጋብቻው ፡ ፍቺ፡በቂ ፡ ምክንያት ፡ ሳያገኙለት ፡ በመቅረታቸው፡ አመልካችዋ ፡ ከባልዋ ፡ ጋር ፡ አብራ ፡ መኖር ፡ አለባት ፡ በማለት ፡ በድምጽ ፡ ብልጫ ፡ ወስነዋል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ አመልካችዋ ፡ በጠባይ ፡ ባለመግባባትና ፡ በየቀኑ ፡ ስለሚ

ደርስባቸው ፡ ስድብና ፡ ውርደት ፡ ምክንያት ፡ ከመልስ ፡ ሰጭው ፡ ጋር ፡ አብረው ፡ ለመኖር ፡ የማይችሉ ፡ መሆናቸውን ፡ ገልጸው ፡ አሁን ፡ የዘመድ ፡ ዳኞች ፡ በድምጽ ፡ ብልጫ ፡ የሰጡት ፡ ውሳኔ ፡ ውድቅ ፡ ሆኖ ፡ በአነስተኛ ፡ ድምፅ ፡ የተሰጠውን ፡ ውሳኔ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እንዲያጸድቅላቸው ፡ አመልክተዋል ። እንዲሁም ፡ መልስ ፡ ሰጭው ፡ በጠበቃቸው ፡ አማካይነት ፡ በጥር ፡ ፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በተጻፈ ፡ የመከላከያ ፡ መልስ ፡ ሲያመለክቱ ፡ የአመልካችዋ ፡ ጠበቃ ፡ በድምጽ ፡ ብልጫ ፡ የተሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ለመሆኑ ፡ ወይም ፡ በበቂ ፡ ምክንያት ፡ የተደገፈ ፡ ለመሆኑ ፡ በማመልከቻቸው ፡ የገለጹት ፡ ምክንያት ፡ የለም ፤ እንዲሁም ፡ የአመልካችዋ ፡ ጠበቃ ፡ ጋብቻው ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ መፍረስ ፡ እንደሚገባው ፡ አላስረዱም ፤ አመልካችዋ ፡ ክርክራቸው ፡ ለዘመድ ፡ ዳኞች ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በቁጥር ፡ ፮፻፳፯ ፡ መሠረት ፡ ጋብቻው ፡ ሊፈርስ ፡ የሚችልበትን ፡ ምክንያት ፡ አላስረዱም ። አመልካችዋ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ሳይጨብጡ ፡ ጋብቻው ፡ እንዲፈርስ ፡ ብለው ፡ ያቀረቡት ፡ አቤቱታ ፡ ሕጋዊ ፡ መስመር ፡ አልያዘም ፤ ምክንያቱም ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ ጋብቻን ፡ ለማፍረስ ፡ የሚችሉት ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ዳኞች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ። አመልካችዋ ፡ ጋብቻው ፡ እንዲፈርስላቸው ፡ ብለው ፡ ያቀረቡት ፡ ጥያቄ ፡ አለአግባብ ፡ ስለሆነ ፡ አመልካችዋ ፡ ያቀረቡት ፡ ጥያቄ ፡ እንዲሠረዝ ፡ በማለት ፡ ክርክራቸውን ፡ አቅርበዋል ። የአመልካች ፡ ጠበቃ ፡ አምስት ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ሽማግሌዎች ፡ የሰጡትን ፡ ውሳኔ ፡ አቅርበዋል ። ውሳኔው ፡ የተሰጠው ፡ በድምጽ ፡ ብልጫና ፡ በአነስተኛ ፡ ድምፅ ፡ ነው ። በድምፅ ፡ ብልጫ ፡ የተሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ እንደ ፡ አውሮፓ ፡ አቆጣጠር ፡ በሐምሌ ፡ ፲፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፳፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሆኖ ፡ ሽማግሌዎቹ ፡ ሁለቱን ፡ ወገኖች ፡ አመልካችዋንና ፡ መልስ ፡ ሰጭውን ፡ አቃርበው ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ ቃላቸውን ፡ ከሰጡ ፡ በኋላ ፡ አመልካችዋ ፡ የጠየቁት ፡ ፍቺ ፡ በበቂ ፡ ማስረጃ ፡ የተደገፈ ፡ ስላልሆነ ፡ የፍችውን ፡ ጥያቄ ፡ አልተቀበልነውምና ፡ አመልካችዋ ፡ ከባልዋ ፡ ጋር ፡ ከምትኖርበት ፡ ቤት ፡ ተመልሳ ፡ ከባሏ ፡ ጋር ፡ አብረው ፡ እንዲኖሩ ፡ ብለው ፡ በድምጽ ፡ ብልጫ ፡ ወስነዋል ። በአነስተኛ ፡ ድምጽ ፡ የተሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ ግን ፡ በሐምሌ ፡ ፲፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የተሰጠ ፡ ሆኖ ፡ በዚሁ ፡ በአነስተኛው ፡ ውሳኔ ፡ መሠረት ፡ ሊፋቱ ፡ ይገባል ፡ ብለው ፡ ወስነዋል ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በድምፅ ፡ ብልጫና ፡ በአነስተኛ ፡ የተሰጡትን ፡ ውሳኔዎች ፡ ሲመለከታቸው ፡ አመልካችዋ ፡ ለፍችው ፡ ምክንያት ፡ አድርገው ፡ ያቀረቡት ፡ ያመሻል ፡ ይጠጣል ፡ ቁማርን ፡ ይጫወታል ፡ ሲሆን ፡ ይኸውም ፡ ጋብቻውን ፡ ለማፍረስ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ፤ ስለዚህ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተዘረዘረው ፡ ምክንያት ፡ በድምጽ ፡ ብልጫ ፡ በሕግ ፡ አግባብ ፡ የተሰጠ ፡ ውሳኔ ፡ ስለሆነ ፡ በድምጽ ፡ ብልጫ ፡ የተሰጠውን ፡ ፍርድ ፡ አጽንተናል ፤ አመልካችዋ ፡ ያቀረቡትን ፡ አቤቱታ ፡ አሰናብተናል ፡ ብሎ ፡ ስለ ፡ ፈረደ ፡ ሚሲስ ፡ ሲልቪያ ፡ ዤቪ ፡ ይግባኝ ፡ ብለው ፡ ቀርበዋል ። በተጠቀሰው ፡ ጽሑፍ ፡ እንደሚከተለው ፡ ዘርዝረዋል ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፡ መልስ ፡ ሰጭን ፡ የካቶሊክ ፡ ሃይማኖት ፡ በሚፈቅደው ፡ መሠረት ፡ የጋብቻውን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በማክበር ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ ፡ ፳፯/፬/፶፰ ፡ አገቡ ።

ዕድሚያቸው ፡ ፭ ፡ ፯ ፡ ፲ ፡ ዓመት ፡ የሆኑ ፡ ሦስት ፡ ልጆች ፡ ወልደዋል ። ከመልስ ፡ ሰጪው ፡ ጋር ፡ ባለመስማማታቸው ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በሚያዝዘው ፡ መሠረት ፡ በሽማግሌ ፡ ፍቺ ፡ የጠየቁ ፡ ሲሆን ፡ አምስት ፡ ሽማግሌዎች ፡ በተገኙበት ፡ ሦስት ፡ ለሁለት ፡ በሆነ ፡ ብልጫ ፡ ለፍቺ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ያለመኖሩን ፡ ፈረዱ ።

በድምፅ ፡ ብልጫ ፡ ሽማግሌዎች ፡ በሰጡት ፡ ብይን ፡ ላይ ፡ ለከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይግባኝ ፡ ቀርቦ ፡ ነበር ። ከብይኑ ፡ ጽሑፍ ፡ እንደሚታየው ፡ የሰጡት ፡ ምክንያት ፡ ሁለቱ ፡ ተከራካሪ ፡ ወገኖች ፡ ሃይማኖታቸው ፡ ካቶሊክ ፡ ስለሆነ ፡ መፋታት ፡ አይ

ችሉም ፡ የሚል ፡ ነው ። ሽማግሌዎች ፡ በድምፅ ፡ ብልጫ ፡ የሰጡት ፡ ውሳኔና ፡ ያቀረ ቡት ፡ ማስረጃዎች ፡ ለሕግ ፡ ተቃራኒ ፡ በመሆናቸው ፡ ሽማግሌዎች ፡ ይህን ፡ ብይን ፡ በሰጡበት ፡ ጊዜ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ድንጋጌዎች ፡ አልተመለከቱም ።

ጉዳዩ ፡ ለክቡር ፡ የከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀርቦ ፡ ውሳኔ ፡ ሳይሰጥበት ፡ መልስ ፡ ሰጪው ፡ ሶስቱን ፡ ልጆቹን ፡ ይዞ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ የሄደ ፡ ሲሆን ፡ ይግባኝ ፡ ባይን ፡ በበ ለጠ ፡ ለማስቸገር ፡ ከጠበቃው ፡ ላይ ፡ የውክልና ፡ ሥልጣን ፡ በመውሰድ ፡ ሽሮታል ።

መልስ ፡ ሰጪ ፡ በኢጣሊያ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ በተቋቋመ ፡ ቤድና ፡ ቦርድ ፡ በተ ባለ ፡ ድርጅት ፡ ላይ ፡ ከይግባኝ ፡ ባይ ፡ ተለያይቶ ፡ ለመኖር ፡ ክስ ፡ ያቀረበ ፡ ሲሆን ፡ በፍቺ ፡ ምትክ ፡ የሚሠራበት ፡ ስለሆነ ፡ በካቶሊክ ፡ ሃይማኖት ፡ የተከለከለ ፡ ነው ። የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤትም ፡ መስከር ፤ ቁማር ፡ መጫ ወት ፤ ማታ ፡ ማታ ፡ አምሽቶ ፡ መግባትም ፡ ለፍቺ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ አይሆንም ፡ በማለት ፡ አመልካቿ ፡ ያቀረቡትን ፡ አቤቱታ ፡ በስህተት ፡ ውድቅ ፡ እንዲሆን ፡ አድር ጎታል ።

ይግባኝ ፡ ባይና ፡ መልስ ፡ ሰጭ ፡ ተለያይተው ፡ ከሦስት ፡ (፫) ዓመት ፡ በላይ ፡ ኖረዋል ። ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተዘረዘሩት ፡ ፍሬ ፡ ነገሮች ፡ መሠረት ፡ በመጀመሪያ ፡ መጠቀስ ፡ የሚገባው ፡ ሕጋዊ ፡ ጉዳይ ፡ በሁለቱ ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ግንኙነት ፡ በማን ፡ ሕግ ፡ ለመፈጸም ፡ የሚቻል ፡ መሆኑን ፡ ለማወቅ ፡ የግል ፡ የኢንተ ርናሽናል ፡ ሕግን ፡ የመመርመር ፡ ጉዳይ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ በማክበር ፡ ለማስረ ዳት ፡ የምንፈልገው ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ባልየው ፡ የኢጣሊያ ፡ ዜጋ ፡ ሚስትዮዋም ፡ የፈ ረንሣይ ፡ ዜጋ ፡ ቢሆኑም ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ መኖሪያቸው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ በመ ሆኑ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ስለ ፡ እንደዚህ ፡ ያሉ ፡ ጉዳዮች ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ብዙ ፡ ውሳኔ ዎች ፡ በመሰጠታቸው ፡ ያለ ፡ ጥርጥር ፡ የሚኖሩበት ፡ አገር ፡ ሕግ ፡ የባልና ፡ ሚስቶ ቹን ፡ ጉዳይ ፡ ለመወሰን ፡ ማስቻሉን ፡ ነው ። በጋብቻው ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ የጸና ፡ ለመሆኑ ፡ ይግባኝ ፡ ባይና ፡ መልስ ፡ ሰጭ ፡ የተቀበሉ ፡ ሲሆን ፡ አሁን ፡ በሌላ ፡ ምክንያት ፡ ይግባኝ ፡ ቢቀርብበትም ፡ ክቡር ፡ የከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤትም ፡ በሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ አጽድቆታል ።

በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ በከፍተኛ ፡ ምክንያቶችና ፡ በሌሎች ፡ ምክንያ ቶች ፡ የተነሳ ፡ ፍቺ ፡ ማግኘት ፡ ይቻላል ። ቃሉ ፡ በጣም ፡ ጠቅላላ ፡ በመሆኑ ፡ በፍትሐ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ከአንቀጽ ፡ ፮፻፷፰ና ፡ ከተከታታዮቹ ፡ አንቀጾች ፡ ጋር ፡ የሚስ ማሙ ፡ ሁኔታዎችና ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ካሉ ፡ ማናቸውንም ፡ ነገር ፡ የሚጨምር ፡ ነው ። ለአስታራቂው ፡ ጉባኤ ፡ በቀረበው ፡ የፍቺ ፡ ማመልከቻ ፡ ውስጥና ፡ አስታራቂዎችም፡ እንዲሰሙት ፡ ለፍቺ ፡ የቀረቡት ፡ ምክንያቶች ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ፤

ሀ/ የጠባይ ፡ በፍጹም ፡ አለመስማማት ፤

ለ/ በደረሰባቸው ፡ስድብና ፡ ውርደት ፡ ምክንያት ፡ አመልካች ፡ ከሰው ፡ መለ የታቸው ፤

ሐ/ መልስ ፡ ሰጭ ፡ በጣም ፡ ቁማር ፡ ተጫዋች ፡ በመሆናቸው ፤

ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ የቤተ ፡ ሰቡ ፡ ገንዘብ ፡ በመባከኑ ፡ ከፍተኛ ፡ የገንዘብ ፡ ጉዳት ፡ በመድረሱ ፡ ቤታቸው ፡ ስለተፈታ ። እነዚህ ፡ ምክንያቶች ፡ ለያንዳንዳቸው ፡ ፍቺ ፡ ለማስገኘት ፡ በቂ ፡ ሲሆኑ ፡ ሽማግሌዎቹ ፡ ብይን ፡ ከሰጡ ፡ በኋላ ፡ የሚከተሉት ፡ ለፍቺ ፡ የሚያበቁ ፡ ተጨማሪ ፡ ምክንያቶች ፡ ደግሞ ፡ ደርሰዋል ፤

መ/ ሦስቱን ፡ ልጆቻቸውን ፡ ይዘው ፡ መልስ ፡ ሰጭ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ መልቀቃቸው ፤

ሠ/ ቤድና ፡ ቦርድ ፡ በተባለው ፡ ድርጅት ፡ ላይ ፡ መልስ ፡ ሰጭ ፡ ክስ ፡ በማቅረባቸው ፤

ረ/ ባልና ፡ ሚስት ፡ ከሦስት ፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ ተለያይተው ፡ ይህ ፡ ምክንያት ፡ ብቻ ፡ ያለጥርጥር ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጠቀሱት ፡ ምክንያቶች ፡ የተነሳ ፡ የይግባኝ ፡ ባይና ፡ የመልስ ፡ ሰጭ ፡ ቤት ፡ በምንም ፡ መንገድ ፡ በማያንሠራራ ፡ ሁኔታ ፡ የተፈጸመ ፡ ከመሆኑ ፡ በላይ ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ ለመኖር ፡ ፍጹም ፡ የማይችሉ ፡ መሆኑን ፡ ያስረዳል ።

ሁለቱ ፡ ተከራካሪ ፡ ወገኖች ፡ ካቶሊክ ፡ መሆናቸው ፡ የሕጉን ፡ ሁኔታ ፡ በምንም ፡ ምክንያት ፡ ሊለውጠው ፡ ካለመቻሉም ፡ በላይ ፡ መኖሪያቸው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ካቶሊክ ፡ በመሆናቸው ፡ በካቶሊክ ፡ ሃይማኖት ፡ መሠረት ፡ ፍቺ ፡ አይቻልም ፡ ማለት ፡ በግልጽ ፡ የሕግ ፡ ተቃራኒ ፡ ነው ። ይግባኝ ፡ ባይ ፡ በሕግ ፡ መሠረት ፡ (አንቀጽ ፡ ፯፻፴፮) ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሽማግሌዎቹ ፡ ያለአግባብ ፡ የሰጡትን ፡ ውሳኔና፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤትም ፡ ስካር ፡ ቁማር ፡ መጫወትና ፡ አምሽቶ ፡ መግባት ፡ ለፍቺ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ አይሆንም ፡ ብሎ ፡ የሰጠውን ፡ ፍርድ ፡ ለመቃወም ፡ ይችላሉ ። ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተባሉት ፡ ምክንያቶችና ፡ ሽማግሌዎች ፡ ከበየኑ ፡ በኋላ ፡ የደረሱት ፡ ምክንያቶች ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ ሲደመሩ ፡ በሕግ ፡ መሠረት ፡ ፍቺ ፡ ለማስገኘት ፡ በሕግ ፡ ፊት ፡ ዋጋ ፡ ያላቸውና ፡ በቂ ፡ ምክንያቶች ፡ ናቸው ። በተለይም ፡ ይህ ፡ የተጠየቀው ፡ ፍቺ ፡ በተጋቢዎቹ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ የከረረውን ፡ የጋብቻ ፡ ሁኔታ ፡ ሕጋዊ ፡ በማድረግ ፡ ከማቃለሉም ፡ በላይ ፡ ጉዳዩ ፡ የሚመለከታቸውንም ፡ ሰዎች ፡ ኃዘንና ፡ ችግር ፡ ያቃልልላቸዋል ። ስለዚህ ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፡ ለክቡር ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ፡ ቤት ፡ የሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ በተለይም ፡ በኋላ ፡ በደረሱት ፡ ሁኔታዎች ፡ የተነሳ ፡ ውድቅ ፡ እንዲሆንላቸው ፡ በአነስተኛ ፡ የድምፅ ፡ ብልጫ ፡ ሽማግሌዎቹ ፡ መፋታት ፡ ይገባቸዋል ፡ በማለት ፡ የሰጡት ፡ ብይን ፡ እንዲጸድቅ ፡ በማክበር ፡ አመለክታለሁ ፡ በማለት፡ አመለከቱ ።

የሬናቶ ፡ ዤቪ ፡ ጠበቃ ፡ መልስ ፡ ለመስጠት ፡ አልችልም ፡ ስላሉ ፡ መልስ ፡ ሰጭ ፡ ሬናቶ ፡ ዤቪ ፡ በአገሩ ፡ መኖር ፡ ወይም ፡ አለመኖሩን ፡ ለማረጋገጥ ፡ በሚያዝያ ፡ ፳፬፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ለአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ (ኢሚግሬሽን ፡ ክፍል) ፡ ተጻፈ።

አገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ በደብዳቤ ፡ ቁጥር ፡ ፫/፫ሺ፭፻፪/፫/፹፰/፰/፳፱ ፡ ሚያዝያ ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሚስተር ፡ ሬናቶ ፡ ዤቪ ፡ በ፲፭/፲፩/፶፭ ፡ ወደ ፡ ትውልድ ፡ አገሩ ፡ ኢጣሊያ ፡ መሄዱን ፡ አረጋግጧል ። ምንም ፡ እንኳን ፡ የመውጫ ፡ ፈቃድ ፡ ተሰጥቶት ፡ ቢሆን ፡ ምናልባት ፡ ገና ፡ አገር ፡ ያለቀቀ ፡ እንደሆነ ፡ እንዲቀርብ ፡ ለማድረግ ፡ ለይግባኝ ፡ ባይዋ ፡ በሔራልድ ፡ ጋዜጣ ፡ መጥሪያውን ፡ እንዲያሳትሙ ፡ አዘዘ ።

ጉዳዩ ፡ ለ፳፱ ፡ ግንቦት ፡ ፶፯ ፡ ተቀጠረ ። ይግባኝ ፡ ባይዋ ፡ በታዘዙት ፡ መሠረት ፡ ግንቦት ፡ ፲፰ ፡ እና ፡ ፳፭ ፡ በወጣው ፡ የሔራልድ ፡ ጋዜጣ ፡ ሚስተር ፡ ሬናቶ ፡ ዤቪ ፡ ለ፳፱ ፡ ግንቦት ፡ እንዲቀርቡ ፡ መታዘዛቸውን ፡ አስታውቀዋል ።

ነገር ፡ ግን ፡ መልስ ፡ ሰጪ ፡ ሳይቀርብ ፡ ቀረ ። ስለዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የፍርድ ፡ መዝገብና ፡ የቀረቡ ፡ ጽሑፎች ፡ መርምሮ ፡ ቅን ፡ ሆኖ ፡ የተሰማውን ፡ ፍርድ ፡ ለመስጠት ፡ ይገደዳል ።

አምስት ፡ የዘመድ ፡ ሽማግሌዎች ፡ ሁለቱን ፡ ወገኖች ፡ አቅርበው ፡ ከሰሙዋቸው ፡ በኋላ ፡ ለዕርቅ ፡ የተደረገው ፡ ሙከራ ፡ ሳይሆንላቸው ፡ ስለቀረ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡

በሚስስ ፡ ሲልቪያ ፡ ዤቪ ፡ የቀረበው ፡ የጋብቻ ፡ ፍቺ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ያልያዘ ፡ ቢሆንም ፡ የሽማግሌዎቹ ፡ ቦርድ ፡ የፍቺ ፡ ምክንያት ፡ እንዳለው ፡ ለማመዛዘን ፡ ባደረጉት ፡ ጥረት ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፯፻፳፫ ፡ መሠረት ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ያለው ፡ አድርገው ፡ አግኝተውታል ። ነገር ፡ ግን ፡ ሦስት ፡ ሽማግሌዎች ፡ የተጠየቀው ፡ የጋብቻ ፡ ፍቺ ፡ የማይቻል ፡ መሆኑን ፡ በድምጽ ፡ ብልጫ ፡ ወስነዋል ። ሁለት ፡ ሽማግሌዎች ፡ ግን ፡ ጋብቻው ፡ የተቋረጠና ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ ሆነው ፡ እንደማይኖሩ ፡ ወስነዋል ። ስለ ፡ ልጆቻቸው ፡ ቀለብና ፡ አስተዳደርም ፡ ውሳኔ ፡ ሰጥተዋል ።

በመልስ ፡ ሰጭ ፡ ላይ ፡ የቀረቡ ፡ ክሶች ፡ ኃይለኛነት ፡ ቁማር ፡ መጫወት ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ የቤተ ፡ ሰብ ፡ ገንዘብ ፡ አባክኖ ፡ በችግር ፡ ላይ ፡ መጣል ፤ አምሽቶ ፡ መግባት ፤ ስድብ ፤ ከማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ መለየት ፤ የተጋቢዎቹ ፡ የመንፈስ ፡ መፈቃቀድ ፡ የተቋረጠ ፡ መሆኑና ፡ ሊታደስ ፡ የማይቻል ፡ መሆኑ ፡ ነው ። ሽማግሌዎቹ ፡ በጻፉት ፡ እንደተገኘውም ፡ «ባልዬውም ፡ በሱዋ ፡ ስሕተት ፡ ምክንያት ፡ የጋብቻ ፡ ፍቺ ፡ ጥያቄ ፡ እንዲያቀርብ ፡ መብት ፡ የተጠበቀለት ፡ እንዲሆን ፡ ሲል ፡ ጠይቋል» ፡ ይላል ።

ይህ ፡ መልስ ፡ ሰጭም ፡ ለጋብቻው ፡ መፍረስ ፡ ምኞት ፡ እንደነበረው ፡ ያስረዳል ። መልስ ፡ ሰጭ ፡ ሕግ ፡ እንደሚጠይቀው ፡ ሚስቱን ፡ ማክበር ፤ መጠበቅና ፡ መቀለብ ፡ እንዳላሟላ ፡ ተረጋግጧል ። በሁለቱ ፡ ተጋቢዎች ፡ የስምምነት ፡ መንፈስ ፡ በፍጹም ፡ ታጥቶ ፡ ስለነበረ ፡ ለረጅም ፡ ጊዜ ፡ ተለያይተው ፡ ይኖራሉ ።

ፍቺው ፡ ሊፈቀድ ፡ አይቻልም ፡ የተባለው ፡ ጋብቻው ፡ በካቶሊክ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ስለተፈጸመ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ነው ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ የሃይማኖታቸው ፡ አስተያየት ፡ ቢኖር ፡ በይግባኝ ፡ ባይዋ ፡ ላይ ፡ የተዋሉት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ በደሎች ፡ ጋብቻው ፡ ጸንቶ ፡ እንዲኖር ፡ ለመወሰን ፡ አያስደፍሩም ። አብረው ፡ እንዲኖሩ ፡ ማስገደድ ፡ ሕግ ፡ የሚጠላቸውን ፡ ጉዳዮች ፡ እንዲከተሉ ፡ ማድረግ ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ የቀረበውን ፡ ይግባኝ ፡ በሙሉ ፡ ተቀብለን ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሰጠውን ፡ ፍርድ ፡ በሙሉ ፡ ሰርዘነዋል ። በአነስተኛ ፡ ድምጽ ፡ የዘመድ ፡ ዳኞች ፡ ጋብቻው ፡ የተቋረጠና ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ ሆነው ፡ እንደማይኖሩ ፡ ወስነናል ፤ ባልየውም ፡ ከጋብቻው ፡ ለተገኙት ፡ ሦስት ፡ ልጆች ፡ በየወሩ ፡ ፪፻ ፡ ብር ፡ (ሁለት ፡ መቶ) ብር ፡ ይከፍላል ፤ ልጆቹም ፡ ከእናታቸው ፡ ጋር ፡ መቀመጥ ፡ አለባቸው ፤ አባትየውም ፡ ልጆቹን ፡ በማናቸውም ፡ በፈለገበት ፡ ጊዜ ፡ ለመጐብኘት ፡ መብት ፡ አለው ፤ እንዲሁም ፡ ባልየው ፡ ማናቸውንም ፡ የጋብቻ ፡ ስጦታዎችንና ፡ ጥሎሾችን ፡ ለሚስትዮዋ ፡ ሊመልስላት ፡ ይገባል ፡ ብለው ፡ የሰጡትን ፡ ውሳኔ ፡ በሙሉ ፡ አጽንተናል ። ይህ ፡ ፍርድ ፡ ዛሬ ፡ ሰኔ ፡ ፳፩ ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ በግልጽ ፡ ችሎት ፡ ተሰጠ ።

SUPREME IMPERIAL COURT

Addis Ababa, Div. No. 6

Justices:

Mr. Justice Debbas
Mr. Justice Tessema Negede
Mr. Justice Tseggai Teferi

SYLVIA ZEVI v. RENATO ZEVI

Civil Appeal No. 1109-56

Family Law—Divorce—Family arbitrators—Right of Appeal to Court from Arbitrators' award—Nationality and Religion as causes for divorce—Civil Code Art. 736.

On appeal from the decision of the High Court rejecting an application to revise arbitral award by the majority of family arbitrators refusing divorce to plaintiff.

Held: Decision reversed.

1. Manifestly unreasonable decisons by family arbitrators are appealable to a court.

2. Arbitrators are empowered to consider neither the nationality nor the religion of the spouses. In making their decisions arbitrators have to follow strictly provisions of the Civil Code.

3. A life of dissination by a spouse, disrupting the stability of the family and humiliating the other spouse. is a sufficient ground for divorce under the Civil Code.

DECISION

This is an appeal against the decision of the High Court (2nd commercial division) dated 6th March, 1963, in Civil Case No. 112-55, whereby the High Court rejected the petition of the Appellant to revise the decision of the majority of the arbitrators, denying her divorce from her husband, the present Respondent.

Whereas the Respondent seemed to be away from Ethiopia, and although the memorandum of appeal is more than clear, we nevertheless deemed it proper to enquire from the Security Department about the Respondent. In its letter dated 7-5-63 No. 7-7502-Z-88, the Security Department notified us that the Respondent had definitely left Ethiopia on 22.9.62 i.e. about ten months ago. He had no re-entry visa. Although the letter of the Security Department was enough evidence of the Respondent's absence from Ethiopia, we nevertheless wanted to give him more chance to defend himself, if he has any defence at all, and we summoned him through the "Ethiopian Herald" in two different notices published on 26.5.63 and 29.5.63, respectively. The consequence of our-summons in the "Ethiopian Herald" is that Mr. Vosikis appeared on the 6th of June, 1963 and alleged that he represented Renato Zevi; he produced us a two-page letter in French, which we would have liked to keep and study; but Mr. Vosikis openly told the Presiding Judge that there was "secret matter" in the lettter and that he would not like that paper to remain in the Court file. He withdrew his paper. Under the circumstances, we cannot consider that Renato Zevi entered a proper appearance on the date he was summoned to appear, as he did not appear in person, and did not send us a properly delegated counsel. The sense of "properly delegated counsel" is not unknown to a lawyer of so many years of experience like Mr. Vosikis. His own client Renato Zevi having rescinded his power of attorney after he ran away from Eth-

iopia, cannot ask him through a simple letter which we did not even see as it contained secrets - to reappear for him; he cannot revalidate the power of attorney so cheaply. A power of attorney originating from a foreign country must necessarily be signed by Renato Zevi in the presence of a Notary Public, legalised by the competent authorities of Italy, and finally legalised by our Ministry of Foreign Affairs. This has not been done in the case of Zevi and we consequently rule that he did not enter an appearance either in person or through a properly delegated counsel, as called upon in the newspaper. Under the circumstances, whereas we cannot leave this helpless woman neither married nor divorced, we have decided to give our final opinion forthwith, as to whether the majority or minority arbitral award should be considered as valid and executed.

It is established and undisputed that both Appellant and Respondent were married on 26.4.52 according to the rites of the Catholic Church. As a result of this marriage, they had three children who are at present 10, 7 and 5 years respectively. The marriage was solemnized in the Catholic Church of Addis Ababa.

Both Appellant and Respondent were living in Ethiopia for very long years, and they hold Foreigners' Identity Cards as foreign residents in Ethiopia. As residents, they are entitled to the protection of our Civil Code. This very same division of the Supreme Imperial Court has, in two previous appeals, i.e. 633-55 and 724-56, held that if either of the two spouses was domiciled in Ethiopia at the relevant time, the family arbitrators shall be entitled to entertain a petition for divorce, as is the present case.

Bearing in mind that she was domiciled in Ethiopia, and on grounds of matrimonial differences with her husband, the Appellant applied for divorce through arbitration, in accordance with the relevant provisions of the Civil Code. Five arbitrators heard both spouses, and it was held by a majority of 3 to 2 that there existed no good ground for divorce. The majority arbitral award dated 17th July, 1962 states, among others, that both spouses being of Italian nationality, and having solemnized their marriage according to the Catholic Dogma, are authomatically not entitled to divorce, as the Roman Catholic Church does not allow divorce. The minority arbitral award, on the other hand, dated 19th July, 1962, did not go into questions of religion or nationality. It openly mentioned at the beginning thereof, among other things, that the husband Renato Zevi "reserves his right to bring a petition for divorce because of alleged faults of his wife." But the husband, at that time, asked the arbitrators to dismiss his wife's petition for divorce. In brief, whereas we shall go at a later stage lengthily into the arguments of the arbitrators, the minority arbitral award held that the petitioner Sylvia Zevi had advanced sufficiently reasonable grounds to entitle her to divorce from her husband; and the minority thereupon declared the dissolution of the marriage between the two spouses.

Basing herself on Article 736 of the Civil Code, which authorizes an appeal to Court against a manifestly unreasonable decision of arbitrators, the Appellant Sylvia Zevi appealed to the High Court for reversal of the majority arbitral award and the confirmation of the minority arbitral award, granting her divorce. The High Court dismissed her appeal, considering that drunkenness, gambling and going home late in the evenings, which is tantamount to social isolation of the wife, are not sufficient grounds to grant a divorce.

The above is a brief resume of Sylvia Zevi's case, so far that is why she appealed again to the Supreme Imperial Court, asking for reversal of the majority arbitral award and the confirmation of the minority award, or in brief, the quashing of the decision of the High Court, and the confirmation of the minority opinion of the arbitrators.

Before coming to the merits of the appeal, it is interesting to emphasize that the husband absconded from Ethiopia about three or four months prior to the decision of the High Court. When he so absconded, he took with him the three minors born out of the marriage with Sylvia Zevi. He completely disregarded the fact that they are not only his own childeren but those of Sylvia too. Furthermore, by so escaping from Ethiopia while his case was still pending before the High Court, we are forced to deduce that he intended to run away from the jurisdiction of our Courts, as he was domiciled here and was subject to our laws and decisions. By going to a foreign land, i.e. his country of origin Italy, he would thus change his personal status and avoid the application of Ethiopian law against him, in case the High Court pronounces a decision adverse to him. And by leaving Ethiopia before the final decision of the High Court, it is more than clear that he was afraid of the result of the High Court decision, particularly that he took with him three minor children, who are now subject of this final decision of the Supreme Imperial Court, but who are not within our jurisdiction. Last but not least, Renato Zevi cancelled, from Italy, the power of attorney that he had given to Mr. Vosikis in Ethiopia; the High Court records clearly show us that his advocate produced the letter of cancellation of his mandate, and walked out from the Court-room. By so cancelling the power of attorney, the intention of Renato Zevi is clear to us: he urges us to deduce that he wanted his helpless wife to continue living alone, on pure uncertainty of the future, and hopelessness as to her children. Such a shameful attitude on the part of a man forces us to find as a fact that he is a person of bad faith, with whom a lady cannot continue existing and killing her future.

There are other facts of which we are, officially unaware, namely (1) instituting in Italy proceedings against his wife, seeking separation from bed and board; those are proceedings allowable in Italy in lieu of divorce as divorce is not allowed under the Catholic dogma. (2) Both spouses have been living separately in Ethiopia for more than 3 years.

The latter two grounds will not affect us much, as the shameful attitude of this man forces us to make our deductions.

To start with, it is clear beyond the least shadow of doubt that all five arbitrators, and the High Court, found as a fact that the husband is a gambler, a drunkard, and a man who was abusing his wife all day through, coming late at night, and having no respect whatsoever to his helpless wife. As a result of his inveterate gambling, the financial stability of the family has been shattered. As a result of his continued insults and abuse of his wife, there arose the question of absolute incompatibility of character, coupled with the social isolation of his wife. In our opinion, those grounds are more than sufficient to allow a divorce. The majority of the arbitrators should have realized that more harm can befall a husband and wife who are forced to live together out of social necessity, when the spiritual communion and mutual respect between them have ceased to exist. This is an argument that all arbitrators should, in the future, consider before pronouncing themselves on a question of divorce. They have certainly tried their best to reconcile them but in vain. So what is the use of forcing them to live together, especially that they have lost the mutual respect they owe to each other. The arbitrators may have very well known that both spouses were living separately in Ethiopia for the last three years; so what is the use again to force them to keep "officially married" but hating each other and disrespecting themselves in the presence of their minor children. If Renato Zevi reserved his right to petition for divorce, as it clearly set down in the minority arbitral award, so again what is the use of forcing them to live

together? Abuse of the wife, inveterate gambling and drunkenness amount to social isolation of the wife and disregard of her very existence. So what is the use of forcing those two human beings to keep officially married? It is preferable to divorce two such persons than to let them plan their very destruction. One can see the irresponsibility of this type of man who takes away the three minor children, completely disregarding the existence of their mother; his irresponsibility is still more striking when, through gambling, he shattered the financial stability of the whole family. Consequently, for such a man, no opening is available but throw him out of the family through divorce. The woman is not his slave to continue living in hopeless uncertainty.

In addition, it is of extreme importance to underline in the present appeal and for the future, that the question of religion and nationality which the majority arbitral award seems to have based itself thereon, should not affect the arbitrators. In this case, the learned majority of the arbitrators mentioned in its award that both parties being Italians, married according to the Catholic dogma, cannot obtain divorce, as divorce is not allowed according to the rites of the Catholic Church. This argument may very well be strong before an Ecclesiastical Court but not before a Civil Court. We are not concerned with religious matters. If the Civil Code allows divorce to be pronounced by arbitartors, it is irrespective of religion and nationality. What is conclusive is the law of domicile; and we have established this principle in two previous appeals, as well as in the present one. Sylvia Zevi, as a foreign resident domiciled in Ethiopia, is entitled to the protection of our Civil Code. The Ethiopian Civil Code mentions no religion and no nationality. It simply authorizes family arbitrators to pronounce a divorce, if all conditions of the Civil Code are complied with. In this particular case, the family arbitrators were entitled to entertain the petition for divorce; and despite what they heard , they refused the petition by three to two. The opinion of the High Court upholding the majority is, in our opinion, wrong.

In view af all the above reasons, and whereas the Appellant is entitled to impugn any manifestly unreasonable decision of family arbitrators under Article 736 of the Civil Code; and whereas the Appellant did so before the High Court but unsuccessfully; and whereas more harm can befall a husband and wife who are forced to live together out of social necessity, because they are so ordered by the family arbitrators, although the spiritual communion between them has ceased to exist; and whereas it has resulted before the family arbitrators and the High Court that the husband is an inveterate gambler, drunkard, socially isolating his wife; and whereas the question of religion and nationality cannot be considered in this case and all other similar cases; and whereas it is literally detrimental to both spouses to continue living together in pure unhappiness, when the marital bond has been finally severed; and whereas we consider that all the above arguments logically justify a divorce and dissolution of marriage according to the Civil Code; we therefore allow this appeal, and as already pronounced by the minority of the arbitrators, we hereby declare the dissolution of the marriage between Renato Zevi and Sylvia Zevi as from the date of the minority arbitral award. This is tantamount to a reversal of the decision of the High Court and a confirmation of all the minority arbitral award.

A copy of this decision shall be served on the High Court for execution.

Given and delivered in open Court this 11th day of June 1963 in the presence of the Appellant in person and of her attoney Mr. Hamawi. Given in default of Respondent for reasons explained in this decision.

ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤
አዲስ ፡ አበባ ፤ የንግድ ፡ ችሎት ።

ዳኞች ፤

አቶ ፡ ንጉሤ ፡ ፍትሕ ፡ አወቀ ፤
አቶ ፡ መሐመድ ፡ ብርሃን ፡ ኑርሁሴን ፤
አቶ ፡ ዘለቀ ፡ ደስታ ።

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፱፻፷/፷ ።

ዋስትና ፤ የጠለፋ ዋስትና ፣ የዋስትና ማስረጃ ፣ የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥሮች ሺ፯፻፳፭ (ሀ) ሺ፱፻፷፪ ፤ ፪ሺ፩ ፪ሺ፫ ፤ ፪ሺ፬፻፸፪ ።

የአውራጃው ፍ/ቤት የጠለፋ ዋስትና ውልን ለማረጋገጥ የቃል ምስክር ስለ ተቀበለ የቀረበ ይግባኝ ፤ ውሳኔ ፤ ፍርዱ እንዲለወጥ ተወስኖ ጉዳዩ ወደ አውራጃው ፍርድ ቤት ተመለሰ ።

የቃል ምስክር ለመቀበል የሚቻለው መጀመሪያ ውሉ ያለበት ጽሑፍ መጥፋቱን አመልካቹ ካረጋገጠ በኋላ ነው ። ጠፋ ብሎ መናገር ብቻ አይበቃም ።

ፍርድ

በመሠረቱ ፡ ይህ ፡ ክስ ፡ በመጀመሪያ ፡ የቀረበው ፡ በመናገሻ ፡ አውራጃ ፡ ግዛት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሲሆን ፡ የመጀመሪያው ፡ ከሳሽ ፤ ያሁን ፡ መልስ ፡ ሰጭ ፤ ፪ኛው ፡ ተከሳሽ የመንግሥት ፡ ገንዘብ ፡ በማጉደሉ ፡ ተከስሶ ፡ በፍርድ ፡ ተወስኖ ፡ በፍርዱ ፡ መሠረት ፡ ዋስ ፡ ነህና ፡ ክፈል ፡ ተብዬ ፡ ስለተገደድኩ ፡ በጠለፋ ፡ ዋስ ፡ ላይ ፡ ክስ ፡ ማቅረብ ፡ ግድ ፡ ሆነብኝ ፡ ብለዋል ። የመጀመሪያው ፡ ፩ኛ ፡ ተከሳሽ ፤ ያሁኑ ፡ በይግባኝ ፡ ከሳሽ ፤ መልስ ፡ ሲሰጡ ፡ በጠለፋ ፡ ዋስ ፡ ሆነው ፡ እንዳልፈረሙና ፡ የጠለፋ ፡ ዋሱ ፡ ፊርማ ፡ ጠፋ ፡ ከተባለ ፡ የሰው ፡ ምስክር ፡ ለማሰማት ፡ የማይቻል ፡ መሆኑን ፡ በመግለጽ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪ሺ፬፻፸፪ ፡ በመጥቀስ ፡ ተከራክረዋል ።

የመናገሻው ፡ አውራጃ ፡ ግዛት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የጠለፋ ፡ ዋሱ ፡ ፊርማ ፡ ጠፋ ፡ ከተባለ ፡ በጽሑፍ ፡ ላይ ፡ የነበሩት ፡ እማኞች ፡ ቀርበው ፡ እንዲመሰክሩ ፡ አዝዞ ፡ አራት ፡ ምስክሮች ፡ ቀርበው ፡ አራቱም ፡ የዋስትና ፡ ማረጋገጫ ፡ እንደተጻፈና ፡ እነ ሱም ፡ በጽሑፍ ፡ ላይ ፡ እንደፈረሙ ፡ ገልጸዋል ።

አሁን ፡ በይግባኝ ፡ ከሳሹ ፡ ፍርዱን ፡ በመቃወም ፡ በድጋሚ ፡ ሀ/ በበኩሌ ፡ የጠ ለፋ ፡ ዋስ ፡ ሆኜ ፡ መፈረም ፡ የለብኝም ፤ ለ/ በፍትሐብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪ሺ፬፻፸፪ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ከ፭፻ ፡ ብር ፡ በላይ ፡ የሰው ፡ ምስክር ፡ ሊቆጠር ፡ የማይገባ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፱፻፸፪ ፡ በተመለከተው ፡ ዋስ ፡ ለመሆኔ ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ማስረጃ ፡ ማቅረብ ፡ እንጂ ፡ ዋስትና ፡ በሰው ፡ ምስክር ፡ ማስረዳት ፡ ስለማይቻል ፤ ሐ/ የጠለፋው ፡ ዋስትና ፡ ለመኖሩ ፡ መልስ ፡ ሰጭው ፡ ያቀረ ባቸው ፡ ምስክሮች ፡ ዘመዶቹ ፡ መሆናቸውንና ፡ የሐሰት ፡ ምስክሮች ፡ ስለሆኑ ፡ ኃላፊ ነት ፡ የለብኝም ፡ በማለት ፡ ተከራክሯል ።

መልስ ፡ ሰጭው ፡ በበኩሉ ፤ ፩ኛ/ የይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ልጅ ፤ አቶ ፡ አሰፋ ፡ ደምሴ ፤ በገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ ሥራ ፡ ሲቀጠር ፡ መልስ ፡ ሰጪው ፡ ተያዥ ፡ ሆኜ ፡ እንድፈርም ለት ፡ ለምነውኝ ፡ እንድፈርም ፡ ሲያደርጉ ፡ ኃላፊ ፡ ጠለፋ ፡ ዋስ ፡ ለልጄ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፤ ለማንኛውም ፡ ተጠያቂ ፡ ነኝ ፡ ሲሉ ፡ ስለፈረሙ ፡ ተያዥ ፡ ሆኜ ፡ ለመፈረም ፡ ቻልኩ ፤ ፪ኛ/ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ የጠለፋ ፡ ዋስ ፡ የሆኑበት ፡ የጽሑፍ ፡ ማስረጃ ፡ ስለጠፋብኝ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪ሺ፪-፪ሺ፫ ፡ በሚያዝዘው ፡ መሠረት ፡ በጽሑፍ ፡ ላይ ፡ የነበሩትን ፡ እማኞች ፡ ለሁለታችንም ፡ ዝምድናቸው ፡ ትክክል ፡ የሆኑትንና ፡ የነበሩትን ፡ አቅርቤ ፡ በአውራጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አስመሰከርኩ ፤ ፫ኛ/ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ከምስክሮቹ ፡ ዝምድና ፡ የሌላቸው ፡ በማስመሰል ፡ ያልሆነውን ፡ በማተት ፡ የወንጀል ፡ ክስና ፡ ክርክር ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ክስ ፡ ላይ ፡ መነገር ፡ የማይገባውን ፡ በመጥቀስ ፡ ጽፈዋል ፤ ፬ኛ/ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ የብድር ፡ ገንዘብ ፡ ለማስመስል ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፬፻፸፪ ፡ ጠቅሰው ፡ ጽሑፉ ፡ ቢጠፋም ፡ በሰው ፡ ምስክር ፡ ከ፭፻ ፡ ብር ፡ በላይ ፡ አያስመሰክርም ፡ እያሉ ፡ የጻፉት ፡ የመንግሥት ፡ ገንዘብ ፡ ዕዳ ፡ አከፋፈልን ፡ የሚመለከት ፡ አይደለም ፤ ለብድር ፡ ገንዘብ ፡ ብቻ ፡ ነው ። በኃላፊነትም ፡ ከፍለው ፡ ከዕዳው ፡ አድኑኝ ፡ በማለት ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፡ ክሱ ፡ የብድር ፡ ገንዘብ ፡ አለብዎት ፡ የሚል ፡ አይደለም ፡ በማለት ፡ መልሳቸውን ፡ አቅርበዋል ።

በይግባኝ ፡ ከሳሹም ፡ የመልስ ፡ መልሳቸውን ፡ ሲሰጡ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪ሺ፬፻፸፪ ፡ ንዑስ ፡ ቁጥር ፡ (፫) የሚደግፋቸው ፡ መሆኑን ፡ በመግለጽና ፡ በጽሑፉ ፡ ላይ ፡ ያሉት ፡ እማኞች ፡ ዝምድናቸው ፡ ከመልስ ፡ ሰጭ ፡ ብቻ ፡ መሆኑን ፡ በማብራራት ፡ ጽፈዋል ።

በመሠረቱ ፡ በዚህ ፡ ይግባኝ ፡ ላይ ፡ ዋናው ፡ የሕግ ፡ ክርክር ፡ የጠለፋ ፡ ዋስ ፡ ፎርማ ፡ ጠፋ ፡ ከተባለ ፡ በጽሑፉ ፡ ላይ ፡ የነበሩት ፡ እማኞች ፡ ቀርበው ፡ ሊመሰክሩ ፡ ይችሉ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ። የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪ሺ፫ ፡ ስለማስረጃ ፡ ማቅረብ ፡ ሁኔታ ፡ ሳያትት ፡ ውሉ ፡ በጽሑፍ ፡ እንዲሆን ፡ ሕግ ፡ ባዘዘ ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ ጽሑፍ ፡ የተቀደደ ፤ የተሠረቀ ፤ የጠፋ ፡ ለመሆኑ ፡ ካልተረጋገጠ ፡ በቀር ፡ ውሉን ፡ በምስክሮች ፡ ወይም ፡ በሕሊና ፡ ግምት ፡ ለማስረዳት ፡ አይቻልም ፡ ይላል ። የዋስትና ፡ ውል ፡ በጽሑፍ ፡ መሆን ፡ እንዳለበት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፯፻፳፭ ፡ (ሀ) ያስረዳል። የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪ሺ፬፻፸፪ ፡ ንዑስ ፡ ቁጥር ፡ (፫) የሚያስረዳው ፡ ስለ ብድር ፡ ስለሆነ ፡ ስለዋስትና ፡ ኃላፊነት ፡ በቀረበው ፡ ክስ ፡ የተባለውን ፡ ሕግ ፡ መጥቀስ ፡ አግባብ ፡ አይደለም ። ስለማስረጃ ፡ አቀራረብ ፡ ክልል ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪ሺ፫ ፡ በመጥቀስ ፡ ተከሳሹ ፡ በጽሑፍ ፡ ግዴታ ፡ የገባበት ፡ የጠለፋ ፡ ዋስትና ፡ ሠነድ ፡ ጠፍቷል ፡ በማለት ፡ በእማኝነት ፡ በሠነዱ ፡ ላይ ፡ የፈረሙት ፡ ምስክሮች ፡ ቀርበው ፡ እንዲመሰክሩ ፡ የቀረበው ፡ ጥያቄ ፡ ተቀባይነት ፡ የሚያገኘው ፡ ምን ፡ ሁኔታ፡ ለመኖሩ ፡ ሲረጋገጥ ፡ ነው ? ቁጥር ፡ ፪ሺ፫ ፡ የሚለው ፡ ውሉ ፡ በጽሑፍ ፡ እንዲሆን ፡ ሕግ ፡ ባዘዘ ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ ጽሑፍ ፡ የተቀደደ ፤ የተሰረቀ ፤ የጠፋ ፡ መሆኑ ፡ ካልተረጋገጠ በቀር ፡ ውሉን ፡ በምስክሮች ፡ ለማስረዳት ፡ አይቻልም ፡ ይላል ። በዚህ ፡ ሕግ ፡ ለመጠቀም ፡ መጀመሪያ ፡ የተባለው ፡ የጠለፋ ፡ ዋስትና ፡ ውል ፡ የተቀደደ ፤ የተሠረቀ ፡ ወይም ፡ የጠፋ ፡ ለመሆኑ ፡ መረጋገጥ ፡ አለበት ፡ ማለት ፡ ነው ። ካልተረጋገጠ ፡ በቀር ፡ የሚለው ፡ አነጋገር ፡ በጽሑፍ ፡ ማመልከቻ ፡ ማስረጃው ፡ ጠፍቷል ፡ በማለት ፡ አነጋገር ፡ በመግለጽ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ለመጥፋቱ ፡ በማስረጃ ፡ ማረጋገጥ ፡ ይገባል ። ማስረጃ ፡ ጠፋ ፡ ወይም ፡ ተሰረቀ ፡ ወይም ፡ ተቀደደ ፡ በማለት ፡ አነጋገር ፡ ብቻ ፡ የሰው ፡ ምስክር ፡ የሚቀርብ ፡ ከሆነ ፡ ሕጉ ፡ የሚጠይቀው ፡ የጽሑፍ ፡ ማስረጃ ፡ መኖር ፡ ዋጋቢስ ፡ ይሆናል ፡ ማለት ፡ ነው ። የሕጉ ፡ ዓላማ ፡ እርግጥ ፡ የጽሑፍ ፡ ማስረጃ ፡ ካለና ፡ በአጋጣሚ ፡ ሁኔታ ፡ የጠፋ ፡ ወይም ፡ የተሰረቀ ፡ ወይም ፡ የተቀደደ ፡ ለመሆኑ ፡ በማስ

ረጃ ፡ ከተረጋገጠ ፡ ውል ፡ እንደነበረ ፡ በሰው ፡ ምስክር ፡ ለማስረዳት ፡ የሚቻል ለመ ሆኑ ፡ ነው ። አንድ ፡ ሰው ፡ የጽሑፍ ፡ ማስረጃ ፡ ካለው ፡ በአጋጣሚ ፡ ሁኔታ ፡ ቢጠፋ በትም ፡ በውሉ ፡ ያገኘው ፡ መብት ፡ ቀሪ ፡ እንዳይሆንበት ፡ በማሰብ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ የአውራጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የተባለው ፡ የጠፋ ፡ ዋስትና ፡ ሰነድ ፡ ለመጥፋቱ ፡ በማ ስረጃ ፡ ሳያረጋግጥ ፡ ከሳሹ ፡ ጠፍቷል ፡ በማለት ፡ በክሱ ፡ ማመልከቻ ፡ በመግለጡ ፡ ብቻ ፡ እንደበቂ ፡ ማስረጃ ፡ ቆጥሮ ፡ የሰው ፡ ምስክር ፡ የተቀበለው ፡ ከቁጥር ፡ ፪ሺ፫ ፡ አነ ጋገር ፡ ውጭ ፡ ስለሆነ ፡ የአውራጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በመዝገብ ፡ ቁጥር ፡ ፲፱፻፷፩/፷ ፡ የሰጠውን ፡ ፍርድ ፡ ሽረን ፡ እንደገና ፡ የአውራጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የጠፋው ፡ ዋስ ትና ፡ ውል ፡ የጠፋ ፡ ለመሆኑ ፡ መጀመሪያ ፡ በማስረጃ ፡ ካረጋገጠ ፡ በኋላ ፡ በግራ ፡ ቀኙ ፡ በኩል ፡ የሚቀርበውን ፡ ማስረጃ ፡ ሰምቶ ፡ ፍርድ ፡ እንዲሰጥ ፡ ፍርዱን ፡ ሰብረን ፡ መልሰን ፡ ለመናገሻ ፡ አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ልከናል ።

በዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ያለውን ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ኪሣራ ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ ይቻቻሉ ፡ ብለናል ።

ይህ ፡ ፍርድ ፡ ዛሬ ፡ መስከረም ፡ ፳፰ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ተሰጠ ።

HIGH COURT

Addis Ababa, Commercial Division

Judges:

Ato Negussie Fitawake

Ato Mohamed Berhan Nurhussien

Ato Zelleke Desta

Civil Appeal No. 1220-60

Suretyship—counter guarantee–proof of guaranty–Civ. Code Arts. 1922, 2472, 2002, 2003, 1725(a)

Appeal from the ruling of the Awraja Court admitting oral evidence to prove the existence of a contract of counter–guarantee.

Held: Decision quashed and remanded.

For an oral proof to be admittted one has to establish that the document bearing the contract was lost. Mere allegation is not enough.

JUDGMENT

Initially this suit had been instituted in the Menaghesha Awraja Court. The Plaintiff, present Respondent, stated that as the second Defendant had misappropriated a certain sum from the government revenue he (the Respondent) was ordered to pay in his capacity as a guarantor, and that he was compelled to institute a suit against the counter-guarantor. The Defendant-appellant, in his reply contended that he did not sign as a counter-guarantor; and that if it is alleged that the document that evidences the counter-guarantee has been lost then it is not possible to introduce witnesses to show the existence thereof and invoked Article 2472 of the Civil code in support of his contention.

The Menaghesha Awraja Court directed the witnesses who had attested to the making of the contract to give their testimony; four witnesses testified that a document of counter-guarantee was executed and that they had signed it.

The Appellant, who objects to the judgment of the lower court, contends that: 1) he did not bind himself as a counter-guarantor; 2) pursuant to Article 2472, since the amount of money involved exceeds E$ 500, the claim cannot be proved by witnesses; and according to Article 1922 a guarantee must be proved expressly and not by witnesses; 3) the witnesses introduced are the Respondent's relatives and as such not trustworthy.

The Respondent submits that: 1) when the Appellant's son, Ato Assefa Demissie, was employed by the Ministry of Finance Appellant requested Respondent to act as a guarantor for his son; that when the Respondent bound himself as guarantor, the Appellant undertook to act as a counter-guarantor in favour of his son; 2) as the document embodying the counter-guarantee was lost, he called witnesses pursuant to Articles 2002-2003; that these witnesses who testified at the Awraja Court had attested to the making of the contract and were as closely related to Appellant as

to himself; 3) the Appellant, who asserts that he is not related to the witnesses, made references to a criminal charge which does not at all have any bearing on the civil case; 4) that Article 2472 of the Civil Code cited by the Appellant is not relevant in the case of a debt owed to the state but to a contract of loan. That the action was brought to compel Appellant to effect payment in comformity with his undertaking and that the complaint does not allege that Appellant owes money as a result of a contract of loan.

In his reply, the Appellant stated that Article 2472 (3) of the Civil Code supports his argument and that the witnesses were related only to the Respondent.

The main issue in the case at bar is whether witnesses who signed the document of counter-guarantee may give testimony when said document is allegedly lost. Article 2003 of the Civil Code, relating to modes of proof, provides that where the law requires written form for the completion of a contract such contract may not be proved by witnesses or presumed unless it is established that the document evidencing the contract has been destroyed, stolen or lost. Article 1725 (a) requires that contracts of guarantee shall be in writing. Article 2472 (3) of the Civil Code which relates to a contract of loan is not relevant to a cause of action founded on the liability of a guarantee. What conditions must be fulfilled prior to allowing the Plaintiff to introduce oral evidence pursuant to Article 2003 of the Civil Code where Plaintiff alleges that the document embodying the counter-guarantee has been lost and applies to call the witnesses who have attested to the existence thereof? Article 2003 states that where the law requires written form for the completion of a contract, such contract may not be proved by witnesses unless it is established that the document evidencing the contract has been destroyed, stolen or lost. One who seeks to avail himself of this provision must primarily establish that the said document has been destroyed, stolen or lost. The term "unless it is established" shows that the mere allegation that a certain document has been lost does not suffice but the loss thereof must be proved by evidence. If it be allowed to call witnesses merely by alleging that a document has been lost, stolen or destroyed, it would render ineffective the legal requirement of documentary proof. The purpose of the law is to enable a person to prove by witnesses the existence of a contract where he succeeds in establishing that in actual fact a written contract existed and that such contract has been lost, stolen or destroyed due to some fortuitous event. The object of the law is to prevent the extinction of a right created by a contract merely by reason of the loss of a written document due to some fortuitous event. However, the Awraja Court, without establishing the loss of the document evidencing the counter-guarantee, admitted oral evidence merely on the basis of the allegations contained in the plaintiff's statement of claim. We do not find the ruling of the Awraja Court to be consistent with Article 2003. We therefore quash the judgment passed by the said lower Court in Civil file No. 661-60 and remand the case for further proceeding not inconsistent with this opinion.

Each party shall bear his own cost incurred during the proceedings in this Court.

October 8, 1968.

ጠቅላይ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤

አዲስ ፡ አበባ ፤ ፩ኛ ፡ ችሎት ።

ዳኞች ፤

አፈንጉሥ ፡ ተሾመ ፡ ኃይለ ፡ ማርያም ፤

አቶ ፡ ታደሰ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፤

ቀኛዝማች ፡ ሙላት ፡ በየነ ።

በይግባኝ ፡ ከሳሽ ፤ ወይ/ ጥሩነሽ ፡ ይግለጡ ፤

በይግባኝ ፡ ተከሳሽ ፤ አቶ ፡ ኪዳኔ ፡ ደገፉ ።

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቁጥር ፡ ፱፻፷፫/፷ ።

ክስን ስለመተው ፤ ለዳኝነት የተከፈለ ገንዘብ ስለመመለስ ፤ የፍትሐ ብሔር ሕግ ሥነ ሥርዓት ቊጥሮች ፪፻፴፩—፪፻፴፪ ፤ የሕግ ማስታወቂያ/፲፱፻፶፫ ዓ. ም. ቊ. ፩፻፹፯/ ቊጥሮች ፲፩ ፤ ፳፩ ።

ክሱ በፍ/ቤት መሰማት ከመጀመሩ በፊት ክስ ስለተውኩ ለዳኝነት የከፈልኩት ገንዘብ እንዲመለስልኝ ብሎ የጠየቀውን ከፍተኛው ፍ/ቤት አይገባህም ስላለው አመልካች ያቀረበው ይግባኝ ፤

ውሳኔ፡— ፍርዱ ተሽሯል ።

አንድ ባለጉዳይ ባለጋራው ከመጠራቱ በፊት ክሱን ከተወ ለዳኝነት ከተከፈለው ገንዘብ በሕግ የተወሰነው ከተቀነሰ በኋላ የቀረው ለከፋዩ ተመላሽ ነው ።

ይግባኝ ፡ ባይ ፡ ይህን ፡ የይግባኝ ፡ አቤቱታ ፡ ያቀረቡት ፡ በከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ጀምረውት ፡ የነበረውን ፡ ክስ ፡ ተከሳሹ ፡ ተጠርቶ ፡ ከመቅረቡና ፡ ክርክሩም ፡ ከመጀመሩ ፡ በፊት ፡ በማንሳታቸው ፡ መዝገቡ ፡ ስለተዘጋ ፡ የዳኝነት ፡ ገንዘብ ፡ ሕጉ ፡ በሚያዘው ፡ መሠረት ፡ ሊመለስልኝ ፡ ይገባል ፡ በማለት ፡ ያቀረቡትን ፡ ጥያቄ ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አልቀበልም ፡ ስላላቸው ፡ ነው ።

በዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ ክርክር ፡ ሌላ ፡ ተከራካሪ ፡ ወገን ፡ ስለማያሻና ፡ ቀድሞውንም ፡ ቀርቦ ፡ የተከራከረ ፡ ተከሳሽ ፡ ስላልነበረ፡ የይግባኝ ፡ ባዩን ፡ አቤቱታ ፡ ለመስማት ፡ መልስ ፡ ሰጭ ፡ አላስፈለገም ። ይግባኝ ፡ ባይ ፡ የጻፉትን ፡ የይግባኝ ፡ ማመልከቻና ፡ የከፍተኛውም ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ትዕዛዝ ፡ የሰጠበትን ፡ መዝገብ ፡ እንደተመለከትነው ፤ ይግባኝ ፡ ባይ ፡ የሚከራከሩት ፡ አቅርቤ ፡ የነበረውን ፡ ክስ ፡ ተከሳሹ ፡ ከመቅረቡ ፡ በፊት ፡ ካነሳሁና ፡ መዝገቡ ፡ ከተዘጋ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በቁጥር ፡ ፪፻፴፪ ፡ እንዲሁም ፡ ስለዳኝነት ፡ አከፋፈል ፡ የወጣው ፡ ደንብ ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ቁጥር ፡ ፲፰ ፡ አንቀጽ ፡ ፲፩ ፡ በሚያዝዘው ፡ መሠረት ፡ የዳኝነቱ ፡ ገንዘብ ፡ ሊመለስልኝ ፡ ይገባል ፡ በማለት ፡ ነው ።

የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ግን ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በቁጥር ፡ ፪፻፴፪ ፡ የተደነገገው ፡ የሚመለከተው ፡ ተቀባይነትን ፡ በማጣት ፡ የተሠረዘ ፡ ክስን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከሳሹ ፡ ክሱን ፡ በመተው ፡ የተዘጋውን ፡ መዝገብ ፡ አይደለም ፡ በሚል ፡ አስተያየት ፡ የይግባኝ ፡ ባይን ፡ ጥያቄ ፡ ውድቅ ፡ አድርጎባቸዋል ።

እንግዲህ ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ ትክክል ፡ ነው ፡ አይደ ለም ፡ ለማለት ፡ ይግባኝ ፡ ባይዋ ፡ የጠቀሷቸውን ፡ ድንጋጌዎች ፡ መመርመር ፡ ያሻል ፡፡

ስለዳኝነት ፡ ሥራ ፡ አመራር ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ቁጥር ፡ ፲፫ ፡ ሐምሌ ፡ ፳፩ ፡ ቀን፡ ፲፱፻፵፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የወጣው ፡ ደንብ ፡ በአንቀጽ ፡ ፲፩ ፡ ላይ ፡ እንደሚደነግገው ፤ ከሳሽ ፡ ክርክር ፡ ከመጀመሩ ፡ በፊት ፡ ክሱን ፡ ያነሳ ፡ እንደሆነ ፡ ከተከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ ላይ ፡ በኪሣራ ፡ ስም ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ ገቢ ፡ የሚሆነው ፡ ከተቀነሰ ፡ በኋላ ፡ ቀሪው ፡ የዳኝ ነት ፡ ገንዘብ ፡ ለከሳሹ ፡ ይመለስለታል ፡ ይላል ። የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥር ዓት ፡ ደግሞ ፡ በቁጥር ፡ ፪፻፴፪ ፡ ንዑስ ፡ ቁጥር ፡ ፩(ለ) ላይ ፡ በቁጥር ፡ ፪፻፴፩ ፡ መሠረት ፡ ክሱ ፡ ተቀባይነትን ፡ ያጣ ፡ ወይም ፡ የተሠረዘ ፡ እንደሆነ ፡ ከሳሹ ፡ ከፍሎት ፡ የነበረው ፡ ዳኝነት ፡ በደንቡ ፡ መሠረት ፡ የሚቀነሰው ፡ ከተቀነሰ ፡ በኋላ ፡ ቀሪው ፡ ይመለስለ ታል ፡ ይላል ። እነዚህ ፡ ሁለቱ ፡ ድንጋጌዎች ፡ አንዱ ፡ ሌላውን ፡ ያሟላሉ ፡ እንጂ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተቃራኒዎች ፡ አይደሉም ፤ ናቸውም ፡ ተብለው ፡ አይተረጎሙም ። ስለዳኝነት ፡ አከፋፈል ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ የወጣው ፡ ደንብ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በቁጥር ፡ ፪፻፴፪ ፡ ላይ ፡ ከተደነገገው ፡ ጋር ፡ ሲነበብ ፡ ከሳሹ ፡ ክሱን ፡ በማንሳቱ ፡ መዝገቡ ፡ ከተዘጋ ፤ ክሱንም ፡ ያነሳው ፡ ክርክር ፡ ከመጀመሩ ፡ በፊት ፡ ከሆነ ፡ ለዳኝነት ፡ የከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ ሕጉ ፡ በሚያዝዘው ፡ መሠረት ፡ የሚቀነሰው ፡ ተቀንሶ ፡ ቀሪው ፡ የሚመለስለት ፡ መሆኑን ፡ በጉልህ ፡ ያስረዳል ። የከፍተኛውን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ያሳሳተው ፡ "ተቀባይነት ፡ ያጣ" ፡ የሚለው ፡ አነጋገር ፡ ነው ። የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በቁጥር ፡ ፪፻፴፩ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የቀረበለትን ፡ ክስ ፡ የሚሠርዝ በትን ፡ ሁኔታ ፡ ከዘረዘረ ፡ በኋላ ፡ በቁጥር ፡ ፪፻፴፪ ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ የክሱ ፡ መሠረዝ ፡ ስለሚያስከትለው ፡ ውጤት ፡ ሲደነግግ ፤ በቁጥር ፡ ፪፻፴፪ ፡ ንዑስ ፡ ቁጥር ፡ ፩ (ለ) ፡ ላይ ፡ የቀረበው ፡ ክስ ፡ ተቀባይነትን ፡ ያጣ ፡ ወይም ፡ የተሠረዘ ፡ ሲሆን ፡ የዳኝነቱ ፡ ወጭ ፡ በደንቡ ፡ መሠረት ፡ ለከሳሹ ፡ ይመለስለታል ፡ ስለሚል ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይህ ፡ ድንጋጌ ፡ ተፈጻሚ ፡ የሚሆነው ፡ ተቀባይነት ፡ በማጣት ፡ ለተሠረዘ ፡ ክስ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ አስተያየት ፡ ወስዷል ።

ለፍርድ ፡ ቤት ፡ የቀረበ ፡ ክስ ፡ የሚሠረዘው ፡ ተቀባይነትን ፡ በማጣት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ከሳሹም ፡ ክሱን ፡ በማንሳቱም ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። እንግዲህ ፡ ሕጉ ፡ ተቀባ ይነትን ፡ በማጣት ፡ ክሱ ፡ ሲሠረዝ ፡ የዳኝነቱ ፡ ገንዘብ ፡ ለከሳሹ ፡ ይመለስለታል ፡ ሲል ፡ ከሳሹ ፡ ክሱን ፡ በማንሳቱ ፡ ምክንያት ፡ ክሱ ፡ ሲሰረዝ ፡ ግን ፡ አይመለስለትም ፡ ለማለት ፡ እንዴት ፡ ይችላል ? እዚህ ፡ ላይ ፡ ዳኝነት ፡ የሚከፈልበትን ፡ ዓላማ ፡ ማብ ራራት ፡ የሚያስፈልግ ፡ መስሎ ፡ ታይቶናል ፤ በመሠረቱ ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ዳኝነት ፡ የሚከፍለው ፡ ከፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለሚያገኘው ፡ አገልግሎት ፡ ነው ፤ ይኸውም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከሳሽንና ፡ ተከሳሽን ፡ አቃርቦና ፡ አከራክሮ ፡ የሁለቱን ፡ ሕጋዊ ፡ መብት ፡ በማረ ጋገጥ ፡ የሚሰጠው ፡ አገልግሎት ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ተከሳሹ ፡ ቀርቦ ፡ ክርክር ፡ ከመ ደረጉ ፡ በፊት ፡ ክሱን ፡ ካነሳ ፡ ከሳሽ ፡ ከፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ያገኘው ፡ አገልግሎት ፡ የለም ፡ ማለት ፡ ነው ። እንግዲህ ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ ከፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሊያገኝ ፡ የነበረውን ፡ አገልግሎት ፡ ክሱን ፡ በማንሳቱ ፡ ካላገኘና ፡ ፍርድ ፡ ቤቱንም ፡ ካላደከመ ፡ ሙሉ ፡ ዳኝ ነት ፡ የሚከፍልበት ፡ ምክንያት ፡ የለም ፤ ሕጉም ፡ ከሳሹ ፡ ክሱን ፡ ካነሳ ፡ መዝገብ ፡ በማስከፈቱና ፡ የፍርድ ፡ ቤቱንም ፡ ጊዜ ፡ በመጠኑ ፡ በመውሰዱ ፡ ለዚህ ፡ አገልግሎት ፡ የሚገባው ፡ ተቀንሶ ፡ ቀሪው ፡ ይመለስለት ፡ የሚለው ፡ ስለዚህ ፡ ነው ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደገለጽነው ፡ ተከሳሹ ፡ ከመቅረቡ ፡ በፊት ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፡ ክሱን ፡ በማንሳቱ ፡ ለዳኝነት ፡ የከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ የሚመለስለት ፡ መሆኑን ፡ ስለዳ ኝነት ፡ የወጣው ፡ ቁጥር ፡ ፲፫ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ በአንቀጽ ፡ ፲፩ ፡ ላይ ፡ ግልጥ ፡ አድ

ርጐ ፡ ስለሚናገር ፡ ይኸውም ፡ ድንጋጌ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በቁ ጥር ፡ ፱፻፴፪ ፡ ንዑስ ፡ ቁጥር ፡ ፩ ፡ (ለ) ከደነገገው ፡ ጋር ፡ ተስማሚ ፡ ስለሆነ ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ከፍሎት ፡ ከነበረው ፡ የዳኝነት ፡ ገንዘብ ፡ ላይ ፡ ደንቡ ፡ የሚያዝዘው ፡ ተቀንሶ ፡ ቀሪው ፡ እንዲመለስለት ፡ አዝዘናል ።

ግንቦት ፡ ፲፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፳፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡

SUPREME IMPERIAL COURT

Addis Ababa, Div. No. 1

Justices:

Afenegus Teshome Haile Mariam
Ato Tadesse Tekle Giorghis
Kegnazmatch Mulat Beyene

TIRUNESH YIGLETU v. KIDANE DEGEFA

Civil Appeal No. 923-60

Withdrawal from Suit—refund of Court fees, Civ. Pro. Code Arts. 231,232, Legal Notice No. 177 of 1953 Arts. 11, 21.

An appeal against the judgment of the High Court denying the request of appellant to be refunded the Court fees he had paid on the ground that he withdrew from the suit before trial was commenced.

Held: Reversed.

When a party withdraws from a suit, before the other party is summoned, the court fees he had paid shall be refunded after a portion prescribed by law is deducted.

The Appellant, who had withdrawn from suit pending in the High Court before the Defendant was summoned and before trial was commenced, applied to be refunded the Court fees she had paid. The Court denied the application and this appeal is preferred against the said denial.

Cases similar to the subject case do not require presence of the opposite party and so we do not consider that the appearance of Defendant is necessary for determing the instant appeal. It appears from an examination of the memorandum of appeal and the record of the High Court that the Appellant contends that as she had withdrawn from the suit she had instituted before the Defendant was summoned, and since subsequently, the file was closed she should be refunded the court fees pursuant to the Civil Procedure Code, Article 232 and Article 11 of the Court Fees Rules, Legal Notice No. 177 of 1953, Negarit Gazetta year 12 No. 15.

However, the High Court denied the Appellant's application holding that Civil Procedure Code Article 232 applies to statements of claim which have been rejected and not to the case where the Plaintiff withdraws from a suit.

In order to determine whether the decision rendered by the High Court is valid as a matter of law, it is necessary to examine the provision cited by the Appellant.

Article 11 of Legal Notice No. 177 of 1953, published pursuant to authority vested by the Administration of Justice Proclamation, provides that where the Plaintiff withdraws his claim before trial, he will be refunded the court fees paid, after a certain portion thereof is deducted. Article 232 (1) (b) of the Civil Procedure Code provides that where a statement of claim is rejected under Article 231 the plaintiff shall be refunded with the prescribed portion of the court fees paid on filing the statement of claim. These two provisions are supplementary to and not

contradictory with each other, nor may they be interpreted in such manner as would render them contradictory. When the Court Fees Rules are read in conjunction with Article 232 of the Civil Procedure Code it becomes clear that where the Plaintiff withdraws his suit before the case goes to trial and where the file is closed as a consequence thereof, the Plaintiff shall be refunded the prescribed portion of the Court Fees. The High Court erred in its interpretation of the term 'rejected' The Civil Proceduce Code in Article 231 lays down the conditions for rejection and in Article 232 the effect thereof. Article 232 (1) (b) states that if a claim is rejected, the Plaintiff shall be refunded the prescribed portion of the court fees and the High Court was of the opinion that this provision is applicable only in the case where statements of claim have been dismissed by reason of rejection of the claim.

A suit is dismissed not only when it is rejected but also when the Plaintiff withdraws from the suit. Since the law provides that the Plaintiff should be refunded with the prescribed portion of the Court fees, where a suit is dismissed because the statement of claim is rejected, it is not proper to hold that the Plaintiff shall not be refunded the court fees when the suit is dismissed as a result of his withdrawal from the suit. We deem it necessary at this point to expound on the rationale for requiring the payment of court fees. The fundamental principle is that a person pays court fees in consideration of the services which the court renders to him. The constitutive elements of the said service are the summoning of the parties to appear in court, the hearing of the arguments tendered by both parties and finally the adjudication of the rights of the parties. However, the Court would not render such services where the Plaintiff withdraws his claim before the Defendant appears and the case proceeds to trial. Therefore, if by reason of his withdrawal the Plaintiff does not obtain the services he is otherwise entitled to by law and if he does not make a demand upon the Court's time there is no reason why he should be required to pay the court fees in full. That is why the law provides that where the Plaintiff withdraws his claim he should be refunded the court fees he had paid after a certain portion thereof is deducted in consideration of the filing of the suit and the use of some of the Court's time.

Whereas, as we have already observed, the Plaintiff had withdrawn her suit before the Defendant was summoned, and whereas Article 11 of the Court Fees Rules provides that the plaintiff shall in such cases be refunded the court fees and whereas this provision is consistent with article 232 (1) (b) of the Civil Procedure Code, we hereby direct that the Plaintiff be refunded the court fees she had paid after the prescribed portion thereof is deducted pursuant to the Court Fees Rules.

June 20, 1969

ጠቅላይ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤

አዲስ ፡ አበባ ፤ ፩ኛ ፡ ችሎት ።

ዳኞች ፤

አፈንጉሥ ፡ ተሾመ ፡ ኃይሌ ፡ ማርያም ፤

አቶ ታደሰ ተክለ ጊዮርጊስ ፤

ቀኛ/ ሙላት በየነ ።

ይግባኝ ባይ ፤ አቶ ፡ ሰብስቤ ፡ ዑስማን ፤

መልስ ፡ ሰጭ ፤ አክበሪሊ ፡ ካሞሩዲናንና ፡ ኩባንያው ።

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቁጥር ፡ ፳፻፴፯/፶፱ ።

የንግድ ሕግ ፤ የተስፋ ሠነድ ፤ የተስፋ ሠነድ ስለማስተላለፍ ፤ የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥሮች ሺ፫፻፺፯ ፤ ሺ፫፻፩ ፤ የንግድ ሕግ ቁጥሮች ፪፻፴፩ ፤ ፫፻፷፫ ፤ ፫፻፷፯/፪/

ይግባኝ ባዩ ያለበትን ዕዳ የተስፋ ሠነድ ለተላለፈለት ሶስተኛ ሰው መክፈል አለበት ሲል የከፍተኛው ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ ላይ የቀረበ ይግባኝ ።

ውሳኔ፡—የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሳኔ ጸንቷል ።

፩. የተስፋ ሠነድን በማስተላለፍ ዕዳን መክፈል ይቻላል ።

፪. የሠነዶቹን ትክክለኛነት በመቃወም ካልሆነ በስተቀር የሠነዶችን መተላለፍ ለማስቀረት አይቻልም ።

፫. ቀኑ በኋላ የተሞላበት ወይም ያልተሞላበት የተስፋ ሠነድ እንኳን ቢሆን ሠነዱ በመጥፎ ልቦና የተገኘ ካልሆነ የቀኑ በኋላ መሞላት መቃወሚያ ሊሆን አይችልም ።

፬. በቅን ልቦና የተስፋ ሠነድ በያዘ ሰው ላይ የማያውቀውን ገደብ መቃወሚያ አድርጎ ማቅረብ አይቻልም።

ይግባኝ ፡ ባዩና ፡ መልስ ፡ ሰጭ ፡ በተሰማው ፡ ፍርድ ፡ ይሰጠን ፡ አሉ ፤ እኛም ሁለቱም ፡ ወገን ፡ በከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የተከራከሩበትን ፡ መዝገብ ፡ መርም ረን ፡ እንዲሁም ፡ በየበኩላቸው ፡ በቃል ፡ ያመለከቱትንና ፡ በጽሑፍም ፡ ያቀረቡትን ፡ የፍሬ ፡ ነገርና ፡ የሕግ ፡ ክርክር ፡ አመዛዝነን ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ፍርድ ፡ ሰጥ ተናል ።

ፍርድ

በዚህ ፡ ነገር ፡ መልስ ፡ ሰጭ ፡ የሥር ፡ ከሳሹ ፡ ሲሆን ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፡ የሥር ፡ ተከ ሳሽ ፡ ነው ። ከሳሽ ፡ የአሁን ፡ መልስ ፡ ሰጭ ፡ በተከሳሹ ፡ ባሁን ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፡ ላይ ፡ ክስ ፡ ያቀረበው ፡ ተከሳሹ ፡ የአሁኑ ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፡ የመክፈያ ፡ ጊዜያቸውን ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ ፡ መጋቢት ፡ ፳፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እና ፡ ሚያዝያ ፡ ፲፰ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አድርጎ ፤ እ ፤ ኤ ፡ አ ፡ የካቲት ፡ ፲፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሁለት ፡ የተ ሰሩ ፡ ሰነዶች ፡ ፈርሞ ፡ ስለነበር ፤ ክፈለኝ ፡ ብለው ፡ አልከፍልም ፡ ስላለኝ ፡ በፈረመው፡ መሠረት ፡ አርባ ፡ ሺህ ፡ ብር ፡ ከነወለዱ ፡ ሊከፍለኝ ፡ ይገባዋል ፡ በማለት ፡ ሲሆን ፡

ክስ ፡ የቀረበባቸውን ፡ ሰነዶች ፡ ፎቶ ፡ ኮፒና ፡ ራቲላል ፡ የተባለው ፡ ነጋዴ ፡ ጽፎለት ፡ የነበረውን ፡ ደብዳቤ ፡ ፎቶ ፡ ኮፒ ፡ በማስረጃነት ፡ አቅርቧል ። ተከሳሹ ፤ የአሁኑ ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፤ የክሱ ፡ ማመልከቻና ፡ ከሳሹም ፤ የአሁኑ ፡ መልስ ፡ ሰጭ ፤ ያቀረባቸው ፡ ማስረጃዎች ፡ ከደረሱት ፡ በኋላ ፡ ለክሱ ፡ በሰጠው ፡ መልስ ፡ ፩ኛ/ የተሰፋ ፡ ሰነዶች ፡ ቀን የሌለባቸው ፡ ስለሆኑ ፡ ፪ኛ/ በከሳሹና ፡ በተከሳሹ ፡ መካከል ፡ የንግድ ፡ ግንኙነት ፡ የሌለ ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ ከሳሹ ፡ ክስ ፡ ላቀረበባቸው ፡ የተሰፋ ፡ ሰነዶች ፡ አንዳችም ፡ የንግድ ፡ ዕቃ ፡ ለተከሳሹ ፡ ባለመስጠቱ ፤ ፫ኛ/ ራቲላል ፡ ሻንማሌ ፡ ለራሱና ፡ ለከሳሹ ፤ የማይገባ ፡ ብልጽግና ፡ ለማግኘት ፡ በማለት ፡ በያንዳንዱ ፡ ተሰፋ ፡ ሰነድ ፡ ላይ ፡ የተመለከተውን ፡ ገንዘብ ፡ ፪ሺ ፡ ብር ፡ የሚለውን ፡ አንድ ፡ ዜሮ ፡ በመጨመር ፡ ፳ሺ ፡ ብር ፡ በማድረጉ ፡ የተሰፋ ፡ ሰነዶቹ ፡ ዋጋ ፡ የላቸውም ፡ በማለት ፡ ተከራክሯል ። የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በከሳሹ ፤ ባሁኑ ፡ መልስ ፡ ሰጭና ፤ በተከሳሹ ፤ ባሁኑ ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፤ በኩል ፡ የቀረቡትን ፡ ማስረጃዎች ፡ ከተቀበለና ፡ በሕግም ፡ በኩል ፡ ያሰሙትን ፡ ክርክር ፡ ካመዛዘነ ፡ በኋላ ፤ ተከሳሹ ፡ ክስ ፡ የቀረበበትን ፡ ገንዘብ ፡ ከነወለዱ ፡ እንዲሁም ፡ አንድ ፡ ሺህ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ የዳኝነትና ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ኪሣራ ፡ ለከሳሽ ፡ እንዲከፍል ፡ ፈርዶበታል ።

ተከሳሹም ፡ በዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቅር ፡ ተሰኝቶ ፡ ይህን ፡ የይግባኝ ፡ መዝገብ ፡ ስለከፈተ ፡ መልስ ፡ ሰጭው ፡ እንዲቀርብ ፡ ተደርጐ ፡ ሁለቱም ፡ ወገን ፡ በፍሬ ፡ ነገሩና ፡ በሕጉም ፡ ስላለው ፡ አስተያየት ፡ ሰፊ ፡ ክርክር ፡ አሰምተዋል ።

በመጀመሪያ ፡ በይግባኝ ፡ ባዩ ፡ በኩል ፡ የቀረበውን ፡ ክርክር ፡ እንመረምራለን ። ይግባኝ ፡ ባይ ፡ ክስ ፡ የቀረበባቸውን ፡ የተሰፋ ፡ ሰነዶች ፡ መፈረሙን ፡ አልካደም ፤ ነገር ግን ፡ በነዚህ ፡ የተሰፋ ፡ ሰነዶች ፡ አልጠየቅም ፡ በማለት ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከቱትን ፡ ዐቢይ ፡ ክርክሮች ፡ አቅርቧል ፤ ይኸውም ፤ ፩ኛ/ መልስ ፡ ሰጭው ፡ ራቲላል ፡ ሻንማሌ ፡ የጻፈው ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ያቀረበው ፡ የመገዳደሪያ ፡ ሰነድ ፡ "በአውሮፕላን ፡ የሞት ፡ አደጋ ፡ የደረሰበት ፡ እንደሆነ" ፡ የሚል ፡ ገደብ ፡ ስላለበት ፡ ይህ ፡ ገደብ፡ ሳይፈጸም ፡ መልስ ፡ ሰጭው ፡ ክስ ፡ ያቀረበው ፡ በማይገባ ፡ ነው ፤ ፪ኛ/ ፡ በተሰፋ ፡ ሰነዶቹ ፡ ላይ ፡ የተጻፈበት ፡ ቀን ፡ አልተመለከተም ፤ ፫ኛ/ በይግባኝ ፡ ባዩና ፡ በመልስ ፡ ሰጭው ፡ መካከል ፡ አንዳችም ፡ የንግድ ፡ ግንኙነት ፡ ስለሌለና ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ከመልስ፡ ሰጭው ፡ የገዛው ፡ የንግድ ፡ ዕቃ ፡ ባለመኖሩ ፡ መልስ ፡ ሰጭ ፡ በነዚህ ፡ የተሰፋ ፡ ሰነዶች ፡ ሊጠቀም ፡ አይችልም ፤ ፬ኛ/ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ የተባሉትን ፡ የተሰፋ ፡ ሰነዶች ፡ ለራቲላል ፡ ሻንማሌ ፡ የፈረመ ፡ መሆኑ ፡ ቢረጋገጥም ፡ ራቲላል ፡ ሻንማሌ ፡ ለራሱና ፡ ለመልስ ፡ ሰጭው ፡ የማይገባ ፡ ጥቅም ፡ ለማግኘትና ፡ ለማስገኘት ፡ በያንዳንዱ ፡ የተሰፋ ፡ ሰነድ ፡ ላይ ፡ የተመለከተውን ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፡ በማጭበርበር ፡ ሁለት ፡ ሺህ ፡ የሚለውን ፡ ዜሮ ፡ በመጨመር ፡ ሃያ ፡ ሺህ ፡ ስላደረገው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፩ሺ፯፻፺፯ ፡ እና ፡ ፩ሺ፯፻፱ ፡ ንዑስ ፡ ቁጥር ፡ ፩ ፡ በሚያዝዘው ፡ መሠረት ፡ ተሰፋ ፡ ሰነዶቹ ፡ ውድቅና ፡ ፍርስ ፡ መሆን ፡ ይገባቸዋል ፡ የሚል ፡ ክርክር ፡ ነው ።

መልስ ፡ ሰጭ ፡ ክስ ፡ የቀረበባቸውን ፡ የተሰፋ ፡ ሰነዶች ፡ ያገኘው ፡ ከራቲላል ፡ ሻንማሌ ፡ ነው ፤ ራቲላል ፡ ሻንማሌ ፡ የተባለው ፡ ነጋዴ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ለቆ ፡ ከመሄዱ ፡ በፊት ፡ እነዚህን ፡ የተሰፋ ፡ ሰነዶች ፡ ከደብዳቤ ፡ ጋር ፡ ለመልስ ፡ ሰጭው ፡ ልኳል ፤ በጻፈው ፡ ደብዳቤ ፡ ወደጅቡቲ ፡ ብቻዬን ፡ የምሔድ ፡ ስለሆነ ፡ ማናቸውም ፡ አደጋ ፡ ቢደርስብኝ ፡ እነዚህን ፡ የተሰፋ ፡ ሰነዶች ፡ ላለብኝ ፡ ዕዳ ፡ ትቼልዎታለሁ ፡ ብሏል ።

ራቲላል ፡ ሻንማሌ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሳይመለስ ፡ በዚያው ፡ ቀርቷል ፤ ይግባኝ ፡ ባዩም ፡ የሚከራከረው ፡ ራቲላል ፡ ሻንማሌ ፡ የጻፈው ፡ ደብዳቤ ፡ የሞት ፡ አደጋ ፡ የደረሰብኝ ፡ እንደሆነ ፡ ስለሚል ፡ በአደጋ ፡ መሞቱ ፡ ሳይረጋገጥ ፡ መልስ ፡ ሰጭው ፡ በነ

ዚህ ፡ ተስፋ ፡ ሰነዶች ፡ ሊጠቀም ፡ አይችልም ፡ በማለት ፡ ነው ። ይህን ፡ ክርክር ፡ ግን ፡
ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አልተቀበለውም ። ራቲላል ፡ ሻንማሌ ፡ የመልስ ፡ ሰጭው ፡ ዕዳ ፡ ያለ
በት ፡ መሆኑን ፡ አምኖ ፡ ለዚሁም ፡ ዕዳው ፡ መክፈያ ፡ የሚሆን ፡ ሁለት ፡ የተስፋ ፡ ሰነ
ዶች ፡ ለመልስ ፡ ሰጭው ፡ ሰጥቶ ፡ ከሔደ ፤ እነዚህም ፡ የተስፋ ፡ ሰነዶች ፡ እንደ ፡ ገንዘብ ፡
ስለሚቆጠሩ ፡ መልስ ፡ ሰጭው ፡ በራቲላል ፡ ሻንማሌ ፡ ላይ ፡ የነበረውን ፡ ዕዳ ፡ እንደ
ተከፈለ ፡ ያስቆጥረዋል ። እንግዲህ ፡ መልስ ፡ ሰጭው ፡ የተስፋ ፡ ሰነዶች ፡ አውጭ ፡
የሆነውን ፡ ይግባኝ ፡ ባዩን ፡ ክፈለኝ ፡ ብሎ ፡ ሲጠይቀው ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ባይሆን ፡ የተ
ስፋ ፡ ሰነዶች ፡ ሕጋዊ ፡ አይደሉም ፡ ብሎ ፡ ይከራከር ፡ እንደሆነ ፡ እንጂ ፡ ራቲላል ፡
ሻንማሌ ፡ አደጋ ፡ ካልደረሰበት ፡ አልጠየቅም ፡ የማለት ፡ ክርክር ፡ ማቅረብ ፡ አይችልም ።
በርትዕም ፡ ሆነ ፡ በሕግ ፡ ረገድ ፡ መልስ ፡ ሰጭው፡ በራቲላል ፡ ሻንማሌ ፡ ላይ ፡ የነበረውን፡
ዕዳ ፡ ባለዕዳው ፡ እስኪሞት ፡ ድረስ ፡ ሳይቀበል ፡ ይቆይ ፡ ማለት ፡ የሚቻል ፡ መስሎ ፡
አልታየንም ። በተስፋ ፡ ሰነዶቹ ፡ ላይ ፡ የተጻፉበት ፡ ቀን ፡ አልተመለከተም ፡ በማለት ፡
ስላቀረበውም ፡ ክርክር ፤ የተስፋ ፡ ሰነዶቹን ፡ ኦሪጅናል ፡ አስቀርበን ፡ በመመልከት ፡
ቀን ፡ የተጻፈባቸው ፡ መሆኑን ፡ አረጋግጠናል ። ቀኑ ፡ በኋላ ፡ የተሞላ ፡ ነው ፡ ለሚለ
ውም ፡ ቢሆን ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ በቁጥር ፡ ፰፻፳፭ ፡ ንዑስ ፡ ቁጥር ፡ ፪ ፡ እና ፡ በቁጥር ፡
፯፻፴፬ ፡ ላይ ፡ እንደሚደነግገው ፡ መልስ ፡ ሰጭው ፡ የተባሉትን ፡ ሰነዶች ፡ በመጥፎ ፡
ልቡና ፡ ወይም ፡ በተንኰል ፡ አግኝቷል ፡ ካልተባለ ፡ በቀር ፡ የቀኑ ፡ በኋላ ፡ መሞላት ፡
በመልስ ፡ ሰጭው ፡ ላይ ፡ መቃወሚያ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ።

ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ከመልስ ፡ ሰጭው ፡ ጋር ፡ የንግድ ፡ ግንኙነት ፡ ስለሌለውና ፡ ከመ
ልስ ፡ ሰጭውም ፡ የተቀበለው ፡ የንግድ ፡ ዕቃ ፡ ስለሌለ ፡ በተስፋ ፡ ሰነዶች ፡ ሊጠየቅ ፡
አይገባም ፡ በማለት ፡ ስላቀረበው ፡ ክርክር ፡ የንግዱን ፡ ሕግ ፡ እንመረምራለን ። የን
ግድ ፡ ሕግ ፡ በቁጥር ፡ ፰፻፳፫ ፡ ላይ ፡ ስለተስፋ ፡ ሰነድ ፡ አሠራር ፡ ይደነግጋል ፤ ይኸውም
ማናቸውም ፡ የተስፋ ፡ ሰነድ ፡ የተወሰነ ፡ ገንዘብ ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡
በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ ለእገሌ ፡ ወይም ፡ ላምጭው ፡ ይከፈላል ፡ በማለት ፡ ተዘጋጅቶ በተስፋ
ሰነድ ፡ ሰጭው ፡ ከተፈረመ ፡ በሕግ ፡ ፊት ፡ ዋጋ ፡ ያለውና ፡ አስገዳጅ ፡ ነው ። የዚህ ፡
ዓይነቱን ፡ የተስፋ ፡ ሰነድ ፡ አውጪ ፡ የሆነ ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ፊርማው ፡ የራሱ ፡
መሆኑን ፡ ካመነ ፡ ሌላ ፡ ክርክር ፡ ሊያቀርብ ፡ አይችልም ።

ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ በተስፋ ፡ ሰነዶች ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ፊርማ ፡ የራሱ ፡ መሆኑን ፡ አም
ኗል ፤ አልከፍልም ፡ በማለት ፡ የሚከራከረው ፡ ከመልስ ፡ ሰጭው ፡ ጋር ፡ የንግድ ፡ ግን
ኙነት ፡ የለኝም ፡ በማለትና ፡ ራቲላል ፡ ሻንማሌም ፡ ለነዚህ ፡ የተስፋ ፡ ሰነዶች ፡ መሸ
ፈኛ ፡ የሚሆን ፡ የንግድ ፡ ዕቃ ፡ ሊያቀርብልኝ ፡ ስምምነት ፡ ነበረኝ ፡ በማለት ፡ ነው ።
ነገር ፡ ግን ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ በቁጥር ፡ ፰፻፳፫ ፡ ላይ ፡ እንደሚደነግገው ፡ ማናቸውም
የተስፋ ፡ ሰነድ ፡ ገደብና ፡ ውለታ ፡ ሊኖርበት ፡ ስለማይችልና ፡ በነዚህም ፡ የተስፋ ፡
ሰነዶች ፡ አንዳችም ፡ ገደብ ፡ የሌለ ፡ በመሆኑ ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ የንግድ ፡ ግንኙነት ፡ የለ
ኝም ፤ ከመልስ ፡ ሰጭውም ፡ የተቀበልኩት ፡ ነገር ፡ የለም ፡ የሚል ፡ ክርክር ፡ ሊያቀርብ ፡
አይችልም ።

የተስፋ ፡ ሰነድ ፡ እንደጥሬ ፡ ገንዘብ ፡ የሚቆጠር ፡ ነው ፤ እንደጥሬ ፡ ገንዘብ ፡
ከመቆጠሩም ፡ የተነሳ ፡ ካንዱ ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ ወደሌላው ፡ ሰው ፡ ሊተላለፍ ፡ ይችላል ፤
በተስፋ ፡ ሰነድ ፡ ላይ ፡ ማናቸውም ፡ ገደብ ፡ አይኑር ፡ የሚባለውም ፡ ስለዚህ ፡ ነው ።
እንግዴህ ፡ እንደጥሬ ፡ ገንዘብ ፡ ተቆጥሮ ፡ የሚሠራበትን ፡ ሰነድ፡ በያዘው ፡ ሰው ፡ ላይ
የማያውቀውን ፡ ገደብ ፡ መቃወሚያ ፡ አድርጎ ፡ ማቅረብ ፡ አይቻልም ፤ ቢሆንም ፡ የተ
ስፋ ፡ ሰነድ ፡ አውጭ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ የተስፋ ፡ ሰነዱን ፡ ሲሰጥ ፡ ከአምጭው ፡ ጋር
የገባው ፡ የጽሑፍ ፡ ስምምነት ፡ ያለ ፡ እንደሆነ ፡ ይህንኑ ፡ በአምጭው ፡ ላይ ፡ መቃወ

ሚያ ፡ አድርጐ ፡ ሊያቀርብ ፡ ይችላል ፤ በቅን ፡ ልቡና ፡ ባገኘው ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ላይ ግን ፡ ሊያቀርብ ፡ አይችልም ፤ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ እንደሚለው ፡ ራቲላል ፡ ሻንማሌ ፡ የንግድ ፡ ዕቃ ፡ ሊያቀርብለት ፡ በጽሑፍ ፡ የገባው ፡ ግዴታ ፡ ቢኖር ፡ ኖሮ ፡ በተቀበልነው ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ የሰው ፡ ምስክር ፡ ላቅርብ ፡ ከማለት ፡ በቀር ፡ የጽሑፍ ፡ ስምምነት ፡ ያለው ፡ መሆኑን ፡ ሊያስረዳ ፡ አልቻለም ፤ በሰው ፡ ምስክር ፡ ላስረዳ ፡ የሚለው ፡ በጽሑፍ ፡ ያለውን ፡ በሰው ፡ ማስረጃነት ፡ ማፍረስ ፡ ስለማይችል ፡ አልተቀበልነውም ። ራቲላል ፡ ሻንማሌ ፡ ለተቀበላቸው ፡ የተስፋ ፡ ሰነዶች ፡ መሸፈኛ ፡ የሚሆን ፡ የንግድ ፡ ዕቃ ፡ ለይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ሊያቀርብ ፡ የገባው ፡ ግዴታ ፡ አለ ፡ ቢባልም ፡ ኖሮ ፡ የዚህ ፡ ግዴታ ፡ መኖር ፡ በመልስ ፡ ሰጭው ፡ ላይ ፡ መቃወሚያ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ፡ ነበር ። ምክንያቱም ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ የመልስ ፡ ሰጭው ፡ ስም ፡ በተስፋ ፡ ሰነዱ ላይ ፡ በመጻፉ ፡ እንደመጀመሪያው ፡ አምጭ ፡ የሚቆጠር ፡ ቢሆንም ፡ መልስ ፡ ሰጭው የተባሉትን ፡ የተስፋ ፡ ሰነዶች ፡ ያገኘው ፡ ካራቲላል ፡ ሻንማሌ ፡ ላይ ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ በመሆኑ ፡ እንደሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ስለሚቆጠር ፤ በራቲላል ፡ ሻንማሌና ፡ በይግባኝ ፡ ባዩ ፡ መካከል ፡ የነበረ ፡ ስምምነት ፡ በመልስ ፡ ሰጭው ፡ ላይ ፡ መቃወሚያ ፡ ሊሆን ፡ ስለማይችል ፡ ነው ።

በተስፋ ፡ ሰነዶች ፡ ላይ ፡ የተጻፈው ፡ ገንዘብ ፡ በሐሰት ፡ ተለውጧል ፡ ስለተባለውም ፤ ሃያ ፡ ሺህ ፡ ብር ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ በአሐዝና ፡ በፊደል ፡ የተመለከተ ፡ በመሆኑ ፡ በሁለቱ ፡ መካከል ፡ ልዩነት ፡ ስላልተገኘ ፡ የማጭበርበር ፡ ተግባር ፡ ተፈጽሟል ፡ ለማለት ፡ አልተቻለም ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደገለጽነው ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ እነዚህን ፡ የተስፋ ፡ ሰነዶች ፡ ፈርሞ ፡ ለራቲላል ፡ ሻንማሌ ፡ በመስጠቱ ፡ ራቲላል ፡ ሻንማሌ ፡ ስላለበት ፡ ዕዳ ፡ ለመልስ ፡ ሰጭው ፡ ሰጥቷቸዋል ፤ መልስ ፡ ሰጭውም ፡ እነዚህን ፡ የተስፋ ፡ ሰነዶች ፡ ያገኘው ፡ በመጥፎ ፡ ልቡና ፡ ወይም ፡ ከሕግ ፡ ጋር ፡ ተቃራኒ ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ መሆኑን ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ አላስረዳም ፤ ስለዚህ ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ላይ ፡ የወሰነውን ፡ አጽንተን ፡ ይግባኙን ፡ አሰናብተናል ።

ግንቦት ፡ ፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷ ፡ ዓ ፡ ም ፡

SUPREME IMPERIAL COURT

Addis Ababa, Div. No. 1

Justices:

Afenegus Teshome Haile Mariam

Ato Tadesse Tekle Giorghis

Kegnazmatch Mulat Beyene

SUBSIBE OSMAN v. AKBERILE CAMORUDANE & Co.

Civil Appeal No. 537-59

Commercial Law—Promissory Notes—Transfer of Promissory Notes—
Comm. Code Arts. 744, 823 825(2): *Civ. Code Arts.* 1696, 1704.

On appeal from the decision of the High Court holding that the Defendant pay debts he owed to the plaintiff who possessed promissory notes validly transferred to him.

Held: Decision affirmed.

1. As promissory notes are deemed to be equivalent to cash, one can transfer them to a creditor to pay off debts, and may be challenged only by showing the invalidity of the notes.

2. Even an undated promissory note may be valid unless it is proved that it was acquired fraudulently or in bad faith.

3. Unless other wise provided in writing, a promissory note may not be burdened with any kind of condition to be used against the interest of a bearer in good faith.

JUDGMENT

In the Case at bar the Respondent is the original Plaintiff and the Appellant is the original Defendant. Plaintiff, the present Respondent, instituted suit against the Defendant on two promissory notes drawn by the same on February 12, 1966 and maturing on March 22, 1966 and April 15, 1966 respectively. The Plaintiff claimed relief in the sum of E $ 40,000 together with interest thereon. He has offered in evidence photocopies of the documents, the subject matter of the dispute and photocopy of the letter addressed to him from a trader, one Rattelal Shanemel. Defendant, after receiving a copy of the statement of claim submitted and the documents introduced by the Plaintiff replied that:

1. The promissory notes do not bear the date of the making thereof.

2. No business relations existed between him and the Defendant.

3. Rattelal Shanmel, with a view to procure unjust enrichment for the Plaintiff and for himself, added one zero to the E $ 2,000 appearing in each promissory note, thereby making it E $ 20,000. The Defendant argued that the two promissory notes are, therefore, of no effect.

After admitting the evidence submitted by both parties and after considering the legal arguments tendered by the parties, the High Court held that Defendant

shall pay Plaintiff the amount claimed together with interest and Court fees in the sum of E $ 1,500 and E $ 500 costs.

The Defendant, aggrieved by the judgment, lodged this appeal. The Respondent was summoned to appear and both parties submitted in detail their argument with regards to both facts and the law.

We shall primarily consider the Appellant's contentions. The Appellant did not deny that he had endorsed the promissory notes but has raised the following contentions in support of his position that he is not liable theron. He argues that:

1. Since the document produced by the Respondent allegedly written by Rattelal Shanmel contains the conditional clause, "in the event that he (Rattelal Shanemel) dies from an airplane accident," Respondent may not maintain an action unless said condition is fulfilled.

2. The promissory notes do not bear the date of issue.

3. There were no business relations between the Appellant and the Respondent; the Appellant has purchased no merchandise from the Respondent; and that the Respondent may not therefore benefit himself by the promissory notes.

4. Even if it had been established that the Appellant had issued the promissory notes in Rattelal Shanmel's name, Shanmel, with a view to obtaining unjust enrichment for the Respondent and for himself, had fraudulently added one zero on the E $ 2,000 indicated in the notes, thereby making it E $ 20,000 and that the notes are therefore, null and void by virtue of Articles 1696 and 1704 (1) of the Civil Code.

The Respondent acquired the promissory notes from Rattelal Shanmel who, before he left Ethiopia, dispatched these notes together with a letter to the Respondent. Shanmel wrote, "I am leaving for Djibouti alone, and should anything happen to me, I leave these promissory notes in satisfaction of my debts"

Shanmel did not return to Ethiopia. The Appellant argued that the letter Shanmel wrote reads, "should I meet with an accident resulting in my death" and therefore the Respondent may not make use of the promissory notes unless it is established that Shanmel died as a result of an accident. But the Court overruled this contention. Since Rattelal Shanmel did not deny that he was indebted towards the Respondent and since he departed from Ethiopia after transferring to him (the Respondent) the promissory notes in satisfaction of his debt, the debt is considered to have been paid, for the promissory notes are deemed to be equivalent to cash. Therefore when the Respondent requires the Appellant, the drawer of the notes, to pay, the Appellant may argue that the promissory notes are not valid, but he may not refuse payment on the ground that Shanemel had not met with an accident. We do not, as a matter of law or equity, think that it is fair to order the Respondent to wait until after Shanmel's death in order to recover the debts owed to him.

With respect to the argument that no date was indicated on the promissory notes, we ordered the production of the originals and we have ascertained that the original documents contain dates. Furthermore, the Appellant may not avail himself of this argument unless he can establish in accordance with Articles 825 (2) and 744 of the Commercial Code that the Respondent acquired the instrument fraudulently or in bad faith.

We shall examine the Commercial Code with regard to the argument that as there were no business relations between the Appellant and the Respondent and as the Respondent had not received delivery of commercial goods, he is not liable on the promissory notes. Article 823 of the Commercial Code sets out the condition required in the making of a promissory note. Where a promissory note contains a promise to pay a sum certain in money at sight or on a fixed date to a specified person or to the bearer and where it bears the drawer's signature, such promissory notes shall be valid and binding. The drawer may not set up any defence other than disclaiming the signature appearing thereon.

The Appellant has admitted that the signature appearing on the promissory note is his. He submits that he shall not effect payment on the ground that no business relations existed between him and the Respondent and that Rattelal Shanmel had agreed to deliver to him commercial goods in consideration of these promissory notes. However, according to Article 823 of the Commercial Code a promissory note cannot contain a condition and as these promissory notes contain no such condition, the Appellant may not set up the defence that he had no business relations with the Respondent and that he had not received delivery of anything from the Respondent.

A promissory note is equivalent to cash and it may therefore be transferred from one person to another; that is why the law requires a promissory note not to be subject to any condition. A condition of which he was not aware may not be set up against the holder of the instrument which is equivalent to cash. If at the time of issue, the drawer has entered into a written agreement with the holder then he may set up the agreement against said person; but he may not do so against a third party who has acquired the notes in good faith.

The defence of the Respondent would have been tenable if Shanmel had in writing undertaken an obligation to deliver commercial goods to the Appellant. However the Appellant merely applied to produce witnesses to prove such agreement and did not succeed in establishing the existence of a written agreement. Even if Shanmel had entered into an obligation to deliver commercial goods to the Appellant in consideration of the promissory notes, such obligation may not be set up against the Respondent, because although the fact that the Respondent's name appears on the promissory notes makes him the first bearer, he acquired the notes from Shanmel in good faith. Therefore, the agreement existing between Shanmel and the Appellant may not be set up against the Respondent.

With respect to the argument that the sum appearing on the notes has been fraudulently altered, the sum E$ 20,000 is expressed both in words and figures. Since there is no discrepancy between the two, we could not find fraud.

As we have already observed the Appellant had issued these promissory notes in favour of Rattelal Shanmel and Shanmel had in turn transferred the notes to the Respondent in satisfaction of his debt. The Appellant has not shown that the Respondent acquired these notes in bad faith. Therefore, we hereby afirm the judgment of the High Court and dismiss the appeal.

May 15, 1967

ከ
አበራ ፡ ጀምበሬ ፡*

" ኢትዮጵያ ፡ ተካፋይ ፡ (የ) ምትሆንባቸው (የ) ኢንተርናሲዮናል ፡ ውሎች ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ የበላይ ፡ ሕግ ፡ ይሆናሉ ።"
የተሻሻለው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፳፪ ።

መግቢያ ።

"ውል" ፡ ለሚለው ፡ ለአማርኛው ፡ ቃል ፡ ትርጉም ፡ የሆነው ፡ "ትሪቲ" የሚ ለው ፡ የእንግሊዝኛው ፡ ቃል ፡ የተወሰደው ፡ "የስምምነት ድርድር" የሚል ፡ ትር ጓሜ ፡ ከሚሰጠው ፡ "ትሪቴ ፡" ከሚለው ፡ የፈረንሳዊኛ ፡ ቃል ፡ ሲሆን ፤ የሚያመለክ ተው ፡ "የአስገዳጅነት ፡ ጠባይ ፡" እንዲኖራቸው ፡ ታስበው ፡ የተደረጉትን ፡ የኢንተ ርናሲዮናል ፡ ስምምነቶች ፡ ነው ።[1]

"ውል" ፡ የሚለው ፡ ሥረወ ፡ ቃል ፡ በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ የገባው ፡ "ውል" "ፕሮቶኮል" ፤ "የኢንተርናሲዮናል ፡ ስምምነት" ፤ ጠበብ ፡ ባለ ፡ ትርጓሜም ፡ "ግዴታ"[2] ፡ ለሚባሉት ፡ የስምምነት ፡ ዓይነቶች ፡ አጠቃላይ ፡ መጠሪያ ፡ ሁኖ ፡ ነው ። ይህም ፡ የሆነበት ፡ ምክንያት ፡ እነዚህ ፡ ሰነዶች ፡ ያላቸው ፡ የዓይነት ፡ (የፎርም) ፡ ልዩ ነት ፡ ወደሚያስከትሉት ፡ ሕጋዊ ፡ ውጤት ፡ ስለማይሸጋገርና ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ሕግም ፡ በሀገሮች ፡ መካከል ፡ ወይም ፡ በአንድ ፡ ሀገርና ፡ በኢንተርናሲዮናል ፡ ድርጅ ቶች ፡ መካከል ፡ ምንም ፡ ልዩነት ፡ ሳያደርግ ፡ ሁሉንም ፡ ስለሚያጸና ፡ ነው ።

አፕንሃይም ፡ "ውሎች ፡ ተዋዋዮቹ ፡ ወገኖች ፡ እንደ ፡ ሕግ ፡ አድርገው ፡ ሊያከብ ሩዋቸው ፡ የሚገቡትን ፡ ሥርዓቶች ፡ ስለሚወስኑ ፡ በመሠረቱ ፡ ውሎች ፡ ሁሉ ፡ ሕግ ፡ መሥራቾች ፡ ናቸው ፡"[3] እንዳሉት ፡ ሁሉ ፤ ሕግ ፡ መሥራቾች ፡ ተብለው ፡ በታወቁ ትና ፡ በሌሎች ፡ ውሎች ፡ መካከል ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ልዩነት ፡ ባለመኖሩ ፤ ሁለቱም ፡ ዓይነት ፡ ስምምነቶች ፡ "ውል" ፡ በሚለው ፡ ስያሜ ፡ ተጠቃለው ፡ በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ገብተው ፡ ይገኛሉ ።

---

* ቢ.ኤ ፤ ኤል.ኤል.ቢ ። ይህ ፡ (የምርምር) ፡ ድርሰት ፡ "የውል ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ የበላይ ፡ ሕግነት ፡" በሚል ፡ አርእስት ፡ መጀመሪያ ፡ ተዘጋጅቶ ፡ በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ለሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ በ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ለኤል ፡ ኤል ፡ ቢ ፡ ዲግሪ ፡ በማሟያነት ፡ ከቀረቡት ፡ ጽሑፎች ፡ አንዱ ፡ ነበር ። አሁን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውል ፡ የመዋዋልን ፡ ሥልጣን ፡ እንዲጨምር ፡ ተደርጎ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ መጽሔት ፡ ውስጥ ፡ ለመታተም ፡ በሚስማማ ፡ አኳኋን ፡ ተሻሽሏል ።

1. አርነስት ፡ ሳተው ፡ ኤ ፡ ጋይድ ፡ ቱ ፡ ዲፕሎማቲክ ፡ ፕራክቲስ ፡ (አራተኛ ፡ እትም ፡ የ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡) ቁጥር ፡ ፳፻፶፫ ፡ ገጽ ፡ ፫፻፳፮ ።
2. ወደፊት ፡ ገጽ ፡ ፫፻፹፯ ፡ ላይ ፡ ይመለከቷል ።
3. ኤል ፡ አፕንሃይም ፡ ኢንተርናሺናል ፡ ሎው ፡ (ቲሪቲስ) ፡ (፰ኛ እትም ፡ ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡) ቮልዩም ፡ ፩ ፡ ቁጥር ፡ ፬፻፺፬ ፡ ገጽ ፡ ፫፻፸፬ ።

በዚህ ፡ የምርምር ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ስለሚከተሉት ፡ ጥያቄዎች ፡ እንመራመራለን ።

፩/ ውል ፡ መዋዋል ፡ የንጉሡ ፡ ነገሥቱ ፡ ብቻ ፡ የሆነ ፡ የተለየ ፡ ሥልጣን ፡ ነውን ?

፪/ ይህንንስ ፡ ሥልጣን ፡ ለሌላ ፡ ባለሥልጣን ፡ በውክልና ፡ ለማስተላለፍ ፡ ይቻላልን ?

፫/ አንድ ፡ ውል ፡ የሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ አናቅጻትም ፡ ሆነ ፤ በሥራ ፡ ላይ ፡ ያሉትን ፡ ሕግጋት ፡ ሊለውጥ ፡ ወይም ፡ ሊያሻሽል ፡ ይችላልን ?

፬/ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ከመውጣቱ ፡ በፊትና ፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ የተደረጉት ፡ ውሎች ፡ በእኩል ፡ ደረጃ ፡ የበላይ ፡ ሕግ ፡ ናቸውን ?

፭/ ውሎችን ፡ ተፈጻሚ ፡ ለማድረግ ፡ በሀገር ፡ ውስጥ ፡ ስለዚሁ ፡ ሕግ ፡ ማውጣት ፡ ያስፈልጋልን ?

፮/ በሀገሪቱ ፡ ሕግና ፡[4] በውሎች ፡ መካከል ፡ የሚኖር ፡ መጻረርን ፡ ለማስታረቅ ፡ የሚቻለው ፡ እንዴት ፡ ነው ?

እነዚህን ፡ ጥያቄዎች ፡ ለመመለስ ፡ የዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ደራሲ ፡ ለጉዳዩ ፡ አግባብ ፡ ያላቸውን ፡ ሁለት ፡ የሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ አናቅጻት ፡ ሊተነትን ፡ ይሞክራል ። እነርሱም ፦

ሀ/ ስምምነት ፡ የመዋዋል ፡ ሥልጣንን ፡ የሚሰጠው ፡ አንቀጽ ፡ ፴ ፡ እና ፡

ለ/ ውሎችን ፡ የብሔራዊ ፡ ሕግ ፡ አካል ፡ የሚያደርገውና ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛትም ፡ የበላይ ፡ ሕግ ፡ ሁነው ፡ ተፈጻሚ ፡ መሆን ፡ እንደሚገባቸው ፡ የሚደነገገው ፡ የበላይ ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ የሆነው ፡ አንቀጽ ፡ ፻፳፪፡

ናቸው ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ የተጻፉ ፡ ብዙ ፡ የምርምር ፡ ጽሑፎች ፡ ባለመኖራቸው ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፤ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥትም ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ከዋለ ፡ ጊዜው ፡ አጭር ፡ በመሆኑ ፡ ያስገኘው ፡ ሕጋዊ ፡ ተለምዶ ፡ ሰፊ ፡ ካለመሆኑ ፡ የተነሳ ፡ ይህ ፡ ምርምር ፡ በግድ ፡ የጠቅላላ ፡ አቀራረብ ፡ ጠባይ ፡ ይኖረዋል ።

በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ስለ ፡ ውሎች ፡ የተሰጠ ፡ የፍርድ ፡ ውሳኔና ፡ የመሳሰሉት ፡ ጽሑፎች ፡ እጠትና ፡ የሕገ ፡ መንግሥት ፡ ረቂቅም ፡ ሆነ ፡ የዝግጅት ፡ ጽሑፍ ፡ ወይም ፡ ስለሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ የተጻፈ ፡ መንግሥታዊ ፡ (ኦፊሴላዊ) ፡ ማብራሪያ ፡ አለመኖር ፤ ከጉዳዩ ፡ አስቸጋሪነት ፡ ጋር ፡ ተዳምሮ ፡ የጸሐፊውን ፡ ሥራ ፡ ከባድ ፡ አድርጎታል ።

ክፍል ፡ አንድ ፤

ውል ፡ የመዋዋል ፡ ሥልጣን ፤

"ውል ፡ መዋዋል" ፡ የሚለው ፡ አገላለጽ ፡ ውል ፡ መደራደርን ፤ በረቂቁ ፡ ላይ ፡ ምልክት ፡ (ፓራፍ) ፡ ማድረግን ፤ መፈራረምን ፤ ውሉን ፡ መቀበልን ፤ ውሉ ፡ የጸደቀበትን ፡ ሰነድ ፡ መለዋወጥን ፤ የሀገሩ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ስምምነቱን ፡ ያጸደቀበትን ፡

4. "የሀገሪቱ ፡ ሕግ" ፡ (ሙኒሲፓል ፡ ሎው) ፡ የሚባለው ፡ የአንድ ፡ ሀገር ፡ ውስጣዊ ፡ ወይም ፡ ብሔራዊ፡ ሕግ ፡ ነው ።

አዋጅ ፡ አሳትሞ ፡ ማውጣትንና ፡ ከመንግሥታትም ፡ ሆነ ፡ ከኢንተርናሲዮናል ፡ ድርጅቶች ፡ ጋር ፡ የተደረገው ፡ ውል ፡ በሀገሩ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የተፈጸመና ፡ በሕግ ፡ የተደገፈ ፡ መሆኑንና ፤ ፈራሚውም ፡ ባለሥልጣን ፡ ውሉን ፡ ለመዋዋል ፡ ተገቢው ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጠው ፡ መሆኑን ፡ ማረጋገጥንም ፡ ያጠቃልላል ።

ሆኖም ፡ ይህ ፡ ጽሑፍ ፡ አሁን ፡ ባሉት ፡ ሕግጋት ፡ መሠረት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውል፡ የመዋዋል ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ማን ፡ እንደሆነና ፡ ወይም ፡ የሚያስከትለውን ፡ ውጤት፡ ለማሳየት ፡ ይሞክራል ፡ እንጂ ፤ ሻምበል ፡ ሽመልስ ፡ መታፈሪያ ፡[5] በጻፉት ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ተጠቃልሎ ፡ ከተገለጸው ፡ የውል ፡ መዋዋል ፡ ሥርዓት ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ ዝር ዝሩን ፡ ሊያስረዳ ፡ አይሞክርም ።

ቢሆንም ፤ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ከመውጣቱ ፡ በፊትና ፡ ከወጣ ፡ ወዲህ ፡ ውል ፡ በማዋዋል ፡ ረገድ ፡ መሠረታዊ ፡ ልዩነት ፡ መኖሩን ፡ ማመልከት ፡ ያሻል ።

ሀ/ <u>ውል ፡ ለመዋዋል ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ያለው ፡ ልዩ ፡ ሥልጣን ፤</u>

የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ከወጣበት ፡ ከጥቅምት ፡ ፳፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በፊት ፡ ስምምነት ፡ የመዋዋል ፡ ሥልጣን ፡ የነበረው ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ብቻ፡ ሲሆን ፤ ይህም ፡ ሥልጣኑ ፡ ገደብ ፡ አልነበረውም ፤ ወይም ፡ ለዚህ ፡ ሥልጣኑ ፡ ገደብ ፡ አልተበጀለትም ፡ ነበር ።

ይህንኑም ፡ "ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ እንደ ፡ ሕጉ ፡ ማናቸውንም ፡ ዓይነት ፡ ውል ፡ ለመዋ ዋልና ፡ ለመፈረም ፡ ይችላል" ከሚለው ፡ ከ፲፱፻፳፫ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረቱ ፡ ሕገ ፡ መንግ ሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፲፬ ፡ ይረዷል ።

በገቢር ፡ እንደሚታየው ፡ ግን ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ በ፲፱፻፴፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ትእዛዝ ፡ ቁጥር ፡ ፩ ፡ ውሎችንና ፡ ስምምነቶችን ፡ ተነጋግሮ ፡ ለመዋዋል ፡ ያላቸውን ፡ ሥልጣን ፡ እርሳቸውን ፡ ወክሎ ፡ ውል ፡ እንዲዋዋል ፡ ለውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ሥልጣን ፡ ሰጥተ ውታል ።[6] የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ከወጣ ፡ ወዲህም ፡ ቢሆን ፤ ይህ ፡ ውክልና ፡ ሲሠራበት ፡ ቆይቶ ፡ ነበር ። ሆኖም ፡ ወደፊት ፡ እንደሚገለጸው ፡ ሁሉ ፤ ይህ ፡ ውክልና ፡ በ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ ፡ ምሕረቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ቁጥር ፡ ፳፯ ፡ ተሻሽሎአል ።

የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ከወጣ ፡ ወዲህም ፡ ውል ፡ መዋዋል ፡ ንዑስ ፡ ክፍሉ ፡ የሆነው ፡ ከውጭ ፡ ሀገር ፡ ጋራ ፡ የሚደረገውን ፡ ግንኙነት ፡ የመምራቱ ፡ ሥል ጣን ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አንቀጽ ፡ ፴ ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ተሰጥቶታል ።[7] ቢሆንም ፡

---

5. ሽመልስ ፡ መታፈሪያ ፤ <u>በኢትዮጵያ ፡ ስምምነት ፡ የመዋዋል ፡ ሥልጣን</u> ፡ (ለኤል ፡ ኤል ፡ ቢ ፡ ዲግሪ ፡ በማሟያነት ፡ የቀረበ ፡ ጽሑፍ ፡ በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት፡ ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡)

6. በ፲፱፻፴፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ስለ ፡ ሚኒስትሮች ፡ ሥልጣን ፡ አወሳሰን ፡ የወጣው ፡ ትእዛዝ ፡ ቁጥር ፡ ፩ ፡ አንቀጽ ፡ ፴፫ ፡ (ረ ፡ እና ፡ ሰ) ፡ <u>ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡</u> ፪ኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፫ ።

7. የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፴ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ።

ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ጋራ ፡ የሚደረገውን ፡ ግንኙነት ፡ የበላይ ፡ ሆኖ ፡ ይመራል ። ንጉሠ፡ ነገሥቱ ፡ አምባሳደሮችን ፡ ሚኒስትሮችንና ፡ መልእክተኞችን ፡ እየሾመ ፡ ይልካል ። በዚህም ፡ ዓይነት ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ እየተሾሙ ፡ የሚመጡትን ፡ ይቀበላል ። ከውጭ ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ ያለውን ፡ ክርክር ፡ ሕጋዊ ፡ በሆነና ፡ በሰላማዊ ፡ መንገድ ፡ ለመወሰን ፡ እንዲሁም ፡ ፀጥታና ፡ የጋራ ፡ መከላከያ ፡ በሚጠበ ቅበት ፡ ረገድ ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥታት ፡ ጋር ፡ ተባብሮ ፡ መሥራት ፡ የእርሱ መብት ፡ ነው ።

በኢትዮጵያ ፡ ስም ፡ ውሎችንና፡ ሌሎችንም፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ስምምነቶች፡ ለማጽደቅና ፡ በንጉሠ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ ሊፈጸሙ ፡ ግዴታ ፡ ከመሆናቸው ፡ አስቀድሞ ፡ የትኞቹ ፡ ውሎችና ፡ የኢን ተርናሲዮናል ፡ ስምምነቶች ፡ መጽደቅ ፡ እንደሚገባቸው ፡ የመወሰኑ መብት ፡ የርሱ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ከዚህ ፡ በታች ፡ እንደተገለጸው ፡ አንዳንዶቹን ፡ ውሎች ፡ ፓርላሜንቱ ፡ እንዲቀበላቸው ፡ የሚያስፈልግ ፡ መሆኑ ፡ በተጠቀሰው ፡ አንቀጽ ፡ ውስጥ ፡ ተመልክቷል ።

ለ/ የሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ የአንቀጽ ፡ ፴ ፡ ትንታኔ።

(ሀ) በአማርኛውና ፡ በእንግሊኛው ፡ ጽሑፍ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ልዩነት ፤

የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ከውጭ ፡ ሀገሮች ፡ ጋራ ፡ የሚያደርጉትን ፡ ግንኙነቶች ፡ በመምራትና ፡ ውሎችንም ፡ በመዋዋል ፡ ረገድ ፡ ያለውን ፡ ልዩ ፡ ሥልጣንና ፡ የተጣለበትንም ፡ የሥልጣን ፡ ገደብ ፡ ባጭሩ ፡ ያስረዳል ። የዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ትንታኔ ፡ የሚከተሉትን ፡ ፍሬ ፡ ነገሮች ፡ ያመለክታል ።

ከሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፴ ፡ የአማርኛው ፡ ጽሑፍ ፡ እንደ ፡ እንግሊዝኛው ፡ ሳይሆን ፡ በሁለት ፡ ንዑሳን ፡ ክፍሎች ተከፍሏል ። የመጀመሪያው ፡ ክፍል ፡ የሚናገረው ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥታት ፡ ጋራ ፡ ስለሚደረገው ፡ ግንኙነት ፡ በጠቅላላ ፡ ሲሆን ፤ ሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ ግን ፡ በተለይ ፡ የሚናገረው ስምምነት ፡ ስለመዋዋል ፡ ጉዳይ ፡ ነው ። ቢሆንም ፡ "ከውጭ ፡ ሀገር ፡ ጋራ ፡ የሚደረገውን ፡ ግንኙነት ፡ የበላይ ፡ ሆኖ ፡ ይመራል ፡" የሚለው ፡ የመጀመሪያው ፡ ሐረግ ፡ ውል ፡ የመዋዋልንም ፡ ሥልጣን ፡ የሚጨምር ፡ መሆኑን ፡ መገንዘብ ፡ ያሻል ። (እንክሮው ፡ የደራሲው ፡ ነው) ።

ሁለተኛም ፡ የዚሁ ፡ አንቀጽ ፡ የአማርኛው ፡ ጽሑፍ ፡ "እርሱ ፡ ብቻ" ፡ የሚሉትን ፡ ቃላት ፡ የሚጨምረው ፡ በሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ በመንግሥታት ፡ መካከል ፡ ያሉትን ፡ ክርክሮች ፡ በመወሰንና ፡ ከውጭ ፡ ሀገር ፡ መንግሥታት ፡ ጋር ፡ ተባብሮ ፡ መሥራትን ፡ በሚመለከቱ ፡ ጉዳዮች ፡ ውል ፡ የመዋዋል ፡ ሥልጣኑን ፡ (ይኸውም ፡ ማንኛውንም ፡ ዓይነት ፡ ስምምነት ፡ መዋዋልን ፡ የሚጨምር ፡ ሲሆን) ፡ ለሌላ ፡ ባለሥልጣን ፡ ሊያስተላልፈው ፡ ሲችል ፤ ውሎችን ፡ በማጽደቅ ፡ ረገድ ፡ ያለውን ፡ ሥልጣኑን ፡ ግን ፡ ለሌላ ፡ ባለሥልጣን ፡ በውክልና ፡ ሊያስተላልፈው ፡ አይችልም ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ።

በዚሁ ፡ በሚተነተነው ፡ አንቀጽ ፡ በአምስተኛው ፡ ዐረፍተ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ እንደተመለከተው ፤ የትኞቹ ፡ ውሎች ፡ መጽደቅ ፡ እንደሚገባቸው ፤ የትኞቹ ፡ መጽደቅ ፡ እንደማይገባቸው ፡ የመወሰኑ ፡ መብት ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ቢሆንም ፡ ፓርላሜንቱ ፡ እንዲቀበላቸው ፡ የሚያስፈልጉት ፡ ውሎች ፡ የትኞቹ ፡ እንደሆኑ ፡ በመወሰን ፡ ረገድ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ያለው ፡ ልዩ ፡ ሥልጣን ፡ መጠን ፡ የሚለካውና ፡ ሊለካም ፡ የሚገባው ፡ በአንቀጽ ፡ ፴ ፡ ውስጥ ፡ "ይሁን ፡ እንጂ" ፡ በሚለው ፡ ንዑስ ፡ አረፍተ ነገር ፡ ውስጥ ፡ በተመለከተው ፡ አጠቃላይ ፡ መምሪያ ፡ መሠረት ፡ ነው ።

የዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ደራሲ ፡ በአንቀጽ ፡ ፴ ፡ ውስጥ ፡ "ይሁን ፡ እንጂ" ፡ በሚለው ገደብ ፡ አውጭ ፡ የአነጋገር ፡ ስልት ፡ ውስጥ ፡ ስለተዘረዘሩት ፡ ውሎችና ፡ ስምምነቶች፡

"ይሁን ፡ እንጂ ፡ የሰላምን ፡ ውሎች ፡ ሁሉ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ አገር ፡ ወይም ፡ ከግዛቱ ፡ ማናቸውንም ፡ ክፍል ፡ ወይም ፡ ገዢነት ፡ ወይም ፡ ዳኝነትን ፡ ሥልጣን ፡ የሚያሻሽሉ ፡ ወይም ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ዜጎች ፡ ላይ ፡ ግዴታን ፡ የሚያስከትሉ ፡ ወይም ፡ ጸንቶ ፡ የቆመውን ፡ ሕግ ፡ የሚያሻሽሉ ፡ ወይም ፡ የመንግሥት ፡ ገንዘብ ፡ ወጪ ፡ እንዲሆንባቸው ፡ የሚጠይቁ ፡ ወይም ፡ ብድሮች ፡ ወይም ፡ ሞኖፖል ፡ ያለባቸው ፡ ውሎችና ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ስምምነቶች ፡ በንጉሠ ነገሥቱ ፡ ከመጽደቃቸው ፡ በፊት ፡ ለፓርላሜንት ፡ መቅረብ ፡ አለባቸው ። ሁለቱ ፡ ምክር ፡ ቤቶች ፡ በዚህ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ በአንቀጽ ፡ ፺፰ ፡ እስከ ፡ ፺ ፡ በተጻፈው ፡ መሠረት ፡ የተቀበሏቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እንዲጸድቁ ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ይቀርባሉ ።"

የሻምበል ፡ ሽመልስ ፡[8] ባደረጉት ፡ ትንታኔና ፡ በሰጡትም ፡ መደምደሚያ ፡ አሳብ ፡ በጠቅላላው ፡ ሲሰማማ ፤ በኢትዮጵያ ፡ ዜጎች ፡ ላይ ፡ በግል ፡ (ማለት ፡ በየሰው ፡ ላይ) ፡ ግዴታን ፡ ስለሚያስከትሉ ፡ ውሎች ፡ በሚገልጸው ፡ ዓረፍተ ፡ ነገር ፡ በአማርኛውና ፡ በእንግሊዝኛው ፡ ጽሑፍ ፡ መካከል ፡ ልዩነት ፡ መኖሩን ፡ ለማመልከት ፡ ይሻል ። ከሁሉ አስቀድሞ ፡ በእንግሊዝኛው ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ለሚገኘው ፡ "በየሰው ፡ ላይ» ፡ ለሚ ለው ፡ ቃል ፡ በአማርኛው ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ተመጣጣኝ ፡ የሚሆነው ፡ ቃል ፡ አይገኝለ ትም ። ሁለተኛም ፡ "በርደን" ፡ (burden) የሚለው ፡ የእንግሊዝኛው ፡ ቃል ፡ "ጉዳት" ፡ በሚለው ፡ የአማርኛ ፡ ቃል ፡ ተተርጉሞአል ። በአማርኛ ፡ "ጉዳት" ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ሁለት ፡ ዓይነት ፡ አገባብ ፡ አለው ። ይኸውም ፡ (ሀ) በአካል ፡ ላይ ፡ የሚደርስ ፡ ጉዳት ፤ (ለ) የንብረት ፡ መጥፋት ፡ ወይም ፡ በንብረት ፡ ላይ ፡ የሚደርስ ፡ ጉዳት ፡ የማለት ፡ ትርጉም ፡ የሚሰጥ ፡ ሲሆን ፤ "በኢትዮጵያ ፡ ዜጎች ፡ ላይ ፡ ግዴታን ፡ የሚያ ስከትሉ ፡ የስምምነት ፡ ውሎች" ፡ የሚለው ፡ የእንግሊዝኛው ፡ ዐረፍተ ፡ ነገር ፡ ወደ ፡ አማርኛ ፡ ሲተረጎም ፡ "በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ዜጎች ፡ ላይ ፡ ጉዳ ትን ፡ የሚያመጡ ፡ ---ውሎች" ፡ ተብሏል ።

ስለዚህ ፡ የሀገሪቱ ፡ መደበኛ ፡ ቋንቋ ፡ በሆነው ፡ በአማርኛው ፡ ጽሑፍ ፡ መሠረት ፤ ሀብትነቱ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጎች ፡ በሆነ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ጉዳትን ፡ ወይም ፡ ጥፋትን ፤ አለዚያም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ዜጎች ፡ ላይ ፡ የአካል ፡ ጉዳትን ፡ የሚያደርስ ፡ (ሊያደርስ ፡ የሚችል) ፡ ማናቸውም ፡ የውል ፡ ስምምነት ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ከመጽደቁ ፡ በፊት ፡ ለፓርላሜንቱ ፡ መቅረብ ፡ አለበት ። ስለዚህ ፡ (ሀ) ለአንድ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥት፡ ለኢምባሲው፡ ማሠሪያ፡ የሚያስፈልገውን፡ መሬት፡ ከባለንብረቱ፡ ጋር ፡ ስለዋጋ፡ በቀጥታ፡ በመዋዋል ፡ ፈንታ ፡ ባለርስቱን ፡ በማስለቀቅ ፡ (ኤክስፐሮፕሪየሺን) ፡ ሥርዓት ፡ መሠ ረት ፡ የመውሰድን ፡ መብት ፡ እና ፡ (ለ) ፡ በሀገሪቱ ፡ ውስጥ ፡ ከሚኖሩት ፡ የዲፕሎማ ቲክ ፡ ሠራተኞች ፡ ማናቸውም ፡ ቢሆን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ዜጎች ፡ ላይ ፡ የአካል ፡ ጉዳትን፡ ቢያደርስ ፡ በቂ ፡ ካሣ ፡ እንዳይከፍል ፡ መብት ፡ ይሰጣል ፡ ተብሎ ፡ ሊተረጎም ፡ የሚ ችል ፡ ስምምነት ፡ በሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፴ ፡ በአማርኛው ፡ ጽሑፍ ፡ ከተመለከ ቱት ፡ ለፓርላማ ፡ ሊቀርቡ ፡ ለሚገቡት ፡ የውል ፡ ዓይነቶች ፡ እንደምሳሌ ፡ ሊጠቀስ ፡ ይቻላል ። በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ የእንግሊዝኛው ፡ ጽሑፍ ፡ የበለጠ ፡ ትክክል ፡ ሆኖ፡ የሚቆጠር ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ በሻምበል ፡ ሽመልስ ፡ እንደተብራራው ፡ ሁሉ ፤ ለአንድ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥት ፡ ወታደራዊ ፡ ተራድኦን ፡ የሚፈቅድ ፡ የስምምነት ፡ ውልም ፡ ሆነ ፤ ለአንድ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥት ፡ ጥቅም ፡ ሲባል ፡ የተጣለ ፡ ግብር ፡ በኢትዮጵያ ፡ ዜጎች ፡ ላይ ፡ ግዴታን ፡ ሊያስከትል ፡ ይችላል ።

(ለ) ውል ፡ የመዋዋል ፡ ሥልጣንን ፡ በውክልና ፡ ስለማስተላለፍ ፤

የ፲፱፻፶፰ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ቁጥር ፡ ፵፮ ፡ ከወጣ ፡ ወዲህ ፡ የውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስትር ፤ የገንዘብ ፡ ሚኒስትርና ፡ የልማትና ፡ የፕላን ፡ ሚኒስትር ፡ የኢንተር ናሲዮናል ፡ ውሎችን ፤ ስምምነቶችንና ፡ ድርድሮችን ፡ ተነጋግሮ ፡ ለመዋዋል ፡ በዚሁ ፡ ትእዛዝ ፡ ሥልጣን ፡ ሲሰጣቸው ፤ የመከላከያና ፡ የውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስትሮች ፡ ደግሞ፡ እነዚህ ፡ ውሎችና ፡ ስምምነቶች ፡ የሚያስከትሉት ፡ ግዴታ ፡ መፈጸሙን ፡ እንዲያረ

8. እላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፰ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ገጽ ፡ ፩፻፵፪—፩፻፵፬ ፤ ፩፻፶፪—፩፻፶፬ ፤ ፩፻፶፰—፩፻፷ ፤ ፩፻፸፩—፩፻፸፪ ፤ ፩፻፸፭—፩፻፸፰ ፤ ፩፻፺፩—፩፻፺፫ ፤ ፩፻፺፯—፩፻፺፰ ፤ ይመለከቷል ።

ጋግጡና ፡ የሀገሪቱን ፡ ውሎች ፡ ስምምነቶችና ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ግዴታዎች ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲያውሉ ፡ ተደርጎአል ።[9]

ስለዚህ ፡ ሥልጣኑ ፡ በተለይ ፡ ለሌላ ፡ ሚኒስትር ፡ ወይም ፡ የመንግሥት ፡ ባለሥልጣን ፡ ካልተሰጠ ፡ በቀር ፤ የተወሰኑ ፡ ዓይነት ፡ ውሎችን ፡ ተነጋግሮ ፡ ለመፈረም ፡ ለውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስትር ፡ በትእዛዙ ፡ በቁጥር ፡ ፳፰ ፡ (ሐ) ፡ ሥልጣን ፡ ተሰጥቶታል። ሌሎች ፡ ሚኒስትሮች ፡ ወይም ፡ የመንግሥት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ተነጋግረው ፡ ለመዋዋል፣ የሚችሉት ፡ የውል ፡ ዓይነት ፤ የገንዘብ ፡ ሚኒስትር ፡ የሚያደርገው ፡ የብድርና ፡ የክሬዲት ፡ ስምምነት ፡ ሲሆን ፤ የቀድሞው ፡ የልማትና ፡ ፕላን ፡ ሚኒስትር ፡ ብቻውን ፡ ያደርገው ፡ የነበረውና ፡ አሁን ፡ ግን ፡ በ፲፱፻፷፪ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ቁጥር ፡ ፷፫ ፡ በአንቀጽ ፡ ፭ ፡ በንዑስ ፡ አንቀጽ ፡ ፫ ፡[10] እንደተገለጸው ፡ የጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ አካል ፡ የሆነው ፡ የአሁኑ ፡ የፕላን ፡ ኮሚሽን ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ የበላይ ፡ ሹም ፡ ጉዳዩ ፡ ከሚመለከተው ፡ ሚኒስትር ፡ ጋር ፡ ሆኖ ፡ የሚያደርገው ፡ የኤኮኖሚና ፡ የቴክኒክ ፡ ተራድኦ ፡ ስምምነት ፡ ነው ።

ሌሎች ፡ ሚኒስትሮችና ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ የበላይ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ የአስፈጻሚው ፡ ክፍል ፡ ወኪሎች ፡ እንደመሆናቸው ፡ መጠን ፤ እላይ ፡ በተጠቀሱት ፡ ሚኒስትሮች ፡ ባንደኛው ፡ ወይም ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ውሉን ፡ ወይም ፡ ስምምነቱን ፡ እንዲዋዋል ፡ "ሙሉ ፡ ሥልጣን" ፡ በተሰጠው ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ በሚገኝ ፡ የኢትዮጵያ ፡ አምባሳደር ፡ ወይም ፡ ሚኒስትር ፡ በተፈረመ ፡ ውል ፡ ሥር ፡ የሚጠቃለሉ፡ ውሎችን ፡ ወይም ፡ ስምምነቶችን ፡ ለመዋዋል ፡ (ለመፈራረም) ፡ ይችላሉ ። ስለባህል ፡ ግንኙነት ፡ የሚደረግ ፡ ስምምነት ፡ ወይም ፡ አንድን ፡ እቅድ ፡ ለማስፈጸም ፡ (ለምሳሌ፣ አንድ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ከሁለት ፡ ተዋዋይ ፡ ወገኖች ፡ በተውጣጣ ፡ የጋራ ፡ ገንዘብ ፡ ለማሠራት) ፡ የሚደረግ ፡ ስምምነት ፡ በሌሎች ፡ ሚኒስትሮችና ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ የበላይ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ለሚፈረሙ ፡ ስምምነቶች ፡ እንደ ፡ ምሳሌ ፡ መጥቀስ ፡ ይቻላል ።

(ሐ) የሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አንቀጽ ፡ ፴ ፡ ምርምር ፡ ማጠቃለያ ፡ አሳብ ፤

በዚህ ፡ በአርዕስቱ ፡ በተጠቀሰው ፡ አንቀጽ ፡ ውስጥ ፡ "ይሁን ፡ እንጂ" በሚለው፡ ገደብ ፡ አውጪ ፡ የአነጋገር ፡ ስልት ፡ ውስጥ ፡ የተዘረዘሩት ፡ አንዳንድ ፡ ዓይነት ፡ ስምምነቶችና ፡ ውሎች ፤ በፓርላሜንት ፡ መጽደቅ ፡ አለባቸው ፡ የሚለው ፡ ሳይጓደል፤ በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፴ ፡ መሠረት ፡ ውል ፡ መዋዋል ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የተለየ ፡ ሥልጣን ፡ ነው ። በ፲፱፻፷፮ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ቁጥር ፡ ፵፮ ፡ መሠረት ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ውሎችንና ፡ ስምምነቶችን ፡ ተነጋግሮ ፡ ለመዋዋል ፡ ያላቸውን ፡ ሥልጣን ፡ ለውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስትር ፤ ለገንዘብ ፡ ሚኒስትርና ፡ ለቀድሞው ፡ የልማትና ፡ የፕላን ፡ ሚኒስትር ፡ (ለአሁኑ ፡ የፕላን ፡ ኮሚሽን ፡ ዋና ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የበላይ ፡ ሹም ፡) ሰጥተዋል ። የተቀሩት ፡ ሚኒስትሮችና ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ የበላይ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ሊዋዋሉ ፡ የሚችሉት ፡ የባህል ፡ ነክ ፡ ስምምነቶችንና፡ ቀደም ፡ ሲል ፡ መንግሥቱን ፡ ወክሎ ፡ ውል ፡ ለመዋዋል ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጠው ፡ ባለ

---

9. በ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ስለሚኒስትሮች ፡ ሥልጣን አወሳሰን ፡ የወጣው ፡ (ማሻሻያ ፡ ቁጥር ፡ ፩) ፡ ትእዛዝ ፡ ቁጥር ፡ ፵፮ ፡ አንቀጽ ፡ ፳፮ ፡ (ሰ ፡ እና ፡ ሸ) ፡ አንቀጽ ፡ ፳፰ ፡ (ሐ ፡ እና ፡ መ) ፡ አንቀጽ ፡ ፳፱ ፡ (ሸ) ፡ አንቀጽ ፡ ፴፫ ፡ (ሸ) ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፳፭ኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፳፫ ፤
10. በ፲፱፻፷፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ስለ ፡ ፕላን ፡ ኮሚሽን ፡ የወጣ ፡ ትእዛዝ ፤ (ትእዛዝ ፡ ቁጥር ፡ ፷፫) ፡ አንቀጽ ፡ ፭ ፡ (፫) ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፳፱ኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፲፱ ።

ሥልጣን ፡ ካደረገው ፡ ስምምነት ፡ ውስጥ ፡ የተመለከቱት ፡ እቅዶችና ፡ ፕሮግራሞች ፡ የሚፈጸሙበትን ፡ ሁኔታ ፡ በመወሰን ፡ የሚደረጉ ፡ ስምምነቶች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ።

በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ በአንቀጽ ፡ ፴ ፡ ውስጥ ፡ የተመለከተው ፡ የተጠበቀ ፡ ሆኖ ፤ በኢትዮጵያ ፡ ስም ፡ ውሎችንና ፡ ሌሎችንም ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ስምምነቶች ፡ የማጽደቅና ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ ሊፈጸሙ ፡ ግዴታ ፡ ከመሆናቸው ፡ አስቀድሞ ፡ የትኞቹ ፡ ውሎችና ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ስምምነቶች ፡ መጽደቅ ፡ እንደሚገባቸው ፡ የመወሰኑ ፡ ሥልጣን ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ብቻ ፡ የሆነ ፡ ሥልጣን ፡ ነው ። ይህም ፡ የሆነበት ፡ ምክንያት ፤ የአንቀጽ ፡ ፴ ፡ የአማርኛውና ፡ የእንግሊዝኛው ፡ ጽሑፍ ፡ ሁለቱም ፡ ባንድነት ፡ ይህ ፡ መብት ፡ ያለው ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ብቻ ፡ እንደሆነ ፡ ስለሚገልጹ ፡ ነው ። ይህም ፡ ሥልጣን ፡ ለማናቸውም ፡ ባለሥልጣን ፡ ቢሆን ፡ በውክልና ፡ የማይሰጥ ፡ ነው ።

(መ) የሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አንቀጽ ፡ ፩ ፡ እና ፡ አንቀጽ ፡ ፴ ፡ የሚስማሙበት ፡ ሁኔታ፤

በሻምበል ፡ ሽመልስ ፡ ጽሑፍ ፡[11] ውስጥ ፡ በሚገባ ፡ እንደተገለጸው ፤ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፩ ፡ እንዳለ ፡ ሲነበብ ፤ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ የሆኑ ፡ ክፍለ ፡ ሀገሮችንና ፡ የገዢነት ፡ መብቶችን ፡ ለባዕድ ፡ ሊያስተላልፉ ፡ የሚችሉ ፡ ውሎች ፡ እንዳይደረጉ ፡ የሚከለክል ፡ ይመስላል ። በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ስምምነቱ ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ከመጽደቁ ፡ አስቀድሞ ፡ ፓርላሜንቱ ፡ እንዲቀበለው ፡ ለፓርላሜንቱ ፡ የሚቀርብ ፡ ሆኖ ፤ የንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ ግዛት ወይም ፡ ከግዛቱ ፡ ማናቸውንም ፡ ክፍል ፡ ወይም ፡ ገዢነቱን ፡ የሚያሻሽሉ ፡ ውሎችን ፡ ለመዋዋል ፡ የሚያስችል ፡ መንገድ ፡ የሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አንቀጽ ፡ ፴ ፡ ይከፍታል ። ስለዚህ ፡ በሁለቱ ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ አናቅጻት ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ መሠረታዊ ፡ መጻረር ፡ እንደምንም ፡ ብሎ ፡ ማስታረቅ ፡ ይገባል ።

ማናቸውም ፡ ሀገር ፡ ቢሆን ፡ በራሱ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ለራሱ ፡ ጥቅም ፡ የሚሆኑትን ፡ ውሎች ፡ ከሌላ ፡ መንግሥት ፡ ጋር ፡ እንዳይዋዋል ፡ ራሱን ፡ ስለማይከለክል ፤ የዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ደራሲ ፡ እነዚህን ፡ ሁለት ፡ አናቅጻት ፡ ለማስማማት ፡ የሚሻው ፡ ስለተለየ ፡ ጉዳይ ፡ የሚናገረው ፡ የሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ስለጠቅላላው ፡ በሚናገረው ፡ የሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ላይ ፡ የበላይነት ፡ አለው ፡ በሚለው ፡ በታወቀው ፡ የሕግ ፡ አተረጓጎም ፡ ዘዴ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ፩ ፡ ጠቅላላ ፡ አነጋገር ፡ ከመሆኑም ፡ ሌላ ፡ የሚገኘው ፡ በጠቅላላው ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ስለሆነ ፤ መተርጎም ፡ የሚገባው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ በተለይ ፡ ስምምነት ፡ ስለመዋዋል ፡ ሥልጣን ፡ በሚናገረው በአንቀጽ ፡ ፴ ፡ መሠረት፡ ሊሆን ፡ ይገባል ።

ሐ/ የፓርላሜንቱ ፡ መቀበል ፡ አስፈላጊ ፡ ስለመሆኑ ፤

በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፴ ፡ ውስጥ ፡ እንደተመለከተው ፡ ቀጥሎ ፡ የተዘረዘሩትን ፡ ጉዳዮች ፡ የሚመለከቱ ፡ ውሎች ፡ ሁሉ ፡—

፩/ የሰላም ፡ ውሎች ፡

፪/ የንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ሀገር ፡ የሚያሻሽሉ ፡ ውሎችና ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ስምምነቶች ፡

---

11. አላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፭ ፡ የተጠቀሰውን ፤ ከገጽ ፡ ፩፻፵—፩፻፵፪ ፡ ያለውን ፡ ይመለከቷል ።

፫/ ከግዛቱ ፡ በማናቸውም ፡ ክፍል ፡ ላይ ፡ የበላይ ፡ ገዢነትንም ፡ ሆነ ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣንን ፡ የሚያሻሽሉ ፡ ውሎችና ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ስምምነቶች ፤

፬/ በኢትዮጵያ ፡ ዜጎች ፡ ላይ ፡ ግዴታን ፡ የሚያመጡ ፡ (ወይም ፡ እንደ ፡ አማርኛው ፡ ጽሑፍ ፤ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ዜጎች ፡ ላይ ፡ የአካል፡ ወይም ፡ የንብረት ፡ ጉዳትን ፡ የሚያመጡ) ፡ ውሎችና ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ስምምነቶች ፤

፭/ ጸንቶ ፡ የሚሠራበትን ፡ ሕግ ፡ የሚያሻሽሉ ፡ ውሎችና ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ስምምነቶች ፤

፮/ የመንግሥት ፡ ገንዘብ ፡ ወጪ ፡ እንዲሆንባቸው ፡ የሚጠይቁ ፡ ውሎች ፤

፯/ ስለብድሮች ፡ የተደረጉ ፡ ውሎችና ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ስምምነቶች ፤

፰/ እንዲሁም ፡ ሞኖፖል ፡ ያለባቸው ፡ ውሎችና ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ስምምነቶች ፤

በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛትና ፡ በነዋሪዎቹ ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚ ፡ ግዴታ ፡ ከመሆናቸው ፡ በፊት ፤ ማለት ፡ በሀገሪቱ ፡ ውስጥ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ከመዋላቸውና ፡ ከመፈጸማቸው ፡ አስቀድሞ ፡ ፓርላሜንቱ ፡ እንዲቀበላቸው ፡ ያስፈልጋል ።

የዚህ ፡ ዓይነት ፡ ጠባይ ፡ ያላቸው ፡ ውሎችና ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ስምምነቶች ፡ በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ከአንቀጽ ፡ ፹፰ ፡ እስከ ፡ ፺ ፡ በተመለከተው ፡ የሕግ ፡ አወጣጥ፡ሥርዓት ፡ መሠረት ፡ ሁለቱም ፡ ምክር ፡ ቤቶች ፡ (የመወሰኛውና ፡ የመምሪያው)፡ በድምፅ ፡ ብልጫ ፡ ከተቀበሏቸው ፡ በኋላ ፡ በንጉሡ ፡ ነገሥቱ ፡ መጽደቅ ፡ አለባቸው ።[12] የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ከመውጣቱ ፡ በፊት ፡ ለተደረጉት ፡ ውሎችና ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ስምምነቶች ፡ ይህ ፡ የአሠራር ፡ ዘዴ ፡ ተፈጻሚነት ፡ የለውም ፡ ነበር ። የ፲፱፻፳፫ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረቱ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፲፬ ፡ አንድን ፡ ስምምነት ፡ ፓርላሜንቱ ፡ እንዲቀበለው ፡ ስለማያዝ ፡ ማናቸውም ፡ ውል ፡ ወይም ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ስምምነት ፡ ፓርላሜንቱ ፡ መቀበል ፡ ሳያስፈልገው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ ሊፈጸም ፡ ግዴታ ፡ ይሆን ፡ ነበር ። ስለዚህ ፤ ስምምነቶቹ ፡ የተደረጉት ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ከወጣ ፡ በኋላ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፤ ፓርላሜንቱ ፡ ተቀብሎአቸው ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መጽደቅ ፡ የሚገባቸው ፡ የውል ፡ አንቀጾች ፡ ቢኖሩባቸውም ፡ እንኳ ፡ ከጥቅምት ፡ ፳፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በፊት ፡ የተደረጉ ፡ ውሎችና ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ስምምነቶች ፡ ይህንን ፡ ባያሟሉም ፡ አሁንም ፡ ቢሆን ፡ በሀገሪቱ ፡ ላይ ፡ ግዴታ ፡ ሆነው ፡ ተፈጻሚነት ፡ አላቸው ።

የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፳፪ ትን ፡ በሚመለከት ፡ ጭብጥ ፡ በተነሳው ፡ ክርክር ፡ ላይ ፤ የተባለው ፡ አንቀጽ ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ በወጣበት ፡ ጊዜ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ በነበሩት ፡ ሕጎች ፡ (አዋጆች) ፤ ትእዛዞች ፤

12. ውልን ፡ ማጽደቅ ፡ ማለት ፡ የአንድን ፡ ውል ፡ ድርድር ፡ ፓርላሜንቱ ፡ ከተቀበለው ፡ በኋላ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ይህንኑ ፡ አጽንቶ ፡ በሙሉ ፡ ለመስማማቱ ፡ ፈቃደኛ ፡ መሆኑን ፡ በመግለጽ ፡ በውሉ ፡ ውስጥ ፡ ሌላ ፡ ስምምነት ፡ ከሌላ ፡ በቀር ፡ የማጽደቂያው ፡ ሰነድ ፡ ከተለዋወጡበት ፡ ቀን ፡ አንስቶ ፡ ውሉ ፡ ለመፈጸም ፡ ያለውን ፡ አስገዳጅነት ፡ መቀበሉን ፡ የሚገልጽ ፡ ድርጊት ፡ ነው ።

ወዘተ ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚነት ፡ የለውም ፡ ሲል ፡ በይኖአል ።[13] ስለዚህ ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፳፪ ፡ በግልጽም ፡ ባይሆን ፡ በውስጠ ፡ ታዋቂነት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ወደፊት ፡ ተካፋይ ፡ የምትሆንባቸው ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ውሎች ፤ ስምምነቶችና ፡ ግዴታዎች ፡ ከሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ጋር ፡ የማይስማሙ ፡ ሲሆኑ ፡ ዋጋ ፡ የሌላቸውና ፡ የማያገለግሉ ፡ ይሆናሉ ፡ የሚለው ፡ ሐረግ ፤ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ በወጣበት ፡ ጊዜ ፡ ጸንተው ፡ ይሠራባቸው ፡ የነበሩትን ፡ ውሎችና ፡ ስምምነቶች ፡ አይጨምርም ።

አንድን ፡ ውል ፡ ፓርላሜንቱ ፡ የሚቀበለው፡ "ዘ፡ሎው፡ሜኪንግ፡ፕሮሰስ፡ኢን፡ኢትዮጵያ"[14] (በኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ አወጣጥ ፡ ሥርዓት) ፡ በተባለው ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ የተገለጸውን ፡ የሚመስል ፡ ደረጃ ፡ በደረጃ ፡ የሆነ ፡ ሥርዓትን ፡ ተከትሎ ፡ ነው ። በፓርላሜንቱ ፡ መቀበል ፡ ረገድ ፡ በሕግ ፡ አሳብና ፡ በውል ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ልዩነት ፤ የሕግ ፡ አሳብ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ፓርላሜንቱ ፡ ማሻሻያ ፡ አሳብ ፡ ሊያክልበት ፡ ሲችል፤ በውል ፡ ላይ ፡ ግን ፡ ሊያደርግ ፡ የሚችለው ፡ በአስፈጻሚው ፡ ወገን ፡ የቀረበውን ፡ ያለማሻሻያ ፡ እንዳለ ፡ መቀበል ፡ ወይም ፡ በጠቅላላ ፡ አለመቀበል ፡ ብቻ ፡ ነው ። ፓርላሜንቱ ፡ አንድን ፡ ውል ፡ ወይም ፡ ስምምነት ፡ ሲቀበል ፡ በተዋዋዮቹ ፡ መካከል ፡ የተፈረመው ፡ ውል ፡ ወይም ፡ ስምምነት ፡ ተቀባይነት ፡ ማግኘቱን ፡ የሚገልጽ ፡ ከውሉ ፡ ጋር ፡ የቀረበለትን ፡ የአዋጅ ፡ ረቂቅም ፡ አብሮ ፡ ያሳልፋል ። ውሉ ፡ ከማጽደቂያው ፡ አዋጅ ፡ ጋር ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ላይ ፡ ታትሞ ፡ ከወጣው ፡ ከአፍሪካ ፡ አንድነት ፡ ድርጅት ፡ ውል ፡ በቀር ፤ ዘወትር ፡ የሚደረገው ፡ የውሉን ፡ ወይም ፡ ስምምነቱን ፡ ቃል ፡ ሳይሆን ፡ የማጽደቂያውን ፡ አዋጅ ፡ ብቻ ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ አትሞ ፡ ማውጣት ፡ ነው ።

ራይት ፡ ከጽሑፋቸው ፡ በአንደኛው ፡ "የሕግ ፡ አውጭው ፡ ክፍልም ፡ በነገሩ ፡ ተካፋይ ፡ እንዲሆን ፡ ማስፈለጉ ፡ የውሎችን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ መዋል ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ሊያዘገያቸው ፡ ቢችልም ፤ በውጭ ፡ ጉዳይ ፡ አመራር ፡ የሕዝቡ ፡ ተካፋይነት ፡ ልማዳዊ ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ሕግና ፡ ውል ፡ የሚያስከትሉትን ፡ የተለምዶ ፡ ግዴታዎችን ፡ ለመፈጸም ፡ አንድን ፡ ሀገር ፡ በበለጠ ፡ እንደሚያስችሉት ፡ አይጠረጠርም"[15] ብለው ፡ ጽፈዋል ።

በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፴ ፡ ውስጥ ፡ "ይሁን ፡ እንጂ" ፡ በሚለው ፡ ንዑስ ፡ ዓረፍተ ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ የሚወጣው ፡ የውል ፡ ማጽደቂያ ፡ አዋጅ ፡ ውሉን ፡ ወይም ፡ ስምምነቱን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ተፈጻሚ ፡ ሆኖ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ ያደርገዋል ።

ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ፕሪየዝ ፡ ሲጽፉ ፡ "አንድ ፡ ውል ፡ እንደ ፡ ሕግ ፡ ሆኖ ፡ አስገዳጅ ፡ የሚሆነው ፡ ስለተዋዋሉት ፤ ተፈጻሚ ፡ የሚሆነው ፡ ስለተቀበሉት ፤ በሥራ ፡ ላይ ፡ የሚውለው ፡ አትመው ፡ ስላወጡት ፡ ነው"[16] ብለዋል ።

---

13. ክቡር ፡ ልጅ ፡ አርአያ ፡ አበበ ፡ ከሳሽ ፤ የቴሌኮሚኒኬሽን ቦርድ ፡ መልስ ፡ ሰጭ ፡ (ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ መጽሔት ፡ ፪ኛ ፡ ቮልዩም ፡ (፲፱፻፶፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡) ገጽ ፡ ፫፻፷) ።

14. ኬኔት ፡ ሮበርት ፡ ሬደን ፤ ዘ ፡ ሎው ፡ ሜኪንግ ፡ ፕሮሴስ ፡ ኢን ፡ ኢትዮጵያ ፡ (፲፱፻፶፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡) በኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ አወጣጥ ፡ ሥርዓት ፡ ገጽ ፡ ፳፱—፴ ።

15. ኩዊንሲ ፡ ራይት ፡ «የኢንተርናሺናል ፡ ሕግ ፡ ከሕገ ፡ መንግሥት ፡ ጋር ፡ ያለው ፡ ግንኙነት» ፡ አሜሪካን፡ ጁርናል ፡ ኦፍ ፡ ኢንተርናሽናል ፡ ሎው ፡ ፲፯ኛ ፡ ቮልዩም ፡ (፲፱፻፲፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡) ቁጥር ፡ ፩ ፡ ገጽ ፡ ፩፻፴፯ ።

16. ሎውራንስ ፡ ፕሪየዝ ፡ «በፈረንሣይ ፡ የሕገ ፡ መንግሥት ፡ ቅንጅት ፡ ውስጥ ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ሕግ ፡ ከብሔራዊ ፡ ሕግ ፡ ጋራ ፡ ያለው ፡ ግንኙነት» ፡ አሜሪካን ፡ ጁርናል ፡ ኦፍ ፡ ኢንተርናሽናል ፡ ሎው ፡ ቮልዩም ፡ ፵፬ ፡ (፲፱፻፵፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡) ገጽ ፡ ፯፻፶ ።

ስለዚህ ፡ ለውሎች ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ውጤት ፡ ስለሚሰጣቸው ፡ ፓርላሜንቱ ፡ አንድን ፡ ውል ፡ በመቀበል ፡ ረገድ ፡ ያለው ፡ ተግባር ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው ። ቢሆ ንም ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ሠራተኞች ፡ ድርጅት ፡ ያሳለፈውን ፡ ስምምነት ፡ ማጽደቅ፡ አንድ ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ እንደራሴ ፡ ተነጋግሮ ፡ የተፈራረመውን ፡ ውል ፡ ከማጽ ደቅ ፡ የሚለይ ፡ መሆኑን ፡ መገንዘብ ፡ ያሻል ።[17] ይህም ፡ የሆነበት ፡ ምክንያት ፡ እንደ ዚህ ፡ ያሉት ፡ ውሎች ፡ በገዛ ፡ ራሳቸው ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ስለማይውሉና ፡ እንዲውሉም ፡ ያልታቀዱ ፡ በመሆናቸው ፡ ነው ።

ያንድ ፡ ውል ፡ መጽደቅ ፡ ውጤት ፡ ወደኋላ ፡ ተመልሶ ፡ ውሉን ፡ የተዋዋዮቹ ፡ ልዑካን ፡ ከፈረሙበት ፡ ቀን ፡ አንስቶ ፡ ተፈጻሚ ፡ ያደርገው ፡ ወይም ፡ አያደርገው ፡ እንደሆነ ፡ ለመወሰን ፡ በሊቃውንቱ ፡ መካከል ፡ ብዙ ፡ የሀሳብ ፡ ልዩነት ፡ አለ ።

ውሎችን ፡ ማጽደቅ ፡ ወደኋላ ፡ ተመልሰው ፡ እንዲሠሩ ፡ ያደርጋቸዋል ፤ የሚ ለው ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ሕግ ፡ ባሕረ ፡ ሀሳብ ፡ ስለ ፡ ኢንተርናሲዮናል ፡ ሕግ ፡ በመ ጻፍ ፡ በታወቁት ፡ ምሁራን ፡ ዘንድ ፡ ተቀባይነትን ፡ አግኝቷል ፡ በማለት ፡ ሚስተር ፡ ጆንስ ፡ ጽፈዋል ። እኒህ ፡ ምሁር ፡ በጽሑፋቸው ፡ ውስጥ ፡ የሚያብራሩት ፡ ባሕረ ፡ ሀሳብ ፡ "የውሉን ፡ የማጽደቂያ ፡ ጽሑፍ ፡ (ሰነድ) ፡ መለዋወጡ ፡ ውሉን ፡ ወደኋላ ፡ ተመልሶ ፡ የሚሠራ ፡ በማድረግ ፡ ከመጀመሪያው ፡ ቀን ፡ አንስቶ ፡ ስለሚያጸናው ፤ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ስምምነት ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ አንድ ፡ ውል ፡ በተዋዋዮቹ ፡ ወገኖች ፡ መካከል ፡ ከተፈረመበት ፡ ቀን ፡ አንስቶ ፡ አስገዳጅነት ፡ ይኖረዋል"[18] የሚል ፡ ነው ።

በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ አፐንሃይም ፡ "አንድ ፡ ውል ፡ ተፈጻሚ ፡ ለመሆን ፡ የአስ ገዳጅነት ፡ ኃይሉን ፡ የሚያገኘው ፡ ውሉ ፡ ሲጸድቅ ፡ ቢሆንም ፡ ማጽደቅ ፡ በተለምዶ ፡ ውሉን ፡ ወደኋላ ፡ ተመልሶ ፡ እንዲሠራ ፡ አያደርገውም"[19] ይላሉ ።

የዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ደራሲ ፡ ግን ፡ የአፈጻጸም ፡ ችግርን ፡ ለማስወገድ ፡ ሲባል ፡ በኢ ትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ተቀባይነት ፡ ማግኘት ፡ የሚገባው ፡ በመጨረሻ ፡ የተጠቀሰው ፡ አስተያየት ፡ ቢሆን ፡ እንደሚሻል ፡ ያምናል ። ይህም ፡ ማለት ፡ ተቃራኒ ፡ ስምምነት ፡ ካልተደረገ ፡ በቀር ፤ ኢትዮጵያ ፡ ተካፋይ ፡ የምትሆንበት ፡ ውል ፡ ሊፈጸም ፡ ግዴታ ፡ መሆን ፡ የሚገባው ፡ ከተፈረመበት ፡ ቀን ፡ አንስቶ ፡ ሳይሆን ፤ ከጸደቀበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ፡ መሆን ፡ አለበት ፡ ማለት ፡ ነው ።

መ/ አንድ ፡ ውል ፡ ሕጋዊ ፡ ዋጋ ፡ እንዴት ፡ ሊኖረው ፡ እንደሚችል ፤

የኢንተርናሲዮናል ፡ ሕግ ፡ ሊቃውንት ፡ እንደሚሉት ፡ አንድ ፡ ውል ፡ ሙሉ ፡ የግዴታ ፡ ኃይል ፡ እንዲኖረው ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ግዴታ ፡ ለመሆን ፡ ይበቃ ፡ ዘንድ ውሉ ፡ በተደረገበት ፡ ጊዜና ፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ የጸና ፡ ከመሆን ፡ በላይ ፤ በተጨማሪ ፡ አንድ ፡ ውል ፡ ሊኖረው ፡ የሚገቡትን ፡ መሠረታውያን ፡ ነገሮች ፡ አሟልቶ ፡ የያዘ ፡ መሆን ፡ ይገባዋል ።[20] "የቀድሞ ፡ ጽኑነት" ፡ እና ፡ "የኋላ ፡ ጽኑነት" ፡ የሚሉት ፡ ቃላት ፡ እንደነገሩ ፡ ሁኔታ ፡ የውሉን ፡ በመጀመሪያ ፡ በሚገባ ፡ መፈጸም ፡ (መፈራረም)፡ እና ፡ ከዚያን ፡ ጊዜም ፡ ጀምሮ ፡ ሳይቋረጥ ፡ ውሉ ፡ የጸና ፡ መሆኑን ፡ ያመለክታሉ ።[21]

---

17. ጄ ፡ ኤል ፡ ብራየርሊ ፤ ዘ ፡ ሎው ፡ ኦፍ ፡ ኔሺንስ ፡ (፲፱፻፷፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡)ገጽ ፡ ፫፻፴፩ ።
18. መርብኒ ፡ ጆንስ ፡ "የውሎች ፡ መጽደቅ ፡ ወደኋላ ፡ ተመልሶ ፡ በመሥራት ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤት"፡ አሜሪካን ፡ ጆርናል ፡ ኦፍ ፡ ኢንተርናሺናል ፡ ሎው ፡ ቮልዩም ፡ ፳፱ ፡ (፲፱፻፴፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡) ገጽ ፡ ፶፩ ፡
19. አፐንሃይም፤ እላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፫ ፡ የተጠቀሰ ፤ ተራ ፡ ቁጥር ፡ ፭፻፲፰ ፡ ገጽ ፡ ፱፻፲፯ ።
20. የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፤ ይር ፡ ቡክ ፡ ኦፍ ፡ ዘ ፡ ኢንተርናሽናል ፡ ሎው ፡ ኮሚሽን ፡ (፲፱፻፶፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡) ፪ኛ ፡ ቮልዩም ፡ ገጽ ፡ ፳፫ ።
21. ከዚያው ።

ስለሆነም ፡ አንድ ፡ ውል ፡ በሕግ ፡ ተፈጻሚነት ፡ እንዲኖረው ፡ ሹማን ፡ እንዳመለከቱት ፡ የሚከተሉትን ፡ ሁኔታዎች ፡ ያሟላ ፡ ሆኖ ፡ መገኘት ፡ አለበት ።

፩/ ተዋዋይዎቹ ፡ ውሉን ፡ ለመዋዋል ፡ ሕጋዊ ፡ ችሎታ ፡ እንዲኖራቸው ፡ ያስፈልጋል ። ይህም ፡ ማለት ፡ ተዋዋይዎቹ ፡ በሀገራቸው ፡ ሕገ ፡ መንግሥትና፡ ቀደም ፡ ሲል ፡ በተደረጉት ፡ ውሎች ፡ ውስጥ ፡ ውሉን ፡ ከመዋዋል ፡ የሚከለክላቸው ፡ ነገር ፡ መኖር ፡ የለበትም ።

፪/ ተዋዋይዎቹ ፡ ውሉን ፡ ለመዋዋል ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ እንደራሴዎች ፡ ሁነው ፡ የተዋዋሉትም ፡ በተሰጣቸው ፡ ሥልጣን ፡ ክልል ፡ ውስጥ ፡ መሆን፡ አለበት ።

፫/ ውሉን ፡ ለመዋዋል ፡ በሚነጋገረው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ የማታለልም ፡ ሆነ ፡ የማስገደድ ፡ ምልክት ፡ ሳይኖር ፡ ፈቃድን ፡ የመስጠት ፡ ነፃነት ፡ መኖር ፡ አለበት ።

፬/ ውሎች ፡ ከኢንተርናሲዮናል ፡ ሕግ ፡ ጋር ፡ ተስማሚ ፡ ከመሆናቸውም ፡ ሌላ ፡ የሦስተኛ ፡ ሀገርን ፡ መብት ፡ መንካት ፡ የለባቸውም ።[22]

ይሁንና ፡ ውሎች ፡ ኢንተርናሲዮናል ፡ የሆነ ፡ ዋጋ ፡ ያላቸው ፡ ስለመሆናቸውና ስምምነት ፡ በመዋዋል ፡ ረገድም ፡ ስላለው ፡ የሥልጣን ፡ ችሎታ ፡ የተለያዩ ፡ ሀሳቦች ፡ ያሏቸው ፡ ሁለት ፡ የሊቃውንት ፡ ምድቦች ፡ አሉ ። ፕሮፌሰር ፡ ብሪግስ ፡ ሊቃውንቱ ፡ የሚለያዩባቸውን ፡ ሁለት ፡ ሀሳቦች ፡ ከሥረ ፡ ምንጩ ፡ ጠቅሰው ፡ እንደሚከተለው ፡ ጽፈዋል ።

እንደ ፡ ሀርቫርድ ፡ ምርምር ፡ በኢንተርናሲዮናል ፡ ሕግ ፡ ሊቅነታቸው ፡ የታወቀላቸው ፡ የምሁራን ፡ አሳብ ፡ --- ፤[23] ውሎች ፡ ኢንተርናሺናል ፡ ዋጋ ፡ እንዳላቸው ፡ የሚወሰነው ፡ በኢንተርናሲዮናል ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ መሆኑን ፡ የሚያመለክቱ ፡ ብዙ ፡ ባሕረ ፡ ሀሳቦች ፡ አሉ ። አንድ ፡ ሀገር ፡ ስምምነት ፡ የመዋዋልን ፡ ሥልጣኑን ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ውስጥ ፡ ገደብ ፡ አበጅቶ ፡ ቢወስነውና ፡ ሁኔታም ፡ ቢያበጅለት ፤ እንደዚህ ፡ ያሉት ፡ ወሳኝ ፡ አንቀጾች ፡ ኢንተርናሲዮናል ፡ የሆነ ፡ ታዋቂነት ፡ የላቸውም ። ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ስምምነት ፡ የመዋዋልን ፡ ሥልጣን ፡ በሚሰጣቸው ፡ ክፍሎች ፡ የተደረጉ ፡ ስምምነቶች ፡ ሁሉ ፡ ከተሰጠው ፡ ሥልጣን ፡ ክልል ፡ ውጭ ፡ ቢፈጸሙም ፡ እንኳ ፡ እንደ ፡ ኢንተርናሲዮናል ፡ ግዴታዎች ፡ ሆነው ፡ አስገዳጅነት ፡ አላቸው ።

በዚህም ፡ አንፃር ፤ የነዚሁኑ ፡ ያህል ፡ ታዋቂነት ፡ ያላቸው ፡ ሌሎች ፡ ምሁራን ፡ እንደሚሉት ፡ — ፡[24] ፤ ውሎች ፡ ኢንተርናሲዮናላዊ ፡ ዋጋ ፡ እንዳላቸውና ፡ ተዋዋይ ፡ ባለሥልጣኖችም ፡ ለመዋዋል ፡ በቂ ፡ ችሎታ ፡ (ሥልጣን) ፡ ያላቸው ፡ መሆኑ ፡ በከፊልም ፡ ቢሆን ፡ የሚወሰነው ፡ በተዋዋይዎቹ ፡ ሀገሮች ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ መሠረት ፡ ስለሆነ ፤ የኢንተርናሲዮናል ፡ ሕግም ፡ ይህ ፡ አግባብ ፡ ያለው ፡ ሆኖ ፡ መቆጠር ፡ እንደሚገባው ፡ ተገንዝበታል ። አንድ ፡ ሀገር ፡ ለመዋዋል ፡ በሚነጋገርበት ፡ ወቅት ፤ ስለሌለኛው ፡ ሀገር ፡ ተዋዋይ ፡ የመዋዋል ፡ ችሎታ ፡ (ሥልጣን ፡ መጠንና ፡ ገደብ) ፡ ጠቃሚ ፡ መረጃዎችን ፡ በመሰብሰብ ፡ ማረጋገጥ ፡ መብቱና ፡ ግዴታው ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ሕገ፡ መንግሥቱን ፡ በመቃረን ፡ ወይም ፡ ከተዋዋይዎቹ፡ ባለሥልጣ

22. ፍሬደሪክ ፡ ኤል ፡ ሹማን ፤ ኢንተርናሽናል ፡ ፖለቲክስ ፡ (፯ኛ ፡ እትም ፡ ፲፱፻፶፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡) ገጽ ፡ ፩፻፳፮ ፡

23. የሊቃውንቱ ፡ ስም ፡ ተትቶአል ።

24. የደራሲዎቹ ፡ ስም ፡ ተትቶአል ።

ኖች ፡ ችሎታ ፡ (ሥልጣን) ፡ ማጣት ፡ የተነሳ ፡ ባልተሰጡት ፡ ሥልጣን ፡ ወይም ፡ ሥል ጣናቸው ፡ ከሚፈቅድላቸው ፡ ውጭ ፡ የተደረገ ፡ ስምምነት ፡ ዋጋ ፡ የሌለውና ፡ የማያ ገለግል ፡ ሆኖ ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ በተጣሰበት ፡ ሀገር ፡ ላይ ፡ አስገዳጅነት ፡ አይኖረ ውም ።[25]

ይኸው ፡ ሥርወ ፡ ምንጭ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ሀገሮች ፡ ያለውን ፡ ባሕረ ፡ ሐሳብ ፣ ልምድና ፡ የሕግ ፡ ሳይንስ ፡ ከመረመረ ፡ በኋላ ፡ የሀርቫርድ ፡ ምርምር ፡ የሚከተለውን ፡ ማጠቃለያ ፡ አሳብ ፡ ይሰጣል ። "ባጭሩ ፡ ከቀረበው ፡ ባሕረ ፡ ሀሳብ ፣ ልምድና ፡ የሕግ ፡ ሳይንስ ፡ በግልጽ ፡ መረዳት ፡ እንደሚቻለው ፡ የአብዛኞቹ ፡ ሊቃውንት ፡ ሀሳብ ፡ አዝ ማሚያ ፡ የሚከተሉትን ፡ አስተያየቶች ፡ ወደ ፡ መደገፉ ፡ ያዘነበለ ፡ ይመስላል ።

፩/ የአንድ ፡ ሀገር ፡ የውል ፡ ተዋዋይ ፡ ክፍሎች ፡ ሥልጣን ፡ (ችሎታ) ፡ የሚወ ሰነው ፡ በዚያው ፡ ሀገር ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ነው ።

፪/ በአንድ ፡ ሀገር ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ሥልጣን ፡ ሳይሰጣቸው ፡ ያንን ፡ ሀገር ፡ ወክሎ ፡ ተዋዋይ ፡ በመሆን ፡ የተደረጉ ፡ ውሎች ፣ በዚያ ፡ ሀገር ፡ ላይ ፡ ተፈ ጻሚ ፡ የመሆን ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ አስገዳጅነት ፡ የላቸውም" ።[26]

የዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ደራሲ ፡ ግን ፡ የሀርቫርድ ፡ ምርምር ፡ በሰጠው ፡ ማጠቃለያ ፡ አሳብ ፡ ባለመስማማት ፣ ሀሳባቸው ፡ በመጀመሪያ ፡ የተጠቀሰውን ፡ የሊቃውንት ፡ ምድብ ፡ ፈለግ ፡ በመከተል ፣ ለተዋዋይዎቹ ፡ ክፍሎች ፡ የሀገሩ ፡ ሕግ ፡ በቂ ፡ ሥልጣን ፡ ሳይሰጣቸው ፡ አንድን ፡ ሀገር ፡ በመወከል ፡ የሚያደርጉት ፡ ውል ፡ (ይህም ፡ ማለት ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊን ፡ ገደብ ፡ በማለፍ ፡ የተደረገ ፡ ውል) ፣ ምንም ፡ እንኳን ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ በተጣሰበት ፡ ሀገር ፡ ውስጥ ፡ ተፈጻሚነት ፡ ባይኖረው ፣ ለኢንተርናሲዮ ናል ፡ ውሎችና ፡ ስምምነቶች ፡ ጽናትና ፡ መከበር ፡ ሲባል ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ የኢንተር ናሲዮናል ፡ አስገዳጅነት ፡ እንዲኖረው ፡ ይገባል ፡ ይላል ።

ስለዚሁም ፡ ጉዳይ ፡ በሪስቴትሜንት ፡ አፍ ፡ ዘ ፡ ሎው ፡ ክፍል ፡ ፩፻፳፯ ፡ ስለ ውጭ ፡ ሀገር ፡ ሕግ ፡ የተጻፈው ፡ ማብራሪያ ፡ በከፊል ፡ እንዲህ ፡ ይላል ።

"የኢንተርናሲዮናል ፡ ግንኙነት ፡ ተግባራዊ ፡ ሁኔታዎች ፡ በአንድ ፡ ሀገር ፡ ስም ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ስምምነት ፡ የሚዋዋል ፡ ባለሥልጣን ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱን፡ ወይም ፡ የሀገሩን ፡ ሥልጣን ፡ በመተላለፍ ፡ ያደረገው ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ስምምነት፡ በዚሁ ፡ ሀገር ፡ ላይ ፡ አይጸናም ፡ የሚለው ፡ አስተያየት ፡ ተቀባይነት ፡ እንዳይኖረው ፡ ያደርጋል" ።[27]

ከዚህም ፡ የተነሳ ፣ ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ውል ፡ የመዋዋል ፡ ሥልጣን ፡ በሚሰ ጣቸው ፡ ክፍሎች ፡ በኢትዮጵያ ፡ ስም ፡ የተደረገው ፡ ውል ፡ የተፈጸመው ፡ ከተሰጣቸው፡ ሥልጣን ፡ ውጭ ፡ ከሆነ ፡ የአስገዳጅነት ፡ ኃይል ፡ ኖሮት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ዘንድ ፡ ተፈጻሚ ፡ አይሆንም ። ይሁን ፡ እንጂ ፣ ሌላኛው ፡ ተዋዋይ ፡ ሀገር ፡ በኢትዮጵያ ፡ ስም ፡ የተዋዋለው ፡ መልእክተኛ ፡ ያደረገው ፡ ስምምነት ፡ ከሥልጣኑ ፡ ውጭ ፡ መሆኑን ፡ ካላወቀ ፡ በቀር ፣ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡

25. ሄርበርት ፡ ደብሊዩ ፡ ብሪግስ ፣ ዘ ፡ ሎው ፡ አፍ ፡ ኔሽንስ ፡ (፪ኛ ፡ እትም ፡ ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡) ገጽ ፡ ፫፻፵፯፡

26. ከዚያው ፡ ገጽ ፡ ፫፻፵፯ ፡

27. ዘ ፡ አሜሪካን ፡ ሎው ፡ ኢንስቲትዩት ፡ ሪስቲትሜንት ፡ አፍ ፡ ዘ ፡ ሎው ፣ ዘ ፡ ፎሪን ፡ ሪሌሽንስ ፡ ሎው፡ (፲፱፻፶፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡) ተራ ፡ ቍጥር ፡ ፩፻፳፯ ፡ ገጽ ፡ ፬፻፰፪ ፡

ኢንተርናሲዮናል ፡ የሆነ ፡ አስገዳጅነት ፡ ይኖረዋል ። ይህም ፡ ማለት ፡ በእንደዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ክርክር ፡ ቢነሳ ፡ በሀገሪቱ ፡ ላይ ፡ አስገዳጅነት ፡ እንዲኖረው ፡ የሀገሪቱ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ አያዝዙም ። ነገር ፡ ግን ፡ ክርክሩ ፡ የቀረበው ፡ ለኢንተርና ሲዮናል ፡ ሸንጎ ፡ ከሆነ ፡ የተባለው ፡ ሸንጎ ፡ በኢንተርናሲዮናል ፡ ሕጎችና ፡ ልምዶች ፡ መሠረት ፡ ውሉ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚነት ፡ ያለው ፡ ግዴታ ፡ እንዲሆን ፡ ለመወሰን ፡ ይችላል ።

በኢንተርናሲዮናል ፡ ሕግ ፡ ሊቅነታቸው ፡ የታወቀላቸው ፡ ፕሮፌሰር ፡ ቢሾፕ ፡ ከሐክስዎርዝስ ፡ ዳይጀስት ፡ ኦፍ ፡ ኢንተርናሺናል ፡ ሎው ፡ እንደጠቀሱት ፡ "በሀገሪቱ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ወይም ፡ በአስተዳደሩ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ተፈጻሚ ፡ እንዲሆን ፡ ትእዛዝ ፡ ሊሰጥበት ፡ ባይችልም ፡ እንኳ ፤ አንድ ፡ ውል ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ አስገዳጅነት ፡ እን ዳለው ፡ ሆኖ ፡ ሊኖር ፡ ይችላል ።"[28]

ስለዚህ ፡ አንድ ፡ ውል ፡ በሀገሪቱ ፡ ውስጥ ፡ ሊፈጸም ፡ ግዴታ ፡ ባይሆንም ፡ እንኳ ፤ በፓርላሜንቱም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በአስፈጻሚው ፡ ክፍል ፡ የወጣ ፡ ሕግ ፡ የኢትዮጵ ያን ፡ መንግሥት ፡ በዚያ ፡ ውል ፡ የተነሳ ፡ ከሚደርሱበት ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ግዴ ታዎች ፡ ሊያድነው ፡ አይችልም ። ይህም ፡ የሚሆንበት ፡ ምክንያቱ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ነው ።

ውል ፡ የመዋዋል ፡ ሥልጣን ፡ የሚገኘው ፡ ከሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ስለሆነ ፤ የአን ድን ፡ ሀገር ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ የሚጥስ ፡ ውል ፡ በዚያ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ተፈጻሚነት ፡ ሊኖረው ፡ አይችልም ። ስለዚህም ፡ አንድ ፡ ውል ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ የሚቃረን ፡ አንቀጽ ፡ የያዘ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ በሕግ ፡ አይፈቀድም ።

ሠ/ አንዳንድ ፡ ውሎችን ፡ ለማስፈጸም ፡ በሀገሩ ፡ ሕጎች ፡ መሠረት ፡ መደረግ ፡ ስለሚገባው ፡ ነገር ፤

ተጨማሪ ፡ ድርጊት ፡ ሳያስፈልጋቸው ፡ በቀጥታ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለመዋል ፡ በሚችሉትና ፡ በማይችሉት ፡ ውሎች ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ልዩነት ፡ በቅድሚያ ፡ ማመልከቱ ፡ ጠቃሚ ፡ ይሆናል ። ባይርድ ፡ በሚገባ ፡ እንዳመለከቱት ፤ በገዛ ፡ ራሱ ፡ ተፈጻሚ ፡ የሚሆን ፡ ውል ፡ አንቀጾች ፡ ተጨማሪ ፡ የሕግ ፡ ድጋፍ ፡ ሳያስፈልጋቸው ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለመ ዋል ፡ የሚችሉ ፡ ናቸው ። በቀጥታ ፡ ተፈጻሚ ፡ ስለመሆኑ ፡ ውሉ ፡ ምንም ፡ በማይገል ጽበት ፡ ጊዜ ፤ የውሉ ፡ ዓይነት ፡ በገዛ ፡ ራሱ ፡ ለመፈጸም ፡ የሚገባ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ሌላ ፡ ተጨማሪ ፡ የሕግ ፡ ድጋፍ ፡ ሳያሻው ፡ ውሉ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ እንደሚያዝ ፡ ሆኖ ፡ ትርጉም ፡ ይሰጠዋል ። በቀጥታ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ የመዋል ፡ ችሎታ ፡ የሌለው ፡ ውል ፡ ግን ፡ ተጨማሪ ፡ የሕግ ፡ ድጋፍ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ተመሳሳይ ፡ እርዳታ ፡ ካልተሰጠው ፡ በቀር ፡ ተፈጻሚ ፡ ሆኖ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለመዋል ፡ አይችልም ።[29]

ለተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፴ ፡ ገደብ ፡ በሚያበጀው ፡ "ይሁን ፡ እንጂ" ፡ በሚለው ፡ ንዑስ ፡ ዓረፍተ ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፡ የተዘረዘሩት ፡ ውሎች ፡ በኢት ዮጵያ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ ውሎቹ ፡ በፓርላማ ፡ የተፈቀዱበት ፡ የአዋጅ ፡ ድጋፍ ፡ እንዲኖራቸው ፡ ያሻል ።

---

28. ዊልያም ፡ ደብልዩ ፡ ቢሾፕ ፡ ጁኒየር ፡ ኢንተርናሽናል ፡ ሎው ፡ ኬስ ፡ ኤንድ ፡ ማቴሪያልስ ፡ (፪ኛ ፡ እትም ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡) ገጽ ፡ ፩፻፵፰ ፡
29. ኤልበርት ፡ ኤም ፡ ባይርድ ፡ ጁኒየር ፡ ትሪቲስ ፡ ኤንድ ፡ ኤክስኩቲቭ ፡ አግሪሜንትስ ፡ ኢን ፡ ዘ ፡ ዩናይትድ ፡ ስቴትስ ፡ (፲፱፻፶፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡) ገጽ ፡ ፪፻፪ ።

በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፴ ፡ በአምስተኛው ፡ ዓረፍተ ፡ ነገር ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ የፓርላሜንቱ ፡ መቀበል ፡ ሳያስፈልጋቸው ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ብቻ ፡ ስለሚያጸድቋቸው ፡ ውሎች ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፤ እነዚህን ፡ ውሎች ፡ የሚመለከት ፡ ክርክር ፡ በፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ቢነሳ ፡ ውሎችን ፡ እንደ ፡ ሕጋዊ ፡ አድርገው ፡ ለመውሰድ ፡ እንዲችሉ ፡ ይረዳቸው ፡ ዘንድ ፡ የአስፈጻሚው ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ ስለነዚሁ ፡ ውሎች ፡ ቢያወጣ ፡ የሚበጅ ፡ ይሆናል ።

ኢትዮጵያ ፡ ከመጀመሪያዎቹ ፡ ፈራሚ ፡ ሀገሮች ፡ አንዷ ፡ በመሆን ፡ የተቀበለችው፡ የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ድርጅት ፡ ቻርተር ፡ አንቀጽ ፡ ፶፭ ፡ እና ፡ ፶፮ ፡ በገዛ ፡ ራሳቸው ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለመዋል ፡ ለማይችሉት ፡ አናቅጻት ፡ ምሳሌዎች ፡ ሆነው ፡ ሊጠቀሱ ፡ ይችላሉ ። እነዚህ ፡ የቻርተሩ ፡ አናቅጻት ፡ ለያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ መብትና ፡ ግዴታ ፡ ሊፈጥሩ ፡ የሚችሉት ፡[30] በሥራ ፡ ላይ ፡ ለመዋል ፡ የሚያስችላቸው ፡ የሀገሩ ፡ ደጋፊ ፡ ሕግ ፡ የወጣላቸው ፡ እንደሆነ ፡ ብቻ፡ ነው ።[31] በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ (አንዳንድ) ፡ የሕገ ፡ መንግሥት ፡ አናቅጻት ፡ በኢንተርናሲዮናል ፡ ስምምነት ፡ ካልተደነገጉ ፡ በስተቀር ፡ አንዳንድ ፡ ድርጊቶች ፡ መደረግ ፡ የለባቸውም ፡ ይላሉ ። ለምሳሌ ፡ የተሻሻለው፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፶ ፡ "ሌላውን ፡ ሰው ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ስምምነት ፡ በሚፈቅደው ፡ መሠረት ፡ አኳኋን ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ለውጭ ፡ አገር ፡ አሳልፎ ፡ መስጠት ፡ አይቻልም" ፡ ሲል ፡ ይደነግጋል ።

በገዛ ፡ ራሳቸው ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለመዋል ፡ የሚችሉት ፡ ውሎች ፡ ግን ፡ ውጤት ፡ ለማስገኘት ፡ ወይም ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለመዋል ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ ተጨማሪ ፡ የሕግ ፡ ድጋፍ ፡ አያስፈልጋቸውም ።

ክፍል ፡ ፪ ፤

የውሎች ፡ የበላይ ፡ ሕግነትና ፡ የሚያስከትሉት ፡ ውጤት ፤

ዋጋ ፡ ሊያሰጡት ፡ የሚያስችሉትን ፡ አስፈላጊ ፡ ነገሮች ፡ አሟልቶ ፡ የያዘና ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ በሚያዘው ፡ መሠረት ፡ የተፈጸመ ፤ ኢትዮጵያ ፡ ተካፋይ ፡ የሆነችበት ፡ አንድ ፡ ውል ፡ በአንቀጽ ፡ ፩፻፳፪ ፡ መሠረት ፡ የበላይ ፡ ሕግ ፡ ሁኖ ፡ በሀገሪቱ ፡ ውስጥ ፡ ተፈጻሚነት ፡ ይኖረዋል ።

በጊዜው ፡ ጸንተው ፡ የነበሩትን ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ውሎች ፡ ስምምነቶችና ፡ ግዴታዎች ፡ የ፲፱፻፵፭ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ቁጥር ፡ ፮ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ የበላይ ፡ ሕግ ፡ አካል ፡ ስለሚያደርጋቸው ፡[32] የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ከመውጣቱ ፡ በፊት ፡ የተደረጉትም ፡ ውሎች ፡ ተፈጻሚነት ፡ አላቸው ። ከዚህም ፡ ትእዛዝ ፡ ወሰን ፡ በኋላ ፡ ስለ ፡ ሕዝባዊ ፡ መብት ፡ በወጣው ፡ የ፲፱፻፵፰ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረቱ ፡ አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፴፱ ፡ እንዲሰፋ ፡ ተደርጓል ። አዋጁም ፡ አሁን ፡ የሚገ

30. ብራየርሊ ፤ እላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፲፯ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፩፻፲፯ ፡ ይመለከቷል ።

31. ውልን ፡ የሚያሟላ ፡ ሕግ ፡ ማለት ፡ ራሱን ፡ በራሱ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ የማይችልና ፡ ስምምነት ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ ውሉም ፡ ውጤት ፡ እንዲያስገኝ ፡ ለማድረግ ፡ የሚወጣ ፡ ሕግ ፡ ነው ።

32. የኤርትራን ፡ ግዛት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ በፌዴሬሽን ፡ የመቀላቀልና ፡ የመጨመር ፡ የ፲፱፻፵፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ትእዛዝ ፡ ቁጥር ፡ ፮ ፡ አንቀጽ ፡ ፫ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፲፪ኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፩ ፡

ኙት ፡ ውሎች ፤ የኢንተርናሲዮናል ፡ ስምምነቶችና ፡ ግዴታዎች ፡ ወደፊት ፡ በሚደ ረጉ ፡ ወይም ፡ በሚጸድቁ ፡ ውሎች ፤ የኢንተርናሲዮናል ፡ ስምምነቶችና ፡ ግዴታዎች ፡ እንዲሁም ፡ በአስፈጻሚው ፡ ክፍል ፡ በተደረጉ ፡ ስምምነቶች ፡[33] ላይ ፡ ተጨምረው ፡ የን ጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ የበላይ ፡ ሕግ ፡ በመሆን ፡ ተፈጻሚነት ፡ አላቸው ፡[34] በማ ለት ፡ ይደነግጋል ። ሆኖም ፡ ወደፊት ፡ እንደሚገለጸው ፡ ሁሉ ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መን ግሥት ፡ ከመውጣቱ ፡ በፊት ፡ የተደረጉትም ፡ ሆኑ ፡ ወይም ፡ የጸደቁት ፡ ውሎች ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ ከተደረጉት ፡ ውሎች ፡ ጋር ፡ በበላይ ፡ ሕግነት ፡ ረገድ ፡ ተመሳሳይ ፡ ደረጃ ፤ የላቸውም ።

ሀ/ <u>የሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፳፪ ፡ ትንታኔ ፤</u>

የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፳፪ ፡ የእንግሊዝኛው ፡ ጽሑፍ ፡ ወደ ፡ አማርኛ ፡ ሲተረጎም ፡ እንዲህ ፡ ይላል ።

"የአሁኑ ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ <u>ኢትዮጵያ ፡ ተካፋይ ፡ ከምትሆንባ ቸው ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ውሎች ፤ ስምምነቶችና ፡ ግዴታዎች ፡ ጋር ፡ የንጉሠ ፡ ነገ ሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ የበላይ ፡ ሕግ ፡ ስለሚሆኑ</u> ፡ ወደፊትም ፡ የሚወጡ ፡ ሕጎች ፡ (አዋጆች) ፤ ድንጋጌዎች ፤ ትእዛዞች ፤ ፍርዶች ፤ ውሳኔዎችና ፡ ድርጊቶች ፡ ሁሉ ፡ ከዚህ ፡ ሕገ ፡ መንግሥትና ፡ ኢትዮጵያ ፡ ተካፋይ ፡ ከምትሆንባቸው ፡ የኢንተርናሲዮ ናል ፡ ውሎች ፤ ስምምነቶችና ፡ ግዴታዎች ፡ ጋር ፡ የማይስማሙ ፡ ሆነው ፡ ሲገኙ ፡ ዋጋ ፡ የሌላቸውና ፡ የማያገለግሉ ፡ ይሆናሉ ። (አንክሮው ፡ የደራሲው ፡ ነው) ።

በመጀመሪያ ፡ በአማርኛ ፡ የተጻፈው ፡ የዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ጽሑፍ ፡ ከእንግሊዝ ኛው ፡ የሚለይ ፡ መሆኑን ፡ ማስተዋል ፡ ያሻል ። የሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፳፪፡ የአማርኛ ፡ ጽሑፍ ፡ እንደሚከተለው ፡ ይነበባል ።

"ይህ ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ተካፋይ ፡ ከምትሆንባቸው ፡ ከኢንተርናሲዮናል ፡ ውሎች ፡ ከዓለም ፡ ስምምነቶችና ፡ ግዴታዎች ፡ ጋራ ፡ ባንድነት ፡ ሆኖ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ የበላይ ፡ ሕግ ፡ ይሆናል ። ወደፊትም ፡ የሚ ሠሩ ፡ ሕጎች ፡ ድንጋጌዎች ፡ ውሳኔዎች ፡ ሁሉ ፡ ከዚህ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ጋር ፡ የማ ይስማሙ ፡ ሲሆኑ ፡ ዋጋ ፡ የሌላቸውና ፡ የማያገለግሉ ፡ ይሆናሉ ።"

በዓረፍተ ፡ ነገር ፡ አሰካክ ፡ ረገድ ፡ የእንግሊዝኛው ፡ ጽሑፍ ፡ እንደ ፡ አማርኛው ፡ በሁለት ፡ አጫጭር ፡ ዓረፍተ ፡ ነገሮች ፡ ሳይሆን ፡ በአንድ ፡ ረጅም ፡ ዓረፍተ ፡ ነገር ፡ በመቅረቡ ፡ ረገድ ፡ ካለው ፡ ልዩነት ፡ ሌላ ፤ በሁለቱ ፡ ጽሑፎች ፡ መካከል ፡ ያሉት ፡ ልዩነቶች ፡ የሚቀጥሉት ፡ ናቸው ።

፩/ የእንግሊዝኛው ፡ ጽሑፍ ፡ "የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት" ፡ እና ፡ "የኢንተርናሲዮናል ፡ ስምምነቶች" ፡ ሲል ፡ አማርኛው ፡ በነዚሁ ፡ ሐረጎች ፡ ምፍራ ፡ "የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት" ፡ እና ፡ "የዓለም ፡ ስምምነቶች"፡ ይላል ።

---

33. የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት አንቀጽ ፡ ፩፻፳፪ ፤ በ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ፡ም ፡ እንደወጣው ፡ የሕዝባዊ ፡ መብ ት ፡ አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፵፱ ፡ አንቀጽ ፡ ፩ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ የበላይ ሕግ ፡ ይሆናሉ ፡ ከሚላቸው ፡ የውሎች ፡ ዓይነት ፡ ዝርዝር ፡ ውስጥ ፡ "በመንግሥቱ ፡ የአስፈጻሚው ፡ ክፍል ፡ የተደረጉ ትን ፡ ስምምነቶች" ፡ (Executive Agreements) ፡ የማይጨምር ፡ መሆኑን ፡ መገንዘብ ያሻል ።

34. በ፲፱፻፵፯ ዓ·ም ፡ ስለ ፡ ሕዝብ መብት ፡ የወጣ ፡ አዋጅ ፤ ቁጥር ፡ ፩፻፵፱ ፡ አንቀጽ ፡ ፩ ፡ <u>ነጋሪት ፡ ጋዜጣ</u> ፲፭ኛ ፡ ዓመት ቁጥር ፡ ፪ ፡

፪/ "ትእዛዞች" ፡ እና ፡ "ድርጊቶች" ፡ የሚሉት ፡ የሕግ ፡ ቃላት ፡ በአማርኛው ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ጨርሶ ፡ የሉም ።

፫/ "ከእነዚህም ፡ ጋር" ፡ (therewith) የሚለው ፡ የአነጋገር ፡ ስልት ፡ በእንግ ሊዝኛው ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ የገባው ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱንና ፡ ውሎችን ፡ ለማመልከት ፡ ሲሆን ፤ በዚሁ ፡ አንጻር ፡ የአማርኛው ፡ ሐረግ ፡ "ከዚህ ፡ ሕገ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ የማይስማሙ ፡ ሲሆኑ" ፡ የሚል ፡ ነው ። ይህም ፡ የመ ጨረሻው ፡ ልዩነት ፡ ወደፊት ፡ እንደሚገለጸው ፡ በሁለቱ ፡ ጽሑፎች ፡ መካ ከል ፡ ትልቅ ፡ ልዩነትን ፡ ይፈጥራል ።

<u>ለ/ በአንቀጽ ፡ ፩፻፳፪ ፡ ውስጥ ፡ ስላሉት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቃላት ፡ ትርጉም ፤</u>

፩/ በመጀመሪያ ፡ "ኢንተርናሲዮናል" ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ የሚያመለክተው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከሌላ ፡ ሀገር ፡ ወይም ፡ ሀገሮች ፡ ወይም ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ድርጅቶች ፡ ጋራ ፡ ያደረገችውን ፡ ውል ፡ ስምምነት ፡ ወይም ፡ ግዴታ ፡ ሲሆን ፤ ሁለተኛም ፡ እን ደነዚህ ፡ ያሉት ፡ ውሎች ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ የሚውሉት ፡ በኢንተርናሲዮናል ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ መሆኑን ፡ ነው ።

፪/ "ውል" ፡ በሁለት ፡ ወይም ፡ ከሁለት ፡ በበለጡ ፡ አገሮች ፡ ወይም ፡ የኢንተ ርናሲዮናል ፡ ድርጅቶች ፡ መካከል ፡ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ባላቸው ፡ እንደራሴዎቻቸው ፡ ተፈርሞ ፡ በመካከላቸው ፡ ግንኙነትና ፡ ግዴታን ፡ በመፍጠር ፡ የተዋዋዮዎቹ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ በሚያዘው ፡ መሠረት ፡ በከፍተኛዎቹ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ጸድቆ ፡ በጽሑፍ የሰፈረ ፡ ስምምነት ፡ ነው ።

እዚህ ፡ ላይ ፡ የኰንሴሲዮን ፡ ውል ፡ በአንድ ፡ ሀገርና ፡ በሌላ ፡ ሀገር ፡ ወይም ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ድርጅት ፡ መካከል ፡ የሚደረግ ፡ ውል ፡ ሳይሆን ፤ በአንድ ፡ ሀገ ርና ፡ አንድ ፡ ገንዘቡን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ በሚፈልግ ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ኩባንያ ፡ መካከል ፡ የሚደረግ ፡ ውል ፡ በመሆኑ ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ስምምነት ፡ አለመሆኑን ፡ መገንዘብ ፡ ያሻል ።[35] ከዚህም ፡ የተነሳ ፡ ቁጥራቸው ፡ በጣም ፡ አነስተኛ ፡ ከሆኑ ፡ የተለዩ ፡ ጉዳዮች ፡ በቀር ፡ አንድ ፡ የኰንሴሲዮን ፡ ውል ፡ በጠቅላላው ፡ በኢንተርናሲ ዮናል ፡ ሕግም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ከዚያ ፡ ውስጥ ፡ በውል ፡ ሕግ ፡ ሳይሆን ፡ በተዋዋዩ ፡ ሀገር ፡ መንግሥት ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የሚወሰን ፡ ይሆናል ።

፫/ "ስምምነት" ፡ (ኮንቬንሺን) ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ በብዙ ፡ ተዋዋዮች ፡ ወይም ፡ በሁለት ፡ ተዋዋዮች ፡ መካከል ፡ የሚደረግ ፡ ጠባዩ ፡ ቴክኒካል ፡ የሆነ ፡ ስምምነትን ፡ ወይም ፡ ባንዳንድ ፡ የተለዩ ፡ የሥራ ፡ መስኮች ፡ በሀገሮች ፡ መካ ከል ፡ ያለውን ፡ ግንኙነት ፡ የሚወስነው ፡ የውል ፡ ዓይነት ፡ ነው ። ይህንኑ ፡ በመደገፍ፡ ማየርስ ፡ እንዲህ ፡ ሲሉ ፡ ጽፈዋል ።

"ስምምነት ፡ (ኮንቬንሺን) ፡ በብዙ ፡ ድርጅቶች ፡ መካከል ፡ የአንድ ፡ ሰፊ ፡ አር እስት ፡ አካል ፡ ስለሆነ ፡ የተለየ ፡ ጉዳይ ፡ የሚመለከት ፡ ሰነድ ፡ መደበኛ ፡ ስም ፡ ሆኗል"[36] ። ስለዚህ ፡ ይህ ፡ ቃል ፡- ፩/ በብዙ ፡ ተዋዋዮች ፡ መካከል ፡ የተደረጉ ፡ የሕግ ፡ መሥራች ፡ ውሎችን ፤ ፪/ በዓለም ፡ መንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ ወይም ፡ በተባበሩት ፡

---

35. ኤን ፡ ማርች ፡ ሐኒንግስ ፤ <u>ኢንተርናሽናል ፡ ሎው ፡</u> <u>ኢን ፡ ኤ ፡ ነትሺል</u> ፡ (፲፱፻፶፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡) ገጽ ፡ ፵፮ ።

36. ዴኒስ ፡ ፒ ፡ ማየርስ ፡ "የውሎች ፡ ስምና ፡ ወሰን" ፡ <u>አሜሪካን ፡ ጂርናል ፡ አፍ ፡ ኢንተርናሽናል ፡ ሎው ፡</u> ፶፩ኛ ፡ ቮልዩም ፡ (፲፱፻፶፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡) ገጽ ፡ ፭፻፸፮ ።

መንግሥታት ፡ ድርጅት ፡ አማካይነት ፡ የተደረጉ ፡ ውሎችን ፤ ፫/ በኢንተርናሲዮናል ፡ የሠራተኞች ፡ ድርጅትና ፡ በኢንተርናሲዮናል ፡ ቀይ ፡ መስቀል ፡ ድርጅቶች ፡ ተደራዳሪነት ፡ የተደረጉትን ፡ እንደነገሩ ፡ ሁኔታ ፡ የሠራተኞችና ፡ የቀይ ፡ መስቀል ፡ ስምምነቶችን ፡ ያጠቃልላል ።

፬/ "ግዴታ" ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ሁለት ፡ ትርጉም ፡ ሊኖረው ፡ ይችላል ። ሰፋ ባለ ፡ ትርጓሜው ፡ ሲገባ ፤ ኢትዮጵያ ፡ በኢንተርናሲዮናል ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ማክበር ፡ የሚገባትን ፡ (ያለባትን) ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ግዴታዎች ፡ ይመለከታል ።[37] ስለዚህም ፡ በተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ የጸጥታው ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ውሳኔ ፡ መሠረት ፡ ወታደሮችን ፡ ወደ ፡ ኮሪያና ፡ ኮንጎ ፡ መላክ ፤ የኢንተርናሲዮናል ፡ ሕግን ፡ ማክበርና ፡ የመሳሰሉትን ፡ ግዴታዎች ጠብቆ ፡ መገኘቱ ፡ ለዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ ግዴታ ፡ ምሳሌ ፡ ሆነው ፡ ይጠቀሳሉ ።[38] ጠበብ ፡ ባለው ፡ አባባል ፡ ሲገባ ፡ ደግሞ ፤ ኢትዮጵያ ፡ የገባችባቸውን ፡ የውል ፡ ሁኔታዎች ፡ ወይም ፡ የውል ፡ ግዴታዎች ፡ ያመለክታል ። ለዚሁም ፡ ዓይነቱ ፡ አገባብ ፡ ብሔራዊ ፡ ብድርን ፡ በወቅቱ ፡ መክፈል ፡ ምሳሌ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።[39]

"ግዴታ" ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፳፪ ፡ ውስጥ ፡ የገባው ፡ ሰፋ ፡ ወይም ፡ ጠባብ ፡ ባለው ፡ ትርጓሜው ፡ መሆኑን ፡ ለመናገር ፡ ያስቸግራል ። ቢሆንም ፡ የዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ደራሲ ፡ ቃሉ ፡ የገባው ፡ ጠበብ ፡ ባለው ፡ ትርጓሜው ፡ ነው ፡ ባይ ፡ ነው ። በነገራችን ፡ ላይ ፤ "ግዴታ" ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ውሎችና ፡ ስምምነቶች[40] ፡ ሁሉ ፡ አስቀድመው ፡ መጽደቅ ፡ እንደሚገባቸው ፡ በሚያዝዘው ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ በአንቀጽ ፡ ፴ ፡ ውስጥ ፡ አልተጠቀሰም ።

"የኢንተርናሲዮናል ፡ ግዴታ" ፡ የሚለውን ፡ ሐረግ ፡ በሰፊው ፡ ትርጉሙ ፡ ለማስረዳት ፡ በቀሩት ፡ የሰለጠኑት ፡ ሀገሮች ፡ ያለው ፡ ልማዳዊ ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ሕግ ፡ በኢትዮጵያም ፡ ውስጥ ፡ ተፈጻሚ ፡ ስለመሆኑ ፡ ሰፊና ፡ ብርቱ ፡ ጥናት ፡ ማድረግ ፡ የሚያሻው ፤ ራሱን ፡ የቻለ ፡ ትልቅ ፡ አርእስት ፡ በመሆኑ ፤ ይህ ፡ ድርሰት ፡ እዚያ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ ለማብራራት ፡ አይቃጣም ። ስለዚህ ፡ "ግዴታ" ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ እዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ የገባው ፡ በጠባቡ ፡ ትርጓሜው ፡ ብቻ ፡ ነው ።

፭/ "የበላይ ፡ ሕግ" ፡ የሚለው ፡ ሐረግ ፡ የሚያመለክተው ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥትና ፡ በአንቀጽ ፡ ፩፻፳፪ ፡ እንደተመለከተው ፡ ውሎችም ፡ ጭምር ፡ በኢትዮጵያ ፡ የሕጎች ፡ ማዕረገ ፡ ድርገት ፡ አርከን ፡ ውስጥ ፡ የሕጎች ፡ ሁሉ ፡ የበላይ ፡ መሆናቸውንና ፡ ከእነርሱም ፡ ጋር ፡ የማይስማሙ ፡ ሕጎች ፡ ሁሉ ፡ ዋጋ ፡ የሌላቸውና ፡ የማያገለግሉ ፡ ሆነው ፡ እንዲፈርሱ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የሚያዝዙ ፡ መሆናቸውን ፡ ነው ።[41]

---

37. ቻርለስ ፡ ጂ ፡ ፌንዊክ ፤ ኢንተርናሽናል ፡ ሎው ፡ (፬ኛ ፡ እትም ፡ ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡) ገጽ ፡ ፩፻፲ ።

38. በ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የወጣው ፡ የባሕር ፡ አዋጅ ፤ ቁጥር ፡ ፩፻፵፯ ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፩ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፲፫ኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፩ ፡

39. እላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፱ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ትእዛዝ ፡ ፵፮ ፡ አንቀጽ ፡ ፳፰ ፡ (ሰ) ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፳፰ኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፳፫ ፡ ይመለከቷል ።

40. "የኢንተርናሲዮናል ፡ ስምምነት" ፡ የሚለው ፡ ስያሜ ፡ በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ በአንቀጽ ፡ ፴ ፡ እና ፡ ፶ ፡ እንደተመለከተው ፡ ሁሉ ፡ በአንቀጽ ፡ ፩፻፳፪ ፡ ውስጥ ፡ አልተመለከተም ።

41. አር ፡ ሲ ፡ ሚንስ ፤ " ፡ በመንግሥት ፡ የአስተዳደር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ የተወሰኑ ፡ ጉዳዮችን ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ እንደገና ፡ የማየት ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ የተደገፈ ፡ ሥልጣን ፡ መነሻ ፡ ጥያቄዎች" ፡ የኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ መጽሔት ፡ ፫ኛ ፡ ቮልዩም ፡ (፲፱፻፶፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡) ገጽ ፡ ፩፻፶፱ ፡

እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ቃላት ፡ ባንድነት ፡ ተጠቃለው ፡ ሲታዩ ፤ በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ መሠረት ፡ ተፈጽመው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ተካፋይ ፡ የምትሆንባቸው ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ውሎች ፤ ስምምነቶች ፡ ወይም ፡ ግዴታዎች ፡ ከሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ጋራ ፡ ባንድነት ፡ በኢትዮጵያ ፡ የሕጎች ፡ ማዕረገ ፡ ድርገት ፡ አርከን ፡ ውስጥ ፡ ለተራዎቹ ፡ ሕጎች ፡ የበላይ ፡ መሆናቸውን ፡ በግልጽ ፡ ያመለክታሉ ።[42]

ሐ/ የውል ፡ የበላይ ፡ ሕግነት ፡ ምርምር ፡ ውጤት ፤

በ፲፱፻፵፯ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረቱ ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ መሠረት ፡ የተፈጸሙ ፡ ውሎች ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ የበላይ ፡ ሕግ ፡ እንዲሆኑ ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ያዝዛል ።

ከዚህም ፡ በቀር ፡ በእንግሊዝኛው ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ስለበላይነት ፡ የሚናገረው ፡ ሐረግ ፤ ከሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ጋራ ፡ የማይስማሙ ፡ ወደፊት ፡ የሚወጡ ፡ ሕጎች ፡ (አዋጆች) ፤ ድንጋጌዎች ፤ ትእዛዞች ፤ ፍርዶች ፤ ውሳኔዎችና ፡ ድርጊቶች ፡[43] ሁሉ ፡ ዋጋ ፡ የሌላቸውና ፡ የማያገለግሉ ፡ መሆናቸውን ፡ በግልጽ ፡ ሲያዝ ፤ ከኢንተርናሲዮናል ፡ ውሎች ፡ ጋራም ፡ የማይስማሙቱ ፡ ይኸው ፡ እንደሚፈጸምባቸው ፡ በግልጽ ባይናገርም ፡ ግምት ፡ ለመውሰድ ፡ ይቻላል ። ይህም ፡ ማለት ፡ በመንግሥቱ ፡ የሕግ ፡ አውጪም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በአስፈጻሚው ፡ ክፍል ፡ የወጣ ፡ ማናቸውም ፡ ሕግ፡ (አዋጅ) ፡ በዳኝነትም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በአስተዳደሩ ፡ ክፍል ፡ የተሰጠ ፡ ማናቸውም፡ ውሳኔ ፡ ወይም ፡ ድርጊት ፡ ከዚህ ፡ የበላይ ፡ ሕግ ፡ ጋር ፡ የሚቃረን ፡ ሆኖ ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ ከጣሰ ፡ በሕገ ፡ መንግሥት ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ዋጋ ፡ የሌለውና ፡ የማያገለግል ፡ ይሆናል ። ሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ ይጥሳል ፡ ከተባለም ፡ የሕግ ፡ ኃይል ፡ኖሮት ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ በኢትዮጵያ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ትእዛዝ ፡ አይሰጥበትም ።

በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፤ በአንቀጽ ፡ ፩፻፳፪ ፡ የአማርኛው ፡ ጽሑፍ ፡ የበላይ ፡ ከሆነው ፡ ሕግ ፡ ጋራ ፡ የማይስማሙ ፡ ሆነው ፡ ሲገኙ ፡ ዋጋ ፡ የሌላቸውና ፡ የማያገለግሉ ፡ ስለሚሆኑት ፡ የሕጎችና ፡ (አዋጆች) ፡ የመንግሥት ፡ ድርጊቶች ፡ ዝርዝር ፡ ውስጥ ፡ "ትእዛዝ" ፡ እና ፡ "ድርጊት" ፡ ያልገቡ ፡ ስለሆነ ፤ በአማርኛው ፡ ጽሑፍ ፡ መሠረት ወደፊት ፡ የሚወጡ ፡ "ትእዛዞችና" ፡ ድርጊቶች ፡ ዋጋ ፡ የሌላቸውና ፡ የማያገለግሉ ፡ ተብለው ፡ ሊሻሩ ፡ አይችሉም ። በሁለቱ ፡ ጽሑፎች ፡ መካከል ፡ አለመስማማት ፡ ሲፈጠር ፡ አማርኛ ፡ በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፳፭ ፡ መሠረት ፡ የሀገሪቱ ፡ መደበኛ ፡ ቋንቋ ፡ ስለሆነ ፡ የአማርኛው ፡ ጽሑፍ ፡ ከእንግሊዝኛው ፡ ይልቅ ፡ ተቀባይነት ፡ ያለው ፡ መሆኑ ፡ እሙን ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፤ ይህ ፡ አስተሳሰብ ፡ ትክክለኛ ፡ ነው ፡ ሊባል ፡ አይችልም ። ሕጎች ፡ (አዋጆች) ፡ ድንጋጌዎች ፤ ፍርዶችና ፡ ውሳኔዎች ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ የበላይ ፡ ሕግ ፡ ጋራ ፡ የማይስማሙ ፡ ሲሆኑ ፡ ዋጋ ፡ የሌላቸውና ፡ የማያገለግሉ ፡ ይሆናሉ ፡ ከተባለ ፤ "ትእዛዞች" ፡ እና ፡ "ድርጊቶች" ፡ የበላዩን ፡ ሕግ ፡ እየጣሱ ፡ ፈራሽ ፡ የማይሆኑበት ፡ ምክንያት ፡ የለም ።

በእንግሊዝኛውና ፡ በአማርኛው ፡ ጽሑፍ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ልዩነት ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ከእንግሊዝኛ ፡ ወደ ፡ አማርኛ ፡ ሲተረጎም ፡ የተዘለለ ፡ ስለሚመስልና ፡

42. ጂ ፡ ክሸችኖቪች ፤ "በኢትዮጵያ ፡ የሕጎች ፡ ማዕረገ ፡ ድርገት ፡ አርከን ፡ ደረጃ" ፡ የኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ መጽሔት ፡ ፭ኛ ፡ ቦልዩም ፡ ፲፱፻፶፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ገጽ ፡ ፩፻፫ ፡

43. "ድርጊት" ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ በሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፳፪ ፡ የእንግሊዝኛው ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ፡ የገባው ፡ በአንድ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ግዴታ ፡ የሚያስከትሉትን ፡ የመንግሥትን ፡ አድራጎቶች ፡ ለማመልከት፡ ነው ።

አንቀጹንም ፡ በአንክሮ ፡ ሲያነቡት ፡ ትክክለኛ ፡ መስሎ ፡ የሚታየው ፡ የተዘለሉትን፡ ቃላት ፡ በአማርኛው ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ጨምሮ ፡ ማንበቡ ፡ ስለሆነ ፤ የዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ጸራሲ ፡ የአማርኛው ፡ ጽሑፍ ፡ የእንግሊዝኛው ፡ ጽሑፍ ፡ የሚያዝዘውን ፡ ሁሉ ፡ ጨምሮ ፡ እንደያዘ ፡ ሆኖ ፡ መነበብ ፡ አለበት ፡ ባይ ፡ ነው ።

ከዚህ ፡ ሌላ ፡ ቀደም ፡ ሲል ፡ እንደተገለጸው ፡ ሁሉ ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፳፪ ፡ በእንግሊዝኛው ፡ "ከነዚህም ፡ ጋራ ፡ የማይስማሙ" ፡ በሚለው ፡ ፋንታ ፡ አማርኛው ፡ የሚለው ፡ "ከዚህ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ የማይስማሙ" ፡ ስለሆነ ፤ በሁለቱ ፡ ጽሑፎች ፡ መካከል ፡ ሌላ ፡ ልዩነት ፡ አለ ።

በእንግሊዝኛው ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ የገባው ፡ "ከነዚህም ፡ ጋራ" ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱንና ፡ ውሎችን ፡ የሚያመለክት ፡ ይመስላል ። በሌላ ፡ በኩል ፡ ግን ፡ አማርኛው ፡ የሚጠቀምበት ፡ ሐረግ ፡ "ከዚህ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ የማይስማሙ---" ፡ ስለሚል ፤ ውሎቹን ፡ አይጨምርም ።

የምንነጋገርበት ፡ አንቀጽ ፡ በረጅምና ፡ ውስብስብ ፡ ዓረፍተ ፡ ነገር ፡ የተጻፈ ፡ በመሆኑ ፡ የተባለው ፡ መፋለስ ፡ ሊደርስ ፡ የቻለው ፡ በመጥፎ ፡ ትርጉም ፡ ምክንያት ፡ ነው ። በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፳፪ ፡ በሁለቱም ፤ ማለት ፡ በአማርኛውና ፡ በእንግሊዝኛውም ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፤ ሕገ ፡ መንግሥቱና ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ውሎች ፡ ባንድነት ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ የበላይ ፡ ሕግ ፡ እንዲሆኑ ፡ መታዘዙ ፤ የሕጎች ፡ ሁሉ ፡ የበላይ ፡ በመሆንና ፡ ወደፊትም ፡ በሚወጡ ፡ ብሔራዊ ፡ ሕጎች ፡ (አዋጆች) ፡ ላይ ፡ ገደብ ፡ በማበጀት ፡ ረገድ ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱና ፡ በውሎች ፡ መካከል ፡ የተፈጠረው ፡ ልዩነት ፡ በሕግ ፡ አውጪው ፡ ክፍል ፡ ታስቦ ፡ የተሠራ ፡ ሳይሆን ፤ "ከነዚህም ፡ ጋራ" ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ እንግሊዝኛው ፡ ወደ ፡ አማርኛ ፡ ሲተረጎም ፡ ከተደረገው ፡ ስህተት ፡ የተነሳ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ለመደምደም ፡ ያስችላል ። ያለበለዚያ ፡ ወደፊት ፡ የሚወጡ ፡ ሕጎች ፡ (አዋጆች) ፡ ድንጋጌዎች ፤ ትእዛዞች ፤ ፍርዶች ፤ ውሳኔዎችና ፡ ድርጊቶች ፡ ከነዚህ ፡ ጋራ ፡ (ከውሎች ፡ ጋራ) ፡ የማይስማሙ ፡ ሲሆኑ ፡ ዋጋ ፡ የሌላቸውና ፡ የማያገለግሉ ፡ ይሆናሉ ፡ ካልተባለ ፤ ውሎች ፡ የበላይ ፡ ሕግ ፡ አካል ፡ የሚሆኑበት ፡ ምክንያት ፡ የለም ።

"ከነዚህ ፡ ጋራ" የሚለው ፡ ልዩ ፡ የአነጋገር ፡ ስልት ፡ አገባቡ ፡ አሁን ፡ በምንነጋገርበት ፡ አንቀጽ ፡ የእንግሊዝኛው ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ እንደተመለከተው ፡ ሆኖ ፡ ሁለቱንም ፡ ዓይነት ፡ የበላይ ፡ ሕግ ፡ ማለት ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱንና ፡ ውሎችን ፡ ማመልከት አለበት ። የአንቀጹ ፡ ትክክለኛ ፡ ትርጉምና ፡ ስለ ፡ በላይነት ፡ የሚናገረው ፡ ክፍል ፡ ባሕረ ፡ ሀሳብ ፡ ወደዚህ ፡ መደምደሚያ ፡ አሳብ ፡ ያመራሉ ።

ስለውል ፡ በምንነጋገርበት ፡ ጊዜ ፡ "የማያገለግሉና ፡ ዋጋ ፡ የሌላቸው ፡ ይሆናሉ"፡ የሚሉት ፡ የአንቀጽ ፡ ፩፻፳፪ ፡ ቃላት ፡ የሚያመለክቱት ፡ ውሉ ፡ በሀገሪቱ ፡ ውስጥ ፡ ምንም ፡ ኃይልና ፡ ውጤት ፡ ወይም ፡ አስገዳጅነት ፡ የሌለው ፡ መሆኑን ፡ ነው ። ከዚህም ፡ ቀደም ፡ ሲል ፡ በተሰጠው ፡ ምክንያት ፡ መሠረት ፡ እነዚህ ፡ ውሎች ፡ የሚያስከትሉት፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ግዴታ ፡ የሚወሰነው ፡ በኢንተርናሲዮናል ፡ ሕግ ፡ ስለሆነ ፡ የተጠቀሰው ፡ አፍራሽ ፡ ሐረግ ፡ በውሉ ፡ ውስጥ ፡ የተመለከተውን ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ግዴታ ፡ አያስቀረውም ። ስለዚህ ፡ አንድ ፡ ውል ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ በመጣሱ ፡ በሀገሪቱ ፡ ውስጥ ፡ ዋጋ ፡ ቢስ ፡ ቢሆንም ፤ ይህ ፡ በቂ ፡ ሆኖ ፡ በኢንተርናሲዮናል ፡ መስክ፡ ዋጋ ፡ አያሳጣውም ። ኩሁን ፡ እንደሚሉት ፡ ለአንድ ፡ ውል ፡ ወሰንና ፡ ገደብ ፡ ሊሠ

ራለት ፡ የሚገባው ፡ በኢንተርናሲዮናል ፡ ሕግ ፡ በሚወሰነው ፡ እንጂ ፣ በብሔራዊ ፡ ሕግ ፡ ደረጃ ፡ መሆን ፡ የለበትም ።[44]

ባጭሩ ፡ የውል ፡ የበላይ ፡ ሕግነት ፡ ሲባል ፡ ሁለት ፡ ነገሮችን ፡ የግድ ፡ የሚጠቅስ ፡ መሆን ፡ ይኖርበታል ። በውሉ ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ የስምምነት ፡ ሁኔታዎች ፡ ከሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ በቀር ፡ ለቀሩት ፡ ሕጎች ፡ በሙሉ ፡ የበላይ ፡ ናቸው ፡ (ተቀዳሚነት ፡ አላቸው) ። ከዚህም ፡ በቀር ፡ የውል ፡ ሁኔታዎች ፡ ቀደም ፡ ሲል ፡ የወጡትን ፡ ብሔራዊ ፡ ሕጎችን ፡ በመሻር ፡ ብቻ ፡ ሳይቆጠቡ ፡ ወደፊት ፡ በሚወጡትም ፡ ብሔራዊ፡ ሕጎች ፡ ላይ ፡ ገደብ ፡ ይጥላሉ ፡ (ያበጃሉ) ። (ከገጽ ፡ ፫፻፺፬ ፡ እስከ ፡ ፫፻፺፯ ፡ ያለውን ፡ ይመለከቷል) ። እዚህ ፡ ላይ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ እንደ ፡ አምሳያው ፡ የአሜሪካን ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ሳይሆን ፣ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ከመውጣቱ ፡ (ማለት ፡ ከጥቅምት ፡ ፳፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፰) ፡ በፊት ፡ የተደረጉትን ፡ ውሎች ፡ የሀገሪቱ ፡ የበላይ ፡ ሕግ ፡ አካል ፡ አድርጎ ፡ የማይቆጥራቸው ፡ መሆኑን ፡ መገንዘብ ፡ ያስፈልጋል ።

ይህ ፡ አስተሳሰብ ፡ (ትርጉም) ፡ የተመሠረተው ፡ በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፳፪ ፡ ውስጥ ፡ ባለው ፡ በመጀመሪያው ፡ "ይሆናል" ፡ በሚለው ፡ ቃል ፡ ላይ ፡ ነው ።

በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፳፪ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ "ይሆናል" ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ የገባው ፡ በትንቢታዊ ፡ የአነጋገር ፡ ሥልት ፡ ስለሆነ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ የበላይ ፡ ሕግ ፡ አካል ፡ የሚሆኑት ፡ ከጥቅምት ፡ ፳፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ወዲህ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ያደረገቻቸው ፡ ወይም ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ የተቀበለቻቸው ፡ ውሎች ፡ ብቻ ፡ መሆን ፡ አለባቸው ፡ የሚል ፡ ትርጓሜ ፡ ሊሰጠው ፡ ይገባል ። "ይሆናል" ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ እዚህ ፡ የገባው ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሕግ ፡ ሲረቀቅ ፡ እንደሚደረገው ፡ በትእዛዛዊ ፡ አንቀጽ ፡ አይደለም ። በሌላም ፡ አገላለጽ ፡ ቀጥሎ ፡ በተሰጡት ፡ ምክንያቶች ፡ የቃሉ ፡ አገባብ ፡ ከጥቅምት ፡ ፳፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በፊት ፡ የተደረጉትን ፡ ውሎች ፡ አይጨምርም ።

ሀ/ በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ ጥርጣሬን ፡ ለማስወገድ ፡ ሲባል ፡ ላለፈ ፡ ነገር ፡ ወደፊት ፡ ውጤት ፡ ለማስገኘት ፡ ባስፈለገ ፡ ቁጥር ፡ በ "ይሆናል" ፡ ፋንታ ፡ በማከታተል ፡ "ነው" ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ገብቷል። ለምሳሌ ፡ በሕገ ፡ መንግሥት ፡ አናቅጻት ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፳፫ ፣ ፩፻፳፬ ፣ ፩፻፳፭ እና ፡ ፩፻፳፯ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ በሌሎች ፡ አናቅጻት ፡ ውስጥ ፡ አዘውትሮ ፡ የገባው ፡ "ይሆናል" ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ሳይሆን ፣ "ነው" ፡ የሚለው ፡ ትእዛዛዊ ፡ አንቀጽ ፡ ነው ። በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ሁኔታ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ እነዚያ ፡ አናቅጻት ፡ የሚያመለክቱት ፡ ያለፉ ፡ ሁኔታዎችን ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ ይረዳው ፡ ይሆናል ። አንቀጽ ፡ ፩፻፳፪ ፡ ከጥቅምት ፡ ፳፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በፊት ፡ ለነበሩትና ፡ ከዚያም ፡ ወዲህ ፡ ለተደረጉት ፡ ውሎች ፡ ተመሳሳይ ፡ ደረጃ ፡ እንዲሰጣቸው ፡ ተብሎ ፡ የታቀደ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ "ይሆናል" ፡ በሚለው ፡ ግሥ ፡ ፋንታ ፡ እላይ ፡ እተጠቀሱት ፡ አናቅጻት ፡ ውስጥ ፡ እንደታየው ፡ "ነው" ፡ የሚለው ፡ ግሥ ፡ በገባ ፡ ነበር ።

ለ/ የዚሁ ፡ አንቀጽ ፡ የአማርኛው ፡ ጽሑፍ ፡ በትንቢታዊ ፡ ሥልት ፡ በገባው ፡ "ይሆናል" ፡ በሚለው ፡ ቃል ፡ ይጠቀማል ። በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግ

44. አርተር ፡ ኬ ፡ ኩሁን ፣ "ስምምነት ፡ የመዋዋል ፡ ሥልጣንና ፡ የአንድ ፡ ሀገር ፡ የበላይ ፡ ገዢነት ፡ የተጠበቀ ፡ መብት" ፡ ኰሎምቢያ ፡ ሎው ፡ ሪቪው ፡ ፳፫ ፡ ቮልዩም ፡ (፲፱፻፳ ፡ ዓ ፡ ም ፡) ገጽ ፡ ፩፻፹፮ ።

ትሥ ፡ አንቀጽ ፡ ፩፱፵፰ ፡ መሠረት ፡ አማርኛ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ መደበኛ ፡ ቋንቋ ፡ በመሆኑ ፤ በአማርኛው ፡ ጽሑፍ ፡ የተመለከተው ፡ የመጀመሪያው ፡ "ይሆናል" ፡ የገባው ፡ በትእዛዛዊ ፡ አንቀጽ ፡ ሳይሆን ፡ ጊዜው ፡ ትንቢት ፡ በሆነ ፡ የአነጋገር ፡ ሥልት ፡ ነው ። ሆኖም ፡ ሁለተኛው ፡ "ይሆናል" ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ የገባው ፡ ቃሉ ፡ በትእዛዛዊ ፡ አንቀጽነት ፡ ባለው ፡ ትርጉም ፡ ነው ።

ሐ/ በሕጉ ፡ ውስጥ ፡ በቀጥታ ፡ ካልተገለጸ ፡ በቀር ፡ አንድ ፡ አዲስ ፡ የወጣ ፡ ሕግ ፡ (አዋጅ) ፡ ወደኋላ ፡ ተመልሶ ፡ ለመሥራት ፡ አለመቻሉ ፡ የተረጋገጠ ፡ የሕግ ፡ ደንብ ፡ ነው ። በዚህ ፡ መሠረት ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፩፱፵፰ ፡ በውስጠ ፡ ታዋቂነት ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ከመውጣቱ ፡ በፊት ፡ የተደረጉትን ፡ ውሎች ፡ ወደኋላ ፡ ተመልሶ ፡ የበላይ ፡ ሕግ ፡ አካል ፡ ሆነው ፡ እንዲቆጠሩ ፡ ያደርጋቸዋል ፡ ተብሎ ፡ ሊተረጎም ፡ አይገባም ።

መ/ በመጨረሻም ፡ የዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ደራሲ ፡ በሕግ ፡ አውጪው ፡ ክፍል ፡ ሆነ ፡ ተብሎ ፡ የተሠራ ፡ ነገር ፡ እንዳለ ፡ ለማወቅ ፡ ያደረገው ፡ የመጠያየቅ ፡ ጥናት ፡ ውጤት ፡ የአሁኑ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ከመውጣቱ ፡ በፊት ፡ ለተደረጉት ፡ ውሎች ፡ በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፩፱፵፰ ፡ አማካይነት ፡ የበላይ ፡ ሕግነት ፡ ደረጃ ፡ የመስጠት ፡ እቅድ ፡ እንዳለ ፣ አድርጎ ፡ የሚቆጥረውን ፡ አስተሳሰብ ፡ የማይደግፍ ፡ ሆኗል ።

ስለዚህ ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፩፱፵፰ ፡ የአሁኑ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ከመውጣቱ ፡ በፊት ፡ ለተደረጉት ፡ ውሎች ፡ የእኩልነት ፡ ደረጃን ፡ አይሰጣቸውም ። በሌላ ፡ አነጋገር ፤ ከተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አስቀድሞ ፡ የነበሩት ፡ ውሎች ፡---አሁን፡የሀገሪቱ ፡ (የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት) ፡ የበላይ ፡ ሕግ ፡ አይደሉም።

ይህም ፡ ቢሆን ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ከመውጣቱ ፡ በፊት ፡ የነበሩት፡ ውሎች ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ ከተደረጉት ፡ ውሎች ፡ ጋር ፡ የእኩልነት ፡ ደረጃ፡ የላቸውም፤ ማለት ፡ ኢትዮጵያ ፡ እነዚያ ፡ ውሎች ፡ የሚያስከትሉትን ፡ ግዴታ ፡ አታከብርም ፡ ማለት ፡ አይደለም ። እንዲያውም ፡ ዋጋ ፡ ሊያስጣቸው ፡ የሚችለውን ፡ ነገር ፡ አሟልተው ፡ ከያዙ ፡ ከሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ጋር ፡ የእኩልነት ፡ ደረጃ ፡ ባይኖራቸውም ፡ እንኳ ፤ የተሻሉ ፡ ሁኔታዎች ፡ ባሏቸው ፡ ውሎች ፡ እስከተተኩ ፡ ድረስ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ የሚሠሩና ፡ ለመፈጸምም ፡ አስገዳጅ ፡ እንደሆኑ ፡ ይቆያሉ ። ኢትዮጵያ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ካለ ፡ ሕጉዋ ፡ ጋር ፡ የማይስማማ ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፤ የውል ፡ ግዴታዎን ፡ የምታከብር ፡ ለመሆኗ ፡ በከሳሽ ፡ ተሰማ ፡ ወልደ ፡ ዮሐንስና ፡ በተከሳሾች ፡ ቫን ፡ ቤትቨስንና ፡ ጃክ ፡ ሔንሴል ፡ መካከል ፡ የነበረው ፡ ክርክር ፡[45] እንደማስረጃ ፡ ሆኖ ፡ ሊጠቀስ ፡ ይችላል ።

በተጠቀሰው ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ የአውራጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከሰጣቸው ፡ ውሳኔዎች፡ በተለይ ፡ ቀጥሎ ፡ የተጻፉት ፡ እዚህ ፡ የምርምር ፡ ጽሑፍ፡ ውስጥ ፡ የቀረቡትን ፡ ክርክሮች፡ በይበልጥ ፡ ያብራራሉ ።

፩/ ዋጋ ፡ የሚያሰጡትን ፡ ነገሮች ፡ አሟልቶ ፡ ከያዘ ፤ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ከመውጣቱ ፡ በፊት ፡ በመደረጉ ፡ የሀገሪቱ ፡ የበላይ ፡ ሕግ ፡

45. ተሰማ ፡ ወልደ ፡ ዮሐንስ ፡ ከሳሽ ፡ ቪ ፡ ጂ ፡ ቫን ፡ ቤትቨስንና ፡ ጃክ ፡ ሔንሴል ፡ ተከሳሽ ፡ (የአዲስ ፡ አበባ፡ አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ነገር ፡ ቁጥር ፡ ፫ሺ፫፻፱፱ ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡)

አካል ፡ ያልሆነ ፡ አንድ ፡ ውል ፡ በሚገባ ፡ እስካልተሻረ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ውል ፡ እስካልተተካ ፡ ድረስ ፡ መከበር ፡ አለበት ።

፪/ እንደዚህ ፡ ያሉትን ፡ ጉዳዮች ፡ ለመስማት ፡ ለአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የፍርድ ፡ ሥልጣንን ፡ ይሰጥ ፡ በነበረው ፡ በ፲፱፻፵፩ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረቱ ፡ የዳኝነት ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ አዋጅ ፡ ላይ ፡ ይህ ፡ ውል ፡ ቅድሚያን ፡ በማግኘቱ ፡ አንድ ፡ ውል ፡ በተራው ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ የበላይነት ፡ አለው ።

፫/ በ፲፱፻፵፫ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ቁጥር ፡ ፯ ፡ አንቀጽ ፡ ፳ ፡ እና ፡ በ፲፱፻፶፬ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረቱ ፡ አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፺፭ ፡ አንቀጽ ፡ ፩ ፡ መሠረት ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ከመውጣቱ ፡ በፊት ፡ ለተደረጉት ፡ ውሎች ፡ ተገቢውን ፡ ትርጉም ፡ በመስጠት ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውሉ ፡ ማድረግ ፡ አለባቸው ።

መ/ <u>በሀገሪቱ ፡ ሕግና ፡ በውሎች ፡ መካከል ፡ ስላለው ፡ ግንኙነት ፤</u>

የኢንተርናሲዮናል ፡ ሕግ ፤ ውልም ፡ ጭምር ፤ ከአንድ ፡ ሀገር ፡ ብሔራዊ ፡ ሕግ፡ ጋር ፡ የሚዋሐዱት ፡ በሁለት ፡ መንገድ ፡ ነው ። ይኸውም ፦

ሀ/ የሰለጠኑት ፡ ሀገሮች ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ወንጀል ፡ ነው ፡ ብለው ፡ የተስማሙባቸውን ፡ ድርጊቶች ፡ ቅጣት ፡ በ፲፱፻፵፱ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረቱ ፡ የኢትዮጵያ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ከ፪፻፹፩ ፡ እስከ ፡ ፪፻፺፭ ፡ ድረስ ፡ ባሉት ፡ ቁጥሮች ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ በብሔራዊው ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ በመጻፍ ፤

ለ/ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፳፪ ፡ እንደሚለው ፡ ዓይነት ፡ በሆነ ፡ አጠቃላይ ፡ አነጋገር ፡ ውሎችን ፡ ከብሔራዊው ፡ ሕግ ፡ ጋር ፡ በመቀላቀል ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፳፪ ፡ ከጥቅምት ፡ ፳፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ወዲህ ፡ የተደረጉትን ፡ ውሎች ፡ ከሀገሪቱ ፡ ብሔራዊ ፡ ሕግ ፡ ጋር ፡ ያዋህዳቸዋል ፡ ወይም ፡ የዚሁ ፡ አካል ፡ ያደርጋቸዋል ።

የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ከመውጣቱ ፡ በፊት ፡ የተደረጉት ፡ ውሎችም ፡ በ፲፱፻፵፫ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ቁጥር ፡ ፯ ፡ እና ፡ በ፲፱፻፶፬ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረቱ፡ አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፺፭ ፡ ከሀገሪቱ ፡ ሕግ ፡ ጋር ፡ ተዋህደዋል ።

ያለበለዚያ ፡ በነዚህ ፡ ውሎች ፡ ላይ ፡ ክርክር ፡ ቢነሳ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች፡ በነገሩ ፡ ገብተው ፡ ውሎችን ፡ ለማስፈጸም ፡ የሚያስችላቸው ፡ ሕጋዊ ፡ ድጋፍ ፡ አይኖራቸውም ። ይህንኑ ፡ በመደገፍ ፡ ካፕላንና ፡ ካትዜንባንክ ፦

"ብሔራዊ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የኢንተርናሲዮናልን ፡ ሕግ ፡ ተፈጻሚ ፡ የሚያደርጉበት ፡ ምክንያት ፡ ይህ ፡ ሕግ ፡ አንድም ፡ በብሔራዊ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ በመግባቱ ፤ አለዚያም ፡ ከብሔራዊ ፡ ሕግ ፡ ጋር ፡ በመዋሐዱ ፡ ብቻ ፡ ነው"[46] ፡ ሲሉ ፡ ጽፈዋል ።

---

46. ኤም ፡ ኤ ፡ ካፕላንና ፡ ዴብ ፡ ካትዜንባክ ፡ <u>ዘ ፡ ፖለቲካል ፡ ፋውንዴሺን ፡ አፍ ፡ ኢንተርናሽናል ፡ ሎው ፡</u> (፲፱፻፷፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡) ገጽ ፡ ፪፻፷፰ ፡

ክፍል ፡ ፫ ፤

በውሎች ፡ መካከል ፡ ስለሚኖር ፡ መጻረር ።

ሀ/ በሁለት ፡ ውሎች ፡ መካከል ፡ ስለሚኖር ፡ መጻረር ፤

ከኢንተርናሲዮናል ፡ ሕግ ፡ ሊቃውንት ፡ አንዱ ፡ ኬልሰን ፤ በውሎች ፡ መካከል ፡ ስለሚኖር ፡ መጻረር ፡ በጻፉት ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ እንዲህ ፡ ሲሉ ፡ ደምድመዋል ። "ሁለት ፡ ተጻራሪ ፡ ውሎች ፡ (ተዋዋዮቹ ፡ ሀገሮች ፡ እነዚያው ፡ ሁነው) ፡ በሁለት ፡ ተዋዋይ ፡ ወገኖች ፡ መካከል ፡ በሚደረጉበት ፡ ጊዜ ፡ ሌክስ ፡ ፖስትሪዮሪ ፡ ዴሮጋንት ፡ ፕራዮሪ ፡ የተባለው ፡ አጠቃላይ ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ደንብ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ይውላል። ይህም ፡ ደንብ ፡ "በአመጣጥ ፡ የኋለኛ ፡ የሆነው ፡ ውል ፡ የፊተኛውን ፡ ይሽረዋል" ፡ ይላል። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ለላይኛው ፡ ደንብ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ መሠረታዊ ፡ ሃሳብ ፡ ያለው ፡ የውል ፡ ስምምነት ፡ ሊመሠረት ፡ ይችላል ። ይኸውም ፡ ሌክስ ፡ ፕራዮሪ ፡ ዴሮጋንት ፡ ፖስትሪዮሪ ፡ የሚለው ፡ ደንብ ፡ ሲሆን ፤ እርሱም ፡ "ቀደም ፡ ሲል ፡ ሌላ ፡ ውል ፡ በተዋዋሉ ፡ ወገኖች ፡ መካከል ፡ ዳግመኛ ፡ የተደረገው ፡ ውል ፡ ከመጀመሪያው ፡ ውል ፡ ጋር ፡ የማይስማማ ፡ በሚሆንበት ፡ ጊዜ ፡ ባመጣጥ ፡ የኋለኛ ፡ የሆነው ፡ ውድቅ ፡ ይሆናል"[47] የሚል ፡ ነው ።

በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ደራሲም ፡ አስተሳሰብ ፡ ተጻራሪ ፡ የሆኑ ፡ ሁለት ፡ ውሎች ፡ በኢትዮጵያና ፡ ባንድ ፡ በሌላ ፡ ተዋዋይ ፡ ወገን ፡ መካከል ፡ ተደርገው ፡ ቢገኙ ፡ የኋለኛው ፡ ውል ፡ የፊተኛውን ፡ እንደሚሽረው ፡ ሊቆጠር ፡ ይገባል ።

ነገር ፡ ግን ፡ ሁለቱ ፡ ተጻራሪ ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ውሎች ፡ የተደረጉት ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ከልዩ ፡ ልዩ ፡ ሀገሮች ፡ ጋር ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ውጤቱ ፡ (ከላይኛው) ፡ የተለየ ፡ ይሆናል ።

ተጻራሪ ፡ ከሆኑ ፡ የውል ፡ ግዴታዎች ፡ ውስጥ ፡ ቅድሚያ ፡ መስጠት ፡ የሚገባቸው ፡ የትኞቹ ፡ እንደሆኑ ፡ ብሪግስ ፡ ሲጽፉ ፡-

"በሁለት ፡ ተዋዋይ ፡ ሀገሮች ፡ መካከል ፡ የሚደረግ ፡ ውል ፡ ከነዚሁ ፡ ተዋዋይ ፡ ሀገሮች ፡ አንደኛው ፡ ከሌላ ፡ ሦስተኛ ፡ ሀገር ፡ ጋር ፡ ከሚያደርገው ፡ ውል ፡ ጋር ፡ የማይስማማ ፡ ከሆነ ፡ በአመጣጥ ፡ የኋለኛ ፡ የሆነው ፡ ውል ፡ ፈራሽ ፡ ይሆናል ፡ የሚሉ ፡ ብዙ ፡ ደራሲያን ፡ ቢኖሩም ፡ እንኳ ፤ የሀርቫርድ ፡ ምርምር ፡ ድርሰት ፡ ቁጥር ፡ ፳፪ ፡ (ሐ) ፡ ስለኋለኛው ፡ ውድቅ ፡ መሆን ፡ ሳይናገር ፡ በደፈናው ፡ ቅድሚያ ፡ የሚሰጠው ፡ ባመጣጥ ፡ የፊተኛ ፡ ለሆነው ፡ ውል ፡ ነው ፡ ይላል»[48] ብለዋል ።

የዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ደራሲ ፡ የሚያቀርበው ፡ ሀሳብ ፡ ግን ፡ ባመጣጥ ፡ ሁለተኛ ፡ የሆነው ፡ ውል ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ከመጀመሪያው ፡ ጋር ፡ የማይስማማ ፡ ቢሆንም ፡ ውድቅ ፡ መሆን ፡ ሳይኖርበት ፤ የፊተኛው ፡ ውል ፡ ባፈጻጸም ፡ ረገድ ፡ ቅድሚያ ፡ ተሰጥቶት ፤ የኋለኛውን ፡ ውል ፡ ግን ፡ ለመፈጸም ፡ ባለመቻሉ ፡ ለደረሰው ፡ ጉዳት ፡ ካሣ ፡ መክፈል ፡ ይገባል ፡ የሚል ፡ ነው ። ባመጣጥ ፡ የፊተኛው ፡ ለሆነው ፡ ውል ፡ ባፈጻጸም ፡ ረገድ ፡ ቅድሚያ ፡ የሚሰጥበት ፡ ምክንያት ፡ ለሚፈጠረው ፡ ችግር ፡ እልባት ፡ ለመስጠት ፡ ታስቦ

---

47. ሀንስ ፡ ኬልሰን ፤ ዘ ፡ ሎው ፡ ኦፍ ፡ ዘ ፡ ዩናይትድ ፡ ኔሺንስ ፡ (፲፱፻፶፯) ፡ ገጽ ፡ ፭፻፲፪ ።
48. ብሪግስ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፳፭ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፱፻፷ ፡ ይመለከቷል ።

ክፍል ፡ ፫ ፤

<u>በውሎች ፡ መካከል ፡ ስለሚኖር ፡ መጻረር ።</u>

ሀ/ <u>በሁለት ፡ ውሎች ፡ መካከል ፡ ስለሚኖር ፡ መጻረር ፤</u>

ከኢንተርናሲዮናል ፡ ሕግ ፡ ሊቃውንት ፡ አንዱ ፡ ኬልሰን ፤ በውሎች ፡ መካከል ፡ ስለሚኖር ፡ መጻረር ፡ በጻፋት ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ እንዲህ ፡ ሲሉ ፡ ደምድመዋል ። "ሁለት ፡ ተጻራሪ ፡ ውሎች ፡ (ተዋዋዮቹ ፡ ሀገሮች ፡ እነዚያው ፡ ሁነው) ፡ በሁለት ፡ ተዋዋይ ፡ ወገኖች ፡ መካከል ፡ በሚደረጉበት ፡ ጊዜ ፡ <u>ሌክስ ፡ ፖስትሪዮሪ ፡ ዴሮጋንት ፡ ፕራዮሪ</u> ፡ የተባለው ፡ አጠቃላይ ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ደንብ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ይውላል። ይህም ፡ ደንብ ፡ "በአመጣጥ ፡ የኋለኛ ፡ የሆነው ፡ ውል ፡ የፊተኛውን ፡ ይሽረዋል"፡ ይላል። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ለላይኛው ፡ ደንብ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ መሠረታዊ ፡ ሃሳብ ፡ ያለው ፡ የውል፡ ስምምነት ፡ ሊመሠረት ፡ ይችላል ። ይኸውም ፡ <u>ሌክስ ፡ ፕራዮሪ ፡ ዴሮጋንት ፡ ፖስትሪዮሪ</u> ፡ የሚለው ፡ ደንብ ፡ ሲሆን ፤ እርሱም ፡ "ቀደም ፡ ሲል ፡ ሌላ ፡ ውል ፡ በተዋዋሉ፡ ወገኖች ፡ መካከል ፡ ዳግመኛ ፡ የተደረገው ፡ ውል ፡ ከመጀመሪያው ፡ ውል ፡ ጋር ፡ የማይስማማ ፡ በሚሆንበት ፡ ጊዜ ፡ ባመጣጥ ፡ የኋለኛ ፡ የሆነው ፡ ውድቅ ፡ ይሆናል"[47] የሚል ፡ ነው ።

በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ደራሲም ፡ አስተሳሰብ ፡ ተጻራሪ ፡ የሆኑ ፡ ሁለት ፡ ውሎች ፡ በኢትዮጵያና ፡ ባንድ ፡ በሌላ ፡ ተዋዋይ ፡ ወገን ፡ መካከል ፡ ተደርገው ፡ ቢገኙ ፡ የኋለኛው ፡ ውል ፡ የፊተኛውን ፡ እንደሚሽረው ፡ ሊቆጠር ፡ ይገባል ።

ነገር ፡ ግን ፡ ሁለቱ ፡ ተጻራሪ ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ውሎች ፡ የተደረጉት ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ከልዩ ፡ ልዩ ፡ ሀገሮች ፡ ጋር ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ውጤቱ ፡ (ከላይኛው) ፡ የተለየ ፡ ይሆናል ።

ተጻራሪ ፡ ከሆኑ ፡ የውል ፡ ግዴታዎች ፡ ውስጥ ፡ ቅድሚያ ፡ መስጠት ፡ የሚገባቸው፡ የትኞቹ ፡ እንደሆኑ ፡ ብሪግስ ፡ ሲጽፉ ፡-

"በሁለት ፡ ተዋዋይ ፡ ሀገሮች ፡ መካከል ፡ የሚደረግ ፡ ውል ፡ ከነዚሁ ፡ ተዋዋይ ፡ ሀገሮች ፡ አንደኛው ፡ ከሌላ ፡ ሦስተኛ ፡ ሀገር ፡ ጋር ፡ ከሚያደርገው ፡ ውል ፡ ጋር ፡ የማይስማማ ፡ ከሆነ ፡ በአመጣጥ ፡ የኋለኛ ፡ የሆነው ፡ ውል ፡ ፈራሽ ፡ ይሆናል ፡ የሚሉ ፡ ብዙ ፡ ደራሲያን ፡ ቢኖሩም ፡ እንኳ ፤ የሀርቫርድ ፡ ምርምር ፡ ድርሰት ፡ ቁጥር ፡ ፳፪ ፡ (ሐ) ፡ ስለኋለኛው ፡ ውድቅ ፡ መሆን ፡ ሳይናገር ፡ በደፈናው ፡ ቅድሚያ ፡ የሚሰጠው ፡ ባመጣጥ ፡ የፊተኛ ፡ ለሆነው ፡ ውል ፡ ነው ፡ ይላል»[48] ብለዋል ።

የዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ደራሲ ፡ የሚያቀርበው ፡ ሀሳብ ፡ ግን ፡ ባመጣጥ ፡ ሁለተኛ ፡ የሆነው ፡ ውል ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ከመጀመሪያው ፡ ጋር ፡ የማይስማማ ፡ ቢሆንም ፡ ውድቅ ፡ መሆን ፡ ሳይኖርበት ፤ የፊተኛው ፡ ውል ፡ ባፈጻጸም ፡ ረገድ ፡ ቅድሚያ ፡ ተሰጥቶት ፤ የኋለኛውን ፡ ውል ፡ ግን ፡ ለመፈጸም ፡ ባለመቻሉ ፡ ለደረሰው ፡ ጉዳት ፡ ካሣ ፡ መክፈል ፡ ይገባል ፡ የሚል ፡ ነው ። ባመጣጥ ፡ የፊተኛው ፡ ለሆነው ፡ ውል ፡ ባፈጻጸም ፡ ረገድ ፡ ቅድሚያ ፡ የሚሰጥበት ፡ ምክንያት ፡ ለሚፈጠረው ፡ ችግር ፡ እልባት ፡ ለመስጠት ፡ ታስቦ

---

47. ሀንስ ፡ ኬልሰን ፤ <u>ዘ ፡ ሎው ፡ ኦፍ ፡ ዘ ፡ ዩናይትድ ፡ ኔሺንስ</u> ፡ (፲፱፻፶፩) ፡ ገጽ ፡ ፩፻፲፪ ።
48. ብሪግስ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፳፮ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፱፻፷ ፡ ይመለከቷል ።

ሲሆን ፤ ይልቁንም ፡ "ፖክታ ፡ ሱንት ፡ ሴርቫንዳ" ፡ ማለት ፡ ስምምነቶች ፡ ምን ፡ ጊዜም፡ ቢሆን ፡ መጠበቅ ፡ አለባቸው ፡ ከሚለው ፡ ጥንታዊ ፡ የሕግ ፡ ዘይቤ ፡ ጋር ፡ የተስማማ ፡ መፍትሔ ፡ በመሆኑም ፡ ነው ። ይህንኑ ፡ በመደገፍ ፡ ፕሮፌሰር ፡ ዌበርግ ፡ ውሎች ፡ ካልተጠበቁና ፡ መሠረታዊ ፡ ሀሳባቸውም ፡ ተገቢ ፡ የመታወቅ ፡ ደረጃ ፡ ካልተሰጠው ፡ በቀር ፡ በሀገሮች ፡ መካከል ፡ ተገቢ ፡ ግንኙነትና ፡ ማናቸውም ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ሕግ ፡ ሊሰምር ፡ አይችልም ፡ ብለዋል ።[49]

ለ) በውሎችና ፡ በብሔራዊ ፡ ሕግ ፡ መካከል ፡ ስለሚኖር ፡ መጻረር ፤

በኢትዮጵያ ፡ በውሎችና ፡ በብሔራዊ ፡ ሕግ ፡ መካከል ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ መንገድ ፡ መጻረር ፡ ሊፈጠር ፡ ይችላል ። ለምሳሌ ፦

(፩) በውልና ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ በወጣ ፡ ዐቢይ ፡ ሕግ ፡ (አዋጅ ፡ ወይም ፡ ድንጋጌ) ፡ መካከል ፡ የሚኖር ፡ መጻረር ፤

(፪) በአንድ ፡ ውልና ፡ ከዚሁ ፡ ውል ፡ በኋላ ፡ በወጣ ፡ ዐቢይ ፡ ሕግ ፡ መካከል፡ የሚኖር ፡ መጻረር ፤

(፫) በውልና ፡ በሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ አናቅጽት ፡ መካከል ፡ የሚኖር ፡ መጻረር ፤ ሊኖር ፡ ይችላል ።

(፩) በውልና ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ በወጣ ፡ ዐቢይ ፡ ሕግ ፡ መካከል ፡ ስለሚኖር ፡ መጻረር፤

የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ከመታወጁ ፡ በፊት ፡ የወጣ ፡ አንድ ፡ ዐቢይ ፡ ሕግ ፡ (አዋጅ ፡ ወይም ፡ ድንጋጌ) እና ፡ ከጥቅምት ፡ ፳፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ፡ም ፡ በፊት፡ የተደረገ ፡ አንድ ፡ ውል ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ጨርሶ ፡ የሚጻረሩና ፡ ሊስማሙም ፡ የማ ይችሉ ፡ ሆነው ፡ ሲገኙ ፤ በ፲፱፻፵፭ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ፮ ፡ ቁጥር ፡ ፰ ፡ እና ፡ በ፲፱፻፵፯ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረቱ ፡ አዋጅ ፡ ፩፻፴፱ ፡ ቁጥር ፡ ፩ ፡ መሠረት ፡ የበላይነት ፡ የሚኖረው ፡ ውሉ ፡ ነው ። እንዲሁም ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ከታወጀ ፡ በኋላ ፡ የወጣ ፡ አንድ ፡ ጸንቶ ፡ የሚሠራበት ፡ ሕግና ፡ ከርሱ ፡ በኋላ ፡ የተደረገ ፡ ውል ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ጨርሶ ፡ የማይስማሙ ፡ ሆነው ፡ ሲገኙ ፤ ውሉ ፡ ቀደም ፡ ሲል፡ የወጣውን ፡ ሕግ ፡ እንዳሻሻለው ፡ ተቆጥሮ ፡ የበላይ ፡ ሕግ ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን ፡ በአንቀጽ ፡ ፩፻፳፪ ፡ መሠረት ፡ ተፈጻሚነት ፡ ይኖረዋል ።

የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፴ም ፡ ጸንተው ፡ የሚሠራባቸውን ፡ ሕጎች ፡ የሚያሻሽሉ ፡ ወይም ፡ የሚሽሩ ፡ ውሎች ፡ ወይም ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ስም ምነቶች ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛትና ፡ በሕዝቡም ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚ ፡ ከመ ሆናቸው ፡ በፊት ፡ ለፓርላሜንቱ ፡ ቀርበው ፡ ፓርላሜንቱ ፡ ሲቀበላቸው ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መጽደቅ ፡ አለባቸው ፡ የሚለው ፡ ይህንን ፡ የመሰለውን ፡ መጻረር ፡ ለማስወ ገድ ፡ ነው ።

49. ሀንስ ፡ ዌበርግ ፤ "ፖክታ ፡ ሱንት ፡ ሴርባንዳ" ፡ አሜሪካን ፡ ጆርናል ፡ ኦፍ ፡ ኢንተርናሽናል ፡ ሎው ፡ ቮልዩም ፡ ፶፫ ፡ (፲፱፻፶፱ ፡ ሰፕ) ፡ ገጽ ፡ ፯፻፹፮ ።

(፪) በአንድ ፡ ውልና ፡ ከዚሁ ፡ ውል ፡ በኋላ ፡ በወጣ ፡ ዐቢይ ፡ ሕግ ፡ መካከል ፡ ስለሚኖር ፡ መጻረር ፤

እንደ ፡ አሜሪካን ፡ ሕግ ፡ ሳይሆን ፤[50] በኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ ሥርዓት ፡ መሠረት ፡ አንድ ፡ ዐቢይ ፡ ሕግ ፡ የወጣው ፡ አንድ ፡ ውል ፡ ከተደረገ ፡ በኋላ ፡ ቢሆንም ፤ በውሉ፡ የተመሠረተውን ፡ መብት ፡ ወይም ፡ ግዴታ ፡ ሊሽር ፡ ወይም ፡ ሊያሻሽል ፡ አይችልም። እንደዚሁም ፡ ማናቸውም ፡ ውል ፡ በኋላ ፡ በወጣ ፡ ዐቢይ ፡ ሕግ ፡ ሊሻር ፡ ወይም ፡ ሊሻሻል ፡ አይችልም ።

በአንድ ፡ ውልና ፡ ከርሱም ፡ በኋላ ፡ በወጣ ፡ ዐቢይ ፡ ሕግ ፡ መካከል ፡ አንዱ ፡ ሌላውን ፡ በማስተባበሉ ፡ ስለሚኖረው ፡ ችግር ፡ የሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ ሕግ ፡ ሊቃውንት ፡ ሲያትቱ ፡ "ውል ፡ ከርሱ ፡ በኋላ ፡ በወጣ ፡ ሕግ ፡ ይሻሻላል ፡ ቢባልም ፡ እንኳ ፤ ሕጉ ፡ ይህን ፡ መሰሉን ፡ አለመስማማት ፡ ሳያስከትል ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ሊውል ፡ የሚችልበት ፡ ሌላ ፡ ቀና ፡ ዘዴ ፡ እስካለ ፡ ድረስ ፡ የኢንተርናሲዮናልን ፡ ሕግ ፡ (ውሎችንም ፡ ጭምር)፡ ሊጥስ ፡ በሚችል ፡ ዓይነት ፡ መተርጎም ፡ የለበትም ፡"[51] ይላሉ ።

የ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፵፱ ፡ በመጨረሻው ፡ ቁጥሩ ፡ ከላይኛው ፡ አስተሳሰብ ፡ ጋር ፡ የተዛመደ ፡ ጠቅላላ ፡ ደንብ ፡ ሲሰጥ ፡-

"ይህ ፡ አንቀጽ ፡ በኢንተርናሲዮናል ፡ ሕግ ፡ ወይም ፡ ተካፋይ ፡ በሆንባቸው ፡ በኢንተርናሲዮናል ፡ ስምምነት ፡ ወይም ፡ ኮንቬንሲዮን ፡ መሠረት ፡ ካሉት ፡ ግዴታዎች ፡ ጋር ፡ እንደማይስማማ ፡ ሆኖ ፡ አይተረጎምም" ፡ ይላል ።[52]

በተጨማሪም ፡ ውሎች ፡ የበላይ ፡ ሕግ ፡ ክፍል ፡ እንደመሆናቸው ፡ መጠን ፡ በማናቸውም ፡ ሕግ ፡ ሊሻሩ ፡ አይችሉም ። ይህም ፡ ማለት ፡ በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ በአንቀጽ ፡ ፩፻፳፪ ፡ እንደተመለከተው ፡ ሁሉ ፡ ውሎች ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ግዛት ፡ የበላይ ፡ ሕግ ፡ ክፍል ፡ በመሆናቸው ፡ ወደፊት ፡ የሚወጡ ፡ ሕጎች ፡ (አዋጆች) ፡ ድንጋጌዎች ፤ ትእዛዞች ፤ ፍርዶች ፤ ውሳኔዎችና ፡ ድርጊቶች ፡ ሁሉ ፡ በሚገባ ፡ ከጸደቀው ፡ ውል ፡ ጋር ፡ የማይስማሙ ፡ ሲሆኑ ፡ ዋጋ ፡ የሌላቸውና ፡ የማያገለግሉ ፡ ይሆናሉ ።

(፫) በውልና ፡ በሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጾች ፡ መካከል ፡ ስለሚኖር ፡ መጻረር ፤

የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ በሚያዘው ፡ መሠረት ፡ የተደረገ ፡ አንድ ፡ ውል ፡ ያለው ፡ ደረጃና ፡ የሚያስከትለው ፡ ግዴታ ፡ ልክ ፡ የሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ ያህል ፡ ነው ። ሁለቱም ፡ የበላይ ፡ ሕግ ፡ ሆነው ፡ ስለተደነገጉ ፡ በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፳፪ ፡ አነጋገር ፡ አንደኛው ፡ ከሌላኛው ፡ ብልጫ ፡ አልተሰጠውም ። ነገር ፡ ግን ፡ ሁለቱ ፡ በማይስማሙበት ፡ ጊዜ ፡ ውል ፡ የተደረገው ፡ ከጥቅምት ፡ ፳፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በኋላ ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፤ ከውሉ ፡ ይልቅ ፡ የበላይነት ፡ የሚኖረው ፡

---

50. በቼሮከ ፡ ቶባኮ ፡ (ቡንዲኖት ፤ ቨርስ ፡ ዩናይትድ ፡ ስቴትስ ፡ ጉዳይ) ፡ ጠቅላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚከተለውን ፡ በይኖአል ። "አንድ ፡ ውል ፡ ቀደም ፡ ሲል ፡ በኮንግሬስ ፡ ከወጣ ፡ ሕግ ፡ ይልቅ ፡ ሕጋዊ ፡ ኃይል ፡ አለው" ። ደግሞም ፡ (ከሳሽ ፡ ፎስተር ፡ እና ፡ ኤለን ፤ ተከሳሽ ፡ ሴልሰን) ፡ በተባለው ፡ ጉዳይ ፡ ፍርድ፡ ቤቱ ፡ ሲበይን ፤ "በኮንግሬስ ፡ የወጣ ፡ ሕግ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ የተደረገን ፡ ውል ፡ ሊሽር ፡ ይችላል" ፡ (ከሳሽ ፡ ቲይለር ፤ ተከሳሽ ፡ ሞርተን) ፡ ብሏል ።

51. ሮናልድ ፡ ጂ ፡ ስታንገር ፤ ኬዝስ ፡ ኤንድ ፡ ማቴሪያልስ ፡ ኦን ፡ ፓብሊክ ፡ ኢንተርናሽናል ፡ ሎው ፡ (፲፱፻፶፱—፲፱፻፶፰) ፡ ያልታተመ ፤ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፤ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ ገጽ ፡ ፩፻፳፫ ።

52. ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፴፰ ፡ ይመለከቷል ።

የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ነው ። ይህም ፡ የሚሆንበት ፡ ምክንያት ፤ አንድ ፡ ውል፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ሕጋዊ ፡ ኃይል ፡ ኖሮት ፡ ለመፈጸም ፡ ግዴታ ፡ ሊሆን ፡ ይችል ፡ ዘንድ ፡ አስቀድሞ ፡ ከሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ጋር፡ መስማማትና፡ የሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ፡ ፴ ፡ የሚያዘውንም ፡ አሟልቶ ፡ መገኘት ፡ ስላለበት ፡ ነው ። ባይርድ ፡ እንደተናገሩት ፡ “---አንድ ፡ የስምምነት ፡ ውል ፡ ጽኑነት ፡ (ባለዋጋ ፡ መሆን) ፡ የሚለካው ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ሲሆን ፤ ይህን ፡ የሚጥስ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ውሉ ፡ ውድቅ ፡ መሆን ፡ አለበት---” ።[53] ስለዚህ ፡ በሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ረገድ ፤ ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ በሚያዘው ፡ መሠረት ፡ የተፈጸመ ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፡ ሌሎችን ፡ የሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ አናቅጻት ፡ የሚጥስ ፡ ውል ፡ በኢትዮጵያ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ዋጋ ፡ የሌለውና ፡ የማያገለግል ፡ ይባላል ። ምክንያቱም ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ውል ፡ በመዋዋል ፡ ሥልጣን ፡ መሠረት ፡ የሚደረግ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አናቅጻት ፡ ገደብ፡ የተበጀለት፡ በመሆኑ ፡ የእነዚህ ፡ ገደቦች ፡ መጣስ ፡ ውሉን ፡ ዋጋ ፡ የሌለውና ፡ የማያገለግል ፡ ስለሚያደርገው ፡ ነው። “ዘ ፡ ሪስቴትሜንት ፡ አፍ ፡ ዘ ፡ ፎሪን ፡ ሪሌሽንስ ፡ ሎውስ ፡” በተሰኘው ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ እንደተጠቀሰው ፡ ሁሉ ፤ በሕገ ፡ መንግሥት ፡ የተሰጠ ፤ ውል ፡ የመዋዋል ፡ ሥልጣን ፡ ዳርና ፡ ድንበሩ ፡ ሊወሰን ፡ የሚገባው ፡ ይህንኑ ፡ ሥልጣን ፡ በሚሰጠው ፡ የሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አንቀጽ ፡ አነጋገር ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፤ ሌሎች ፡ የሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አናቅጻትም፡ በሚጥሉት፡ ገደብ፡ ጭምር፡ ነው ።[54] ይህንኑም ፡ ለመረዳት፡ የሚከተለውን ፡ ምሳሌ ፡ እንመልከት ።

አንድ ፡ ‘ሀ’ ፡ የተባለ ፡ መንግሥት ፡ ከኢትዮጵያ ፡ በተገለጸለት ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ውል ፡ የመዋዋል ፡ ፍላጎት ፡ አጸፋ ፡ አንድ ፡ ውል ፡ ለማድረግ ፡ ፈቃደኛ ፡ ቢሆንና፡ የዚህም ፡ ውል ፡ ዓላማ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ የሚኖሩ ፡ የ‘ሀ’ ፡ መንግሥት ፡ ዜጎች ፡ ማናቸውም ፡ ኪሣራና ፡ ጥፋት ፡ የሚያመጣ ፡ በደል ፡ ቢደርስባቸው ፡ በኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ ክስ ፡ ማቅረብ ፡ አይችሉም ፡ የሚል ፡ ቢሆን ፤ ይህን ፡ ውል ፡ ኢትዮጵያ ፡ እንድታደርግ ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ይፈቅድላታልን ? ለሚለው ፡ ጥያቄ ፡ መልሱ ፡ ያለ ፡ ጥርጥር ፡ አይፈቀድላትም ፡ የሚል ፡ ነው ። ምክንያቱም ፡ ይህ ፡ ዓይነቱ ፡ ውል ፡ በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ምዕራፍ ፡ ፫ ፡ ውስጥ ፡ ከተመለከቱት ፤ ለመከበራቸውም ፡ ማረጋገጫ ፡ ከተሰጣቸው ፡ መብቶች ፡ አንደኛውን ፡ የሚነሳ ፡ በተለይም ፡ በአንቀጽ ፡ ፳፱ ፡ (ለ) ፡ የተመለከተውን ፡ ክስ ፡ የማቅረብ ፡ መብት ፡ የሚከለክል ፡ ስለሚሆን፡ ነው ።

በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ለሚኖሩ ፡ የአንድ ፡ ተዋዋይ ፡ ሀገር ፡ ዜጎች ፡ በአንቀጽ ፡ ፳፱ ፡ (ለ) መሠረት ፡ ክስ ፡ አቅርቦ ፡ ካሣ ፡ ለመጠየቅ ፡ የተሰጣቸውን ፡ መብት ፡ የሚነሳ፡ ውል ፡ ማድረግ ፡ በአንቀጽ ፡ ፳፰ ፡ ከተመለከቱት ፡ የሰውን ፡ መብት ፡ ለመቀነስ ፡ ከሚያበቁት ፡ ምክንያቶች ፡ እንደ ፡ አንዱ ፡ ሁኖ ፡ ስለማይቆጠር ፡ በሕግ ፡ የሚደገፍ ፡ አይደለም ።

በአንቀጽ ፡ ፳፰ ፡ መሠረት ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ምዕራፍ ፡ ፫ ፡ ውስጥ ፡ የተሰጡት ፡ ማናቸውም ፡ መብቶች ፡ የሚቀነሱት ፦

፩/ የሌሎችን ፡ ሰዎች ፡ ነፃነትና ፡ መብት ፡ ለማክበር ፤
፪/ አስፈላጊውን ፡ የሕዝብ ፡ ፀጥታ ፡ ለማስገኘትና ፤

53. ባይርድ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፳፱ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፹፬ ፡ ይመለከቷል ።
54. ዘ ፡ አሜሪካን ፡ ሎው ፡ ኢንስቲትዩት ፤ ከላይ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፳፯ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፬፻፴፯፡ ይመለከቷል ።

፫/ ጠቅላላ ፡ ደህንነትን ፡ ለመጠበቅ ፤
ሲባል ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተመለከትነውም ፡ ውል ፡ በአንቀጽ ፡ ፳፭ ፡ የሚደገፍ ፡ አይደለም ፡ የተባለበትም ፡ ምክንያት ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ ከተዘረዘሩት ፡ በማናቸውም ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ሊመደብ ፡ የማይችል ፡ በመሆኑ ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ ይህ ፡ ዓይነቱ ፡ ውል ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ የሚጥስ ፡ በመሆኑ ፡ ፓርላሜንቱ ፡ ተቀብሎትም ፡ ቢሆን ፡ እንኳ ፡ ሊደረግ ፡ አይገባውም ። ከዚህም ፡ የተነሳ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ስለአንዳንድ ፡ ጉዳዮች ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ውል ፡ በማድረግ ፡ ረገድ ፡ ያለው ፡ ሥልጣን ፡ ሌሎች ፡ የሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አናቅጻት ፡ በሚጥሉትም ፡ ገደብ ፡ የተወሰነ ፡ ነው ።

ሆኖም ፤ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ከመውጣቱ ፡ በፊት ፡ የተደረጉ ፡ ውሎች ፡ በሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ረገድ ፡ አንቀጽ ፡ ፴ ፡ የሚያዘውን ፡ መንገድ ፡ አለመከተላቸው ፡ ውድቅ ፡ አያደርጋቸውም ። አንድ ፡ መንግሥት ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ በመለወጥ ፡ ብቻ ፡ ከውል ፡ ግዴታው ፡ ሊያመልጥ ፡ ስለማይችል ፤ እነዚህም ፡ ውሎች ፡ በኢንተርናሲዮናል ፡ ሕግ ፡ ረገድ ፡ አስገዳጅነታቸው ፡ እንዳለ ፡ ይቆያል ። ከዚህም ፡ በላይ ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ከመውጣቱ ፡ በፊት ፡ የተደረጉ ፡ ውሎች፡ በ፲፱፻፴፭ ፡ ዓ፡ ም፡ በወጣው ፡ ትእዛዝ ፡ ቁጥር ፡ ፮ ፡ እና ፡ በ፲፱፻፴፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በወጣው ፡ አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፴፱ ፡ መሠረት ፡ ከሀገሪቱ ፡ ብሔራዊ ፡ ሕግ ፡ ጋር ፡ ስለተዋሃዱ ፡ በሀገሪቱ ፡ ውስጥም ፡ ተፈጻሚ ፡ የመሆን ፡ ሕጋዊ ፡ ኃይል ፡ አላቸው ። ስለዚህ ፡ በ፲፱፻፳፫ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፲፬ ፡ መሠረት ፡ ወይም ፡ ከ፲፱፻፳፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በፊት ፡ እንደጊዜው ፡ የውል ፡ መዋዋል ፡ ልማድ ፡ የተደረገ ፡ ማናቸውም ፡ ውል ፡ ካሁኑ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አናቅጻት ፡ ጋር ፡ የማይስማማ ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፡ ውሉ ፡ እስከቀረ ፡ ወይም ፡ ከዚያው ፡ ተዋዋይ ፡ ወገን ፡ ጋር ፡ እንደገና ፡ የውል ፡ ድርድር ፡ ተደርጎ ፡ በሌላ ፡ ውል ፡ እስከተተካ ፡ ድረስ ፡ ተፈጻሚነት ፡ ይኖረዋል ። ይህም ፡ የሚሆንበት ፡ ምክንያት ፤ የተሻሻላው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፳፪ ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ በታወጀበት ፡ ጊዜ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ የነበሩትን ፡ ውሎች ፡ ስለማይመለከት ፡ ነው ። በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ የተፈቀዱትን ፡ መብቶች ፡ የሚነሱ ፡ ቢሆኑም ፡ እንኳ ፡ ቀደም ፡ ሲል ፡ በተጠቀሰው ፡ አንቀጽ ፡ መሠረት ፡ ዋጋ ፡ የሌላቸውና ፡ የማያገለግሉ ፡ ሊሆኑ ፡ አይችሉም ።

እንደዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ ውጤት ፡ መንግሥቱን ፡ ከሁለት ፡ አስቸጋሪ ፡ ሁኔታዎች ፡ አንደኛውን ፡ እንዲመርጥ ፡ በማድረግ ፡ ችግር ፡ ላይ ፡ ይጥለዋል ። ምርጫዎቹም ፡-

ሀ/ የውሉን ፡ አናቅጻት ፡ በመተላለፍ ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ውስጥ ፡ የተፈቀዱትን ፡ መብቶች ፡ እንደተጠበቁ ፡ ማቆየት ፤ ወይም ፡

ለ/ በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ የተፈቀዱትን ፡ አንዳንድ ፡ መሠረታዊ ፡ መብቶች ፡ ሕዝቡን ፡ ነፍጐ ፡ የውሉ ፡ አንቀጾች ፡ ከሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አናቅጻት ፡ ጋር ፡ የማይስማሙ ፡ ቢሆኑም ፡ እንኳ ፡ ውሉ ፡ እንዳለ ፡ ሆኖ ፡ እንዲቆይ ፡ ማድረግ ፤ ናቸው ።

በሁለቱም ፡ በኩል ፡ የሚከተለው ፡ ውጤት ፡ በጣም ፡ ከባድ ፡ በመሆኑ ፡ ምርጫው ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው ።

ይሁን ፡ እንጂ ፤ ይህ ፡ መፍትሔ ፡ የሌለው ፡ ችግር ፡ አይደለም ። መንግሥቱ ፡ ከተ ዋዋዩ ፡ ወገን ፡ ጋር ፡ አዲስ ፡ የውል ፡ ድርድር ፡ አድርጎ ፡ የውሉን ፡ ቃል ፡ በመለወጥና ከተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አናቅጻት ፡ ጋር ፡ በማስማማት ፡ ይህን ፡ ችግር ፡ ሊወ ጣው ፡ ይችላል ።

ሐ/ በውሎችና ፡ በተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ድርጅት ፡ ቻርተር ፡ መካከል ፡ ስለሚኖር ፡ መጻረር ፤

ሎርድ ፡ ማክኔር ፡ በሚገባ ፡ እንደገለጹት ፡ ሁሉ ፤ ብዙዎቹ ፡ የተባበሩት ፡ መንግ ሥታት ፡ ድርጅት ፡ ቻርተር ፡ አናቅጻት ፡ እንደማናቸውም ፡ ውሎች ፡ ሁሉ ፡ መብትና ፡ ግዴታ ፡ የሚፈጥሩና ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ ሕጋዊ ፡ ጠባይ ፡ ያላቸው፡ በመሆናቸው ፡ አባል ፡ ሀገሮች ፡ ከነሱ ፡ ውጭም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ እነሱን ፡ የሚሽር ፡ ውል ፡ ሊዋዋሉ ፡ አይችሉም ። ይህንንም ፡ የሚያደርግ ፡ ማናቸውም ፡ ውል ፡ ዋጋ ፡ የሌለውና ፡ የማያገለግል ፡ ይሆናል ።[55]

አሁን ፡ ያልነውን ፡ ጉዳይ ፡ የሚመለከቱት ፡ የቻርተሩ ፡ ክፍሎች ፤ ሀ/ በአባል ፡ መንግሥታት ፡ መካከልና ፤ ለ/ በድርጅቱና ፡ በአባል ፡ መንግሥታት ፡ መካከል ፡ መብ ትንና ፡ ግዴታን ፡ የሚፈጥሩት ፡ የቻርተሩ ፡ የአንቀጽ ፡ ፪ ፡ ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ቁጥር ፡ ፫ ፡ እና ፡ ፬ ፡ ናቸው ።[56]

ከዚህም ፡ በላይ ፡ የቻርተሩ ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፫ ፡ ስለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ ሲገልጽ ፤

"የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ አባል ፡ ሀገሮች ፡ በቻርተሩ ፡ ውስጥ ፡ ባለባቸው ፡ ግዴታና ፡ አባሎቹ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ በሚያደርጉት ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ውል ፡ መካከል ፡ መጻረር ፡ ሲፈጠር ፤ በቻርተሩ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ የአባሎቹ ፡ ግዴታ ፡ የሚያይል ፡ ይሆናል" ፡ ይላል ።

ከቻርተሩ ፡ በፊት ፡ በነበሩ ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ስምምነቶች ፡ ላይና ፡ ወደፊ ትም ፡ በሚደረጉ ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ስምምነቶች ፡ ላይ ፡ ይህ ፡ አንቀጽ ፡ ስላለው ፡ ኃይል ፡ ሎርድ ፡ ማክኔር ፡ የሚከተለውን ፡ ጽፈዋል ።

፩/ በአባል ፡ ሀገሮች ፡ መካከል ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ተደርገው ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ያሉት ፡ ስምምነቶች ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ የተደረገውን ፡ ስምምነት ፡ (ማለት ፡ ቻርተሩን) ፡ በሚስማማ ፡ አኳኋን ፡ ቻርተሩ ፡ በሚገባ ፡ ሊያሻሽላቸው ፡ ይችላል ። በአባል ፡ ሀገሮች ፡ መካከል ፡ የሚደረጉ ፡ የወደፊት ፡ ስምምነቶች ፡ ደግሞ ፡ በተባበሩት ፡ መንግሥታትና ፡ በአባል ፡ ሀገሮች ፡ መካከል ፡ ባለው ፡ ስምምነት ፡ መሠ ረት ፡ አባሎች ፡ ከቻርተሩ ፡ ጋር ፡ በሚጻረር ፡ አኳኋን ፡ ውል ፡ ቢዋዋሉ ፡ ግዴታው ፡ ጽኑነት ፡ አይኖረውም ።

፪/ በአባልና ፡ አባል ፡ ባልሆኑ ፡ ሀገሮች ፡ መካከል ፡ ስለሚደረጉት ፡ ስምምነቶች ፡ ግን ፡ የአንቀጹ ፡ አቋም ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ግልጽ ፡ አይደለም ። በኛ ፡ አስተያየት ፡

---

55. ሎርድ ፡ ማክኔር ፤ ዘ ፡ ሎው ፡ ኦፍ ፡ ትሪቲስ ፡ (፲፱፻፷፩) ፤ ገጽ ፡ ፪፻፲፮ ።

56. የቻርተሩ ፡ አንቀጽ ፡ ፪ ፡ በከፊል ፡ እንዲህ ፡ ይላል ።
"፫ ፡ አባል ፡ ሀገሮች ፡ ሁሉ ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ክርክራቸውን ፡ የዓለምን ፡ ሰላም ፤ ጸጥታና ፡ ትክክ ለኛ ፡ ፍርድ ፡ በማያደፈርስ ፡ የሰላም ፡ መንገድ ፡ መጨረስ ፡ አለባቸው ።
፬ ፡ አባል ፡ ሀገሮች ፡ ሁሉ ፡ በኢንተርናሲዮናል ፡ ግንኙነታቸው ፡ ማናቸውንም ፡ የሌላ ፡ መንግሥት ፡ የፖለቲካ ፡ ነፃነትና ፡ የግዛት ፡ ክልል ፡ ከማስፈራራት ፡ ወይም ፡ በጦር ፡ ኃይል ፡ ከመጠቀምና ፡ ወይም፡ ማናቸውንም ፡ የተባበሩት ፡ መንግሥታትን ፡ ዓላማ ፡ ከሚጻረር ፡ ተግባር ፡ መቆጠብ ፡ አለባቸው" ።

ከቻርተሩ ፡ በፊት ፡ ተደርገው ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ባሉት ፡ ስምምነቶች ፡ በኩል ፡ አባል ፡ ሀገሮች ፡ ከቻርተሩ ፡ ጋር ፡ በሚጻረር ፡ አኳኋን ፡ የተደረገውን ፡ ስምም ነት ፡ ከመፈጸም ፡ ይታገዳሉ ። ከሕግ ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ በኃይል ፡ መጠ ቀምን ፡ የሚፈቅድ ፡ ውል ፡ ለዚሁ ፡ ምሳሌ ፡ ሲሆን ፤ ከዚህም ፡ አልፈው ፡ አባ ሎቹ ፡ ከቻርተሩ ፡ ጋር ፡ ተጻራሪ ፡ የሆኑ ፡ ውሎች ፡ የሚያስከትሉት ፡ ግዴታዎች ፡ አግባብ ፡ ባለው ፡ ሕጋዊ ፡ ዘዴ ፡ በመጠቀም ፡ ራሳቸውን ፡ ለማላቀቅ ፡ ግዴታ ፡ ያለባቸው ፡ ይመስላል ። ወደፊት ፡ በሚደረጉ ፡ ውሎች ፡ ረገድ ፡ ደግሞ ፡ ማናቹ ውም ፡ አባል ፡ ከቻርተሩ ፡ ጋር ፡ ከማይስማማ ፡ ግዴታ ፡ ውስጥ ፡ ቢገባ ፡ ውሉ ፡ ጽኑነት ፡ አይኖረውም ። በተጨማሪም ፡ አባል ፡ ያልሆነው ፡ ተዋዋይ ፡ ወገን ፡ አባል ፡ የሆነው ፡ ሀገር ፡ የዚህን ፡ ዓይነቱን ፡ ውል ፡ ሊገባ ፡ እንደማይችል ፡ ያውቃል ፡ የሚል ፡ ግምት ፡ አለ ። ምክንያቱም ፡ ቻርተሩ ፡ በእንግሊዝ ፡ የሕግ ፡ ባለሙያዎች ፡ አነጋገር ፡ "ኖቶሪየስ ፡ ኢንስትሩሜንት" ማለት ፡ "ዕውቅ ፡ ሰነድ" ፡ መባል ፡ ስላለበትና ፡ በዚህም ፡ የተነሳ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ ሰነዱን ፡ ማወቅ ፡ የሚገባው ፡ ስለሆነ ፡ ነው ። ደግሞም ፡ ይህ ፡ አባል ፡ ያልሆነ ፡ መንግሥት ፡ ሊዋዋለው ፡ ያሰበው ፡ ወገን ፡ የተባበሩት ፡ መንግ ሥታት ፡ ድርጅት ፡ አባል ፡ መሆን ፡ አለመሆኑን ፡ ለይቶ ፡ እንደሚያውቅ ፡ ይገመታል ። ሆኖም ፡ ይህን ፡ ስንል ፡ የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ በቻርተሩ ፡ አማካይነት ፡ አባል ፡ ባልሆኑ ፡ መንግሥታት ፡ ላይ ፡ ሕጋዊ ፡ ኃይል ፡ ያለው ፡ ግዴታ ፡ የመፍጠር ፡ ሥልጣን ፡ አላቸው ፡ ማለታችን ፡ ሳይሆን ፤ አባል ፡ ሀገሮች ፡ አዲስ ፡ መብትና ፡ ግዴታ ፡ የሚፈጥረውን ፡ ሰነድ ፡ ማለት ፡ ቻር ተሩን ፡ በመቀበላቸው ፡ ውል ፡ በማድረግ ፡ ረገድ ፡ በነበራቸው ፡ ሥልጣን ፡ ላይ ፡ ገደብ ፡ አድርገውበታል ፡ ማለታችን ፡ ነው ።"[57]

ስለዚህ ፡ በተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ቻርተር ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፫ ፡ መሠረት ፡ ኢት ዮጵያ ፡ በቻርተሩ ፡ ስር ፡ ባለባትና ፡ በሌላ ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ውል ፡ ተካፋይ ፡ በሆ ነችባቸው ፡ ግዴታዎች ፡ መካከል ፡ መጻረር ፡ ቢፈጠር ፡ የሚያይለው ፡ በቻርተሩ ፡ መሠ ረት ፡ ያለባት ፡ ግዴታ ፡ ይሆናል ፡ ማለት ፡ ነው ። ይህም ፡ አስተያየት ፡ ቻርተሩ ፡ በሚፈጥራቸውና ፡ በአባል ፡ መንግሥታት ፡ መካከል ፡ የተደረጉት ፡ ውሎች ፡ በሚያስ ከትሏቸው ፡ ግዴታዎች ፡ መካከል ፡ ስለሚፈጠረው ፡ መጻረር ፡ "በአጠቃላይ ፡ የኢን ተርናሲዮናል ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ይህ ፡ ዓይነቱ ፡ ውል ፡ የተደረገው ፡ ቻርተሩ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ከመዋሉ ፡ በፊት ፡ ከሆነ ፤ የቻርተሩ ፡ መውጣት ፡ ውሉን ፡ ይሽረዋል ። ውሉ ፡ የተደረገው ፡ ቻርተሩ ፡ ከወጣ ፡ በኋላ ፡ ከሆነ ፡ ግን ፤ በሌሎቹ ፡ የቻርተሩ ፡ አናቅጽት ፡ መሠረት ፡ ከቻርተሩ ፡ ጋር ፡ የማይስማማ ፡ በመሆኑ ፡ ውሉ ፡ ዋጋ ፡ የሌለውና ፡ የማያገ ለግል ፡ ይሆናል ። ምክንያቱም ፡ ይህ ፡ ዓይነቱ ፡ ውል ፡ በተዋዋሉት ፡ አባል ፡ ሀገሮች ፡ መካከል ፡ ቻርተሩን ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ የመሻር ፡ ወይም ፡ የመለወጥ ፡ ሙከ ራ ፡ ያህል ፡ ስለሚቆጠር ፡ ነው"፡[58] በማለት ፡ ኬልሰን ፡ ከሚደግፉት ፡ ጠቅላላ ፡ መሠረታዊ ፡ ሀሳብ ፡ ጋር ፡ ይስማማል ።

ባጭሩ ፡ ከቻርተሩ ፡ በፊት ፡ የነበረ ፡ ውል ፡ በቻርተሩ ፡ የተሻረ ፡ ሲሆን ፤ ቻርተሩ ፡ ከወጣ ፡ በኋላ ፡ የተደረገው ፡ ደግሞ ፡ ከቻርተሩ ፡ ጋር ፡ የማይስማማ ፡ ሆኖ ፡ ከተገኘ ፡ ዋጋ ፡ የሌለውና ፡ የማያገለግል ፡ ነው ።

እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ መጻረር ፡ ለማስወገድና ፡ ሌሎችንም ፡ መንግሥታት ፡ ለማ ስጠንቀቅ ፡ ሲባል ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ስምምነቶች ፡ በሙሉ ፡ በተባበሩት ፡ መንግ

57. ማክኔር ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፶፩ ፡ የተጠቀሰው ፤ ከገጽ ፡ ፪፻፲፯—፪፻፲፰ ፡ ይመለከቷል ።
58. ኬልሰን ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፵፯ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፩፻፲፫ ፡ ይመለከቷል ።

ሥታት ፡ ድርጅት ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ እንዲመዘገቡ ፡ የድርጅቱ ፡ ቻርተር ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፪ ፡ የሚያዝ ፡ መሆኑን ፡ መገንዘብ ፡ ያሻል ። ድርጅቱ ፡ በ፳፮ኛው ፡ ጠቅላላ ፡ ስብሰባው ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፪ን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ ውሳኔ ፡ አሳልፎአል ። ውሎችንም ፡ ያለማስመዝገብ ፡ የውሎቹን ፡ ባለዋጋነት ፡ ሳይነካ ፡ በማናቸውም ፡ የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ሸንጎዎች ፡ በኢንተርናሲዮናል ፡ ፍርድ ፡ ቤትም ፡ ጭምር ፡ ውሉን ፡ ጠቅሶ ፡ ከመከራከር ፡ ያሳግዳል ።[59]

መ/ በውሎችና ፡ በአፍሪካ ፡ አንድነት ፡ ድርጅት ፡ ቻርተር ፡ መካከል ፡ ስለሚኖር ፡ መጻረር ።

በግንቦት ፡ ፲፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የተፈረመው ፡ የአፍሪካ ፡ አንድነት ፡ ቻርተር ፡ ከስሙ ፡ እንደምንረዳው ፡ ሁሉ ፡ በብዙ ፡ ሀገሮች ፡ መካከል ፡ የተደረገ ፡ ውል ፡ ነው ።

በቻርተሩ ፡ በ፳፬ኛው ፡ አንቀጽ ፡ እንደተመለከተው ፡ የያንዳንዱ ፡ ፈራሚ ፡ መንግሥት ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ በሚያዘው ፡ መሠረት ፡ ከተፈረመና ፡ ከጸደቀ ፡ በኋላ ፡ ቻርተሩ ፡ በተፈራሚዎቹ ፡ መንግሥታት ፡ ላይ ፡ ለመፈጸም ፡ ግዴታ ፡ ይሆናል ። በኢትዮጵያም ፡ ውስጥ ፡ ቻርተሩ ፡ በሚገባ ፡ የጸደቀ ፡[60] የኢንተርናሲዮናል ፡ ውል ፡ ስለ ሆነ ፤ በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፳፪ ፡ አነጋገር ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ የበላይ ፡ ሕግ ፡ አካል ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ በአፍሪካ ፡ አንድነት ፡ ድርጅት ፡ ቻርተርና ፡ በኢትዮጵያ፡ ዐበይት ፡ ሕጎች ፡ መካከል ፡ መጻረር ፡ ቢፈጠር ፡ የድርጅቱ ፡ ቻርተር ፡ የኢትዮጵያ ፡ የበላይ ፡ ሕግ ፡ አካልነት ፡ ደረጃ ፡ ስለተሰጠው ፡ ያይላል ፡ ማለት ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ የአፍሪካ ፡ አንድነት ፡ ድርጅት ፡ የመሪዎች ፡ ወይም ፡ የሚኒስትሮች ፡ ጉባኤ ፡ ባሳለፈው ፡ ውሳኔና ፡ በብሔራዊ ፡ ሕግ ፡ መካከል ፡ አለመስማማት ፡ ቢፈጠር ፡ የሚያይለው ፡ ብሔራዊው ፡ ሕግ ፡ ነው ። ይህም ፡ የሚሆንበት ፡ ምክንያት ፤ ይህ ፡ ዓይነቱ ፡ ውሳኔ ፡ በአንድ፡ መሠረታዊ ፡ ሀሳብ ፡ ላይ ፡ አባል ፡ መንግሥታት ፡ የተግባቡና ፡ በተመሳሳይ ፡ መንፈስ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ የተስማሙ ፡ መሆኑን ፡ የሚያሳይ ፡ እንጂ ፡ ለመፈጸም ፡ ሕጋዊ ፡ ኃይል ፡ ያለው ፡ ውል ፡ ባለመሆኑ ፡ ነው ። አንድ ፡ ውል ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ሕጋዊ ፡ ኃይል ፡ ሊኖረው ፡ የሚችለው ፡ ተገቢ ፡ የሆነ ፡ የውል ፡ ድርድር ፡ ተደርጎበትና ፡ በ፲፱፻፵፰ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረቱ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፴ ፡ መሠረት ፡ ጸድቆ ፡ የተገኘ ፡ እንደሆን ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ሠ/ በውሎች ፡ መካከል ፡ መጻረር ፡ ሲፈጠር ፡ ስላለ ፡ መፍትሔ ፤

ኬልሰን ፡ በውሎች ፡ መካከል ፡ መጻረር ፡ ሲፈጠር ፡ እንደመፍትሔ ፡ የሚከተለውን ፡ ሀሳብ ፡-

"ተዋዋዮች ፡ ወገኖቹ ፡ (ከሞላ ፡ ጎደል ፡ እነዚያው ፡ በሆኑ) ፡ በሁለት ፡ ተዋዋይ ፡ ወገኖች ፡ መካከል ፡ ለተደረጉ ፡ ተጻራሪ ፡ ውሎች ፡ አጠቃላዩ ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ሕግ ፡

59. ብራየሊ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፲፯ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፤ ፫፻፺፬ ፡ ይመለከቷል ።
60. የአፍሪካ ፡ አንድነት ፡ ድርጅት ፡ የተቋቋመበትን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ማጽደቂያ አዋጅ ፤ ፲፱፻፶፭ ፤ አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፪ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፳፪ኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፲፯ ፡

ከሚሰጠው ፡ ይልቅ ፡ ለዘብ ፡ ያለ ፡ መፍትሔ ፡ ለመሻት ፡ ሲባል ፡ ከሁለቱ ፡ ተጻራሪ ፡ ውሎች ፡ ፈራሚው ፡ ሀገር ፡ መፈጸም ፡ የሚገባው ፡ የመጀመሪያውን ፡ ውል ፡ ሲሆን ፡ ቀጥሎ ፡ ያደረገውን ፡ ውል ፡ ያላግባብ ፡ ባለመፈጸሙ ፡ ለደረሰው ፡ ጉዳት ፡ ካሳ ፡ መክ ፈል ፡ አለበት ። ስለዚህ ፡ ሁለቱም ፡ ውሎች ፡ ጽኑና ፡ ዋጋ ፡ ያላቸው ፡ እንደሆኑ ፡ ቆይ ተው ፡ ባፈጻጸም ፡ ረገድ ፡ ግን ፡ ለመጀመሪያው ፡ ቅድሚያ ፡ ይሰጠዋል" ፡ የሚል ፡ ሀሳብ ፡ አቅርበዋል ።[61]

በዚህም ፡ መሠረት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ተጻራሪ ፡ የሆኑ ፡ ሁለት ፡ ውሎች ፡ ቢያጋጥሟት፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ መፍትሔ ፡ በመጠቀም ፡ ከችግሩ ፡ ለመውጣት ፡ ትች ላለች ።

ረ/ ብሔራዊ ፡ ሕግን ፡ ከውሎች ፡ ጋር ፡ ስለማስታረቅ ፤

በኢንተርናሲዮናል ፡ ሕግና ፡ ልማድ ፡ መሠረት ፡ ውል ፡ የሚያደርጉ ፡ ተዋዋይ ፡ ወገኖች ፡ ሁሉ ፡ ብሔራዊ ፡ ሕጎቻቸውን ፡ ተካፋይ ፡ ከሆኑበት ፡ ከኢንተርናሲዮናል ፡ ውል ፡ ጋር ፡ ወዲያውኑ ፡ ማስማማት ፡ የሚጠበቅባቸው ፡ ተግባር ፡ ነው ።

ውሎች ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ የበላይ ፡ ሕግ ፡ አካል ፡ በመሆናቸው ፡ ብሔራዊ ፡ ሕጎቿን ፡ ከገባችባቸው ፡ ውሎች ፡ ጋር ፡ የተስማሙ ፡ እንዲሆኑ ፡ ማድረግ ፡ የኢትዮጵያ ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ግዴታዋ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፤ ሕገ ፡ መንግሥቱም ፡ የሚጠይቀው ፡ ጉዳይ ፡ ነው ። ምክንያቱም ፡ ዐበይትና ፡ ንዑሳን ፡ ሕጎች ፡ በጠቅላላ ፡ ከበላዩ ፡ ሕግ ፤ ማለት ፡ ከሕገ ፡ መንግሥቱና ፡ ከውሎች ፡ ጋር ፡ የሚስማሙ ፡ መሆን ፡ አለባቸው ፡ የሚል ፡ ተቀባይነትን ፡ ያገኘ ፡ የሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ ደንብ ፡ ስላለ ፡ ነው ። እንዲያውም ፡ በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፳፪ ፡ መሠረት ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ከታወጀ ፡ በኋላ ፡ የወጡ ፡ ብሔራዊ ፡ ሕጎች ፡ ከጥቅምት ፡ ፳፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ አግባቡ ፡ ተፈጽመው ፡ ዋጋ ፡ ሊያስጣቸው ፡ የሚችለ ውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ አሟልተው ፡ የያዙትን ፡ ውሎች ፡ ሊሽሩ ፡ አይችሉም ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ ይህ ፡ አባባል ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከውሎቿ ፡ ጋር ፡ ለማስማማት ፡ ስትል ፡ የሕገ ፡ መንግሥቷን ፡ አናቅጻት ፡ መለወጥ ፡ አለባት ፡ ተብሎ ፡ መተርጎም ፡ የለበትም ። ምንም እንኳ ፡ ከጥቅምት ፡ ፳፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በኋላ ፡ የተደረጉ ፡ ውሎች ፡ ሁሉ ፡ ከሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ጋር ፡ የእኩልነት ፡ ደረጃ ፡ የተሰጣቸው ፡ ቢሆንም ፤ ዋጋ ፡ ያላቸው ፤ የሚያገለግሉ ፡ እንዲሆኑና ፡ በሀገሪቱም ፡ ውስጥ ፡ ሕጋዊ ፡ ኃይል ፡ እን ዲኖራቸው ፡ ከተፈለገ ፡ ከተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አነጋገር ፡ ጋር ፡ የተስማሙ ፡ መሆን ፡ ያስፈልጋቸዋል ።

ስለዚህ ፡ የውሉ ፡ መዋዋል ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ በተደነገገው ፡ መሠረት ፡ የተ ፈጸመ ፡ ሆኖ ፡ ከተገኘ ፤ እንደዚህ ፡ ላለው ፡ ውል ፡ አለመፈጸም ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከብሔ ራዊ ፡ ሕግዋ ፡ ጋር ፡ አለመስማማትን ፡ መከላከያ ፡ አድርጋ ፡ ልትጠቀስ ፡ አትችልም ።

ይህን ፡ በመሰለ ፡ ጉዳይ ፡ በሄግ ፡ ያለው ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ቋሚ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡[62] በዳንዚንግ ፡ ስላሉት ፡ የፖላንድ ፡ ተወላጆች ፡ አያያዝ ፡ ጉዳይ ፡ በሰጠው ፡ የምክር ፡ አስተያየት ፡-

61. ኬልሰን ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፵፯ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፤ ፩፻፲፯ ፡ ይመለከቷል ።
62. ኢትዮጵያ ፡ አሁን ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በመባል ፡ የሚታወቀውን ፡ የቋሚውን ፡ የኢን ተርናሲዮናል ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሕግ ፡ ያጸደቀችው ፡ በሐምሌ ፡ ወር ፡ ፲፱፻፲፬ ዓ ፡ ም ፡ ነው ።

"በኢንተርናሲዮናል ፡ ሕግም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በውል ፡ ከገባበት ፡ ግዴታ ፡ ለማም ለጥ ፡ ሲል ፡ አንድ ፡ መንግሥት ፡ የራሱን ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ እንደማስረጃ ፡ ለማቅረብ ፡ አይችልም"[63] ብሎአል ።

የሀርቫርድ ፡ የምርምር ፡ ድርሰትም ፡ ስለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ በአንቀጽ ፡ ፳፫ ፡ ላይ ፡ "በውሉ ፡ ውስጥ ፡ በግልጽ ፡ ካልተፈቀደ ፡ በስተቀር ፡ አንድ ፡ መንግሥት ፡ የገባበት ፡ ውል ፡ የሚለው ፡ በብሔራዊ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ያልተፈቀደ ፡ ወይም ፡ ያልተመለከተ ፡ ወይም ፡ ከመንግሥቱም ፡ ሆነ ፡ ከሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ አቋም ፡ ጋር ፡ የማይስማማ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ውሉን ፡ ላለመፈጸሙ ፡ ምክንያት ፡ ሊያቀርብ ፡ አይችልም"[64] ይላል ።

የሩሲያ ፡ የሕግ ፡ ባለሙያዎች ፡ ከዚህም ፡ አልፈው ፡ "የኢንተርናሲዮናል ፡ ሕግና ፡ ብሔራዊው ፡ ሕግ ፡ በተዋዋዮቹ ፡ ሀገሮች ፡ መንግሥታዊ ፡ ድርጅት ፡ ውስጥና ፡ በዜጎቻቸው ፡ ላይ ፡ አስገዳጅ ፡ ሆኖ ፡ ለመፈጸም ፡ ተመሳሳይ ፡ ሕጋዊ ፡ ኃይል ፡ እንዲኖራቸው ፡ ያሻል ። አንድ ፡ የመንግሥት ፡ ባለሥልጣን ፡ ሀገሩን ፡ ወክሎ ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ስምምነት ፡ ማድረግ ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ የሀገሩን ፡ ብሔራዊ ፡ ሕጎች ፡ ከስምምነቱ ፡ ጋር ፡ በሚስማማበት ፡ አኳኋን ፡ ለመለወጥ ፡ ፈቅዷል"[65] የማለት ፡ ሃሳብ ፡ አቅርበዋል ።

ሐኒንግስ ፡ የተባሉት ፡ የሕግ ፡ ሊቅም ፡ ብሔራዊው ፡ ሕግ ፡ በኢንተርናሲዮናል ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ስላለው ፡ ሥፍራ ፡ ሲናገሩ ፡ ዋና ፡ ዋናዎቹን ፡ መሠረታዊ ፡ አሳቦች ፡ እንደሚከተለው ፡ ዘርዝረዋል ።

"ሀ/ አንድ ፡ መንግሥት ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ግዴታውን ፡ የጣሰው ፡ ወይም ፡ ሳይፈጽም ፡ የቀረው ፡ በሕገ ፡ መንግሥት ፡ የማይፈቀድለት ፡ በመሆኑ ፤ ወይም ፡ ሦስቱ ፡ የመንግሥቱ ፡ ክፍሎች ፡ ወይም ፡ ከነዚህ ፡ የተለዩ ፡ ሌሎች ፡ ክፍሎች ፡ ባደረጉት ፡ ወይም ፡ ባላደረጉት ፡ ምክንያት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ለመከራከር ፡ አይችልም ።

ለ/ አንድ ፡ መንግሥት ፡ ለሌላ ፡ መንግሥት ፡ በውል ፡ የተሰጠውን ፡ መብት ፡ የሚያጓድል ፡ ሕግ ፡ ሊያወጣ ፡ አይችልም ።

ሐ/ የኢንተርናሲዮናል ፡ ግዴታ ፡ የገባ ፡ ሀገር ፡ ግዴታውን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ የሚያስችል ፡ ብሔራዊ ፡ ሕግ ፡ ሊያወጣ ፡ ይገባዋል ።

መ/ የኢንተርናሲዮናል ፡ ግዴታን ፡ ከመፈጸም ፡ በሚያሳግድ ፡ ወይም ፡ በሚያፈርስ ፡ በብሔራዊ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የሚደረግ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ይሆናል"[66]

ባጭሩ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ የሚያመለክተው ፤ በውል ፡ የተገባ ፡ ግዴታን ፡ ባለማክበር ፡ በቀረበ ፡ ክስ ፡ ላይ ፡ በብሔራዊ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኝ ፡ ማናቸውም ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ መከላከያ ፡ ሆኖ ፡ ሊቀርብ ፡ አለመቻሉን ፡ ነው ። በአጭሩ ፡ አንድ ፡ ተዋዋይ ፡ መንግ

---

63. ማክኔር ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፶፰ ፡ የተጠቀሰው ፤ ከገጽ ፡ ፩፻—፩፻፩ ፡ ይመለከቷል ።
64. ከዚያው ፤ ከገጽ ፡ ፫፻—፫፻፱ ።
65. አካዳሚ ፡ አፍ ፡ ሳይንስስ ፡ አፍ ፡ ዘ ፡ ዩ ፡ ኤስ ፡ ኤስ ፡ አር ፡ ኢንስቲትዩት ፡ አፍ ፡ ሎው ፤ ኢንተርናሽናል ፡ ሎው ፡ ገጽ ፡ ፲፰ ።
66. ሐኒንግስ ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፴፮ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፳ ፡ ይመለከቷል ።

ሥት ፡ በውል ፡ የገባሁበትን ፡ ግዴታ ፡ ከመፈጸም ፡ ያስታጉለኝ ፡ ወይም ፡ የከለከለኝ ፡ ብሔራዊ ፡ ሕግ ፡ ወይም ፡ ድርጅት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ሊከራከር ፡ አይችልም ።

ስለዚህ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ተካፋይ ፡ ከሆነችበት ፡ ውል ፡ ጋር ፡ የማይስማሙ ፡ ዐበይ ትም ፡ ሆኑ ፡ ንዑሳን ፡ ሕጎች ፡ ቢኖሩ ፤ ይህን ፡ የመሰለው ፡ ችግር ፡ እንዳይገጥማት ፡ እንዲህ ፡ ዓይነቱን ፡ መጻረር ፡ ማስወገድ ፡ አለባት ።

ከዚህም ፡ በላይ ፤ ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ውሎችን ፡ ከራሱ ፡ ጋር ፡ የእኩልነት ፡ ደረጃ ፡ ስለሚሰጣቸው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የቀረበላቸውን ፡ ማናቸውንም ፡ ውል ፡ በመተርጎም ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ማዋል ፡ አለባቸው ። ካፕላንና ፡ ካትዜባንክ ፡ በትክክል ፡ እንዳመለከቱት ፤ በአሜሪካንም ፡ ሀገር ፡ እንደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሁሉ ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ውሎችን ፡ በግልጽ ፡ "የበላይ ፡ ሕግ" ፡ ሲላቸው ፡ የመተርጎሙን ፡ ሥራ ፡ ግን ፡ ለፍ ርድ ፡ ቤቶች ፡ እንደሚሰጣቸው ፡ ግምት ፡ ለመውሰድ ፡ ይቻላል ።[67]

ስለዚህ ፡ የሕግ ፡ አውጭው ፤ የአስፈጻሚውና ፡ የዳኝነቱ ፡ ክፍሎች ፡ በጠቅላላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የገባችባቸውን ፡ ውሎች ፡ የማስፈጸም ፡ ግዴታ ፡ አለባቸው ። የተሻሻለ ውም ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ከመውጣቱ ፡ በፊት ፡ ተደርገው ፡ ከዚሁ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ጋር ፡ ስለማይስማሙት ፡ ውሎች ፡ አዲስ ፡ የውል ፡ ድርድር ፡ በማድረግ ፡ እንዲስ ማሙ ፡ ማድረግ ፡ ያስፈልጋል ።

መደምደሚያ ፡

ከጥቅምት ፡ ፳፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ማለት ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ከመታወጁ ፡ በፊት ፡ ውል ፡ የመዋዋል ፡ ሥልጣን፡ ያለምንም ፡ ገደብ ፡ በ፲፱፻፳፫ ፡ ዓመተ፡ ምሕረቱ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፲፬ ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ተሰጥቶ ፡ ነበር ። የ፲፱፻፵፰ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረቱ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ከወጣ ፡ ወዲህም ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ በአ ንቀጽ ፡ ፴ ፡ ውል ፡ የመዋዋሉ ፡ ሥልጣን ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የተሰጠ ፡ ቢሆንም ፤ በአን ዳንድ ፡ ውሎች ፡ ላይ ፡ የፓርላሜንቱ ፡ ፈቃድ ፡ ስለሚያስፈልግ ፡ አንቀጹ ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የሚሰጠውን ፡ ሥልጣን ፡ እዚያው ፡ ውስጥ ፡ በከፊል ፡ ገደብ ፡ አብጅቶለታል ።

የ፲፱፻፶፱ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ቁጥር ፡ ፵፯ ፡ እስከ ፡ ወጣበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ውሎችንና ፡ ስምምነቶችን ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ስም ፡ ተነጋግሮ ፡ የመዋዋሉ ፡ ሥልጣን ፡ በ፲፱፻፴፭ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ቁጥር ፡ ፩ ፡ አንቀጽ ፡ ፳፫ ፡ (ረ ፡ እና ፡ ሰ) ፡ መሠረት ፡ ለውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ተሰጥቶ ፡ ነበር ። ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ ግን ፡ በ፲፱፻፶፱ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ቁጥር ፡ ፵፯ ፡ እና ፡ በ፲፱፻፷፪ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ቁጥር ፡ ፷፫ ፡ መሠረት ፡ ተነጋግሮ ፡ ስምምነት ፡ የመዋዋል ፡ ሥል ጣን ፡ ለውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስትር ፤ ለገንዘብ ፡ ሚኒስትርና ፡ ፊት ፡ የፕላንና ፡ ልማት ፡ ሚኒስትር ፡ (አሁን ፡ ግን ፡ የፕላን ፡ ኮሚሽን ፡ ዋና ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የበላይ ፡ ሹም)፡ ተሰጥቷል ። ለውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ የተሰጠው ፡ ውል ፡ የመዋዋል ፡ ሥልጣን ፡ ጠቅላላ ፡ ሲሆን ፤ ለገንዘብ ፡ ሚኒስትርና ፡ ለፕላን ፡ ኮሚሽን ፡ ዋና ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የበ ላይ ፡ ሹም ፡ የተሰጡት ፡ ለተለዩ ፡ ጉዳዮች ፡ ነው ። በዚህም ፡ መሠረት ፡ ለገንዘብ ፡ ሚኒስትሩ ፡ የተሰጠው ፡ ስለብድሮችና ፡ የገንዘብ ፡ ስምምነት ፡ የመዋዋል ፡ ሥልጣን ፡

67. ካፕላንና ፡ ካትዜንባግ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፵፯ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፪፻፷፬ ፡ ይመለከቷል።

ሲሆን ፤ ለፕላን ፡ ኮሚሽን ፡ የበላይ ፡ ሹም ፡ የተሰጠው ፡ ደግሞ ፡ ለኢኮኖሚና ፡ የቴክኒክ ፡ እርዳታዎች ፡ የሚደረግ ፡ ስምምነትን ፡ የመዋዋል ፡ ሥልጣን ፡ ነው ።

ሌሎች ፡ ሚኒስትሮችና ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ የበላይ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ደግሞ ፡ ባህል ፡ ነክ ፡ በሆኑ ፡ ጉዳዮች ፡ ፕሮቶኮል ፡ የመፈራረም ፡ ወይም ፡ ቀደም ፡ ብለው ፡ ሙሉ ፡ ውክልና ፡ የተሰጣቸው ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ባደረጉት ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ በተመለከቱት ፤ በተዋዋዮቹ ፡ የጋራ ፡ ገንዘብ ፡ መዋጮ ፡ እንዲሠራ ፡ የተስማሙበት ፡ ዕቅድ ፡ የሚፈጸምበትን ፡ መንገድ ፡ በሚመለከት ፡ ጉዳይ ፡ መዋዋል ፡ ይችላሉ ።

ውሎችን ፡ የማጽደቁና ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ ሊፈጸሙ ፡ ግዴታ ፡ ከመሆናቸው ፡ አስቀድሞ ፡ የትኞቹ ፡ ውሎችና ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ስምምነቶች ፡ መጽደቅ ፡ እንደ ሚገባቸው ፡ የመወሰኑ ፡ መብት ፡ በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፴ ፡ መሠረት ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ብቻ ፡ የተሰጠ ፡ ሥልጣን ፡ ነው ። ቢሆንም ፡ ይህ ፡ ሥልጣን፡ በዚሁ ፡ አንቀጽ ፡ ውስጥ ፡ እንደተመለከተው ፡ ገደብ ፡ የተበጀለትና ፡ ለሌላም ፡ ባለሥልጣን ፡ በውክልና ፡ የማይተላለፍ ፡ ነው ።

የሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አንቀጽ ፡ ፩ ፡ እና ፡ ፴ ፡ ስለሚስማሙበት ፡ የዚህ ፡ ምርምር ፡ ደራሲ ፡ አንቀጽ ፡ ፩ ፡ በጣም ፡ ሰፊ ፡ ከመሆኑም ፡ ሌላ ፡ የሚገኘው ፡ በጠቅላላው ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ በመሆኑ ፡ መተርጎም ፡ የሚገባው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ውል ፡ ስለማዋዋል ፡ ሥልጣን ፡ በተለይ ፡ በሚናገረው ፡ አንቀጽ ፡ ፴ ፡ መሠረት ፡ ነው ፡ ባይ ፡ ነው ። በተጨማሪም ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ በአንቀጽ ፡ ፩፻፳፭ ፡ እንደተመለከተው ፡ አማርኛ ፡ የሀገሪቱ ፡ መደበኛ ፡ ቋንቋ ፡ በመሆኑ ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ በአንቀጽ ፡ ፴ ፡ በአማርኛው ፡ ጽሑፍ ፡ መሠረት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ዜጎች ፡ ላይ ፡ የንብረት ፡ ወይም ፡ የአካል ፡ ጉዳት ፡ ሊያመጡ ፡ የሚችሉ ፡ ውሎች ፡ ሁሉ ፡ ከመጽደቃቸው ፡ በፊት ፡ ለፓርላሜንቱ ፡ መቅረብ ፡ አለባቸው ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ ስለሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፳፪ ፡ የተደረገው ፡ ጥናት ፡ እንደ ሚያመለክተው ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ በሚያዘው ፡ መሠረት ፡ ስምምነት ፡ ተደርጎ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ተካፋይ ፡ የሆነችባቸው ፡ ውሎች ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ የበላይ ፡ ሕግ ፡ ሆነው ፡ መፈጸም ፡ አለባቸው ። ይህም ፡ የሚሆንበት ፡ ምክንያት ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ግልጽ ፡ በሆነ ፡ አነጋገር ፡ እንደዚህ ፡ ያሉትን ፡ ውሎች ፡ ከተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ጋር ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ የበላይ ፡ ሕግ ፡ ስለሚያደርጋቸው ፡ ነው ። በሌላ ፡ አነጋገር ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ በሚያዘው ፡ መሠረት ፡ የተደረጉትን ፡ ውሎች ፡ ለሀገሪቱ ፡ ብሔራዊ ፡ ሕግ ፡ አካል ፡ በሚያደርጋቸው ፡ በአንቀጽ ፡ ፩፻፳፪ ፡ መሠረት ፡ ከሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ጋር ፡ የእኩልነት ፡ ደረጃ ፡ ተሰጥቶአቸው እንደ ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ሁሉ ፡ የተፈጻሚነት ፡ ኃይል ፡ እንዲኖራቸው ፡ ተደርጎአል ።

ውሎች ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ የበላይ ፡ ሕግ ፡ እንደመሆናቸው ፡ መጠን ፡ በሀገሪቱ ፡ ተራ ፡ ሕጎችና ፡ በውሎች ፡ መካከል ፡ መጻረር ፡ ሲፈጠር ፡ ውሎች ፡ ደምሳሽነት ፡ ይኖራቸዋል ። ሆኖም ፡ አለመስማማቱ ፡ የተፈጠረው ፡ ከሕገ ፡ መንግሥቱ ጋር ፡ ሲሆንና ፡ ውሉ ፡ የተደረገው ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ከወጣ ፡ በኋላ ፡ ከሆነ ፡ ግን ፡ የበላይነት ፡ ደረጃ ፡ የሚሰጠው ፡ ለሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ነው ። ምክንያቱም ፡ ውሉ ፡ በኢትዮጵያና ፡ በዜጎቿ ፡ ላይ ፡ ለመፈጸም ፡ ግዴታ ፡ ለመሆን ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ በሚያዘው ፡ መሠረት ፡ የተፈጸመ ፡ ሁኖ ፤ በተጨማሪም ፡ ዋጋ ፡ ሊያስጡት ፡ የሚችሉትን ፡ አስፈላጊ ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ አሟልቶ ፡ መያዝ ፡ ስላለበት ፡ ነው ።

ሥርዓቱን ፡ ጠብቆ ፡ የተደረገ ፡ አንድ ፡ ውል ፡ ዋጋ ፡ ሊያሰጡት ፡ የሚያስፈልጉትን ፡ ሁኔታዎች ፡ ሁሉ ፡ አሟልቶ ፡ ከያዘና ፡ የተደረገውም ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መን

ግሥት ፡ ከታወጀ ፡ በኋላ ፡ ከሆነ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የሕጎች ፡ ድርገት ፡ አርከን ፡ ውስጥ ፡ የበላይነት ፡ ሥፍራ ፡ ይሰጠዋል ። ስለዚህ ፡ ማናቸውም ፡ ዐቢይ ፡ ሕግ ፡ ከውል ፡ ጋር ፡ የማይስማማ ፡ ሆኖ ፡ ከተገኘ ፡ ዋጋ ፡ የሌለውና ፡ የማያገለግል ፡ ይሆናል ። በሌላ ፡ አገላለጽ ፤ በሕግ ፡ አውጭውም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ባስፈጻሚው ፡ ክፍል፡ የወጣ፡ ሕግ ፡ (አዋጅ)፡ ድንጋጌ ፡ ወይም ፡ ባስተዳደሩም ፡ ሆነ ፡ በዳኝነቱ ፡ ክፍል ፡ የተሰጠ ፡ ውሳኔ ፡ ወይም ፡ ድርጊት ፡ የበላዩን ፡ ሕግ ፡ ማለት ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱንና ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ውሎችን ፡ የሚቃረን ፡ ከሆነ ፡ በአንቀጽ ፡ ፩፻፳፪ ፡ እንደተመለከተው ፡ ዋጋ ፡ የሌለውና ፡ የማያገለግል ፡ ይሆናል ። ሆኖም ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ በቀጥታ ፡ የሚቃወም ፡ ውል ፡ ጽኑ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ። እዚህ ፡ ላይ ፡ «ዋጋ ፡ የሌላቸውና ፡ የማያገለግሉ ፡ ይሆናሉ» የሚሉት ፡ ቃላት ፡ የሚያመለክቱት ፡ የተሻሻለውን ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ የሚጥስ ፡ ውል ፡ ወይም ፡ ወደፊት ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ መሠረት ፡ ከተፈጸሙ ፡ ውሎች ፡ ጋር የማይስማሙ ፡ ሕጎች ፡ (አዋጆች) ፡ ድንጋጌዎች ፤ ትእዛዞች ፤ ፍርዶች ፤ ውሳኔዎችና ፡ ድርጊቶች ፡ በሀገሪቱ ፡ ውስጥ ፡ የአስገዳጅነት ፡ ኃይል ፡ የሌላቸው ፡ መሆኑን ፡ ወይም ፡ በሀገር ፡ ውስጥ ፡ ተፈጻሚ ፡ አለመሆናቸውን ፡ ነው ። ይሁን ፡ እንጂ ፤ ውሉ ፡ የሚያስከትለው ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ግዴታ ፡ የሚዳኘው ፡ በኢንተርናሲዮናል ፡ ሕግ ፡ ስለ ሆነ ፡ ይህ ፡ አፍራሽ ፡ አነጋገር ፡ ከሀገሪቱ ፡ ውጪ ፡ ያለውን ፡ ግዴታ ፡ አይጨምርም ።

በተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ቻርተር ፡ ኢትዮጵያ ፡ ባለባት ፡ ግዴታና ፡ በሌሎች ፡ በኢንተርናሲዮናል ፡ ውሎች ፡ በገባቻቸው ፡ ግዴታዎች ፡ መካከል ፡ መጻረር ፡ ሲፈጠር ፡ የቻርተሩ ፡ አንቀጾች ፡ የበላይነት ፡ ይኖራቸዋል ። ምክንያቱም ፡ ቻርተሩ ፡ ሕግ ፡ መሥራች ፡ ውል ፡ በመሆኑና ፡ ኢትዮጵያም ፡ ቻርተሩን ፡ ተቀብላ ፡ በመፈረምዋ ፤ ከርሱ ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ መንፈስ ፡ ውል ፡ ላለማድረግ ፡ ግዴታ ፡ የገባች ፡ በመሆኑዋ ፡ ነው ። በአፍሪካ ፡ አንድነት ፡ ድርጅት ፡ ቻርተርና ፡ ኢትዮጵያ ፡ ተካፋይ ፡ በሆነችባቸው ፡ ሌሎች ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ውሎች ፡ መካከል ፡ መጻረር ፡ ሲፈጠር ፡ ግን ፡ በጊዜ ፡ አመጣጥ ፡ ቀደም ፡ ላለው ፡ የበላይነት ፡ ይሰጠዋል ።

የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ከመታወጁ ፡ በፊት ፡ ስለነበሩት ፡ ውሎች ፡ የሆነ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ ደራሲ ፡ አስተያየት ፡ ከ፲፱፻፵፯ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ቁጥር ፡ ፲ ፡ እና ፡ በ፲፱፻፵፯ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረቱ ፡ አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፵፱ ከብሔራዊው ፡ ሕጎች ፡ ጋር ፡ የተዋሃዱ ፡ ስለሆነ ፣ ዋጋ ፡ ሊያሳጣቸው ፡ የሚያስችላቸውን ፡ ነገር ፡ አሟልተው ፡ እስከያዙ ፡ ድረስ ፡ ተፈጻሚነት ፡ ሊኖራቸው ፡ ይገባል ።

ሆኖም ፡ ከተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ በፊት ፡ የተደረጉት ፡ ውሎች ፡ እላይ ፡ በተጠቀሱት ፡ ሕጎች ፡ መሠረት ፡ የበላይ ፡ ሕግ ፡ መሆንና ፡ ከዚያም ፡ ወዲህ ፡ ስምምነት ፡ ተደርጎባቸው ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፳፪ ፡ መሠረት ፡ የበላይነት ፡ ደረጃ ፡ በተሰጣቸው ፡ ውሎች ፡ መካከል ፡ የደረጃና ፡ የሕጋዊ ፡ ኃይልም ፡ ልዩነት ፡ አለ ።

ከተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ በኋላ ፡ የተደረጉት ፡ ውሎች ፡ የበላይ ፡ ሕግነት፡ ደረጃ ፡ የተሰጣቸው ፡ የበላይ ፡ ሕግ ፡ በሆነው ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ሲሆን ፤ በፊት ፡ የተደረጉት ፡ ውሎች ፡ የበላይ ፡ ሕግነት ፡ ደረጃ ፡ የተሰጣቸው ፡ በተራ ፡ ሕጎች ፡ ነው ። ስለዚህም ፡ ለሁለቱ ፡ የተሰጠው ፡ የበላይ ፡ ሕግነት ፡ ደረጃ ፡ እኩል ፡ አይደለም ። በሕገ፡ መንግሥቱ ፡ መሠረት ፡ የተሰጠው ፡ የበላይነት ፡ እላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ ትእዛዝና ፡ አዋጅ ፡ እንደተሰጠው ፡ ሳይሆን ፤ ውሎችን ፡ ከተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ጋር ፡ በእኩልነት ፡ ስለሚያስቀምጣቸው ፡ ብልጫ ፡ አለው ። ሁለተኛም ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ የመንግሥቱ ፡ ዓይነተኛው ፡ የበላይ ፡ ሕግ ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ በአመጣጥም ፡ ቢሆን ፡

በኋላ ፡ የወጣ ፡ በመሆኑ ፡ የበለጠ ፡ ተሰሚነት ፡ ሊሰጠውና ፡ ከርሱ ፡ በፊት ፡ የወጡት ንም ፡ ትእዛዞችና ፡ አዋጆች ፡ ሊያሻሽል ፡ ይገባል ።

ቀደም ፡ ሲል ፡ የተደረገው ፡ ትንታኔ ፡ እንደሚያመለክተው ፡ ሁሉ ፤ የሕገ ፡ መንግ ሥቱ ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፳፪ ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ከመውጣቱ ፡ በፊት ፡ የተደረጉት ፡ ውሎች ፡ ስላላቸው ፡ ደረጃ ፡ አይናገርም ። የዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ ዝምታና ፡ የአንቀጽ ፡ ፩፻፳፪ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ተመልሶ ፡ አለመሥራት ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ከመታወጁ ፡ በፊት ፡ የነበሩት ፡ ውሎች ፡ ያላቸው ፡ የበላይ ፡ ሕግነት ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ መሠረት ፡ ለተደረጉት ፡ ውሎች ፡ በተሰጣቸው ፡ የበላይ ፡ ሕግነት ፡ ተሽሮአል ፡ ለማለት ፡ ያስችላል ። ከዚህም ፡ የተነሳ ፡ ከርሱ ፡ በፊት ፡ የነበሩትን ፡ ውሎች ፡ የበላይ ፡ ሕግ ፡ ከሚላቸው ፡ ምድብ ፡ ውስጥ ፡ የማይጨምር ፡ አንቀጽ ፡ ያለው ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ መታወጅ ፡ የ፲፱፻፵፭ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረቱን ፡ ትእዛዝ ፡ ቁጥር ፡ ፮ ፡ አንቀጽ ፡ ፫ ፡ እና ፡ የ፲፱፻፵፯ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረቱን ፡ አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፵፱ ፡ አንቀጽ ፡ ፩ ፡ ተግባርና ፡ ውጤት ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ከመውጣቱ ፡ በፊት ፡ የተደረጉትን ፡ ውሎች ፡ ከብሔራዊ ፡ ሕጎች ፡ ጋር ፡ ማዋሃድ ፡ ብቻ ፡ ያደርገዋል ። ውሎችን ፡ የበላይ ፡ ሕግ ፡ የማድረጉ ፡ ተግባር ፡ በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፳፪ ስለተወረሰ ፤ በዚሁ ፡ መሠረት ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ የበላይ ፡ ሕግ ፡ የሚሆኑት ፡ በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ መሠረት ፡ የተደረጉ ፡ ውሎችና ፡ ይኸው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ራሱን ፡ ጨምሮ ፡ የበላይ ፡ ሕግ ፡ የሚያደርጋቸው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ወደፊት ፡ ተካፋይ ፡ የምትሆንባቸው ፡ ውሎች ፤ ስምምነቶችና ፡ ግዴታዎች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ።

በዚሁ ፡ አንቀጽ ፡ ውስጥ ፡ "ተካፋይ ፡ የምትሆንባቸው" የሚሉት ፡ ቃላት ፡ የሚያመለክቱት ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ከታወጀበት ፡ ከጥቅምት ፡ ፳፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በኋላ ፡ የተደረጉትን ፡ ውሎች ፤ ስምምነቶችና ፡ ግዴታዎችን ፡ ነው ። እንደዚሁም ፡ "ይሆናሉ" ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ የገባው ፡ በትንቢታዊ ፡ አነጋገር ፡ ሆኖ ፡ ስለወደፊት ፡ ጊዜ ፡ ለመግለጽ ፡ እንጂ ፡ በሰዋስው ፡ አገባቡ ፡ ባለው ፡ ትእዛዛዊ ፡ አንቀጽ ፡ አይደለም ። ስለዚህ ፡ ውሎች ፡ የሀገሪቱ ፡ የበላይ ፡ ሕግ ፡ የሚሆኑት ፡ በ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በወጣው ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ መሠረት ፡ የተደረጉ ፡ እንደሆነ ፡ ብቻ ፡ ነው ። የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ የሕጎች ፡ አምድና ፡ በሕጎች ፡ ድርገት ፡ አርከን ፡ ውስጥም ፡ ዐቢይ ፡ ሕግ ፡ ስለሆነና ፡ ከዚህም ፡ አልፎ ፡ በአመጣጥ ፡ ረገድም ፡ ኋለኛ ፡ በመሆኑ ፡ ኤርትራን ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ጋር ፡ በሚያዋህደው ፡ በ፲፱፻፵፭ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ቁጥር ፡ ፮ ፡ በአንቀጽ ፡ ፫ ፤ እና ፡ በ፲፱፻፵፯ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረቱ ፡ የሕዝብ ፡ መብት ፡ አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፵፱ ፡ በአንቀጽ ፡ ፩ ፡ ከተመለከተው ፡ ይልቅ ፡ የበላይነት ፡ አለው ።

ከዚህም ፡ በላይ ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ መሠረት ፡ የተደረጉ ፡ ውሎች ፡ ወዲያውኑ ፡ በሀገሪቱ ፡ ውስጥ ፡ ተፈጻሚነት ፡ እንዲኖራቸው ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፳፪ ፡ ያዝዛል ። የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥትም ፡ ከመውጣቱ ፡ በፊት ፡ የተደረጉ ፡ ውሎችም ፡ በሀገሪቱ ፡ ውስጥ ፡ ሕጋዊ ፡ ኃይል ፡ የሚኖራቸው ፡ በ፲፱፻፵፭ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ቁጥር ፡ ፮ ፡ አንቀጽ ፡ ፫ ፡ እና ፡ በ፲፱፻፵፯ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረቱ ፡ አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፵፱ ፡ አንቀጽ ፡ ፩ ፡ መሠረት ፡ ነው ። የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ከመውጣቱ ፡ በፊት ፡ የተደረጉት ፡ ውሎች ፡ የብሔራዊ ፡ ሕግ ፡ ለመሆን ፡ የበቁት ፡ የሕጎች ፡ ሁሉ ፡ አምድ ፡ በሆነው ፡ በሕገ ፡ መንግሥት ፡ ሳይሆን ፡ በሌላ ፡ ዐቢይ ፡ ሕግ ፡ አማካይነት ፡ በመሆኑ ፡ እነዚህን ፡ ውሎች ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ በሚፈለግበት ፡ ጊዜ ፡ ችግር ፡ ሊፈጠር ፡ ይችላል ። ለምሳሌ ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ከመታወጁ ፡ በፊት ፡ የተደረጉትን ፡ ውሎች

ለመፈጸም ፡ ሲባል ፡ በመንግሥቱ ፡ አንድ ፡ ድርጊት ፡ ቢደረግና ፡ ይህም ፡ አድራጎት ፡ ከተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ጋር ፡ የማይስማማ ፡ ቢሆን ፡ በአንቀጽ ፡ ፩፻፳፱ ፡ በመጨረሻው ፡ ክፍል ፡ እንደተመለከተው ፡ ድርጊቱ ፡ ሕጋዊ ፡ ላይሆን ፡ ይችላል ።

የዚህ ፡ ዓይነቱን ፡ ሁኔታ ፡ ለማስወገድ ፡ ከተሻሻለው ፡ ሕግ ፡ መንግሥት ፡ በፊት በተደረገ ፡ ውልና ፡ ባሁኑ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ መካከል ፡ አለመስማማት ፡ በሚፈጠር በት ፡ ጊዜ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ስለፊተኛው ፡ ውል ፡ አዲስ ፡ የውል ፡ ድርድር ፡ አድርጋ ፡ ከተ ሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ጋር ፡ ማስማማት ፡ ይኖርበታል ።

የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ውሎችን ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ የበ ላይ ፡ ሕግ ፡ አካል ፡ ስለሚያደርጋቸው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ብሔራዊ ፡ ሕጎችን ፡ ተካፋይ ፡ ከሆነችባቸው ፡ ውሎች ፡ ጋር ፡ አስማምታ ፡ በመያዝ ፡ በውሎችና ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ መካከል ፡ አለመስማማት ፡ እንዳይፈጠር ፡ ማድረግ ፡ አለባት ።

TREATY-MAKING POWER AND SUPREMACY OF TREATY IN ETHIOPIA

By

*Aberra Jembere**

> " . International treaties. to which Ethiopia shall be party, shall be the supreme law of the Empire. "
> Art. 122 Revised Constitution of Ethiopia.

Introduction

The word "treaty" is derived from "traiter" French for "to negotiate," and denotes those international agreements which are intended to have an "obligatory character."[1]

